# የኢትዮጵያ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አሠራር ።

ከቶማስ ፡ ጋራቲ ።

## መግቢያ ።

ዛሬ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ወረዳና ፡ አውራጃ ፡ ፍ/ቤቶች ፡ የሚቀርቡት ፡ ጉዳዮች ፡ "በድሮ ፡ ጊዜ ፡" በተፈሩና ፡ በተከበሩ ፡ ሽማግሎች ፡ ወይም ፡ በቀበሌው ፡ ዳኞች ፡ በትንንሽ ፡ መንደሮች ፡ ውስጥ ፡ በዛፍ ፡ ሥር ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጥባቸው ፡ የነበሩት ፡ ዓይነት ፡ ሙግቶች ፡ ናቸው ።

ወትሮ ፡ ዛፍ ፡ ይለግሥ ፡ የነበረውን ፡ ጥላ ፡ አሁን ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይሰጣል ፤ ሰፋፊ ፡ ከተሞች ፡ የመንደሮችን ፡ ሥፍራ ፡ ወስደዋል ፡ ዳኞችም ፡ በማእከላዊው ፡ መንግሥት ፡ ተሹመው ፡ በአንድ ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ ነገርን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ወደሚቀጥለው ፡ ያልፋሉ ። ሽማግሌዎች ፡ ነገር ፡ በሚቀርብላቸው ፡ ጊዜ ፡ ዱሮ ፡ ያደርጉት ፡ የነበረውን ፡ የሽምግልና ፡ ተግባር ፡ አሁንም ፡ ይፈጽማሉ ።

ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገልጸው ፡ የጊዜው ፡ "ዝቅተኛ ፡ ፍ/ቤቶች" ፡ እስካሁን ፡ ያደረጉትን ፡ እድገት ፡ ነው ። የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ሠራተኞች ፡ ታሪክና ፡ በቅንጅቱና ፡ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ በማብራራት ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቅንጅት ፡ ዛሬ ፡ ያለበትን ፡ ሁኔታ ፡ ይገልጸል ። በመጨረሻም ፡ በተጨማሪ ፡ ማስረጃው ፡ ውስጥ ፡ (አፔንዲክስ) ፡ ዛሬ ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ረገድ ፡ ያሉትን ፡ መሠረታዊ ፡ ችግሮች ፡ ለማረጋገጥ ፡ ያህል ፡ ከሁለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተወሰዱ ፡ ነገሮች ፡ ይተነተናሉ ።

ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ መፍትሒያቸው ፡ ፍጹም ፡ አዲስ ፡ አጀማመርን ፡ ሳይሻ ፡ በቀላሉ፡ ሊዳኙ ፡ የሚችሉትን ፡ ችግሮች ፡ ያመለክታል ፡ ተብሎ ፡ ተስፋ ፡ ተደርጓል ። እነዚህ ፡ እርምጃዎች ፡ ቢወሰዱ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ሻል ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ የሚቀጥል ፡ ቢሆንም ፡ ወደፊት ፡ እንደሚታየው ፡ ሁሉ ፡ እውነተኛው ፡ መሻሻል ፡ ነገሩ ፡ የሚመለከታቸውን ፡ ሁሉ ፡ መሠረታዊ ፡ የመንፈስ ፡ ለውጥ ፡ ይጠይቃል ።

## ዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ጠቅላላ ፡ መግለጫ ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የአብዛኞቹ ፡ ተሟጋቾች ፡ ክርክር ፡ የሚሰማው ፡ በወረዳና ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የዳኝነት ፡ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች፡

---

1. በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ መረጃ ፡ ደራሲውና ፡ የሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ከአርባ ፡ ሁለት ፡ ዳኞች ፤ ሰባ ፡ ሁለት ፡ ጠበቆች ፤ ሰላሳ ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፤ ሰባ ፡ አምስት ፡ የፍርድ ፡ ጸሐፊዎችና ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ተሟጋቾች ፡ ጋር ፡ ካደረጉት ፡ ጥያቄና ፡ መልስ ፡ የተገኘ ፡ ነው ። ጠቅላላው ፡ የምርምር ፡ ሥራ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባደረገልን ፡ እርዳታ ፡ የተቃለለ ፡ ሆኗል ።

ባንድነት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ግምታቸው ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ የኢት. ብር ፡ በሚደርስ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቶች ፡ ግምታቸው ፡ እስከ ፡ አሥር ፡ ሺህ ፡ የኢት፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።[2] በወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ ረገድም ፡ ሥልጣናቸው ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ሥርቆት ፡ ያሉትን ፡ አነ ስተኛ ፡ ወንጀሎችን ፡ ከመቅጣት ፡ ጀምሮ ፡ የሌብነትን ፡ ክስ ፡ እስከመስማት ፡ ይደር ሳል ። እነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣናቸውን ፡ የሚሠሩ በት ፡ "ወረዳ" ፡ ወይም ፡ "አውራጃ ፡ ግዛት ፡"[3] ተብሎ ፡ በተከፈለው ፡ የሥነ ፡ መንግ ሥታዊ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ነው ። የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ፡ ቤቶች ፡ የይግባኝና ፡ የአስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ናቸው ።

ከወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በታች ፡ በአሥመራና ፡ በባላገር ፡ የቀበሌ ፡ ዳኞች ፡ ወይም ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ይገኛሉ ። እነዚህም ፡ ከግዛታቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚነሱ፡ በጣም ፡ ቀላል ፡ የሆኑ ፡ የፍትሐብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ጉዳዮችን ፡ እንዲሰሙ ፡ በ፲፱፻፴፱ በወጣ ፡ አዋጅ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ነበር ።[4] በ፲፱፻፶፬ የወጣው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቀላል ፡ የወንጀል ፡ ጉዳ ዮችን ፡ እንዲሰሙ ፡ ሥልጣን ፡ ቢሰጣቸውም ፡ በ፲፱፻፶፰ ዓ ፡ ም የወጣው ፡ የፍትሐብ ሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ስላላቸው ፡ ሥልጣን ፡ ምንም ፡ አይናገርም ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ አጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የነበራቸው ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለ ፡ መቆየቱና ፡ አለመቆየቱ ፡ ግልጽ ፡ ስላልነበረ ፤ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ለሁሉም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ በተላከ ፡ አንድ ፡ አዋዲ ፡ ደብዳቤ ፡ ነገርተኞቹ ፡ ነገራቸው ፡ እንዲሰማላቸው ፡ በተስማሙ ፡ ጊዜ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮችን ፡ ሊያነጋግሩ ፡ እንደሚችሉ ፡ በመግለጽ ፡ ነገሩን ፡ ለማብራራት ፡ ሞክሯል ።[5]

ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ በሚገኙ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶችን ፡ የሚያይና ፡ አንድ ፡ የወንጀል ፡ ክሶ ችን ፡ የሚሰማ ፡ ሁለት ፡ ዳኞች ፡ ይሰየማሉ ። ከኤርትራ ፡[6] ውጭ ፡ ያሉ ፡ የአውራጃ ፡ ፍ/ቤቶች፡ ሙግቶችን ፡ ባንድነት ፡ የሚሰሙ ፡ አንድ ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛና ፡ ሁለት ፡ ተባ ባሪ ፡ ዳኞች ፡ ማለት ፡ ሦስት ፡ ዳኞች ፡ አሏቸው ።

በታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ሦስት ፡ ዳኞችን ፡ የያዙ ፡ በተለይ ፡ የፍትሐብሔርን ፡ የወንጀልን ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ክርክርን ፡ የሚሰሙ ፡ የተለያዩ ፡ ችሎቶች ፡ አሏቸው ።

በአዲስ ፡ አበባ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በጣም ፡ የተለመደው ፡ የፍትሐብሔር ፡ ክርክር ፡ ከብድር ፡ ውል ፡ የሚነሳ ፡ አነስተኛ ፡ እዳን ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። እነዚህ፡ እዳዎች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሚገለገልበትን ፡ የዕቃ ፡ ወይም ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋን ፡

---

2. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ፡
3. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፲፬ ፡ "ግዛት" ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ሲተረጐም ፡ "የሚ ገዛ ፡ (የሚተዳደር) ፡ ቦታ" ማለት ፡ ነው ፤ "ወረዳ" አነስተኛው ፡ የአገር ፡ አገዛዝ ፡ ክፍል ፡ ነው ። የመ ጨረሻው ፡ የአገር ፡ አገዛዝ ፡ ክፍል ፡ "ምክትል ፡ ወረዳ" ፡ ነው ። ከወረዳ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ የአገር ፡ አገዛዝ ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ "አውራጃ" ፡ ነው ።
4. በ፲፱፻፴፱ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ አጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ሹመት ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፺
5. ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፲ ።
6. የኤርትራ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አንድ ፡ ክርክር ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ በሚሰሙበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ይኖራቸዋል ። በይግባኝ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ዳኞቹ ፡ ሦስት ፡ ይሆናሉ ።

ካለመክፈል ፡ ወይም ፡ በዕቁብ ፡[7] ውል ፡ ለመርጋት ፡ ፈቃደኛ ፡ ካለመሆን ፡ ሊነሱ ፡ ይችላሉ ። የውዝፍ ፡ ኪራይ ፡ ክርክሮችም ፡ የተለመዱ ፡ ናቸው ።

በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከሚሰሙት ፡ የወንጀል ፡ ነገሮች ፡ ቁጥራቸው ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያሉቱ ፡ ክሳቸው ፡ በተጎጂው ፡ አቤቱታ ፡[8] የቀረበ ፡ ሲሆን ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ የእጅ ፡ እልፊትን ፡ ስድብን ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለፈቃድ ፡ መግባትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። የከተማ ፡ ደንቦችን ፡ በመጣስ ፡ በሕዝብ ፡ ጤንነትና ፡ በትራፊክ ፡ ሥርዓቶች ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙት ፡ ድርጊቶች ፡ ለነዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይቀርባሉ ። በስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ተጠርጥረው ፡ የተያዙትን ፡ ሰዎች ፡ ፖሊሶች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ ተከሳሹ ፡ በፖሊስ ፡ በተያዘ ፡ በ፵፰ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ አለበት ፡ የሚለውን ፡ የ፵፰ ፡ ሰዓት ፡ ወሰን ፡ ለማሟላት ፡ ሲሉ ፡ በዚሁ ፡ ቁጥር ፡ መሠረት ፡ እወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርቧቸዋል ።

ለአንድ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚቀርቡት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክሮች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የርስት ፡ ውርስን ፡ የገንዘቡ ፡ መጠን ፡ ከወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን፡ ላቅ ፡ ያለ ፡ የብድር ፡ ክርክርን ፡ በሰው ፡ ወይም ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ የካሣ ፡ ጥያቄን ፡ በስምምነት ፡ የተፈጸመ ፡ የፍቺ ፡ ውል ፡ የማጽናት ፡ አቤቱታንና ፡ የድንበር ፡ ክርክሮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።

በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከተሰሙት ፡ የወንጀል ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ብዙዎቹ ፡ የስርቆት ፡ ክሶች ፡ የቀረቡት ፡ በዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በኩል ፡ ነው ።

በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰሙ ፡ ቍጥራቸው ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ክርክሮች ፡ በተጎጂው ፡ አቤቱታ ፡ አማካይነት ፡ ለክስ ፡ ቀርበዋል ። እነዚህም ፡ በአንድ ፡ ሰው ንብረት ፡ ላይ ፡ ያለፈቃድ ፡ መግባትን ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ማድረስንና ፡ ከፍተኛ ፡ የእጅ ፡ እልፊትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ከባድ ፡ ክሶች ፡ ናቸው ። በአውራጃ ፡ ፍርድ ቤቶች ፡ ከሚሰሙት ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ብዙዎቹ ፡ በክፍላቸው ፡ ካሉት ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ቤቶች ፡ የሚቀርቡ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ይግባኞች ፡ ናቸው ።

ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በትልቅ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ እንዳቀማመጣቸው ፡ ሁኔታ ፡ የተለያዩ ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክሮችን ፡ ይሰማሉ ። አንድ ፡ ዳኛ ፡ ከሚቀርቡላቸው ፡ ነገሮች ፡ ሰማንያ ፡ በመቶው ፡ የትራፊክ ፡ ጉዳዮች ፡ የሆኑበትን ፡ ምክንያት ፡ ሲናገሩ ፡ ፍርድ ፡ ቤታቸው ፡ በብዙ ፡ የትራፊክ ፡ መብራቶች ፡ አቅራቢያ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ፡ ብለዋል ። በገበያና ፡ በኢንዱስትሪ ፡ ሥፍራዎች ፡ አካባቢ ፡ ያሉ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብዙ ፡ የድብደባና ፡ ያለፈቃድ ፡ በሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ የመግባት ፡ ክሶችን ፡ ይሰማሉ ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ አካባቢ ፡ በሚገኘው ፡ ትልቅ ፡ ፋብሪካ ፡ ባለበት ፡ በአቃቂ ፡ ከተማ ፡ በሠራተኛና ፡ በአሠሪ ፡ መካከል ፡ የሚነሱ ፡ ክርክሮች ፡ የተለመዱ ፡ መሆናቸው ፡ ተጠቅሷል ። የአዲስ ፡ አበባ ፡ አካል ፡ በሆነው ፡ በአዲስ ፡

---

7. ዕቁብ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰበሰብበት ፡ በፈቃደኝነት ፡ የሚመሠረት ፡ ማህበር ፡ ነው ። ዕቁብተኞቹ ፡ የሚደርስባቸውን ፡ የሳምንት ፡ ክፍያ ፡ ያዋጡና ፡ ዕጣ ፡ ይጥላሉ ። ባለዕጣው ፡ የተሰበሰበውን ፡ ገንዘብ ፡ ይወስዳል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሳምንቱ ፡ ባለዕጣ ፡ በሚቀጥለው ፡ ሳምንት ፡ ዕቁቡን ፡ አልጥልም ፡ ይላል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የዕቁብ ፡ "ዳኛው" ፡ አልከፍልም ፡ ባዩን ፡ ዕቁብተኛ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሶ ፡ ዕቁቡ ፡ ሲገባ ፡ በጽሑፍም ፡ ሆነ ፡ በቃል ፡ እስከተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በየሳምንቱ ፡ እከፍላለሁ ፡ ያለውን ፡ በገባው ፡ ውለታ ፡ መሠረት ፡ እንዲከፍል ፡ ያስገድደዋል ።

8. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፯— ፪፻፳፩ ፡ እና ፡ ፪፻፳፭ ።

ከተማ ፡ ውስጥም ፡ ባልተከለለ ፡ ድንበርና ፡ ተፋፍገው ፡ በመኖር ፡ ምክንያት ፡ የተነሳ ፡ ያለፈቃድ ፡ በሰው ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በመግባት ፡ የሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ የተለመዱ ፡ ናቸው ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ በሌላው ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ የስድብ ፡ ክሶች ፡ ልቀው ፡ ይገኛሉ ። የቀበሌው ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ስለዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ክስ ፡ ብዛት ሲናገሩ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እዚያ ፡ ቢሰደብ ፡ አካባቢው ፡ የመኖሪያ ፡ ሥፍራ ፡ በመሆኑ ፡ ወንጀለኛው ፡ የት ፡ እንደሚገኝ ፡ ስለሚያውቅ ፡ ነው ፡ ብለዋል ። በስድብ ፡ ምክንያት ፡ የሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ መጠነኛ ፡ በሆኑበት ፡ በአዲስ ፡ ከተማ ፡ እንደሆነ ፡ የኑዋሪዎቹ ፡ መተዋወቅ ፡ በጣም ፡ የጠበቀ ፡ ካለመሆኑም ፡ በላይ ፡ ለተሳዳቢዎቹ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መኖሪያ ፡ ለመስጠት ፡ አድራሻቸውን ፡ ለማወቅ ፡ አይቻልም ።

የድንበር ፡ ክርክርና ፡ ውርስን ፡ የሚመለከቱ ፡ ርስት ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ክሶች ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ የበዙትን ፡ ያህል ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የተለመዱ ፡ አይደሉም ።

## የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሕንፃ ።

ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሕንፃዎች ፡ በፈራረሰ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ። በከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሕንፃዎች ፡ ብዙዎቹ ፡ የጣሊያን ፡ ወረራ ፡ ቅርስ ፡ የሆኑ ፡ የድንጋይ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ። በየባላገሩ ፡ የሚገኙት ፡ ግን ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከጭቃ ፡ የተሠሩ ፡ ሆነው ፡ የአፈር ፡ ወለል ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

ባንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ዳኞች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ የተለያዩ ፡ ጉዳዮችን ፡ በሚሰሙበት ፡ ወቅት ፡ ተሟጋቾችና ፡ ተመልካቾች ፡ መቀመጫዎቹን ፡ ያጣብባሉ ። ሰዎች ፡ ቅጣታቸውን ፡ ለመክፈልም ፡ ሆነ ፡ የአቤቱታ ፡ ማመልከቻቸው ፡ በቅጹ ፡ መሠረት ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ስለሚዘዋወሩና ፡ የጸሐፊዎቹም ፡ ወንበር ፡ (መቀመጫ) ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ በመሆኑ ፡ ለትፍግፍጉ ፡ ተጨማሪ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖአል ። የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ቢሮ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ ቢሮም ፡ ያገለግላል ። ጸሐፊዎቹ ፡ ማንኛውንም ፡ መዝገብ ፡ በአምስት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ለማውጣት ፡ እንደሚችሉ ፡ ይናገራሉ ። ግን ፡ መዝገቦቹ ፡ የሚቀመጡት ፡ ባንድ ፡ በተለየ ፡ ቦታ ፡ ቢሆንም ፡ ለውጭ ፡ ተመልካች ፡ በጣም ፡ የተዘበራረቀ ፡ መስሎ ፡ በሚታይ ፡ አኳኋን ፡ ነው ።

ለተሟጋቾች ፡ ማመልከቻ ፡ የሚጽፉ ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሚቀመጡት ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ በወንበሮች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በትናንሽ ፡ ጐጆዎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

## በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥና ፡ አካባቢ ፡ ስላሉ ፡ ሠራተኞች ።

በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ክስ ፡ የሚጀመረው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ በማቅረብ ፡ ነው ። አንድ ፡ የተሟላ ፡ ማመልከቻን ፡ በመጻፍ ፡ አንድ ብር ፡ ተኩል ፡ የሚጠይቁት ፡ በግላቸው ፡ የሚሠሩት ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ጠበቃ ፡ ለሌላቸውም ፡ ሆነ ፡ በሕግ ፡ ችሎታቸው ፡ ለማይተማመኑ ፡ ተሟጋቾች ፡ የክስ ፡ ማመልከቻና ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ በመጻፍ ፡ አገልግሎት ፡ ይሰጣሉ ።

በጠቅላላው ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አዘውትረው ፡ ወረዳና ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ትክክለኛውን ፡ የሕግ ፡ ቁጥር ፡ ለመጥቀስ ፡ የሚያስችላቸው ፡ በቂ ፡ የመጻፍና ፡ የማንበብ ፡ ችሎታ ፡ አላቸው ። አንዳንዶቹ ፡ የራሳቸው ፡ የሆነ ፡ የሕጐች ፡ አርእስተ ፡ ጉዳይ ፡ ማውጫና ፡ የማመልከቻ ፡ አጻጻፍ ፡ ቅጽ ፡ አላቸው ። ሌሎቹ ፡ በፍትሐብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ቅጽ ፡ ይከተላሉ ።

በሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊነት ፡ ለመሥራት ፡ በሚፈልጉበት ፡ ጊዜ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ እንዲፈቅድላቸው ፡ ማመልከት ፡ ቢኖርባቸውም ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊዎችን ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ሆነ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አይቆጣጠራቸውም ። ቢሆንም ፡ የክስ ፡ ማመልከቻም ፡ ሆነ ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ ሲጽፉ ፡ ስኅተት ፡ ቢያደርጉ ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ሊገስጻቸው ፡ ይችላል ።

በተጨማሪም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥና ፡ አካባቢ ፡ መሥራትን ፡ ሙያቸው ፡ አድርገው ፡ የያዙ ፡ ለተሟጋቾች ፡ የሚቆሙ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። እነርሱም ፡ ሲከፈሉ ፡ ሁለት ዓይነት ፡ ናቸው ። "ጠበቃ"፡ ሙያው ፡ ጥብቅና ፡ በመሆኑ ፡ ለግል ፡ ተሟጋቾች ፡ ይቆማል ። እርሱም ፡ ይህንኑ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ፈቃድ ፡ ያለው ፡ ነው ።[9] አንድ ፡ ጠበቃ ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚሰጥ ፡ ፈተና[10] ፡ መውሰድና ፡ በያመቱ ፡ የመመዝገቢያ ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ ይኖርበታል ። ጠበቆች ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በሚወስነው ፡ የችሎታ ፡ አርከን ፡ መሠረት ፡ ደረጃቸው ፡ በተለያየ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ይመዘገባሉ ።

ሌሎቹ፡ ሰዎችን፡ የሚወክሉት፡ የሕግ፡ ባለሙያዎች፡ "ወኪል"[11] በመባል ፡ የታወቁት ፡ ወይም ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ በተለመደው ፡ አነጋገር ፡ "ነገረ ፡ ፈጅ"፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። ነገረ ፡ ፈጆች ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ሲሆኑ ፤ አንደኛው ፡ ዓይነት ፡ በሙያቸው ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ የሆኑ ፡ ሁለተኛው ፡ ደግሞ ፡ ነገረ ፡ ፈጅነት ፡ ሙያቸው ፡ ያልሆኑ ፡ ናቸው ። በሙያቸው ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ የሆኑት ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ወይም፡ ባለቤቶቻቸው ፡ መቅረብ ፡ በሚያስፈልግበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የማይኖሩትን ፡ ማኅበሮች ፡ በመወከል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባሉ ።[12] እነርሱም ፈተና ፡ ማለፍ ፡ ሳያስፈልጋቸው ፡ የቀጠራቸውን ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የግል ፡ ድርጅት ፡ በመወከል ፡ ባለማቋረጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባሉ ። እንደ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤትና ፡ እንዳገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ላሉ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሠሩት ፡ የተወሰነ ፡ ሥራ ፡ አላቸው ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤትን ፡ በመወከል ፡ የጽዳት ፡ ደንቦችን ፡ የተላለፉትን ፡ ሰዎች ፡ ሲከስ ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ ግብራቸውን ፡ በወቅቱ ፡ ሳይከፍሉ ፡ በቀሩት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ለማስፈረድ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴርን ፡ ይወክላል ።

ሌሎቹ ፡ በሙያቸው ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ያልሆኑት ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ አባሎችን ፡ በመወከል ፡ ይቀርባሉ ። እነርሱም ፡ በተሟጋችነት ፡ ችሎታቸው ፡ በዘመዶቻቸው ፡ ተመርጠው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ ሊሟገቱ ፡ ይችላሉ ። እነዚህ ፡ የቤተሰብ ፡ ተሟጋቾች ፡ ለድካማቸው ፡ ዋጋ ፡ እንዲቀበሉ ፡ አይፈቀድላቸውም ።[13]

9. ስለጠበቆች ፡ በመዝገብ ፡ መግባት ፡ የወጣ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ደንብ ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፻፸፯ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፰ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ ።

10. በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ይህ ፡ ፈተና ፡ እንደ ፡ "ግብር ፡ አበር ፡ ምንድነው ?" "የማይንቀሳቀስ ፡ ሽያጭ ፡ ውል ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ተፈፃሚነት ፡ የሚኖረው ፡ መቼ ፡ ነው"፡ እና ፡ "የውርስን ፡ አለመቀበል ፡ (መተው) ፡ ተፈፃሚነት ፡ የሚኖረውና ፡ የማይኖረው ፡ መቼ ፡ ነው ?" የሚሉ ፡ ጥያቄዎች ፡ ነበሩበት ። አበራ ፡ ባንቲዋሉ ፡ የዳኝነት ፡ ቦታ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (ያልታተመ)፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ለሚሚያ ፡ የተዘጋጀ ፡ ጽሑፍ ።

11. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፺፰ ፡

12. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፺፰ ፡ እና ፡ ፺፱ ፡

13. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፺፰ ፡

በተጨማሪም ፡ እያንዳንዱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሥራው ፡ ባለሙያ ፡ የሆኑ ፡ ሠራተ
ኞች ፡ አሉት ። እነርሱም ፡ ዳኞች ፡ መዝገብ ፡ ገልባጮች ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ጸሐፊ
ዎች ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹሞችና ፡ ተላላኪዎች ፡ ናቸው ።

እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሠራተኞች ፡ ተቀጥረው ፡ የሚተዳደሩት ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡
ነው ።

## <u>የፍትሐብሐር ፡ ሙግት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ።</u>

አንድ ፡ ተሟጋች ፡ በከሳሽነት ፡ ክሱን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲያቀርብም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በተከሳሽነት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ ሲጠራ ፡ የሚወሰደው ፡ የመጀመሪያ ፡ እርምጃ ፡ ማመልከቻውን ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊ ፡ ማጻፍ ፡ ነው ።[14]

አንድ ፡ ተሟጋች ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊ ፡ ሲቀርብ ፤ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊው ፡ ክርክሩን ፡ ለመተንተን ፡ ይሞክራል ። የክርክሩን ፡ ትክክለኛ ፡ አመጣጥ ፡ አውቆ ፡ ጠቃሚውን ፡ የሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ለመጥቀስ ፡ ይረዳው ፡ ዘንድ ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊው ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ እንደሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥያቄዎችን ፡ ለተሟጋቹ ፡ ያቀርባል ። ለምሳሌ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ገንዘብ ፡ አበድሮ ፡ ተበዳሪው ፡ አልከፍል ፡ በማለቱ ፡ ምክንያት ፡ በቀረበ ፡ የገንዘብ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊው ፡ ተከሳሹ ፡ ገንዘቡን ፡ መበደሩን ፡ ማመን ፡ አለማመኑን ፤ የብድሩ ፡ ውል ፡ በጽሑፍ ፡ መሆኑን ፡ አለመሆኑን ፤ ተከሳሹ ፡ አልከፍልም ፡ ያለበትን ፡ ምክንያት ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የትኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ሲል ፡ ውሉ ፡ የት ፡ እንደተፈጸመና ፡ ተከሳሹ ፡ የት ፡ እንደኖረ ፡ ይጠይቃል ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚደረገው ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊው ፡ ማመልከቻውን ፡ ሲጽፍ ፡ ተሟጋቹ ፡ ተቀምጦ ፡ ይጠብቃል ። ማመልከቻው ፡ ከሳሽ ፡ የሚጠይቀውን ፡ ዳኝነትና ፡ የፍትሐብሐር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ የሚጠይቃቸውን ፡ ነገሮች ፡ መያዝ ፡ አለበት ።[15] በመሠረቱ ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ የከሳሽና ፡ የተከሳሽ ፡ ስምና ፡ አድራሻ ፡ "ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮችና ፡ እነዚሁም ፡ የተፈጠሩበት ፡ ጊዜና ፡ ሥፍራ" ፤ "ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነገሩን ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ስለመሆኑ ፡ የሚያስረዳውን ፡ ሁኔታ ፡" ፤ እና ፡ "ተከሳሹ ፡ ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ አግባብ ፡ እንዳለው ፡ ወይም ፡ ተጠሪ ፡ የሚሆንበትን ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ለሚቀርበው ፡ ክርክር ፡ በአላፊነት ፡ የሚጠየቅበትን ፡ ሁኔታ ፡"[16] መግለጽ ፡ ናቸው ። ከክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ጋር ፡ የምስክሮች ፡ ስምና ፡ ለክሱ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ሰነድ ፡ ተያይዘው ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ።[17]

የመከላከያው ፡ መልስ ፡ ክሱ ፡ የቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ ከሆነ ፡ ይህንኑ ፡ መጥቀስና ፡ ተከሳሹም ፡ ለመከላከያው ፡ የሚረዳውን ፡

---

14. የፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፫ ፡ "ማናቸውም ፡ ክስ ፡ እንደቀረበ ፡ የሚቆጠረው ፡ ዳኝነት ፡ እንዲታይ ፡ የሚጠየቅበት ፡ የክስ ፡ ጽሑፉ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ነው" ፡ ይላል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፴፫ ፡ እና ፡ ፪፻፴፬ ፡ መጥሪያ ፡ የተሰጠው ፡ ተከሳሽ ፡ የመከላከያ ፡ መልሱን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ያዛሉ ።

15. የፍትሐ ፡ ብሐር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፩ ፡

16. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፬ ።

17. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፫ ።

ፍሬ ፡ ነገር ፡ መያዝ ፡ ይኖርበታል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ተከሳሹ ፡ ከዚሁ ፡ ጋር ፡ የምስክሮቹን ፡ ስምና ፡ ይጠቅመኛል ፡ የሚለውን ፡ ሰነድ ፡ አባሪ ፡ አድርጎ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።[18]

ተሟጋቹ ፡ ከሳሽ ፡ ከሆነ ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊው ፡ የሚጽፈውን ፡ ማመልከቻ፡ ለተከሳሾቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዲዳረስ ፡ አድርጎ ፡ ያራባዋል ። ተሟጋቹም ፡ እነዚህን ፡ ማመልከቻዎች ፡ ይወስድና ፡ ለመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ያቀርባል ፤ ሹሙም ፡ ማመልከቻዎቹ ፡ በፍትሐብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ና ፡ ፪፻፳፫ ፡ መሠረት ፡ የተጻፉ ፡ መሆናቸውን ፡ ይመረምራል ። የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ እነዚህ ፡ ማመልከቻዎች ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ተሟልተው ፡ ያልተገኙ ፡[19] ሆነው ፡ ከታዩት ፡ ላይቀበላቸው ፡ ይችላል ። ቢሆንም ፡ የተሟጋቹ ፡ አዲስ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ የመጻፍ ፡ መብቱ ፡ እንደተጠበቀ ነው ።[20]

የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ የከሳሽን ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ የተቀበለው ፡ እንደ ሆነ ፡ የዳኝነት ፡[21] ከተከፈለ ፡ በኋላ ፡ ፋይሉ ፡ ይከፈታል ።[22]

መጥሪያ ፡ ማስወጣት ፡ ገንዘብ ፡ የሚያስከፍልና ፡ መጥሪያውንም ፡ ጽፈው ፡ ወጪ፡ ለሚያደርጉት ፡ ጸሐፊዎች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ መለማመጫ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያስፈልግ፡ በመሆኑ ፡ ከሳሽ ፡ ባላጋራውን ፡ ያለፍርድ ፡ ቤት ፡ መጥሪያ ፡ በማግባባት ፡ ለማቅረብ ፡ ይሞክራል ። ተከሳሹ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ያልቀረበ ፡ እንደሆነ ፤ ከሳሹ ፡ መጥሪያ ፡ አስወጥቶ ፡ ይሰጠዋል ። በመጥሪያውም ፡ ያልቀረበ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፖሊሶች ፡ አስገድደው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርቡታል ።

እንደ ፡ ደንቡ ፡ ምስክሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ መጥሪያ ፡ የሚላክላቸው ፡[23] ይቅረቡልኝ ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ ማቅረብ ሲያቅተው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለአንድ ፡ ምስክር ፡ መጥሪያ ፡ መላክ ፡ ያስፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ መጥሪያው ፡ ለምስክሩ ፡ የሚሄድለት ፡ ይቅረብልኝ ፡ በሚለው ፡ ተሟጋች ፡ እጅ ፡ ነው ።

ክርክሮች ፡ የሚሰሙበት ፡ ተራ ፡ እንደ ፡ አመጣጣቸው ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ የተከፈተ ፡ ፋይል ፡ ነገሩ ፡ መጀመሪያ ፡ ይሰማል ። የተሟጋቹ ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ በመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ክርክሩ ፡ መቼ ፡ እንደሚሰማ ፡ ይነገረዋል ። የክሱ ፡ መዝገብ ፡ በሚከፈትበትና ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ በሚቀርብበት ፡ ወቅት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የጊዜ ፡ ልዩነት ፡ ከአንድ ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ይሆናል ።

ክርክሩ ፡ ሊሰማ ፡ መዝገቡ ፡ ሲቀርብ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ቀርበው ፡ እንደሆነ ፡ ብዙዎቹ ፡ ዳኞች ፡ ለየቀን ፡ ሥራቸው ፡ አስቀድመው ፡ ተዘጋጅተው ፡ ስለማይመጡ ፡ ዳኛው ፡ በመጀመሪያ ፡ የክሱን ፡ ማመልከቻና ፡ የመከላከያ ፡ መልሱን ፡ ያነባል ። ዳኛው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነገሩን ፡ ካጠናው ፡ በኋላ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ለክርክሩ ፡ የየበኩላቸውን ፡ ሃሳብና ፡ ቢያስፈልግም ፡ ምስክሮችን ፡ ያቀርባሉ ። ዳኞች ፡

---

18. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፴፩ ።
19. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፱ ።
20. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፴፪ (፪) ።
21. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፮ ።
22. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፷፯ ፡ እስከ ፡ ፬፻፹ ፡ መሠረት ፡ በድሆች ፡ ሊቀርቡ ፡ ይችላሉ ።
23. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፩ ።

በክርክሩ ፡ አካሄድ ፡ ላይ ፡ ዓይለው ፡ ከመታየታቸውም ፡ ሌላ ፡ ለተሟጋቾቹና ፡ ለምስክሮቹ ፡ ከሚቀርቡት ፡ መስቀልኛ ፡ ጥያቄዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ የሚሰነዘሩት ፡ ከነርሱው ፡ ነው ። በክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠውን ፡ የምስክር ፡ ቃል ፡ ዳኛው ፡ ይመዘግባል ፤ አንዳንዴም ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ምዝገባ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ይሆናል ።

ክሱ ፡ ያልተወሳሰበ ፡ ከሆነና ፡ ዳኛው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ማሰብ ፡ ሳያሻው ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ የሚችል ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ማስረጃቸውን ፡ በሙሉ ፡ አቅርበው ፡ እንደሆነ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ። አለበለዚያ ፡ ግን ፡ የክሱን ፡ ፍሬ ፡ ነገርና ፡ የሕጉን ፡ ጭብጦች ፡ ተመልክቶ ፡ ውሳኔውን ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ ይሰጣል ። ውሳኔዎችን ፡ መጻፍ ፡ ብዙ ፡ ጊዜን ፡ ይፈጃል ፤ ዳኛው ፡ ውሳኔዎችን ፡ የሚጽፈው ፡ ተሟጋቾቹ ፡ ክርክራቸውን ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ጥዋት ፡ ችሎቱ ፡ ከመቀጠሉ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥራ ፡ ቀለል ፡ ሲል ፡ ነው ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የአንድን ፡ ሙግት ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ከሦስት ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ቀጠሮዎች ፡ ያስፈልጋሉ ። በብዙዎች ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ከተከራካሪዎች ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ምስክሮች ፡ ባለመቅረባቸው ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ዳኛው ፡ እንዲያያቸው ፡ በቀረቡት ፡ ክሶች ፡ ብዛት ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ ቀጠሮ ፡ ይሰጣል ። የተረታው ፡ ወገን ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ የሚሻ ፡ ከሆነ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይህንኑ ፡ ፍላጎቱን ፡ ፍርዱ ፡ እንደተሰጠ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለዳኛው ፡ ያስታውቃል ።

ከዚያም ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የተዘጋጀ ፡ የመጀመሪያውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የክርክር ፡ መዝገብ ፡ ግልባጭ ፡ መያዝ ፡ ይኖርበታል ። (ለዚህ ፡ የመገልበጥ ፡ ሥራ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖርም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ለጸሐፊዎቹ ፡ የተለየ ፡ "ችሮታ" ማድረግ ፡ ያስፈልጋል) ። ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ይግባኝ ፡ ያለበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚገልጸውን ፡ የይግባኝ ፡ ማመልከቻ ፡ የሚጽፉት ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ናቸው ። ተሟጋቹ ፡ የመዝገቡን ፡ ግልባጭና ፡ የይግባኙን ፡ ማመልከቻ ፡ ለይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርባል ።

<u>የወንጀል ፡ ሙግት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡</u>

በወረዳና ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ብዙዎቹ ፡ በየፖሊስ ፡ ጣቢያው ፡ በግል ፡ አቤቱታ ፡ መልክ ፡ የሚነሱ ፡ የወንጀል ፡ ክሶች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ክሶች ፡ የሚነሡት ፡ የሰውነት ፡ መብትና ፡ የንብረት ፡ መብት ፡ መድፈርን ፡ ወይም ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ ስድብን ፡ በሚከለክሉት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ በሕግና ፡ ደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ ቊጥሮች ፡ መሠረት ፡ ነው ። ተጐጂው ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ተበደልሁ ፡ ባዩ ፡ ለፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ አቤት ፡ እስኪል ድረስ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በእንዲህ ፡ ያሉት ፡ ወንጀሎች ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ አይችልም ።[24]

እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ አቤቱታ ፡ በማቅረብ ፡ ወደ ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ የሚያመራ ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግለት ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ቀበሌው ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ሄዶ ፡ ክሱን ፡ ያስመዘግባል ። አቤቱታው ፡ በመሥሪያ ፡

24. ፒ. ግራቨን ፡ "ለመክሰስ ፡ መብተኛ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ አቤቱታ ፡ ሲቀርብ ፡ ብቻ ፡ የክሱን ፡ ጉዳይ ፡ ለመከታተል ፡ የሚቻልባቸው ፡ ወንጀሎች" ፡ የኢት. የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ገጽ ፡ ፩፻፲፩ ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ቊ. ፩ ፡ ይመለከቷል ።

ቤቱ ፡ ሠራተኞች ፡[25] ይጻፍና ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ይፈርምበታል ። መርማሪው ፡ ፖሊስ ፡ "የወንጀል ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሟል ፡ የሚያሰኝ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ በሚገኝ ባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ ሁሉ ፡ የተባለውን ፡ ሰው ፡ አቅርቦ ፡[26]" ለመጠየቅ ፡[27] ይችል ፡ ዘንድ ፡ መጥሪያ ፡ ለመላክና ፡ ከቀረበም ፡ በኋላ ፡ የዋስትና ፡ ወረቀት ፡ እንዲፈርም ፡ ወይም ፡ በተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያሲዝ ፡[28] ለማድረግ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

የምርመራው ፡ ውጤት ፡ ለዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡[29] ይተላለፍና ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ተጠ ርጣሪውን ፡ ጥፋተኛ ፡ የሚያደርግ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ መኖር ፡ አለመኖሩን ፡ ይመ ረምራል ። በቂ ፡ ማስረጃ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ከወሰነ ፡ ክሱን ፡ ራሱ ፡ ይከፍታል ።

ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ፈቃደኛ ፡ ካልሆነ ፡ ጉዳዩ ፡ ከሚያገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ በተለይ ፡ ተበዳዩ ፡ ራሱ ፡ የተበደለው ፡ ሰው ፡ እንደራሴ ፡ የተበዳዩ ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ባል ፡ የግል ፡ ክስ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ሊፈቅድላቸው ፡ ይችላል ።[30]

ስለዚህ ፡ በግል ፡ አቤቱታ ፡ አማካይነት ፡ በተነሣ ፡ በአንድ ፡ የወንጀል ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ ለተበዳዩ ፡ ወገን ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ጠበቃው ፡ ሊሆንለት ፡ ይችላል ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ፈቃደኛ ፡ ሳይሆን ፡ ሲቀር ፡ ክሱን ፡ በግላ ቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚያቀርቡት ፡ የግል ፡ አቤት ፡ ባዮች ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። በመሰላቸው ፡ መንገድ ፡ ለመሟገት ፡ የሚፈልጉ ፡ የግል ፡ አቤት ፡ ባዮች ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚከፍሉት ፡ ገንዘብ ፡ ለሙግቱ ፡ በሚጠፋው ፡ ጊዜና ፡ ጉልበት ፡ ምክንያት ፡ ብቻቸውን ፡ ከመሟገት ፡ ይታገዳሉ ።

በግል ፡ አቤቱታም ፡ ሆነ ፡ በዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ከሳሽነት ፡ ክስ ፡ የቀረበባቸው ፡ የወ ንጀል ፡ ተከሳሾች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ ይገጥማቸዋል ። ለሁ ለቱም ፡ ዓይነት ፡ ተከሳሾች ፡ የመጀመሪያው ፡ ችግር ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ከታሠሩ ፡ ወይም ፡ "ከተጠሩ" ፡ በኋላ ፡ የሚያስይዙት ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘቱ ፡ ወይም ፡ ዋስ ፡[31] ማቅረቡ ፡ ነው ። በግል ፡ አቤቱታ ፡ በወንጀል ፡ ነገር ፡ ተከሳሽ ፡ ሆነው ፡ ወረዳና ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከሚቀርቡት ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎቹ ፡ በራሳቸው ፡ የዋስትና ፡ ገንዘብ ፡ ለማስያዝ ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ። ቢሆንም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዋስ ፡ ማቅረብ ፡ አያቅታቸውም ። ግን ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ ወንጀልን ፡ ፈጽመው ፡ በዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በኩል ፡ ክስ ፡ የቀረበባቸው ፡ ተከሳሾች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በሌብነት ፡ የተከሰሱ ፡ ወሮበሎች ፡ ወይም ፡ ለተከሰሱበት ፡ ቀበሌ ፡ ባይተዋር ፡ ስለሚሆኑ ፡ የሚያስይዙት ፡ ገንዘብም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ዋስ ፡ የሚሆናቸው ፡ ሰው ፡ ለማግኘት ፡ አይችሉም ። ስለ ዚህ ፡ ብዙ ፡ ተከሳሾች ፡ የፖሊስ ፡ ምርመራ ፡ አልቆ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እስከሚቀርቡ በት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ መቆየት ፡ ይኖርባቸዋል ። ተከሳሹን ፡ በዋስ ፡ ለመልቀቅም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ቢያስፈልግ ፡ ለምርመራው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ለመፍ ቀድ ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፖሊስ ፡ ተከሳሹን፡

25. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፲፬ ።
26. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ።
27. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፳፯ ፡ (፩) ።
28. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፳፰ ፡ (፩) ።
29. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፴፯ ፡ (፪) ።
30. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፵፬ ፡ እና ፡ ፵፯ ።
31. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ።

በተያዘ ፡ በ፵፰ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡[32] ወደ ፡ አቅራቢያው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ፡ ቢልም ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ የማይሰራበት ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ቢሰራበትም ፡ እንኳን ፡ ፖሊስ ፡ ምርመራው ፡ እስኪያልቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ይጠይቃል ።[33] ፖሊሶች ፡ ይህንኑ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ለመጠየቅ ፡ ከፈለጉ ፡ የፈለጉትን ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ደጋግመው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላሉ ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ ክሱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ተከሳሹ ፡ እምነት ፡ ክህደት ፡ ይጠየቃል ። ጥፋተኛነቱን ፡ ካመነ ፡ ውሳኔ ፡ ተሰጥቶ ፡ ፋይሉ ፡ ይዘጋል ። ግን ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ካለ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክርክሩን ፡ ለመቀጠል ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የማይዘጋጅ ፡ በመሆኑ ፡ ተከሳሹ ፡ ያለው ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ከሆነ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክርክሩን ፡ እስኪያዘጋጅ ፡ ማለት ፡ እስከሚቀጥለው ፡ ቀጠሮ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲመለስ ፡ ይደረጋል ።

አንዳንዴም ፡ ተከሳሹ ፡ ምስክሮቹን ፡ በወቅቱ ፡ ለማቅረብ ፡ ባለመቻሉ ፡ ምክንያት ፡ ለክሱ ፡ መዘግየት ፡ (መራዘም) ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ። ዳኞች ፤ ተከሳሾች ፡ ክርክራቸውን ፡ በጣም ፡ ቀና ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ለማቅረብ ፡ እንዲመቻቸው ፡ ምስክሮቻቸውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችሉ ፡ ዘንድ ፡ እንደፈለጉ ፡ ቀጠሮ ፡ ይሰጧቸዋል ።

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፶፪ ፡ በወንጀል ፡ የተከሰሰ ፡ ሰው ፡ "ስለ ራሱ ፡ ለመከላከል ፡ የጠበቃ ፡ ረዳትነት ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ በራሱ ፡ ችሎታ ፡ ወይም ፡ በገንዘቡ ፡ ጠበቃ ፡ ለመግዛት ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ በሚወሰነው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠበቃ ፡ ያቆምለታል" ፤ ቢልም ፡ በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚቀርቡት ፡ ተከሳሾች ፡ ከመቶ ፡ ዘጠናው ፡ ጠበቃ ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ። ከነዚህም ፡ ተከሳሾች ፡ ብዙዎቹ ፡ ምናልባት ፡ በራሳቸው ፡ ገንዘብ ፡ ጠበቃ ፡ ለመግዛት ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ። ለድሀው ፡ ተከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ ማቆም ፡ ያስፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ በጠበቆች ፡ አመራረጥ ፡ ረገድ ፡ በልማድ ፡ ዳኛው ፡ የሚከተለው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ አንዱን ፡ ጠበቃ ፡ እንዲቆም ፡ ማዘዝ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ትዕዛዝ ፡ የሚሰጠው ፡ በሁለት ፡ ምክንያት ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው ።

አንደኛ ፡ ገንዘብ ፡ ሳይከፍሉ ፡ በነጻ ፡ ጠበቃ ፡ ለማግኘት ፡ መቻላቸውን ፡ የማያውቁ ፡ ድሆች ፡ የወንጀል ፡ ተከሳሾች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ጠበቃ ፡ እንዲቆምላቸው ፡ አይጠይቁም ፤ ዳኛውም ፡ ተሟጋቹ ፡ ካልጠየቀ ፡ በቀር ፡ ጠበቃ ፡ ለማቆም ፡ የሚቻልበትን ፡ መንገድ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይናገርም ።

ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፶፪ ፡ በሙሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ የሚያደርገው ፡ ሌላው ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡት ፡ የወንጀል ፡ ነገሮች ፡ ብዛትና ፡ ጥቃቅንነት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ አንድ ፡ ተከሳሽ ፡ በጐረቤትህ ፡ እንጀራ ፡ ላይ ፡ ውሀ ፡ አፍስሰሃል ፡ በመባል ፡ በወንጀል ፡ ተከሶ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ። በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ የበዙት ፡ የስድብ ፡ ክሶች ፡ ሲሆኑ ፡ ውጤት ፡ የሌላቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ በነዚህ ፡ ወንጀሎች ፡ የተከሰሱ ፡ ሰዎች ፡ ጠበቃ ፡ ለማቆም ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ። ቢሆንም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ቀርቦ ፡ ከሳሽን ፡ በመደገፍ ፡ ሲሟገት ፡ ተከሳሹ ፡ ሊቋቋመው ፡ አይች

32. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ።

33. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፶፱ ።

ልም ። በግል ፡ አቤቱታ ፡ በቀረቡ ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ በጠበቃ ፡ ማቆም ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ እንዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ አለመስተካከል ፡ የፍትሕ ፡ መጓደልን ፡ የሚያስከትል ፡ ቢሆንም ፡ ለማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ክርክር ፡ ጠበቃ ፡ ማቆሙ ፡ ደግሞ ፡ በዘመኑ ፡ የሕግ ፡ ባለሙያዎች ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ እንደሚሆንና ፡ እንዲቆሙ ፡ ከታዘዙት ፡ ጠበቆች ፡ ጋር ፡ ለመመካከሪያና ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረቢያ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ ያለውን ፡ የቀጠሮ ፡ ብዛት ፡ ከፍ ፡ እንደሚያደርገው ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠበቃ ፡ ሳያቆምለት ፡ በወንጀል ፡ ክስ ፡ የተከሰሰ ፡ ሰው ፡ ጠበቃ ፡ እንዳቆመለት ፡ የሚቆጠረው ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ በክሱ ፡ ላይ ፡ በጣም ፡ ከመጫን ፡ ሲቆጠብ ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ዳኞች ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የከሳሽን ፡ ምስክሮች ፡ በተከሳሽ ፡ ወገን ፡ ሆኖ ፡ መስቀልኛ ፡ ጥያቄ ፡ እንዲጠይቅና ፡ በጠቅላላ ፡ አኳኋን ፡ ለተከሳሹ ፡ ሆኖ ፡ እንዲናገር ፡ ያዙታል እየተባለ ፡ ይነገራል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ አያሌ ፡ ድሆች ፡ የወንጀል ፡ ተከሳሾች ፡ በራሳቸው ፡ የክርክር ፡ ችሎታ ፡ ስለሚተማመኑ ፡ ወይም ፡ የሚያውቁትን ፡ ጠበቃ ፡ ስለማያምኑት ፡ ጠበቃ ፡ እንዲቆምላቸው ፡ የማይፈልጉ ፡ አሉ ።

ይኸ ፡ እንግዲህ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አሠራርና ፡ የሚቀርቡላቸው ፡ የክርክር ፡ ዓይነቶች ፡ መሠረታዊ ፡ መግለጫ ፡ ነው ። የሚቀጥለው ፡ ክፍል ፡ የነዚህን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ታሪካዊ ፡ የመሻሻል ፡ ለውጥ ፡ የሚገልጽ ፡ ይሆናል ።

## <u>የአሁኖቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ታሪካዊ ፡ ለውጥ ።</u>

### <u>መግቢያ ፡</u>

ከጣልያን ፡ ወረራ ፡ በፊት ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ተወስኖ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተለዩ ፡ ሕንፃዎች ፡ ተሠርተውና ፡ ሙያቸው ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ የሆኑ ፡ ሠራተኞች ፡ የሚገኙበት ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ አልነበረም ። በተለይም ፡ በዝቅተኛ ፡ ደረጃ ፡ ሙግት ፡ ያላንዳች ፡ ሥርዓት ፡ እንደየቦታው ፡ በተለያዩ ፡ ሕላዊ ፡ ሕግና ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ይካሔድ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ከአንድ ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የዛሬዎቹን ፡ የወረዳና ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ተመጣጣኝ ፡ የሆነ ፡ ደረጃ ፡ ባላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ክርክሩ ፡ እንዴት ፡ ይካሄድ ፡ እንደነበረ ፡ ለመግለጽ ፡ የተሰነዘረው ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ ስለተለዩ ፡ ቀበሌዎች ፡ በተሰጡት ፡ ጥቂት ፡ መግለጫዎች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ። ሆኖም ፡ የዛሬውን ፡ ጊዜ ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ ከጥንቱ ፡ ጋራ ፡ ማመዛዘን ፡ ጠቃሚ ፡ ስለሆነ ፡ በልማድ ፡ ይሠራበት ፡ የነበረው ፡ ያፈጻጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከጥንት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጐብኚዎች ፡ ካገኘናቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የጽሑፍ ፡ መረጃዎች ፡ ማገጣጠም ፡ ይቻላል ። የጥንቱንና ፡ የአሁኑን ፡ ጊዜ ፡ የዳኝነት ፡ አካሔድና ፡ የፍርድ ፡ አሠጣጥን ፡ ሁኔታ ፡ ማወዳደር ፡ አዲሱ ፡ የዳኝነት ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ በውስጣዊ ፡ አስተዳደሩም ፡ ረገድ ፡ ሆነ ፡ በዚሁ ፡ አዲስ ፡ በተፈጠረው ፡ የዳኝነት ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ መራመድ ፡ ባለበት ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ምክንያቶቹን ፡ ለማብራራት ፡ ይቻላል ።

### <u>እስከ ፡ ጣልያን ፡ ወረራ ፡ ድረስ ፡</u>

ኢትዮጵያን ፡ የጎበኙት ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ አውሮፓውያን ፡ ከተዉልን ፡ ማስታወሻ ፡ በጠቅላላው ፡ ለመረዳት ፡ እንደሚቻለው ፡ ከሀያኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ መጀመ

ሪያ ፡ እንስቶ ፡ እስከ ፡ ጣልያን ፡ ወረራ ፡ ድረስ ፡ በነበረው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ሙግት ፡ የሚካሔድባቸው ፡ በመሠረቱ ፡ ሦስት ፡ ደረጃዎች ፡ ነበሩ ።[34]

በዝቅተኛው ፡ ደረጃ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ አስተዳደርና ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታማኝ ፡ የሆነ ፡ ትልቅ ፡ ባለርስት ፡ ዳኛ ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ሥፍራ ዎች ፡ ርስት ፡ ከአባት ፡ ለልጅ ፡ በውርስ ፡ ስለሚተላለፍ ፡ ሹመቱም ፡ እንዲሁ ፡ አብሮ ፡ በውርስ ፡ የሚተላለፍ ፡ ነበር ። ከጥንት ፡ በተገኘው ፡ መረጃ ፡ መሠረት ፡ እን ደዚህ ፡ ያለው ፡ የዳኛ ፡ ሥራ ፡ ከአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ።[35] በሠፈሩ ፡ የሚነሣውን ፡ የመሬት ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ የሌብነትና፡ የስድብ ፡ ክርክር ፡ ይዳኝ ፡ ነበር ። ዳኛው ፡ ራሱ ፡ የሠፈሩ ፡ ሰው ፡ በመሆኑና ፡ የሚከ ራከሩትንም ፡ ሰዎች ፡ በቅርብ ፡ ስለሚያውቃቸው ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠት ፡ ይልቅ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በቅርብ ፡ ያስማማቸው ፡ ነበር ።

የክስ ፡ አቀራረብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከቀበሌ ፡ ቀበሌ ፡ የተለያየ ፡ ሲሆን ፡ በአንድ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ የሚሰራባቸው ፡ የክስና ፡ የማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ እንዲሁም ፡ የምስክር ፡ ቃል ፡ የሚሰማባቸው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ በትክክል ፡ የተጠበቁ ፡ ነበሩ ። አንድ ፡ ጸሐፊ ፡ እንደሚለው ፡ በዳኛው ፡ ፊት ፡ የሚደረጉት ፡ ክርክሮች ፡ ልማዳዊውን ፡ ሕግ ፡ በመጥቀስ ፡ የሚካሄዱ ፡ ሳይሆኑ ፡ ተሟጋቾቹ ፡ በንግግር ፡ ችሎታቸው ፡ ስለቀበሌው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ባላቸው ፡[36] ዕውቀት ፡ በመተማመን ፡ በውሳኔው ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ ነበራቸው ።

ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ለመሟገት ፡ ሲፈልጉ ፡ ለአንደኛው ፡ ወገን ፡ ሲፈረድ ፡ ለፍርዱ ማስፈጸሚያ ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይጠፋ ፡ በማለት ፡ ሁለቱም፡ ዋስ ፡ መጥራት ፡ ነበረባቸው ።[37] በክርክራቸው ፡ እውነተኛነት ፡ እንደመተማመናቸው ፡ መጠን ፡ ሁለቱም ፡ እያንዳን ዳቸው ፡ እሰጥ ፡ አገባ ፡ በመባባል ፡ ለምሳሌ ፡ አንዱ ፡ "ዛፉ ፡ የኔ ፡ እንደሆነና ፡ ዳኛም ፡ እንደሚበይንልኝ ፡ በቅሎ ፡ እሰጥ" በማለት ፡ ይወራረዳል ። ሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በዚያ ፡ በሚመጣጠን ፡ አገባ ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ የበለጠ ፡ ነገር ፡ እሰጥ ፡ በማ ለት ፡ ይወራረዳል ። ይህም ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ የፍርዱ ፡ ብያኔ ፡ ያዋጣናል ፡ ብለው ፡ እስከሚተማመኑበት ፡ መጠን ፡ ድረስ ፡ እሰጥ ፡ አገባው ፡ ይቀጥላል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜም ፡ ውርርዱ ፡ የስሜት ፡ መግለጫ ፡ እንጂ ፡ እውነት ፡ የነገሩ ፡ ውሳኔ ፡ ለኔ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ በመተማመን ፡ አልነበረም ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ተሟጋች ፡ የማይችለውን ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ እቃ ፡ እሰጥ ፡ ብሎ ፡ ይሟገታል ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡

34. ክስ ፡ የመንግሥት ፡ ሹም ፡ ባለበት ፡ የተካሄደው ፡ ሙግት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በሽምግልና ፡ ግልግል ፡ ያለቀውን ፡ ክርክር ፡ አይጨምርም ።

35. "በያንዳንዱ፡መንደር ፡ በምንም ፡ መንገድ ፡ የማይሻር ፡ ከዘር ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ ፡ ሹመት ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አለ ። የተጻፉ ፡ ሕጎች ፡ በሌሉበት ፡ ቦታ ፡ በብጥብጥ ፡ መካከልና ፡ የተፋጠነ ፡ ተከታታይ ፡ የነገሥታትና ፡ የገዥዎች ፡ ለውጥ ፡ በሚደረግበት ፡ ወቅት ፡ የሰላም ፡ ጭላንጭል ፡ የሚታ የው ፡ በዚህ ፡ ሹም ፡ መኖር ፡ ምክንያት ፡ ነው ። ይህ ፡ ቅን ፡ ሹም ፡ ለአለቃው ፡ ከሚሰበስበው ፡ ከአሥር ፡ እጅ ፡ አንዱን ፡ እጅ ፡ ይወስዳል ። ክልሎችንም ፡ ይጠብቃል ። ወሰኖችን ፡ የሚለይባቸው ፡ ምልክቶች ፡ በጣም ፡ ቀላሎች ፡ ናቸው ። ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ ቁጥቋጦ ፡ ወይም ፡ ድንጋይ ፡ የአንድ መንደርን ፡ ወሰን ፡ ይከልላል ። ግን ፡ ዘወትር ፡ እንደሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ የጐረቤቶቹ ፡ ሰዎች ፡ መሬት ፡ ኩታ ፡ ገጠም ፡ ከሆነ ፡ የተወሳሰበ ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚሆን ፡ መጨረሻ ፡ የሌለው ፡ ክርክር ፡ ከማስነሳቱም፡ ሌላ ፡ ብጥብጥ ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ።" ጆ ፡ ሲ ፡ ሆተን ፡ አቢሲኒያና ፡ ሕዝቧ ፡ (በእንግሊዝኛ) ፡ ፲፱፻፷፫ ።

36. "የአንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ክስ ፡ የዕውነት ፡ ማውጫ ፡ ሳይሆን ፡ የቃላት ፡ ችሎታን ፡ ማሳያ ፡ ክርክር ፡ ነው ።" ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷፩ ።

37. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፪፻፷፫ ።

ዳኛው ፡ የእሰጥ ፡ አገባው ፡ ክርክር ፡ ሊፈጸም ፡ በሚችል ፡ እውነተኛ ፡ በሆነ ፡ መንገድ፡ እንዲካሄድ ፡ ይወስናል ። እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ በበኩሉ ፡ ከነማስረጃው ፡ ምስክሮቹን ፡ ለዳኛው ፡ ያቀርባል ። ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በበኩላቸው ፡ ያለውን ፡ ጉዳይ ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ ዳኛው ፡ ወዲያውኑ ፡ ይፈርዳል ። ይህንንም ፡ የሚያደርገው ፡ በጉዳዩ ፡ በጣም ፡ ሳያስብበት ፡ ወይም ፡ በችሎቱ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ ሐሳብ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ነው ።[38] የተረታው ፡ ወገን ፡ እሰጥ ፡ ወይም ፡ አገባ ፡ ብሎ ፡ ያወረደውን ፡ ውርድ ፡ ለዳኛው ፡ ይከፍላል ።[39] በጉዳዩ ፡ ይግባኝ ፡ የተጠየቀበት ፡ እንደሆነ ፡ የውርዱ ፡ ገንዘብ ፡ አከፋፈል ፡ የይግባኙ ፡ ዳኛ ፡ ፍርድ ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ይቆያል ።[40] እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ውርድ ፡ አወራረድ ፡ ባልተለመደበት ፡ በአንዳንድ ፡ ሥፍራ ፡ ዳኛው ፡ የመሰለውን ፡ የዳኝነት ፡ ኪሣራ ፡ በመቁረጥ ፡ የተረታው ፡ ወገን ፡ እንዲከፍል ፡ ወስኖ ፡ ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ለዳኛው ፡ ለራሱ ፡ ገቢ ፡ ይሆናል ።[41]

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ረገድ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሳሽ ፡ ራሱ ፡ ሕግ ፡ ተላላፊውን ፡ ተከሳሽ ፡ እላይ ፡ እተመለከተው ፡ ዳኝነት ፡ ፊት ፡ በራሱ ፡ አነሳሽነት ፡ ያቀርባል ። ለምሳሌ ፡ አበዳሪው ፡ ባለዕዳውን ፡ አነጋግሮት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመቅረብ ፡ ፈቃደኛ፡ ባይሆን ፡ ተበዳሪው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመቅረብ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ መኖርና ፡ አለመኖሩን ፡ ውሃ ፡ ወራጅ ፡ ዳኛ ፡ ይመለከትና ፤[43] ከሳሹ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ኖሮት ፡ ከተገኘ፡ ፍርዱን ፡ ማስፈጸም ፡ ወደሚችል ፡ በሥሩ ፡ ፍርድ ፡ አስፈጻሚዎች ፡ ወደአሉት ፡ የሰፈር ፡ ዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ባለዕዳውን ፡ አቆራኝቶ ፡ ይልካል ። እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ የፍርድ ፡ ማስፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ የነበራቸው ፡ ዳኞች ፡ ባለዕዳውን ፡ በዕዳው ፡ ምትክ ፡ በማሠራት ፡ ወይም ፡ ባለዕዳው ፡ ገንዘቡን ፡ እስኪከፍል ፡ ድረስ ፡ ከወታደር ፡ ጋር ፡

---

38. ኤስ ፡ ዲ ፡ ሜሲንግ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ደገኛው ፡ አማራ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፴ ።
39. በ፲፱፻፳፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በገዢው ፡ በተሾሙት ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ፊት ፡ በአሥመራ ፡ ይሠራበት ፡ የነበረው ፡ የእሰጥ ፡ አገባ ፡ ሥርዓት ፡ በሚከተለው ፡ ዓይነት ፡ ተገልጿል ። "እነዚህን ፡ በሕግ፡ የተቋቋሙ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ያሳወቃቸው ፡ ሌላው ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ በባህላቸው ፡ ያለው ፡ የመነጣጠር ፡ እልክ ፡ ከርትዕና ፡ ከፍትህ ፡ ፍለጋ ፡ ጋር ፡ በገሃድ ፡ መያያዙ ፡ ነው ። ከሁለት ፡ አንደኛው ፡ ወይም ፡ ሁለቱም ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ በየበኩላቸው ፡ ልክ ፡ ለመሆናቸው ፡ እሰጥ ፡ ወይም ፡ አገባ ፡ ባሉ፡ ጊዜ ፡ ሊሰጡና ፡ ወይም ፡ ሊያገቡ ፡ ያሉትን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያሲዛሉ ። ግማሽ ፡ የበግ ፡ ጐን ፡ አንድ ፡ ጣባ ፡ ዱቄት ፡ እንዲያውም ፡ እንደክርክሩ ፡ ሁኔታ ፡ ነጭ ፡ ፈረስ ፡ እሰጥ ፡ ወይም ፡ አገባ ፡ ይባላል ። አንደኛው ፡ ተከራካሪ ፡ እሰጥ ፡ ሲል ፡ ሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ (አገባ) ፡ ማለት ፡ ወይም ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ያመለከተውን ፡ አንስቶ ፡ ክሱን ፡ መተው ፡ ይኖርበታል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በክርክሩ ፡ ላይ ፡ የተወራረዱባቸው ፡ ነገሮች ፡ የኋላ ፡ ኋላ ፡ ለጥሉ ፡ ምክንያት ፡ ከሆኑት ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ጉዳዮች ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ ይኖራቸዋል ። በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡት ፡ እነዚህ ፡ ዳኞች ፡ ደመወዝ ፡ ስለሌላቸው ፡ የሚኖሩት ፡ ከክርክሩ ፡ ውርርድ ፡ በሚያገኙት ፡ ገቢ ፡ ነው ።
የተረታው ፡ ወገን ፡ ለነርሱ ፡ ዋጋቸውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ፡ ስለዚህ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ዳኞች ፡ ትልልቅ ፡ ቤቶች ፡ ስለአላቸው ፡ ደህና ፡ ኑሮ ፡ የሚኖሩ ፡ ይመስላል ፡" ኤች ፡ ፒ ፡ ሊቾን ፡ በርግ ፡ "በሜዳ ፡ ላይ ፡ የሚአስችሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች" ብሔራዊ ፡ የጂግራፊ ፡ መጽሔት ፡ (ቮልዩም ፡ ፷፰ ፡ ቁጥር ፡ ፲) ፡ ኅዳር ፡ ፲፱፻፳፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገጽ ፡ ፯፻፴፫ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ፡ (በእንግሊዝኛ) ።
40. ኤስ ፡ ዲ ፡ ሜሲንግ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፴፩ ።
41. "የገንዘቡ ፡ ልክ ፡ የተወሰነ ፡ አይደለም ። የሚጠይቁትን ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ የሚቆጣጠር ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ዋጋቸው ፡ ከፍተኛ ፡ ከሆነ ፡ የባላገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ክርክር ፡ ማምጣቱን ፡ ያቆማል ። ወይም ፡ ሕዝቡ ፡ ክርክሩን ፡ ባገር ፡ ሽማግሌዎችና ፡ በየጓደኞቹ ፡ ፊት ፡ ያደርጋል ፡ የሚል ፡ ሥጋት ፡ ነው ።" ጂ ፡ ሲ ፡ ሆተን ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፩ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፻፹፫ ።
42. "በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ በድንገት ፡ በሚፈጠሩ ፡ ጥሎች ፡ ተደብቆ ፡ ይኖር ፡ የነበረን ፡ ተበዳሪ ፡ በማግኘት፡ ወይም ፡ በማንኛውም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ ምክንያት ፡ የሚነሱትን ፡ ጥቃቅን ፡ ተመሳሳይ ፡ ክርክሮች ፡ በአቅራቢያው ፡ የተገኘው ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጊዜያዊ ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ እንዲዳኝ ፡ ይገደዳል ፤" ጂ ፡ ሲ ፡ ሆተን ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፩ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፻፹፯ ።
43. አር ፡ ፒ ፡ ዲሞቲዎስ ፡ የሁለት ፡ ዓመታት ፡ ኖሮ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፲፰፻፰፫ ፡ ገጽ ፡ ፰፯ ፡ (በፈረንሣይኛ) ።

በማቆራኘት ፡ ፍርዱን ፡ ያስፈጽማሉ ።[44] በ፲፱፻፴ኛው ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ በአሥመራ ፡ ተሚጋቹ ፡ ተፈርዶበት ፡ የተጣለበትን ፡ መቀጮ ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ገንዘቡን ፡ እስኪከፍል ፡ ድረስ ፡ በዳኛው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ታሥሮ ፡ ይቆይ ፡ ነበር ።[45]

በፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ከተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ መክፈል ፡ አለመቻሉ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በመቆራኘት ፡ ወይም ፡ በአገልግሎት ፡ ያሳለፈው ፡ ጊዜ ፡ ግዴታውን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ እንደመቀጮ ፡ ተቆጥሮለት ፡ በነጻ ፡ ይለቀቃል ።

በከባድ ፡ ወንጀል ፡ የተጠረጠሩ ፡ ወንጀለኞች ፡ ወደዳኛ ፡ ዘንድ ፡ የሚቀርቡት ፡ በጭቃ ፡ ሹሙ ፡ መሪነት ፡ በሠፈሩ ፡ ሰዎች ፡ ተይዘው ፡ ነው ። ሕዝቡ ፡ ወንጀለኛውን ፡ ባያወጣና ፡ ባያስረክብ ፡ የቀበሌው ፡ ሹሞች ፡ በሠፈሩ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ መቀጮ ፡ ስለሚጥሉ ፡ ሕዝቡ ፡ ራሱ ፡ በሠፈሩ ፡ በሚኖረው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ሕግ ፡ አስከባሪና ፡ አስፈጻሚ ፡ ነበር ።[46]

ነፍስ ፡ ገዳዮችንና ፡ ሌቦችን ፡ ለፍርድ ፡ ማቅረቢያ ፡ ሌላው ፡ ዘዴ ፡ ደግሞ ፡ አፈርሳታ ፡ ነበር ።[47] በሠፈሩ ፡ ወንጀል ፡ ሲፈጸም ፡ የቀበሌው ፡ ሹም ፡ በአካባቢው ፡ የሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከካህናት ፡ በቀር ፡ በግዴታ ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ ያደርጋል ። በአካባቢው ፡ ካለው ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ወንጀሉ ፡ መፈጸሙን ፡ ያየ ፡ ወይም ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ አይጠፋም ፡ በሚል ፡ ግምት ፡ የሠፈሩ ፡ ሰዎች ፡ ወንጀለኛውን ፡ እንዲያወጡ ፡ ይገደዳሉ ። የአፈርሳታውም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ ይለያያል ። በአንዳንድ ፡ ሥፍራ ፡ ባንዱ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ማስረጃ ፡ እስኪገኝ ፡ ወይም ፡ በሕዝቡ ፡ መጫን ፡ ምክንያት ፡ ጥፋተኛው ፡ እስኪያምን ፡ ድረስ ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ እያንዳንዱን ፡ ሰው ፡ በመጠየቅ ፡ ይፈጸም ፡ ነበር ። በአንዳንድ ፡ ቦታ ፡ ደግሞ ፡ ሕዝቡ ፡ ተቀምጦ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ይወያያል ፤ ወንጀለኛውም ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ አይበተንም ፤ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ አፈርሳታ ፡ ባልቀረበት ፡ አገር ፡ ሕዝቡ ፡ አይወደውም ። ሠፈረተኛው ፡ በአፈርሳታ ፡ ምክንያት ፡ ጊዜውን ፡ ከሚያባክን ፡ ይልቅ ፡ በወረዳ ፡ ገዢው ፡ የሚጣልበትን ፡ መቀጫ ፡ መክፈሉን ፡ ይመርጣል ።[48] የአንድ ፡ ቀበሌ ፡ ሕዝብ ፡ አፈርሳታ ፡ እንዳይኖር ፡ ሲል ፡ በተቀዳሚ ፡ መቀጮውን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ይከፍል ፡ እንደነበረም ፡ ይነገራል ።

---

44. ኤች ፡ ፒ ፡ ሊቸንፐርግ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፴፮ ።
45. ጂ ፡ ሲ ፡ ሆተን ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፩ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፻፹፮ ።
46. ኤስ ፡ ዲ ፡ ሜሲንግ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷፮ ።
አፈርሳታ ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ በገጠር ፡ ይሠራበታል ።
47. በአንዳንድ ፡ ቦታ ፡ "በአፈርሳታ" ፡ ምክንያት ፡ ከሚከፈለው ፡ መቀጫ ፡ ሌላ ፡ የወረዳው ፡ ገዥ ፡ አግባቡኝ ፡ ይላል ።
48. አንድ ፡ ጸሐፊ ፡ ስለጐንደር ፡ አካባቢ ፡ ሲናገር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ "እስከ ፡ ቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ እንዲያውም ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ በሚገኙ ፡ ወረዳዎች ፡ ዛሬም ፡ ቢሆን ፡ እሰጥ ፡ አገባ ፡ ወይም ፡ በክርክሩ ፡ ውጤት ፡ ላይ ፡ መወራረድ ፡ በአንድ ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ክፍል ፡ ነበር ።" ተረቺው ፡ ያሲያዘውን ፡ ገንዘብ ፡ ዳኛው ፡ ስለሚወስድበት ፡ "የእሰጥ ፡ አገባ" ፡ ሥርዓት ፡ ዛሬ ፡ ለዳኝነት ፡ የሚከፈለውን ፡ ገንዘብ ፡ ቦታ ፡ ይዞ ፡ ነበር ። ይኸም ፡ የዳኛው ፡ ደመወዝ ፡ ነበር ። ይኸንን ፡ መያዣ ፡ ሳይዙ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሄድ ፡ አይቻልም ፡ ነበር ። ድሃ ፡ ሰው ፡ የዘመዶቹ ፡ ርዳታ ፡ እንኳ ፡ ተጨምሮ ፡ ሀብታሙ ፡ ባላጋራው ፡ ለመስጠት ፡ ያቀረበውን ፡ ያህል ፡ ለማግባት ፡ ስለማይችል ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ ይደርስበታል ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ መጠን ፡ አልባ ፡ የዳኝነት ፡ ሥርዓት ፡ ለመወሰን ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ውርርዱ ፡ ልኩ ፡ በገንዘብ ፡ በተወሰነ ፡ ማር ፡ አንድ ፡ ፈረስ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ በቅሎ ፡ እንዲሆን ፡ ሲደነግጉ ፡ ዳኞችም ፡ ትክክለኛነትን ፡ እንዲያሳዩ ፡ አደራ ፡ ጥለውባቸው ፡ ነበር ። ኤስ ፡ ዲ ፡ ሜሲንግ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷፱ ።

ተሚጋቾቹ ፡ የቀበሌውን ፡ ዳኞች ፡ አበል ፡ የሚከፍሉ ፡ ቢሆኑም ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ከዳኝነት ፡ ሥራ ፡ የሚገኘው ፡ ገቢ ፡ የአገሩን ፡ ሕዝብ ፡ የሚያውቁትን ፡ የታወቁትን ፡ ሰዎች ፡ ዳኛ ፡ እንዲሆኑ ፡ የሚያበረታታ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ነበር ። ይህም ፡ አሠራር ፡ መንግሥት ፡ ደሞዝ ፡ ሳይከፍል ፡ ዳኛ ፡ ለመሾም ፡ ያስችለው ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ይህ ፡ አሠራር ፡ በአስተዳደር ፡ በኩል ፡ ከሚያስገኘው ፡ ጥቅም ፡ ይልቅ ፡ ክስ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ለውርድ ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ድኾች ፡ ባላገሮች ፡ ያለ ፡ ዘመድ ፡ እርዳታ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ እንዳይችሉ ፡ ያደርጋቸው ፡ ስለነበር ፡ ጉዳቱ ፡ ይበልጥ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ በአሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ መንግሥት ፡ ይህ ፡ እንዲሻሻል ፡ አድርጐ ፡ ነበር ።[49] አንድ ፡ ጸሐፊ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ዘዴ ፡ ለድኻ ፡ ጠቃሚ እንደነበር ፡ ሲናገሩ ፡ ዳኛው ፡ ከፍተኛ ፡ ገንዘብ ፡ ከሀብታሙ ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችል ፡ ከሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በሀብታሙ ፡ ተሚጋች ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ፡ ይላሉ ።[50]

ኢትዮጵያን ፡ ከጎበኙት ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ አውሮፓውያን ፡ ውስጥ ፡ በልማዳዊው ፡ የዳኝነት ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ የጉቦ ፡ ጉዳይ ፡ እንደ ፡ ብርቱ ፡ ችግር ፡ የሚቆጠር ፡ እንደነበር ፡ የሚናገሩ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። የአሠራሩ ፡ ዘዴ ፡ ጉድለቱ ፡ የዳኞቹ ፡ አለመታመን ፡ ሳይሆን ፡ የእነርሱ ፡ እንደመሰላቸውና ፡ እንደፈቀዳቸው ፡ መሥራት ፡ ይመስላል ።[51] በተጨማሪ ፡ ደግሞ ፡ አገረ ፡ ገዢዎችና ፡ ራሶች ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የነበራቸው ፡ ተጽዕኖ ፡ ተሚጋቾችን ፡ ይጎዳ ፡ ነበር ።[52] የዳኝነት ፡ ነፃነት ፡ አስተሳሰብ ፡ ከቶውንም ፡ አልነበረም ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የጉቦ ፡ ችግር ፡ አልጠፋም ፡ ነበር ። አንድ ፡ ጸሐፊ ፡ በ፲፰፻፺፯ ፡ ዓ. ም. እንደተናገሩት ፡ ተሚጋቾቹ ፡ በንግግር ፡ ስህተት ፡ ምክንያት፡ ለዳኞች ፡ መቀጫ ፡ ስለሚከፍሉና ፡ ጉቦ ፡ ለመቀበልም ፡ ሰፊ ፡ እድል ፡ ስላለ ፡ የነገሩ ፡ በቶሎ ፡ አለመቆረጥ ፡ ለዳኛው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ።[53]

እሰጥ ፡ አገባ ፡ በማለት ፡ በሚካሄደው ፡ የሙግትና ፡ የዳኝነት ፡ ቅንጅት ፡ ሥርዓት ፡ የአድልዎ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ የሚያስችል ፡ ብዙ ፡ መንገድ ፡ ቢኖርም ፡ እንኳ ፤ ብዙዎቹ ፡ ዳኞች ፡ ባለብዙ ፡ ጋሻ ፡ መሬት ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ በየቀበሌያቸው ፡ የተከበሩ ፡ ሰዎች ፡ ስለነበሩ ፤ በአድልዎ ፡ ለመሥራት ፡ የነበራቸው ፡ ዕድል፡ ትንሽ ፡ ነበር ።

በመጀመሪያው ፡ ደረጃ ፡ ከፈረደ ፡ ዳኛ ፡ ይግባኝ ፡ የሚቀርበው ፡ "ለምስለኔ ፡" ነበር ። ይህም ፡ ሹም ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አጼ ፡ ቴዎድሮስ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በሺህ፰፻

---

49. "ዳኛው ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ሊከፍል ፡ በሚችለው ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ለመፍረድ ፡ ያለው ፡ ዝንባሌ ፡ ለድሆች ፡ ተሚጋቾች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጥሩ ፡ ዋስትና ፡ ነው ።" ጂ ፡ ሲ ፡ ሆተን ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፩ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፳፩ ።

50. "ተናጋሪው ፡ በሚያደርገው ፡ በያንዳንዱ ፡ የንግግር ፡ ስሕተት ፡ ላይና ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ተይዞ ፡ በሚደረገው ፡ መሐላ ፡ ላይ ፡ እንደተለመደው ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የሚለያይ ፡ ለዳኛው ፡ የሚከፈል ፡ ልዩ ፡ አበል ፡ አለ ፡ አቤቱታው ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ በሚያስቅ ፡ ድርጊት ፡ ምክንያት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ እጁን ፡ ማንቃነቅ ፡ ወይም ፡ አቅጣጫን ፡ (ቦታን) ፡ መለወጥ ፡ አይቻልም ፡" ከዚያው ።

51. አስተዳዳሪዎቹ ፡ ባላቸው ፡ ተጽዕኖ ፡ ምክንያት ፡ በቀበሌው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍትኅ ፡ የተነፈጋቸው ፡ ተሚጋቾች ፡ ማንኛውንም ፡ ችግር ፡ በመቋቋም ፡ ፍትኅ ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ራስ ፡ ወይም ፡ ገዢ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይሄዳሉ ፤ "የበታች ፡ ገዥዎች ፡ ትክክለኞች ፡ ስላልሆኑ ፡ ፍትህ ፡ የምትገኘው ፡ የነዚህ ፡ የበላይ ፡ ከሆነው ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ (ድሆች ፡ ተሚጋቾች) ፡ የሚጓዙትን ፡ የመንገድ ፡ ርቀት ሲያስቡት ፡ መርታታቸውን ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ሳይንቁት ፡ የሚመለሱበት ፡ ጊዜ ፡ እምብዛም ፡ ነው ።" ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፪፻፳፫ ።

52. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፪፻፳፩ ።

53. ኤስ ፡ ዲ ፡ ሜሲንግ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፶፮ ።

፰ኛውና ፡ በሺህ፰፻፺ኛው ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ለግብር ፡ ሰብሳቢነት ፡ ሲሾሙት ፡ ከአገሬው ፡ ጋር ፡ በምንም ፡ አኳኋን ፡ ግንኙነት ፡ ያልነበረውና ፡ ግብሩን ፡ ለመሰብሰብ ፡ ብቻ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚልከው ፡ ሰው ፡ ነበር ።[54] ከጊዜ ፡ ብዛት ፡ "ምስለኔ ፡" የተባለው ፡ ስያሜ ፡ የአስተዳደርንና ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ አጣምሮ ፡ ለያዘ ፡ በጠቅላይ ገዢው ፡ ለሚሾም ፡ የቀበሌ ፡ ሹም ፡ መጠሪያ ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ።[55] በአሁኑ ፡ ዘመን ፡ በመንዝ ፡ የሚገኙ ፡ አንድ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ እንዳሉት ፡ ከሆነ ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ይህንን ፡ ሹመት ፡ የሚያገኘው ፡ ባለርስት ፡ ከሆኑት ፡ ሀብታሞች ፡ መካከል ፡ ለዚህ ፡ ሹመት ፡ ተጫርቶ ፡ ለጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ የከፈለ ፡ ነው ። እኚህ ፡ ያጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ በተጨማሪ ፡ እንዳሉት ፡ ምስለኔው ፡ ከተረታው ፡ ወገን ፡ የዳኝነት ፡ ከመቶ ፡ አሥሩን ፡ ያገኛል ።[56] ከምስለኔው ፡ ፍርድ ፡ ይግባኙ ፡ ጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ወደሾሙት ፡ "ወምበር" ፡ ይቀርባል ። ይህ ፡ ዳኛ ፡ ከአገረ ፡ ገዢው ፡ ባለሚሎች ፡ እንዳንዱ ፡ የሚቆጠር ፡ ሲሆን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜውን ፡ የሚያሳልፈው ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ቢሆንም ፡ እየዞረ ፡ ያስችላል ።[57]

የነዚህ ፡ የሶስቱ ፡ ማለት ፡ የዳኛ ፡ የምስለኔና ፡ የወምበር ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ተለይቶ ፡ የተወሰነ ፡ አልነበረም ። ማናቸውም ፡ ክስ ፡ የሚያቀርብ ፡ ሰው ፡ እንዳሰኘው ፡ ለምስለኔ ፡ ወይም ፡ ለወምበር ፡ በማቅረብ ፡ ለመጀመር ፡ ይችል ፡ ነበር ። ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በአቅራቢያቸው ፡ በሚገኘው ፡ ሹም ፡ ላይ ፡ ቢካሰሱ ፡ ምቹ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በወጪም ፡ ረገድ ፡ ስለማይጎዱ ፡ በተለምዶ ፡ ይሰራበት ፡ የነበረው ፡ የክስ ፡ አቀራረብ ፡ ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ ሆኖ ፡ አንዱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመጨረሻውን ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣል ፡ በሚል ፡ ተስፋ ፡ ነበር ።

ከመጀመሪያው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወደሚቀጥለው ፡ ከዚያም ፡ እስከ ፡ ዙፋን ፡ ችሎት ፡ ይግባኝ ፡ መጠየቅ ፡ የተለመደ ፡ ነበር ። የዚህም ፡ የይግባኝ ፡ መብት ፡ ወሰን ፡ ገደብ ፡ ስለአልነበረው ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ይሠራበት ፡ ነበር ።[58]

እስከመጨረሻው ፡ ፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ እስከ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ችሎት ፡ ድረስ ፡ ከሚደረገው ፡ ይግባኝ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ በአፊሴል ፡ ባይገቡም ፡ እንኳን ፡ ተሚጋቾቹ ፡ ለየሥፍራው ፡ አገረ ፡ ገዢዎች ፡ በየጊዜው ፡ አቤቱታ ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ። አገረ ፡ ገዢው ፡ ዳኛ ፡ ለመሾም ፡ ለመሻርና ፡ በውስጡ ፡ የሚገ

54. አሁን ፡ ግብር ፡ የሚሰበስቡት ፡ የምክትል ፡ ወረዳ ፡ ገዢዎች ፡ በጥቂቱ ፡ የገጠሩ ፡ ሕዝብ ፡ ምስለኔዎች ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ። ዛሬም ፡ ቢሆን ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ምስለኔዎች ፡ በሕግ ፡ ያልተፈቀደላቸውን ፡ ጥቂት ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ። ክርክሮችንም ፡ በልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ይዳኛሉ ።

55. ባንዳንድ ፡ ሥፍራ ፡ "መልከኞች ፡" ምስለኔዎች ፡ በግዛታቸው ፡ ያላቸውን ፡ ሥልጣን ፡ ዓይነት ፡ አላቸው ። መልከኞች ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከመንገሣቸው ፡ በፊት ፡ በነገሥታቱ ፡ ተመርጠው ፡ ለነገሥታቱ ፡ ግብር ፡ የሚሰበስቡና ፡ ለአገልግሎታቸውም ፡ ዋጋ ፡ መሬት ፡ የተቀበሉ ፡ እንዲሁም ፡ በንጉሥ ፡ ትዕዛዝ ፡ በተላኩበት ፡ ቀበሌ ፡ የተቀመጡ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። አፄ ፡ ቴዎድሮስም ፡ የቀበሌው ፡ መልከኞች ፡ በብዙ ፡ የጥቅም ፡ መተሳሰር ፡ ምክንያት ፡ ሥራቸውን ፡ በሚገባ ፡ ለማከናወን ፡ ሲያቅታቸው ፡ በቀጥታ ፡ የንጉሡ ፡ መልእክተኞች ፡ በመሆን ፡ ለተመሳሳይ ፡ ግብር ፡ ሰብሳቢነት ፡ ሥራ ፡ ምስለኔዎችን ፡ መሾም ፡ ጀምረው ፡ ነበር ። እነርሱም ፡ ደመወዝ ፡ የሚከፈላቸው ፡ የንጉሥ ፡ እንደራሴዎች ፡ ሲሆኑ ፡ በአንድ ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ በመቀመጥ ፡ ልዩ ፡ ዝምድናን ፡ እንዳያፈሩ ፡ በየጊዜው ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ ይዛወሩ ፡ ነበር ። ኤስ ፡ ዲ ፡ ሚሲንግ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፶፯ ።

56. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፳፮ ።

57. ኤም ፡ ፔርሀም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሎንዶን ፡ ፲፱፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገጽ ፡ ፻፵፫ ፡ (በእንግሊዝኛ) ።

58. "...ባንድ ፡ አንድ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ክፍለ ፡ ግዛት ፡ በአስራ ፡ አምስት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ይግባኞችን ፡ ለማቅረብ ፡ ይቻል ፡ ነበር ፤ ለውሳኔውም ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ የሚወሰደው ፡ አንድ ፡ ተሚጋች ፡ ከነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብዙዎቹ ፡ የሱን ፡ ክርክር ፡ በመደገፍ ፡ ፈርደውለት ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።"

ኙትንም ፡ ዳኞች ፡ ለማዘዝ ፡ ሥልጣን ፡ ስለነበረው ፡ በዚህ ፡ ሥልጣኑ ፡ ከመጠቀም ፡ አይቆጠብም ፡ ነበር ። በማንኛውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ የፍርዱ ፡ አስፈጻሚ ፡ ለአገረ ፡ ገዢው ፡ ወይም ፡ ለጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ራስ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ለማዕከላዊ ፡ መንግሥት ፡ ታዛዥ ፡ የሆነው ፡ ወኪል ፡ "የጭቃ ፡ ሹሙ ፡" ነው ። እነዚህ ፡ ሹማምንት ፡ የቀበሌው ፡ መሪዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ተግባራቸውም ፡ ግብር ፡ መሰብሰብና ፡ የመንግሥቱን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ማወጅን ፡ ይጨምራል ።

ስለዚህ ፡ ከጣልያን ፡ ወረራ ፡ በፊት ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሔድ ፡ እንዴት ፡ እንደ ነበረ ፡ ዝርዝር ፡ መረጃ ፡ ባይገኝም ፡ ጥቂት ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየቶች ፡ መስጠት ፡ ይቻላል ።

አንደኛ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ለጠቅላይ ፡ ቅንጅት ፡ ዘዴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የበላይ ፡ መሪ ፡ ቢሆንም ፡ በዳኝነት ፡ ተግባር ፡ የሚሠማሩትንም ፡ ሰዎች ፡ የሚሾሟቸው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደራሴዎችና ፡ አገረ ፡ ገዢዎች ፡ ቢሆኑም ፡ አገሪቱ ፡ ከሃምሳ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ሙሉ ፡ አንድነት ፡ የነበረው ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ ስለአልነበራት ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ መልክ ፡ እንዲይዝ ፡ ለማድረግ ፡ አልተቻለም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ በተለይም ፡ በዝቅተኛው ፡ ደረጃ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱና ፡ ሕላዊ ፡ ሕጉ ፡ በየሥፍራው ፡ የነበረውን ፡ ልማድ ፡ የያዘ ፡ ይመስላል ። አሁን ፡ ከደረሱበት ፡ ደረጃ ፡ የሚያንሱ ፡ ጥንት ፡ ትንሽ ፡ በነበሩት ፡ በአሁኖቹ ፡ ታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ በከተማ ፡ ኑሮ ፡ ምክንያት ፡ ይለወጥ ፡ ከነበረው ፡ አንዳንድ ፡ ልማድ ፡ በስተቀር ፡ ከባላገር ፡[59] ወደነዚህ ፡ ከተሞች ፡ የሚመጣው ፡ ሕዝብ ፡ በሚያውቀው ፡ ልማድ ፡ እንዲሚገት ፡ ይፈቀድለት ፡ ነበር ።

ከሳሽና ፡ ተከሳሹ ፡ የጽሑፍ ፡ አቤቱታ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ አይገደዱም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በመጀመሪያ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ሆነ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ተሚጋቾችን ፡ የሚረዱ ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎችና ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ የሠለጠኑ ፡ ሰዎች ፡ ለሙግቱ ፡ አይፈለጉም ። ተሚጋቾቹ ፡ ዳኛው ፡ ፊት ፡ ሲቀርቡ ፡ የሚፈለግባቸው ፡ በበኩላቸው ፡ ያለውን ፡ ጉዳይ ፡ ለዳኛው ፡ ማመልከት ፡ ብቻ ፡ ነበር ። አያሌ ፡ ሰዎች ፡ እንደነገሩን ፡ ብዙዎች ፡ ተሚጋቾች ፡ የአነጋገር ፡ ችሎታ ፡ የሚማሩት ፡ ተሚጋች ፡ ሆኖ ፡ በማደግ ፡ ሲሆን ፡[60] በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሚገቱትም ፡ እንደሁኔታቸው ፡ አመጣጥ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ እንደታያቸው ፡ ነበር ።

ማስረጃና ፡ ምስክር ፡ ለማቅረብ ፡ በየቀበሌው ፡ የተለዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ ነበሩ። ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ነክ ፡ ባልሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ፍርድ ፡ የሚሰጠው ፡ በአገሩ ፡ ልማድና ፡ በርትዕ ፡ መሠረት ፡ ነበር ። ለምሳሌ ፡ በርስት ፡ የሚሚገት ፡ ሰው ፡ በሠፈሩ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ዘር ፡ መቁጠርና ፡ አንዳንድ ፡ የቀበሌውን ፡ የውርስ ፡ ደንቦች ፡ ማወቅ ፡ ነበረ

---

59. በ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአሥመራ ፡ በአንድ ፡ ተጓዥ ፡ የተነገረው ፡ ክርክር ፡ ቀደም ፡ ባሉ ፡ መንገደኞች ፡ ታይቶ ፡ የተገለጸውን ፡ በባላገሩ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በአሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻ ፡ ገደማ ፡ ይደረግ ፡ የነበረውን ፡ ክርክር ፡ ይመስላል ። "እነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቀዋሚ ፡ የሆነ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የላቸውም ፤ ክርክሩን ፡ ለመስማት ፡ የሚገናኙት ፡ ምቹ ፡ በሆነ ፡ የመንገድ ፡ ማዕዘን ፡ ወይም ፡ የመንደር ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ነው ። እዚያም ፡ እንደ ፡ ነጋዴ ፡ ወይም ፡ ቸርቻሪ ፡ ተቀምጠው ፡ የሚመጡትን ፡ ክርክሮች ፡ ይጠባበቃሉ ።" ኤች ፡ ፒ ፡ ሊችንፐርግ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፱ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፴፫ ።

60. "ኢትዮጵያውያን ፡ ክርክር ፡ ይወዳሉ ፤ ብዙዎቹም ፡ ክርክሩን ፡ ለመርታት ፡ የማያስፈልጉ ፡ የምሳሌያዊ፡ አነጋገርና ፡ የሌሎችም ፡ ጠቃሚ ፡ ዘዴዎች ፡ ባለቤቶች ፡ ናቸው ። ክርክር ፡ የልጆች ፡ ተወዳጅ ፡ ጨዋታ፡ ነው ። በጣም ፡ አነስተኛ ፡ የሃሳብ ፡ ልዩነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወጪን ፡ የሚያስከትልና ፡ የረጅም ፡ ክርክር ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ።" ጂ ፡ ሲ ፡ ሆተን ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፴፮ ።

በት ። ይህንንም ፡ በተፈጥሮ ፡ በቀላሉ ፡ ሊያስታውሰው ፡ ይችላል ። ይህም ፡ የሕላዊ ፡ ሕግና ፡ የሥነሥርዓት ፡ ልምድ ፡ ዕውቀት ፡ ያደገበት ፡ ነገር ፡ ነው ።

በዝቅተኛው ፡ የመንግሥት ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ የሚደረገው ፡ሙግት ፡ በመሠረቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተጀምሮ ፡ በተፋጠነ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያልቅ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ክርክር ፡ በአንድ ፡ ችሎት ፡ ተሰምቶ ፡ ዳኞቹም ፡ የሁለቱን ፡ ወገን ፡ ማስረጃ ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ በዚያው ፡ ችሎት ፡ ወዲያውኑ ፡ ፍርድ ፡ ይሰጣሉ ።

ሌላው ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ የሚወሰደው ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተገለጸው ፡ ሁኔታ ፡ የሚመነጭ ፡ ነው ። ሙግት ፡ እንዲሰሙ ፡ የሚመደቡት ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንት ፡ በጠቅላላው ፡ እያንዳንዱን ፡ ጉዳይ ፡ በጥንቃቄ ፡ ተመልክተው ፡ በፍጥነት ፡ ከመወሰን ፡ የሚያግዳቸው ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ አልነበራቸውም ። ተሟጋቾቹ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ ጉዳያቸው ፡ በዝግታ ፡ እንዲወሰንላቸው ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ።

የአገረ ፡ ገዢዎች ፡ ዳኞችን ፡ የመሾምና ፡ የመሻር ፡ ሥልጣን ፡ የሕግ ፡ ተርጓሚውና ፡ የአስፈጻሚው ፡ መንግሥታዊ ፡ ክፍሎች ፡ የተለያዩ ፡ እንዳልነበሩ ፡ ያስረዳል ። ዳኞች ፡ የሥፍራው ፡ አገረ ፡ ገዢና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንደራሴዎች ፡ እንጂ ፡ (ማለት የሰው ፡ እንጂ) ፡ የሕግ ፡ እንደራሴዎች ፡ አልነበሩም ። ብዙውን ፡ ጊዜም ፡ የአንድ ፡ ቀበሌ ፡ ገዢ ፡ ከዳኞቹ ፡ ጋር ፡ አሁንም ፡ በአንዳንድ ፡ ቦታዎች ፡ እንደሚደረገው ፡ አብሮ ፡ ተሰይሞ ፡ በማስቻል ፡ በፍርድ ፡ አሰጣጥ ፡ ላይ ፡ ተጽዕኖ ፡ ነበረው ።

ተሟጋቾች ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጉንና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱንም ፡ ጭምር ፡ ያውቁ ፡ ስለነበር ፤ ሙግትም ፡ የሚጀመረው ፡ በቀላሉ ፡ ስለነበርና ፡ ከዳኞቹም ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ስለነበሩ ፡ ተሟጋቾች ፡ ሙግት ፡ ይወዱ ፡ ነበር ። በአውሮፓውያን ፡ ልማድ ፡ ሳይያዙ ፡ የጥንት ፡ ተረትና ፡ ምሳሌ ፡ በመጥቀስና ፡ ፈሊጥ ፡ በመናገር ፡ ረገድ ፡ ያላቸውን ፡ ችሎታ ፡ በመተማመን ፡ እንደልማዳቸው ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ ክስ ፡ ያቀርባሉ ።

ማናቸውም ፡ ተሟጋች ፡ የሚከራከረው ፡ ለመናገር ፡ ያሻውን ፡ በመናገር ፡ ስለነበረ ፡ ከሴቶችና ፡ በሕግ ፡ ችሎታ ፡ ከሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ በስተቀር ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ለማያውቁ ፡ መሐይሞችም ፡ እንኳን ፡ ጠበቃ ፡ አስፈላጊ ፡ አልነበረም ።

የጉቦ ፡ ጉዳይ ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ አልነበረም ። ዳኞቹ ፡ በሹመታቸው ፡ የሚኮሩ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ ከተሟጋቾች ፡ የሚቀበሉት ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ በባላገር ፡ ኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ተንደላቀው ፡ እንዲኖሩ ፡ ያስችላቸው ፡ ነበር ።

ዳኞች ፡ በየቀበሌያቸው ፡ የተከበሩና ፡ የተፈሩ ፡ ነበሩ ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሕዝቡን ፡ ስሜት ፡ የሚነካ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ የፈለጋቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለማውጣትና ፡ ነገሮችንም ፡ ለመወሰን ፡ ይችሉ ፡ ነበር ።

የይግባኝ ፡ መብት ፡ የተወሰነ ፡ አልነበረም ። በዝቅተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ የጀመረ ፡ ተሟጋች ፡ እስከ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ድረስ ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ ይችላል ።

በመጨረሻም ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የተወሰነ ፡ አልነበረም ። ስለዚህም ፡ በተለያየ ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ ሰዎችን ፡ የሚመለከት ፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ የሚሰማው ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ በተለያዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሳይሆን ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነበር ።

## የጣልያን ፡ ወረራ ፦

ጣልያኖች ፡ ያንጊዜ ፡ የነበረውን የኢትዮጵያ ፡ የበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አቅዋም ፡ ለማሻሻል ፡ ቢሞክሩም ፡ እንኳ ፤ በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይሠራበት ፡ የነበረው ፡ ቀዋሚውና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓታዊው ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ሳይለወጥ ፡ ቀረ ። ሆኖም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ኢጣልያዊ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ አንዳንድ ፡ ኢጣሊያዊ ፡ የወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተቋቁሞ ፡ ነበር ። ጣሊያኖች ፡ በኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ አውጀው ፡ በፍርድ ፡ ሥራ ፡ በኩልም ፡ ጠቅላላ ፡ የአስተዳደር ፡ ለውጥ ፡ ለማድረግ ፡ ቆርጠው ፡ ቢነሡም ፡ እንኳ ፤ ስለፍርድ ፡ ቤቶች፡ አቅዋም ፡ የተደረጉት ፡ ሙከራዎች ፡ ጥቂት ፡ ነበሩ ። ስለዚህ ፡ የወረራው ፡ ጊዜ፡ በተለይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዝቅተኛ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ መሻሻል ፡ የተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ አልነበረም ። በዚህ ፡ ጹሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱትም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚሠሩት ፡ እንደዱሮው ፡ ነበር ።[61]

## ከጣልያን ፡ ወረራ ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ አለንበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፦

የአሁኑ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የተመሠረተው ፡ ስለ ፡ ዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ በ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ አዋጅና ፡ ኋላም ፡ በወጡት ፡ በሕላዊ ፡ ሕግና ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ ነው ።[62] በርግጥ ፡ በጠቅላላው ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መሠረታዊ ፡ አቋም ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ለውጥ ፡ ያመጡት ፡ ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አመሠራረትና ፡ አስተዳደር ፡ እንዲሁም ፡ መከተል ፡ የሚገባቸውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚገልጹት ፡ አዋጆች ፡ ናቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከ፲፱፻፴፬ ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ልዩ ፡ ልዩዎቹ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ (እንዲሁም ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አሠራር ፡ ጭምር) ፡ የተቋቋሙባቸው ፡ ሕጎች ፡ የተሻሻሉት ፡ አቋማቸውን ፡ ለመለወጥ ፡ ግልጽ ፡ ሆነው ፡ ኋላ፡ በወጡ ፡ ሕጎች ፡ ሳይሆን ፡ በሕግ ፡ ተቋቁመው ፡ የሚገኙ ፡ የሌሎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ሥልጣን ፡ ሳይገልጽ ፡ ያንዳንዶቹን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ከሚዘረዝረው ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ አንቀጾችን ፡ በመተርጎም ፡ ነው ።[63]

የ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ የወጣው ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አሳሳቢነት ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መክሮበት ፡ ፓርላማ ፡ ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ሥራውን ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ በቀጥታ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታውጆ ፡ ነው ።[64] ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሳይመክርበትና ፤ ሳይስማማበት ፡ አዋጁን ፡ ለማውጣት ፡ የቻሉት ፡ በ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፴ ፡ እንደተመለከተው ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ በማይስማማበት ፡ ጊዜ ፡ አስቸኳይ ፡ ጉዳይ ፡ ሲገጥም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ብቻውን ፡ ሕግ ፡ ለማውጣት ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በታች ፡ እን

---

61. እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፮ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፻፶፱-፻፷ ።
62. "አዋጅ" በፓርላማ ፡ አልፎ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የጸደቀ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ኬ ፡ ሬደን ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አወጣጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡" ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገጽ ፡ ፲፪ ፡ ተመልከት ፡ (በእንግሊዝኛ)። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወጣ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፤ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፤ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እና ፡ የባህር ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወጥተዋል ።
63. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ።
64. ስለ ፡ ዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፤ ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መግቢያ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አንደኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፩ ።

ደሚብራራው ፡ በነዚህ ፡ አዋጆችና ፡ ሕግጋት ፡ ዳኞችን ፡ ለመሾም ፡ ቁጥራቸውን ፡ ለመወሰንና ፡ አስፈላጊውንም ፡ ችሎታቸውን ፡ በሕግ ፡ ለመደንገግ ፡ ሥልጣኑ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ነው ። ከዚሁም ፡ ጋር ፡ እንደ ፡ ዓቢይ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ የሚቆጠረው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ በአዋጅ ፡ አቋቁሞ ፡ እንዲያስተዳድሩም ፡ ለአፈ ፡ ንጉሡ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስትሩና ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጣቸው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ነው ።[65]

በ፲፱፻፴፩ ዓ. ም. በተፈጠረው ፡ በአዲሱ ፡ አሠራር ፡ ዘዴ ፡ ማዕከላዊው ፡ መንግሥት ፡ ለጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ተቀዳሚ ፡ ኃላፊነትን ፡ ወሰደ ። ከላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ይህ ፡ ኃላፊነት ፡ ለወትሮው ፡ በጠቅላይ ፡ ገዢዎች ፡ ተይዞ ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

የ፲፱፻፴፬ቱ፡ ዓ.ም. የዳኝነት ፡ ሥራ፡ አካሄድ ፡ አዋጅ ፡ [66]ከከፍተኛው፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡[67] በይግባኝ ፡ የሚመጡትን ፡ ነገሮች ፡ ለመስማት ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ "በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ " የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡[68] በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ እስከ ፡ ፪ሺህ ፡ ብርና ፡ በወንጀል ፡ ደግሞ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ለማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ እሥራትና ፡ ከ፪ሺህ[69] ፡ ብር ፡ የማይበልጥ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጫ ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸውን ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ አቋቋመ ።

በአዋጁ ፡ እንደተደነገገው ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአፈ ፡ ንጉሡ ፡ ፕሬዚዳንትነትና ፡ በሁለት ፡ የከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡[70] ዳኞች፡ የሚካሄድ፡ ነው ። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚሾማቸው ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ዳኞች ፡ እንዲኖራቸው ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ።[71] የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ በያንዳንዱ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ እንዲቋቋሙ ፡ ተደንግጎ ፡ ነበር ። አዋጁ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ በየትኛውም ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ የሚያስችል ፡ አንድ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቋቁሟል ።[72]

ምንም ፡ በደፈናው ፡ "ቢያቋቁሟቸውም"[73] ቅሉ ፡ የ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ምህረቱ ፡ አዋጅ ፡ የአውራጃ ፡ ግዛትን ፡ የወረዳ ፡ ግዛትንና ፡ የምክትል ፡ ወረዳ ፡ ግዛትን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አይገልጽም ። አዋጁ ፡ እነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መቋቋማቸውንና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ስለ ፡ ዳኞቹ ፡ ብዛት ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ የሥራ ፡

65. ስለ ፡ ዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፬ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቁጥር ፡ ፳ ።
66. በመጀመሪያ ፡ ይህ ፡ አዋጅ ፡ እንግሊዝና ፡ ኢትዮጵያ ፡ በጥር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ላደረጉት ፡ ስምምነት ፡ አባሪ ፡ ነበር ። ኤም ፡ ፔርሃም ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፻፶፬ ፡ እና ፡ ፬፻፳፫ ፡ ይመለከቷል ።
67. ስለ ፡ ዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፬ ፡ የተጠቀሰ ፡ ክፍል ፡ ሁለት ።
68. ከዚያው ፡ ክፍል ፡ ሶስት ።
69. ከዚያው ፡ ክፍል ፡ ሶስት ፡ አራት ።
70. ከዚያው ፡ ክፍል ፡ ሁለት ።
71. ከዚያው ፡ ክፍል ፡ አራትና ፡ ሶስት ፡ (፰) ።
72. ከዚያው ፡ ክፍል ፡ ሶስት ፡ (፱) ።
73. ከዚያው ፡ ክፍል ፡ አንድ ፡ (፪) (መ-ረ) ።

ነገር ፡ የዳኝነትና ፡ የይግባኝ ፡ ሥልጣን ፡ በተጨማሪም ፡ "የሚከተሉትን ፡ ሕግ ፡[74] ለመወሰን" ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ ይናገራል ።

በ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ማለት ፡ የአውራጃ ፡ የወረዳና ፡ የምክትል ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተቋቋሙትና ፡ ሥልጣና ቸውም ፡ የተዘረዘረው ፡ ምናልባት ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባስተላለፈው ፡ ዚሬ ፡ ደብ ዳቤ ፡ (ሰርኩለር) ፡ ሳይሆን ፡ አልቀረም ።[75] አገረ ፡ ገዥዎችና ፡ ምስለኔዎች ፡ በኋላ ፡ በተላለፈ ፡ ትዕዛዝ ፡ መሠረት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ሆነው ፡ ለማስቻል ፡ ሥልጣን ፡ ነበራ ቸው ።[76] በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በአገር ፡ ቤት ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ በታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ አይሠራበትም ።

በ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጊዜው ፡ የነበሩት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚሠሩበት ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ደንብ ፡ ወጣ ።[77] የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሔድ ፡ በተጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በነበረው ፡ የእንግሊዝ ፡ ተጽዕኖ ፡ (በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የከፍ ተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሦስት ፡ ዳኞች ፡ እንግሊዞች ፡ ነበሩ) ።[78] ፡ ምክንያት ፡ የወ ጣው ፡ ደንብ ፡ የእንግሊዝን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተከተለ ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ ደንብ ፡ ግምቱ ፡ ከሁለት ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የሆነውን ፡ ክስ ፡ ተቀብሎ ፡ ክርክሩን ፡ በመ ጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ለመስማት ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቷል ፤ እን ዲሁም ፡ ክስ ፡ የሚቀርብበትን ፡ ሁኔታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚከተለውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ስለሚነጋገረው ፡ ጠበቃ ፡ ፈቃድ ፡[79] ነገረተኞችንና ፡ ክሶችን ፡ በአንድነት ፡ ስለማጣመር ፡ ጉዳይ ፡ የጥሪ ፡ ማዘዣ ፡ ስለመላክና ፡ ስለመስጠት ፡ ስለአ ቤቱታ ፡ ስለ ፡ ይግባኝና ፡ ስለቀሩትም ፡ ጉዳዮች ፡ በጠቅላላው ፡ ደንግጓል ።

እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ማናቸውም ፡ ክስ ፡ ሲጀመር ፡ "የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ አገባብ ፡ ላለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሬጅስትራር ፡ በማቅረብ ፡ እንዲጀመር ፡ ያዛሉ ።[80] አቤቱታው ፡ ባይ ጸፍም ፡[81] ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ የሚበቃ ፡ ምክንያት ፡ ያገኙ ፡ እንደሆነ ፡ በጽሕፈት ፡ ሊቀርብ ላቸው ፡ የሚገባው ፡ በቃል ፡ አመልካችነት ፡ ብቻ ፡ እንዲቀርብላቸው ፡ ለመፍቀድ ፡ ይች ላሉ ፡ በማለት ፡ ደንግገዋል።[82] ይህ ፡ ደንብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በቂ ፡ ሠራተኞች ፡ ከሌሏቸው፡ ይህንን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሳይከተሉ ፡ እንዲሠሩ ፡ ፈቅዷል ። በተጨማሪ ፡ እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከአውራጃ ፡ ግዛት ፡ ወይም ፡ ከወረዳ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጉዳዩን ፡ ወደ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲዛወርለት ፡ ለማድ ረግ ፡ እንደሚችል ፡ ይደነግጋሉ ። እነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የወጡት ፡ ምናልባት ፡ የተማሩ፡ ሰዎች፡በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እምነት ፡ ስለማይኖራቸውና ፡ እንዲሁም ፡ ምናልባት ፡

---

74. ከዚያው ፡ ክፍል ፡ አምስት ።
75. እር ፡ ሴድለር ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፲፱፻፷—ገጽ ፡ ፱ ።
76. የአገር ፡ አገዛዝ ፡ ደንብ ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ ድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ አንድ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አንደኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲ ።
77. ስለ ፡ ዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የወጣ ፡ ደንብ ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፴፫ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፪ ።
78. ኤም ፡ ፔርሃም ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፻፶፯ ።
79. በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለጠበቆች ፡ ፈቃድ ፡ አይሰጥም ፡ ነበር ።
80. ስለ ፡ ዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የወጣ ፡ ደንብ ፡ ፲፱፻፴፮ ፡ ክፍል ፡ ሁለት ፡ (፩) እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፸፰ ፡ የተጠቀሰ ።
81. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፴(፩) ።
82. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፴(፲፪) ።

የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ለመከራከር ፡ እንዳይገደዱ ፡ በማሰብ ፡ ይሆናል ።[83]

ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ስለሚቀርብበት ፡ ሁኔታ ፡ በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሌላ ፡ ደንብ ፡ ወጥቷል ።[84] ጠበቆች ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፤ ስለፈቃድና ፡ ስለሚከተሉትም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚያዝዝ ፡ ደንብ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወጥቷል ።[85]

በማንኛውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሠራበት ፡ የፍርድ ፡ ማስፈፀምያ ፡ ደንብ ፤ የፍርድ ፡ አስፈፃሚ ፡ (የፍ/ሚኒስቴር ፡ የሚሾመው ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሰው) ፡ ከሚያስከብራቸው ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔዎች ፤ እንደ ፡- የፍርድ ፡ ባለዕዳ ፡ የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ የሚይዝበትንና ፡ የሚያሥርበትን ፡[86] ንብረት ፡ አስከብሮ ፡ የሚሸጥበትን ፡[87] መንገድ ፡ የሚናገር፡ አዋጅ ፡ ወጥቷል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ መክፈል ፡ አለመቻሉን ፡ ካመነ ፡[88] ወደ ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ እንዳይሄድ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ በፍርዱም ፡ ማስፈጸም ፡ ምክንያት ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ዕዳውን ፡ በመክፈል ፡ ምክንያት ፡ የዕለት ፡ ጉርሱን ፡ የሚነሣው ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቡ ፡ ለፍርድ ፡ ባለዕዳው ፡ ለመኖር ፡ የሚያስችለውን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ በየጊዜው ፡ እንዲከፍለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲወስን ፡ የ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ደንብ ፡ ያዛል ።[89] ሕጉ ፡ በተጨማሪ ፡ ንብረቱ ፡ ተሸጦ ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ፍርዱን ፡ ለማስፈጸም ፡ እንዲቻል ፡ ንብረቱ ፡ የሚሸጥበትን ፡ ሁኔታ ፡ ይዘረዝራል ፡ (ይደነግጋል) ።

ስለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሔድ ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ መሠረት የተረታው ፡ ሰው ፡ የሚከፍለውን ፡ ኪሣራ ፡ የሚወስንበት ፡ ደንብ ፡ ወጥቷል ።[90] ለዳኝነት ፡ ስለሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ የሚያስረዳ ፡ ዝርዝር ፡ ሌላ ፡ ደንብ ፡ ደግሞ ፡ ወጥቷል ።[91]

ዓቃብያነ ፡ ሕግን ፡ የሚመረጡበት ፡ መንገድና ፡ ደረጃቸው ፡ ስለአቃቤ ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ተደንግጓል ።[92] በዚሁ ፡ አዋጅ ፡

---

83. ኤም ፡ ፔርሃም ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፻፶፬ ።
84. ስለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የወጣ ፡ ደንብ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ የሕግ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፻፶፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አሥረኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ ።
85. ስለጠበቆች ፡ በመዝገብ ፡ መግባት ፡ የወጣ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ደንብ ፡ እላይ ፡ በማስታወጣሻ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ የተጠቀሰ ።
86. ስለፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ የወጣ ፡ ደንብ ፡ ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አንቀጽ ፡ ፯ (ሀ) ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፻፸፯ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፪ ።
87. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፯(ለ) ።
88. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፰ ።
89. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳዎች ፡ ዕዳቸውን ፡ ለአበዳሪዎቻቸው ፡ በጉልበት ፡ ሥራ ፡ እንዲከፍሉ ፡ የሚደረገውን ፡ የሚመለከት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ስለፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ የወጣው ፡ ደንብ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ፡ አንድን ፡ ፍርድ ፡ በእሥራት ፡ የባለዕዳውን ፡ ገንዘብ ፡ በማስከበር ፡ እና ፡ ለፍርድ ፡ አፈጻጸሙ ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ሌላ ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ በማድረግ ፡ ለማስፈጸም ፡ ይቻላል ፡ ይላል ። ይህ ፡ የኋለኛው ፡ ደንብ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳዎችንም ፡ ማሠርን ፡ ሊጨምር ፡ ይችላል ።
90. ስለኪሣራና ፡ ስለጠበቃ ፡ አበል ፡ የወጣ ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፻፸፯ ፡ ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አሥራ ፡ ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፬ ።
91. ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ አከፋፈል ፡ ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፻፸፯ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አሥራ ፡ ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ ።
92. ስለዐቃብያነ ፡ ሕግ ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፪ ።

በፍርድ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ አቅራቢነት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዳኞችን ፡ የሚሾሙና ፡ የፍርድ፡ ሚኒስቴሩም ፡ የሚቆጣጠራቸውና ፡ መምሪያም ፡ የሚሰጣቸው ፡ መሆኑ ፡ ተደንግጓል ።[93] በዚህ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ዐቃብያነ ፡ ሕግ ፡ የተሟላ ፡ የሕግ ፡ ችሎታ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ያገለገሉ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከረዳት ፡ መኰንንነት ፡ በላይ ፡ በፖሊስ ፡ ሥራ ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ እንዲሆኑ ፡ ያስፈልጋል ።[94]

ናኢባ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአዋጅ ፡ ታውቀው ፡ ወይም ፡ ተቋቁመው ፡ ስለቤተሰብ ፡ ስለጋብቻና ፡ ስለውርስ ፡ ጉዳዮች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቷቸዋል ።[95] ሆኖም ፡ አዋጁ ፡ የነዚህን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣንና ፡ የሚመሩበትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዲደነግግላቸው ፡ ያዛል ።[96]

ስለዳኝነት ፡ አካሄድ ፡ ጉዳይ ፡ በየጊዜው ፡ ከወጡት ፡ አዋጆች ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ ስለአጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ የወጣው ፡ ነው ። በ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ግምቱ ፡ እስከ ፡ $ 26.00 ፡ የሚደርስ ፡ የፍትሐብሔር ፡ ነገርና ፡ ከ$ 15.00 ፡ የበለጠ ፡ ቅጣት ፡ የማያስቀጣ ፡ የወንጀል ፡ ነገርን ፡ ሊያነጋግሩ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ አጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ፡[97] በያንዳንዱ ፡ ቀበሌ ፡ ይሾማሉ ። ከእነርሱም ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ወደ ፡ አቅራቢያው ፡ ምክትል ፡ ወረዳ ፡ ወይም ፡ ወረዳ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይወሰዳል ።[98] በመሠረቱ ፡ እነዚህ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ሆነው ፡ የሚሾሙት ፡ ሰዎች ፡ በቀበሌው ፡ ከሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ የሚፈሩና ፡ አብዛኛውንም ፡ ጊዜ ፡ ባሉበት ፡ ቀበሌ ፡ ባለብዙ ፡ ርስት ፡ የሆኑ ፡ ደንበኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከሚገኙባቸው ፡ ቦታዎች ፡ በሩቁ ፡ ሥፍራዎች ፡ የሚነሱትን ፡ ጠብና ፡ ጭቅጭቅ ፡ በእርቅ ፡ እንዲያበርዱ ፡ የሚሾሙ ፡ ናቸው ።[99] አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ዳኞች ፡ ከመሾማቸው ፡ በፊት ፡ ለቀበሌ ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ዳኞች ፡ ከመሾማቸውም ፡ በፊት ፡ በቀበሌ ፡ ዳኞች ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ የተመለከተውን ፡ ሥልጣን፡ ኦፊሲየል ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ሲሠሩበት ፡ የቆዩ ፡ ናቸው ።

በመጨረሻም ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ አስተዳደር ፡ የሚመለከተው ፡ ሌላው ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ በቅርቡ ፡ ያወጣው ፡ አዋጅ ፡ ነው ።[100]

ይህ ፡ አዋጅ ፡ ከኤርትራ ፡ በስተቀር ፡ በሌሎቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ ቢደረግም ፡ በአዋጁ ፡ መሠረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖር ፡ የተፈለገው ፡[101] <u>የፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ቅንጅት ፡ በመሠረቱ ፡ አሁን ፡ የሚሠራበት ፡ ሲሆን ፡</u> ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህ ፡ አዋጅ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋል ፡ ቢታገድም ፡ ከዚህ ፡በታች፡እንደተ

93. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፳ ።
94. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፬ ፡ (ሀ—ሐ) ።
95. ስለቃዲና ፡ የናኢባ ፡ ጉባኤ ፡ አዋጅ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፳፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ሦስተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ።
96. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ።
97. በ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ አጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ሹመት ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፺ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ስድስተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ (ሀ—ሐ) ።
98. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፳ ።
99. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ።
100. ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፻፺፭ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ሃያ ፡ ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፯ ።
101. ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ ማሻሻያ ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ፪፻፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ሃያ ፡ ሁለተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ።

መለከተው ፡ በአዋጁ ፡ አማካይነት ፡ ሊገኙ ፡ የነበሩት ፡ ለውጦች ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ በሞላ ፡ ጐደል ፡ ተገኝተዋል ። ይህ ፡ አዋጅ ፡ የምክትል ፡ ወረዳና ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ በማስቀረት ፡[102] በአራት ፡ ደረጃ ፡ የተከፈለ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ አቋቋሚል ። እነርሱም ፡ ስለተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ እስከ ፡ የኢ.ት ፡ ፭፻ ፡ ብር ፡ ስለመሬት ፡ ጉዳይ ፡ እስከ ፡ የኢ.ት ፡ ፩ሺ ፡ ብር፡[103] የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የወረዳ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ የሚሰማ ፡[104] እና ፡ ለተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት፡ ከኢ.ት፡ ፭፻፡ ብር ፡ እስከ፡ ኢ.ት ፡ ፭ሺህ፡ ብር፡ እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀስ፡ ንብረት፡ ከኢ.ት ፡ ፩ሺህ ፡ ብር፡ እስከ ፡ የኢ.ት ፡ ፲ሺህ ፡ ብር ፡[105] የሚዳኝ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የዚህን ፡ ይግባኝ ፡ የሚሰማና፡ ለተንቀሳቃሽ ፡ ንብረት ፡ ከኢ.ት ፡ ፭ሺህ፡ ብር፡ በላይ፡ እንዲሁም፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከኢ.ት ፡ ፲ሺህ ፡ ብር ፡ በላይ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡[106] እንዲሁም ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ የሚሰማ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡[107] ናቸው ።

በዚህ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የከፍተኛውና ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፤ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አስፈላጊና ፡ ተስማሚ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ በማናቸውም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የእነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የችሎት ፡ ክፍሎች ፡ እንዲያስችሉ ፡ ያደርጋል ።[108] የወረዳና ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ግን ፡ የሚያስችሉት ፡ ባሉበት ፡ በወረዳ ፡ ግዛትና ፡ በአውራጃ ፡ ግዛት ፡ ሲሆን ፡ በክልላቸው ፡ ውስጥ ፡ በተሰጣቸው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ተወስነው ፡ የሚያስችሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ።

በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሦስት ፡ ዳኞች ፡ ያስችል ፡ የነበረውን ፡ የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ሲያስችሉ ፡ በአንድ ፡ ዳኛ ፡ ብቻ ፡ ሊያስችሉ ፡ እንደሚችሉና ፡ በይግባኝ ፡ ለቀረበላቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሦስት፡ ሆነው ፡ እንዲያስችሉ ፡ ደንግጓል ።[109]

የጥቅም ፡ ግጭት ፡ ካለ ፡ ዳኛው ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡[110] ወይም ፡ ከተከራካሪዎቹ ፡ በአንደኛው ፡ አመልካችነት ፡[111] ከችሎት ፡ መነሳት ፡ ይችላል ።

በ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ለአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ የተሰጠውን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ አጽድቆታል ።[112]

---

102. ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፻፩ ፡ የተጠቀሰ ።
103. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፯(፩) ።
104. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፰(ሀ) ።
105. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፯(፪) ፡ ፰(ሀ) ።
106. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፯(፫) ፡ (፩) ።
107. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፰(ሐ) ።
108. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ ፳ ።
109. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፬ ።
110. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፲፯(፪) ።
111. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ።
112. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ።

በዚህ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ደህንነት ፡ ስለ ፡ ጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ ጸጥታና ፡ ሰላም ፡ የምስክር ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ እንደልብ ፡ ለመስጠት ፡ ካላስቸገረ ፤ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ልጆች ፡ ጥቅማቸው ፡ እንዲጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ችሎቱ ፡ ካልተዘጋጀ ፡ በስተቀር ፡ ማናቸውንም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርም ፡ ሆነ፡ የወንጀል ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በግልጽ ፡ ችሎት ፡ መሰማት ፡ አለበት ።[113]

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ አዋጅ ፡ ያመጣቸው ፡ ለውጦች ፡-

፩/ ሁለቱን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ማለትም ፡ የምክትል ፡ ወረዳንና ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛትን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ማስቀረቱ ፤

፪/ የምክትል ፡ ወረዳና ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የነበራቸውን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ እንደገና ፡ ማደላደሉ ፤

፫/ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሚቀርብለትን ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ብቻ ፡ እንዲሰማ ፡ በማድረጉ ፡ ለአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሙሉ ፡ ችሎት ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ዳኞች ፡ ቁጥር ፡ መቀነስና ፤

፬/ የከፍተኛውና ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ክፍሎች ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ተቋቁመው ፡ እንዲያስችሉ ፡ መፈቀዱ ፡ ነው ።

ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደተነገረው ፡ ምንም ፡ ይህ ፡ አዋጅ ፡ ከኤርትራ ፡[114] በስተቀር ፡ በቀሩት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ እንዳይሠራበት ፡ ቢታገድም ፡ እንኳን ፡ በአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሚቀርበውን ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ብቻ ፡ ያስችላል ፡ ተብሎ ፡ ከተደነገገው ፡ በስተቀር ፡ የቀሩት ፡ ለውጦች ፡ በሙሉ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ውለዋል ።

የምክትል ፡ ወረዳና ፡ የጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቀርተዋል ። ለዚህም ፡ ማረጋገጫ ፡ የሆነው ፡ በ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ፡ ሥርዓትና ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አለመሰጠታቸው ፡ ነው ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡[115] ለወረዳ ፡ ለአውራጃ ፡ ለከፍተኛውና ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጣቸው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ በ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ላይ ፡ ከተዘረዘረው ፡ ዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ።

የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ዋና ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚያስችል ፡ ሲሆን ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ደግሞ፡ በአሥመራ ፡ አንድ ፡ ቅርንጫፍ ፡ አለው ።[116]

113. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፲፬ ።

114. ስለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣውን ፡ አዋጅ ፡ ማሻሻያ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፫ ፡ የተጠቀሰ ።

115. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ — ፲፮ ።

116. ስለዚህ ፡ የ፲፱፻፶፮ ፡ ዓመተ ፡ ምህረቱ ፡ አዋጅ ፡ የሚደነግጋቸው ፡ የማሻሻያ ፡ ሕጎች ፡ ዛሬ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ውለው ፡ ሲታይ ፡ አዋጁ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ እንዳይሠራበት ፡ ታገደ ፡ ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ ይቻላል ። አዋጁ ፡ በፓርላማ ፡ አልፎ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከፀደቀ ፡ በኋላ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አዋጁ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ለመሥራት ፡ የማይችል ፡ በመሆኑ ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ አዋጁ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ የሚጠይቅ ፡ ሴርኩላር ፡ (ደብዳቤ) ፡ አስተላለፈ ። ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ማገጃ ፡ በኋላም፡ የሕግ ፡ መምሪያና ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ የ፲፱፻፶፮ ፡ ዓመተ ፡ ምህረቱ ፡ አዋጅ ፡ እንዳይሠ

የአራቱን ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ማለት ፡ የወረዳ ፡ የአውራጃ ፡ የከፍተኛው ንና ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የሚወስ ነው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚገኙትን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቁጥራቸውንና ፡ ችሎታቸውን ፡ የሚደነግጉ ፡ ሕጎች ፡ ሆነዋል ።

በአጭሩ ፡ እንግዲህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ በአ ራት ፡ ደረጃ ፡ የተከፈሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚመ ለከታቸው ፡ የሁለቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡በ፲፱፻፶፰፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ እንደሚመለከተው፡ ተገልጿል ።

"ቁጥር ፡ ፲፫ ፡- የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ተመድቧል ።

(ሀ) በሚንቀሳቀሱ ፡ ንብረት ፡ ከ፭፻ ፡ የኢ.ት/ብር ፡ የማይበልጥ ፡ ክስ ፡

(ለ) በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከ ፭ሺህ ፡ የኢ.ት/ብር ፡ የማይበልጥ ፡ ክስ ።

ቁጥር ፡ ፲፬ ፡- የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሁኔታ ፡ ተመድቧል ።

(ሀ) በሚንቀሳቀስ ፡ ሀብት ፡ ከ፭ሺህ ፡ የኢ.ት/ብር ፡ የማይበልጥ ፡ ክስ ።

(ለ) በማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ከ፲ሺህ ፡ የኢ.ት/ብር ፡ የማይበልጥ ፡ ክስ ።

ማናቸውም ፡ ክስ ፡ መቅረብ ፡ የሚገባው ፡ ክሱን ፡ ለመቀበል ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ "ዝቅተኛ ፡ ደረጃ ፡" ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።[117]

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ "በገንዘብ ፡ ግምት ፡ ሊወሰን ፡ በማይችል ፡ ሀብት ፡ ምክንያት ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ የሚታየው ፡ ክሱ ፡ በተነ ሣበት ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡" በማለት ፡ ለአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተጨ ማሪ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቷል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ክስ ፡ ስለፍቺ ፡ ጉዳይ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ውሳኔዎችን ፡ መስማት ፡ ፍቺ ፡ ለማጽደቅ ፡ ማመልከቻ ፡ መቀ በልና ፡ ንብረት ፡ ለመውረስ ፡ ባለመብት ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ መብቱን ፡ ማሳወቅ ፡ የመ ሳሰሉትን ፡ ይጨምራል ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ወረዳ ፡ ግዛት ፡ አንድ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እን ደዚሁም ፡ በያንዳንዱ ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ አንድ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አለ ። እነ ዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በግዛታቸው ፡ ውስጥ ፡ በሚኖሩ ፡ ወይም ፡ በግዛታቸው ፡ ውስጥ ሥራ ፡ በሚሠሩ ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡[118] የሚነሣውን ፡ ክስ ፡ እንዲሁም ፡ የክሱ ፡ ምክ

ራበት ፡ ወሰኑ ። ሆኖም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኤርትራ ፡ የዳኝነት ፡ አሠራሯን ፡ ከእንግሊዞች ፡ ሥርዓት ፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ ፡ የዳኝነት ፡ ሥርዓት ፡ በመመለስ ፡ ላይ ፡ ስለነበረች ፡ የ፲፱፻፶፭ ፡ ዓመት ፡ ምህረቱን ፡ አዋጅ፡ ቀደም ፡ አድርጋ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አውላው ፡ ስለነበር ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሠራበት ፡ ተፈቀደ ። ኤን ፡ ሜትዠር ፡ በኤርትራ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ (ያልታተመ) ፡ (በእንግሊዝኛ) ፡ አሥ መራ ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ገጽ ፡ ፯ ፡ ይመለከቷል ። ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መጻሕፍት ።

117. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቍጥር ፡ ፲፪ ።

118. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ።

ንያት ፡ በግዛታቸው ፡ ውስጥ ፡ የደረሰ ፡ እንደሆነ ፤[119] ክሱን ፡ ይሰማሉ ። የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በዳኝነት ፡ ሥልጣናቸው ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ከወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚመጣውን ፡ ይግባኝ ፡ ይሰማሉ ።[120] ለምሳሌ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዳኝነት ፡ ሥልጣኑ ፡ ውስጥ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙ ፡ አሥር ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሲኖሩ ፡ የእነርሱን ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ይሰማል ። በሌሎቹ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በዳኝነት ፡ ሥልጣናቸው ፡ ውስጥ ፡ ከሦስትና ፡ ከአራት ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ያላነሱ ፡ ይገኛሉ ። የእነርሱንም ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ይሰማሉ ።

የወረዳና ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወንጀል ፡ ዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ በ፲፱፻፶፬ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተደንግጓል ። በጠቅላላው ፡ የወንጀል ፡ ነገር ፡ የሚሰማው ፡ "ማንኛውም ፡ ወንጀል ፡ በተፈጸመበት ፡ ሥፍራ ፡ ሥልጣኑ ፡ በሚፈቅድለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡" ነው ።[121]

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በአንቀጽ ፡ ፬ ፡ መሠረት ፡ ከሕጉ ፡ ጋራ ፡ በተያያዘው ፡ ሠንጠረዥ ፡ የተመለከቱትን ፡ ወንጀሎች ፡ ለማየት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቷቸዋል ። በመሠረቱ ፡ እንደወንጀሉ ፡ ከባድነት ፡ መጠን ፡ ወንጀሉን ፡ ለመስማት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደዚሁ ፡ ከፍ ፡ ይላል ። ለምሳሌ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ስለእጅ ፡ እልፊት ፡ ጉዳይ፤[122] ስለአምባጓሮ ፤[123] ስለዛቻ ፤[124] ለክስ ፡ ወይ ፡ ለማዋረድ ፡ ስለሚደረግ ፡ ዛቻ ፤[125] ስለስድብና ፡ ስለማዋረድ ፤[126] ስለመገናኛ ፡ የጸጥታን ፡ ደንብ ፡ ስለመጣስ ፤[127] የሰውን ፡ የግል ፡ ነፃነት ፡ ስለመንካት ፤[128] አደገኛ ፡ ስለሆነ ፡ ሥራ ፡ ፈትነት ፤[129] በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ ሰዶ ፡ ስለማበላሸት ፤[130] እና ፡ በሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ ስለማንሣት ፡ ጉዳይ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።[131]

---

119. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ቁጥር ፡ ፳፬ ፡ በውሉ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ካልተገለጸ ፡ በቀር ፡ በውል ፡ ምክንያት ፡ ክርክር ፡ የተነሳ ፡ እንደሆነ ፡ ውሉን ፡ በተዋዋሉበት ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ውሉ ፡ እንዲፈጸም ፡ በታቀደለት ፡ ክፍል ፡ በሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክሱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ይፈቅዳል ። በቁጥር ፡ ፳፯ ፡ መሠረትም ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በሚንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ላይ ፡ በደረሰ ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ካሣ ፡ የመጠየቅ ፡ ክርክር ፡ የተነሳ ፡ እንደሆነ ፡ ክሱ ፡ ጉዳቱ ፡ በደረሰበት ፡ ሥፍራ ፡ ለሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ወይም ፡ ተከሳሹ ፡ በሚገኝበት ፡ አካባቢ ፡ ለሚገኘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ።
120. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፳፩ ።
121. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፺፱ ፡ ድርጊቱ ፡ ባንድ ፡ የአገዛዝ ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ ተፈጽሞ ፡ ውጤቱ ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ሲሆን ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፻) ፡ በየትኛው ፡ ሥፍራ ፡ ወንጀሉ ፡ እንደተፈጸመ ፡ ያልተረጋገጠ ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፻፪) ፡ ወንጀሉ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውጭ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፻፬) ፡ ጉዳዩ ፡ በሌሎች ፡ ቁጥሮች ፡ ይመራል ።
122. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፵፬ ።
123. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፵፱ ።
124. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፶፪ ።
125. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፷፫ ።
126. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፹፫ ።
127. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፹፫ ።
128. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፺፯ ።
129. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፸፩ ።
130. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፵፱ ።
131. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፶ ።

አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰሙት ፡ የወንጀል ፡ ክሶች ፡ በግል ፡ ከሳሽ ፡ የሚቀርቡት ፡ ናቸው ።[132] በጠቅላላው ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ክሶች ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚነሡት ፡ ጭቅጭቆች ፡ በድንገት ፡ ተነሣሥቶ ፡ የሚፈጸመው ፡ ወንጀሎች ፡ በቸልተኝነት ፡ ምክንያት ፡ ስለሚደርሱ ፡ ጥፋቶች ፡ በግድየለሽነት ፡ የሚደረጉ ፡ ጥፋቶች ፡ ስለጤና ፡ አጠባበቅ ፡ ጉዳይና ፡ በመደሰቻ ፡ ቦታዎች ፡ የሰዓት ፡ እላፊ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤትን ፡ ደንብ ፡ የመጣስ ፡ የመስፋፋት ፡ ወንጀሎች ፡ ናቸው ።

የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ስለስርቆት ፤[133] በንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለማድረግ ፡ ከባድ ፡ ሁኔታ ፤[134] ስለ ፡ መጥለፍ ፤[135] ስለማስወረድ ፡ ተግባር ፤[136] ታስቦ ፡ ስለተደረገ ፡ ከባድ ፡ የአካል ፡ጉድለት ፤[137] በሰነድ ፡ ላይ ፡ ስለሚደረግ ፡ ማጭበርበር ፤[138] የሳይንስ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ወይም ፡ የንግድ ፡ ምስጢር ፡ ስለመግለጽ ፤[139] እና ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ ስለመፈጸም ፤[140] የሚቀርቡትን ፡ ክሶች ፡ ለመስማት ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

ዳግም ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ስለወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ በዳኝነት ፡ ሥልጣናቸው ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚቀርቡላቸውን ፡ ይግባኝ ፡ ለመስማት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።[141]

## ኤርትራ ።

ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ኤርትራ ፡ በተለይም ፡ ስለ ፡ አሥመራ ፡ የዳኝነት ፡ አስተዳደር ፡ ደጋግሞ ፡ ስለሚያወሳና ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ከ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የኤርትራ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ከቀሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ በተለየ ፡ መንገድ ፡ ይመራ ፡ ስለነበር ፡ ስለኤርትራ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሔድና ፡ ስለአመጣጡ ፡ መግለጫ ፡ መስጠት ፡ ተገቢ ፡ ነው ። ይህም ፡ ማብራሪያ ፡ በ፲፱፻፵፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ አስተዳደር ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኤርትራ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የወረዳና ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ እርምጃ ፡ በመግለጽ ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ።

ጣልያኖች ፡ ኤርትራን ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ፲፱፻፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ይዘው ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ አደረጓት ። እነርሱም ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አቋቋሙ ፤ አንደኛው ፡ ለጣሊያኖችና ፡ ከኤርትራውያን ፡ ጋራ ፡ ለተደባለቁት ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ግን ፡ ለኤርትራ ፡ ተወላጆች ፡ ብቻ ፡ ነበር ።[142] የቅኝ ፡ አገዛዙ ፡ አስተዳደር ፡ በኤርትራ ፡ ተወላ

---

132. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ እና ፡ ፵—የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፲፯ — ፪፻፳፪ ፡ እና ፡ ፯፻፳፮ ።
133. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፴ ።
134. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፶፬ ።
135. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፶፰
136. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፳፱ — ፭፻፴ ።
137. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፴፰ ።
138. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፹፫ ፡ ፫፻፹፬ ።
139. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፱ ።
140. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፲፯ ።
141. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፺፹፪(፩)(ሀ) ።
142. ኤን ፡ ሚሪያን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛት ፡ ፌዴሬሽንና ፡ ሕጐች ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገጽ ፡ ፫፻፸፩ ፡ (በእንግሊዝኛ) ።

ጆች ፡ መካከል ፡ ስለሚደረገው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክር ፡ ጉዳይ ፡ "በኤርትራው ያን ፡ ዳኞች ፡"[143] እንዲዳኙ ፤ ሆኖም ፡ ዳኞቹ ፡ በሚሰሙት ፡ ነገር ፡ በአንድ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚነሣውን ፡ ክርክር ፡ ብቻ ፡ እንዲሰሙ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶ ፡ ነበር ።[144] ጣሊያኖች ፡ ደግሞ ፡ የእስላም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በዚሁ ፡ አኳኋን ፡ እንዲሠሩ ፡ ፈቅ ደው ፡ ነበር ።[145]

የጣሊያን ፡ የክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ እንደራሴና ፡ የአውራጃው ፡ ገዥ ፡ በሁለት ፡ የተለ ያዩ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ባላቸውና ፡ በተለያዩ ፡ ጐሣዎች ፡ በሆኑ ፡ በኤርትራውያኖች ፡ መካከል ፡ የሚነሣውን ፡ ክርክር ፡ ይሰማሉ ። ከኤርትራውያን ፡ ረዳቶች ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ የኤርትራውያን ፡ ዳኞችን ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ። በተጨማሪም ፡ እነዚሁ፡ ሹሞች ፡ በኤርትራውያን ፡ መካከል ፡ የሚነሡትን ፡ የወንጀል ፡ ነገሮች ፡ ይዳኙ ፡ ነበር ።[146]

ከክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ እንደራሴና ፡ ከአውራጃው ፡ ገዥ ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ ኤርትራው ያን ፡ በሚፈጽሙት ፡ በከፍተኛ ፡ ከባድ ፡ ወንጀል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ጎሣዎች ፡ መካከል ፡ ስለሚነሣው ፡ ጠብና ፡ በቅኝ ፡ አገዛዙ ፡ አስተዳደር ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ወንጀል ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የነበረው ፡ የጣልያን ፡ ኮሚሽነር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነበር ፤[147] ከኮ ሚሽነሩ ፡ ጋራ ፡ ኤርትራውያን ፡ እንደአማካሪ ፡ ሆነው ፡ ይቀመጣሉ ።[148]

የቅኝ ፡ ግዛቱ ፡ ጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ ከአራት ፡ ጣሊያኖችና ፡ ከአራት ፡ ኤርትራ ውያን ፡ አማካሪዎች ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ከኮሚሽነር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርበውን ፡ ይግ ባኝ ፡ ይሰማል ።[149]

ኤርትራውያን ፡ በትግርኛ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፉ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕጎች ፡ ስለነበራቸው፡ በኤርትራውያን ፡ መካከል ፡ በሚነሣው ፡ ክርክር ፡ የሚሠራበት ፡ ሕግ ፡ ይኸው ፡ ልማ ዳዊው ፡ ሕግ ፡ ነበር ።[150] ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ አብዛኛው ፡ ይከተሉት ፡ የነበረው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ የተገለጸው ፡ የቀሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ የነበሩት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይከተሉት ፡ የነበረው ፡ ዓይነት ፡ ነበር ።

እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንግሊዞች ፡ ኤርትራን ፡ ያዙ ። በእንግሊዝ ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ የየመንደሩ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ክሶች ፡ ለመስማት ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጣቸው ።[151] የአውራጃ ፡ ሹሞችና ፡ ባላባቶች ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚዎች ፡ ነበሩ ።[152] "ቋሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡" ተብሎ ፡ ይጠራ ፡ የነበረው ፡ የእንግሊዝ ፡ ዳኞች ፡ የነበሩት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በከባድ ፡ ወንጀል ፡ የሚከሰ ሱትን ፡ ኤርትራውያን ፡ ጉዳይ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።[153]

143. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፸፫ ።
144. ከዚያው ።
145. ከዚያው ።
146. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፸፬ ።
147. ከዚያው ።
148. ከዚያው ።
149. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፸፰ ።
150. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፸፱ ።
151. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፹፩ ።
152. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፹፪ ።
153. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፹፬ ።

የጣሊያን ፡ ኮሚሽነር ፡ በኤርትራውያን ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የወሰደው ፡ እንግሊዞች ፡ "የአገሩ ፡ ተወላጅ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡" ብለው ፡ ያቋቋሙት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይካሄዱ ፡ የነበሩት ፡ በኤርትራው ያን ፡ ዳኞች ፡ ሆኖ ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ሲኖራቸው ፡ በወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ የተወሰነ ፡ ነበር ። በወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ እነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይሠሩበት ፡ የነበረው ፡ ሕግ ፡ የእንግሊዝ ፡ አስተዳ ደር ፡ አሻሽሎ ፡ ያወጣው ፡ የጣልያን ፡ ሕግ ፡ ነበር ።[154] በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ እነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ በመጠቀም ፡ ኤርትራውያን ፡ ባላባቶች ፡ የሰጡትን ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኤርትራ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ በፌዴሬሽን ፡ ተቀላቀለች ። ከፌ ዴሬሽኑ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ የዳኝነት ፡ አስተዳደር ፡ አዋጅ ፡ ወጣ ። አዋጁም ፡ በኤርትራ ፡ የዳኝነት ፡ አስተዳደር ፡ ከአስፈጻሚው ፡ ቅርንጫፍ ፡ ነፃ ፡ ሆኖ ፡ የሚሠራ ፡ መሆኑን ፡ በኃይለ ፡ ቃል ፡ በማውሳት ፡ ገልጿል ።[155] አዋጁ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ አንድ ፡ ዓይ ነት ፡ ተመሳሳይ ፡ ሁኔታ ፡ ካላቸው ፡ እንደአገባቡ ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በእስ ላም ፡ ሕግ ፡ እንዲዳኙ ፡ በተለይ ፡ ደንግጓል ።[156] ሕጎቹ ፡ ምናልባት ፡ ተቃራኒ ፡ ሆነው ፡ ቢገኙ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ወገኖች ፡ በየትኛው ፡ ሕግ ፡ እንደሚዳኙ ፡ ይመርጣሉ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይመርጥላቸዋል ።[157] የሚሠራበት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ መንግሥት ፡ በጽሑፍ ፡ ያወጣው ፡ ሕግ ፡ ነበር ።[158] አዋጁ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ የማጅስትሬት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ የአስታራቂ ፡ ወይም ፡ የገላጋይ ፡ ፍርድ ፡ ቤትንና ፡ ልዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ አቋቋመ ።[159]

የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ የማጅስትሬት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚዳኙት ፡ በል ማዳዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ ስለወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ ግን ፡ የነበራቸው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የተወሰነ ፡ ነበር ። ይህ ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ምና ፡ በ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተከታታይ ፡ በወጡ ፡ ማሻሻያዎች ፡ ተለውጧል ። የአሁኑ ፡ የዳኝነት ፡ አሠ ራር ፡ በቀዳሚነት ፡ መሠረቱን ፡ የጣሉት ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ፡—

፩/ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ በእስላም ፡ ሕግና ፡ በመንግሥት ፡ ሕግ ፡ የሚያስችሉትን ፡ የልዩ ፡ ልዩዎቹን ፡ የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የችሎት ፡ ክፍሎች ፡ ፍርድ ፡ ተቀ ብሎ ፡ ይግባኝ ፡ የሚሰማውን ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

፪/ እላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የችሎት ፡ ክፍሎች ፡ ይዞ ፡ ከአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ይግባኝ ፡ የሚሰማ ፡ የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

፫) በልማዳዊ ፡ ሕግና ፡ ልማዳዊ ፡ ባልሆኑ ፡ ሕጎች ፡ የሚሠሩና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔ ርን ፡ የወንጀል ፡ ነገሮችን ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሚሰሙና ፡ መንግሥት ፡ ያወጣ ውን ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውሉ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡

154. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፹፯ ።
155. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፺፪ ።
156. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፺፭ ።
157. ከዚያው ።
158. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፺፯ ።
159. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፫፻፺፯ ።

ቤቶች ፡ ሲሆኑ ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ የሚሠሩት ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከምስለ ኔው ፡ ፍርድ ፡ የሚመጡትን ፡ ይግባኞች ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ።

፬/ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ስለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክርና ፡ በመንደረተ ኞች ፡ በጎሣዎችና ፡ በያንዳንዱ ፡ በግል ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ የሚደረገውን ፡ የጋራ ፡ የመ ሬት ፡ ክርክር ፡ የሚሰማ ፡ ምስለኔ ። ምስለኔ ፡ ከጭቃ ፡ ሹሙ ፡ የሚመጣውን ፡ ይግባኝ ፡ ይሰማል ።

፭/ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክር ፡ ጉዳይ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ የሚሠራ ፡ የጭቃ ፡ ሹም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።[160]

ከነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በስተቀር ፡ በሕግ ፡ በተሰጣቸው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የሚያስችሉ ፡ የእስላም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ነበሩ ።

ኢትዮጵያና ፡ ኤርትራ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ። ከዚህ ፡ በታች ፡ የሚብራራው ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ የጸደቀው ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲሆን ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ የጸናውም ፡ ከሚያ ዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ። እንግሊዞች ፡ ለኤርትራ ፡ ያወጡ ትን ፡ የዳኝነት ፡ አሠራር ፡ ከአዲሱ ፡ አዋጅ ፡ ጋር ፡ እንዲያስማማ ፡ ጉዳዩ ፡ "ለሕግ ፡ ኮሚቴ ፡" ቀረበ ። ይህም ፡ ኮሚቴ ፡ በአዲሱ ፡ አሠራር ፡ መንገድ ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፫ ፡ ለአጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ በተሰጠው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ጭቃ ፡ ሹም ፡ ሥራውን ፡ እንዲቀጥል ፡ ምስለኔ ፡ የዳ ኝነት ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ የሚሠራው ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ "የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡" ተብሎ ፡ እንዲሰየምና ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አዋጅ ፡ ለወ ረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተሰጠው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ እንዲሠራ ፡ በየአውራጃው ፡ ግዛት ፡ ዋና ፡ ከተሞች ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንዲቋቋሙና ፡ የከፍተኛውና ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ልዩ ፡ ልዩዎቹ ፡ የችሎት ፡ ክፍሎች ፡ እንዲጠቃለሉ ፡ ወሰነ ።[162] አዋጁን ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሰኔ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሲያግደው ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ ተደርጐ ፡ በኤርትራ ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ ስለነበር ፡ በኤርትራ ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ መሠ ረት ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ እንዲቀጥል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፈቀዱ ።

ስለዚህ ፡ ኤርትራ ፡ በማናቸውም ፡ የዳኝነት ፡ አሠራርና ፡ የሕላዊና ፡ የሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ ሕግ ፡ ታሪክ ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ የውጪ ፡ ተጽዕኖ ፡ ያለበት ፡ ነው ። በጣልያንና ፡ በተለይም ፡ በእንግሊዝ ፡ አስተዳደር ፡ ዘመን ፡ ኤርትራውያን ፡ ዳኞች ፡ የዳኝነትና ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ከመማራቸውም ፡ በላይ ፡ የዳኝነቱ ፡ ክፍል ፡ ከአስፈጻሚው ፡ ቅር ንጫፍ ፡ ነፃ ፡ ሆኖ ፡ መሥራቱ ፡ በትክክል ፡ የተጠበቀ ፡ ነበር ። በተጨማሪ ፡ ደግሞ፡ በእንግሊዝ ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ በጠበቆች ፡ ላይ ፡ ቅጣት ፡ ለመወሰን ፡ የሚችል ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ተቋቁሞ ፡ ነበር ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አቋም ፡ የተወሳሰበ ፡ ቢሆንና ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣ ንም ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ተደራራቢ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ በቅኝ ፡ አገዛዝ ፡ አስተዳደር ፡ በመመራት ፡ በኤርትራ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ የቀለጠፈ ፡ ነበር ።

---

160. ኤን ፡ ሚትዝር ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፯ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፫—፬ ።
161. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፮ ።

ከ፲፱፻፶፬ ፡ ዓ፡ም፡ በኋላ ፡ በኤርትራ፡ የዳኝነት፡ ሥራ፡ ለጥቂት፡ ዓመታት፡ ብቻ ፡ የውጪ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ እርዳታ ፡ ከማስፈለጉ ፡ በስተቀር ፡ በኤርትራውያን ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ይመራ ፡ ጀመር ። ምንም ፡ ባለፉት ፡ ሰባ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ኤርትራ ፡ ከቀሩት፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ ተነጥላ ፡ ልዩ ፡ የዳኝነት ፡ አሠራር ፡ ልምድ ፡ ቢኖራትም ፤ ኢትዮጵያና ፡ ኤርትራ ፡ ከተዋሀዱ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የኤርትራ ፡ የዳኝነት ፡ አሠራር ፡ አቋም ፡ ከቀሩት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ ጋራ ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሆኗል። የማዕከላዊው ፡ መንግሥት ፡ በኤርትራ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ተጽዕኖ ፡ ምክን ያት ፡ የኤርትራ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የቀሩትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ የዳኝ ነት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ በተፋጠነ ፡ ሁኔታ ፡ በመከተል ፡ ላይ ፡ ነው ።

## <u>የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ።</u>

የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የኢትዮጵያን ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሔድ ፡ ይቆጣጠራል ። አራት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ አሉት ። ከፍተኛው ፡ ክፍል ፡ ግን ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ነው ። ሚኒስትሩ ፡ የሚሾመው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲሆን ፡ ሥልጣ ኑም ፡ እንደሚከተለው ፡ ተገልጿል ።

የፍርድ ፡ ሚኒስትር ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ ከሚያከናውኑት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች፡ አንዱን ፡ ማለት ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴርን ፡ በበላይነት ፡ የሚመራ ፡ ነው ። የፍርድ ፡ ሚኒ ስትር ፡ ሕግን ፡ ተከትሎ ፤

ሀ) ዳኞች ፡ ለሹመት ፡ የሚታጩበትን ፤ እድገት ፡ የሚያገኙበትን ፤ ከሥራ ፡ የሚ ወገዱበትን ፡ ሁኔታ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ መፈጸሙን ፡ ይከተላል ።

ለ) በመላ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ተገቢ ፡ የሆኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚቋቋሙበትንና ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ ያደራጃል ።

ሐ) ፍርድ ፡ ያለአድልዎ ፡ በትክክል ፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጣል ፤ ይቆጣ ጠራልም ።

መ) ሕግ ፡ መከበሩንና ፡ ስለፍርድ ፡ አስተዳደርም ፡ በሕግና ፡ በደንብ ፡ የተደነ ገጉትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶችና ፡ ፎርሞች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ መዋላቸውን ፡ ያረጋግጣል ።

ሠ) በመንግሥት ፡ በኩል ፡ ለሚቀርቡት ፡ ለወንጀል ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ ኃላፊ ፡ ይሆናል ።

ረ) በመንግሥትም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ የሚቀርቡትን ፡ የፍትሐ ብሔር ፡ ክሶችና ፡ ጥያቄዎችን ፡ ሁሉ ፡ ይቆጣጠራል ።

ሰ) በመንግሥት ፡ በኩል ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ በቀረበው ፡ ክስ ፡ የሚ ከራከሩ ፡ ሕግ ፡ አስከባሪዎችንና ፡ ጠበቆችን ፡ ይመክራል ፡ ይረዳልም ።

ሸ) በመንግሥት ፡ ስም ፡ የቀረቡ ፡ ወይም ፡ መልስ ፡ የተሰጠባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ እንዳስፈላጊነቱ ፡ ተገቢ ፡ መዝገቦችን ፡ ያደራጃል ። እንዲሁም ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውሳኔዎችና ፡ የዳኞችም ፡ አስተያየት ፡ ጭምር ፡ በሚገባ ፡ እየታተሙ ፡ እንዲወጡ ፡ ያደርጋል ።

ቀ) የሞት ፡ ፍርድ ፡ የተፈረደበትን ፡ ጉዳይ ፡ መዝገብ ፡ ከአስተያየቱ ፡ ጋራ ፡ ለእኛ ፡ ያቀርባል ።

በ) የፍርድ ፡ ምሕረት ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚቀርበውን ፡ ማናቸውንም ፡ ልመና ፡ ከአስተያየት ፡ ጋር ፡ ለእኛ ፡ ያቀርባል ።

ተ) ከፍ ፡ ያለ ፡ የሞራል ፡ ጠባይና ፡ ደንበኛ ፡ የትምህርት ፡ ችሎታ ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ በጥብቅና ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ፈቃድ ፡ ይሰጣል ። በጥብቅና ፡ ተግባራቸውም፡ ምንጊዜም ፡ ተስማሚ ፡ መሆናቸውን ፡ ያረጋግጣል ።

ቸ) ለማናቸውም ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ያቀርባል ።[162]

በአሁኑ ፡ አሠራር ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዳኞችን ፡ አቀጣጠር ፡ ጉዳይ ፡ ይቆጣጠራል ።[163] ሥራቸውን ፡ ይመረምራል ፤ የሥራ እድገት ፡ ይሠጣል ፤ ከሥራ ፡ በደረጃ ፡ ዝቅ ፡ ለማድረግና ፡ ከሥራ ፡ ለማሰናበትም ፡ ይችላል ። ይህንንም ፡ ተግባር ፡ የሚፈጽመው ፡ በሚኒስቴሩ ፡ ሌሎች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ አማካይነት ፡ ነው ።

ከነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ አንዱ ፡ ለበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዳኞችን ፡ ይመለምላል ። በዳኝነት ፡ ለመቀጠር ፡ ከሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ ማመልከቻ ፡ የሚቀበለው ፡ ይኸው ፡ ክፍል ፡ ነው ። የአመልካቹ ፡ ጠባይና ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩ ፡ ይመረመርና ፡ አመልካቹ ፡ የመጀመሪያውን ፡ የጠባይ ፡ ማጣሪያ ፡ ካለፈ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያወጣውን ፡ ፈተና ፡ እንዲቀበል ፡ ይፈቀድለታል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ፎርማሊቴ ፡ ሳይጠበቅ ፡ ይሾማሉ ።

የዋናው ፡ ኢንስፔክተር ፡ ክፍል ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሚሾም ፡ በዋና ፡ ኢንስፔክተር ፡ እየተመራ ፡ የዳኞችን ፡ ፍርድ ፡ እንዲመለከቱና ፡ የሚያረጋግጡ ፡ በችሎት ፡ ጊዜ ፡ ተገኝተው ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መጠበቁን ፡ ተቆጣጣሪዎች ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እየላከ ፡ ዳኞችን ፡ ይቆጣጠራል ። አንድ ፡ ተሟጋች ፡ በዳኛው ፡ ላይ ፡ በደረሰበት ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ተጽዕኖ ፡ ወይም ፡ በግልጽ ፡ ስኅተት ፡ በተሰጠ ፡ ፍርድ ፡ ምክንያት ፡ ተጎዳሁ ፡ በማለት ፡ ሲያመለክት ፡ እነዚህ ፡ ተቆጣጣሪዎች ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ መስጠት ፡ አለመስጠቱን ፡ ለማረጋገጥ ፡ መዝገቡን ፡ ይመረምራሉ ። ተቆጣጣሪዎቹ ፡ በፍርድ ፡ አሰጣጡ ፡ ላይ ፡ ጉድለት ፡ ቢያገኙ ፡ ወይም ፡ የዳኝነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ስኅተት ፡ መኖሩን ፡ ከተረዱ ፡ ይህንን ፡ ስህተት ፡ ፍርዱን ፡ ከሰጠው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ጋር ፡ ከተነጋገሩበት ፡ በኋላ ፡ ለዋናው ፡ ኢንስፔክተር ፡ ክፍል ፡ ሪፖርት ፡ ያቀርባሉ ። የዋናው ፡ ኢንስፔክተር ፡ ክፍል ፡ ሪፖርቱን ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ይልካል ። የፍርድ ፡ ሚኒስትሩም ፡ የዲሲፕሊን ፡ እርምጃ ፡ እንዲወሰድ ፡ ለጥፋተኛው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኛ ፡ ደብዳቤ ፡ ይጽፋል ፡ ወይም ፡ የዲሲፕሊን ፡ እርምጃ ፡ ይወሰዳል ።

በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የዋናው ፡ ኢንስፔክተር ፡ ክፍል ፡ ሠራተኞች ፡ ተፈላጊው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ አልነበራቸውም ።[164] የአሁኑም ፡ ዋና ፡ ኢንስፔክተር ፡ የሕግ ፡

162. ስለሚኒስትሮች ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ የወጣ ፡ ትዕዛዝ ፡ መሻሻያ ፡ ቁጥር ፡ ሁለት ፡ ትዕዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፶፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ሃያ ፡ አምስተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ።

163. አ ፡ ባንቲዋሉ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አቋም ፡ በኢትዮጵያ ። ፲፱፻፶፰ ፡ (ያልታተመ) ፡ (በእንግሊዝኛ) ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ቤት ፡ መጻሕፍት ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ገጽ ፡ ፳፬ ፡ እና ፡ ተከታዮቹ ።

164. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፴፫ ።

ትምህርት ፡ የላቸውም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የክፍሉ ፡ ባልደረቦች ፡ በሙሉ ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ አላቸው ።[165] በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ከዩኒቨርሲቲው ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ በዲግሪ ፡ የተመረቀ ፡ አንድ ፡ ሠራተኛ ፡ ሲኖር ፡ አንድ ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ አገልግሎቱን ፡ በዚሁ ፡ በዋናው ፡ ኢንስፔክተር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በማበርከት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ባልደረቦች ፡ ላይ ፡ የሚቀርቡ ፡ አቤቱታዎችን ፡ የሚመለከትና ፤ እነሱም ፡ አጥፍተው ፡ ሲገኙ ፡ የሚቀጣ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አለው ። ሚኒስቴሩ ፡ በተጨማሪ ፡ በሥሩ ፡ ካሉት ፡ ክፍሎች ፡ አንዱ ፡ በሆነው ፡ በጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አማካይነት ፡ የመንግሥቱን ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ያስተዳድራል ። የሚኒስቴሩ ፡ እያንዳንዱ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አቅራቢነት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሚሾም ፡ አንድ ፡ ሹም ፡ ይመራል ።

## መደምደሚያ ።

የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ በመንግሥቱ ፡ በማዕከላዊ ፡ አስተዳደር ፡ ሥር ፡ ተጠቃሎ ፡ መመራቱና ፡ የሕላዌና ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በየመልኩ ፡ መደራጀቱ ፡ ከ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ ለተገኘው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ አስተዳደር ፡ መሻሻል ፡ አንድ ፡ ምስክር ፡ ነው ። የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ እንዲመራ ፡ ሲደረግ ፡ በጠቅላላው ፡ አሠራር ፡ ላይ ፡ ለውጥ ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡ በሕላዌና ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፡ ከላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ጋር ፡ ሲወዳደሩ ፡ በጣም ፡ በተለያየ ፡ መንገድ ፡ ይሠሩ ፡ በነበሩት ፡ በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ በተለይ ፡ ያስከተለውን ፡ ችግር ፡ መመርመር ፡ ነው ።

## ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ።

ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ ከሚሠሩት ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛውን ፡ ስፍራ ፡ የያዙ ፡ ናቸው ። መሀይም ፡ የሆኑ ፡ ተሟጋቾችና ፡ ስለ ሕላዌ ፡ ሕግና ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሚፈጸመው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የማያውቁ ፡ ሰዎች ፡ ያለእነርሱ ፡ እርዳታ ፡ ጉዳያቸውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ አይችሉም ። የራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ መኖር ፤ የክርክሩን ፡ መነሻ ፡ ለመለየት ፡ ከአስፈላጊው ፡ በላይ ፡ ጊዜ ፡ ሳያጠፉ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ በቀላሉ ፡ ለመረዳት ፡ የሚያስችላቸውን ፡ የክስ ፡ ማመልከቻና ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ጠቅላላው ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ የመዝገብ ፡ መሠረት ፡ እንዲኖረው ፡ ይረዳል ። በአጭር ፡ ሆኖ ፡ በቀላሉ ፡ ለማግኘት ፡ የሚረዳቸውን ፡ ለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሔድ ፡ መሠረታዊ ፡ መነሻ ፡ የሚሆነውን ፡ መዝገብ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ይረዳል ።

ዳግም ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ተሟጋቾች ፡ የአቤቱታ ፡ ማመልከቻዎችን ፡ ለማን ፡ እንደሚሰጡ ፡ ዳኛው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣንና ፡ የተሟጋቹን ፡ የመርታት ፡ ወይም ፡ የመረታት ፡ እድል ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ የተለመዱ ፡ ነገሮችን ፡ ለተሟጋቾች ፡ ያስረዳሉ ።

---

165. ከዚያው ።

ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ በዚሁ ፡ ተግባር ፡ ከአ ሥር ፡ ዓመታት ፡ በላይ ፡ ቆይተዋል ። ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከመሆናቸው ፡ በፊት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ተቀጥረው ፡ ከሠሩ ፡ በኋላ ፡ በጡረታ ፡ ምክንያት ፡ ሥራ ፡ የለቀቁ ፡ ወይም ፡ ከሥራ ፡ የተወገዱ ፡ ወይም ፡ ራሳ ቸውን ፡ ችለው ፡ ነፃ ፡ ሆነው ፡ ለመሥራት ፡ በማሰብ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ሥራ ፡ የለቀቁ ፡ ናቸው ። ጥቂቶች ፡ ደግሞ ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ከሠረው ፡ ሥራቸውን ፡ የተዉ ፡ ናቸው ። ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ መካከል ፡ አንዳቸውም ፡ ማመልከቻ ፡ በመ ጻፍ ፡ ሥራ ፡ የጀመሩ ፡ ባለመሆናቸው ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ለጊዜው ፡ ሥራቸውን ፡ የሚ ወዱ ፡ መስለው ፡ ቢታዩም ፡ የመጀመሪያው ፡ እቅዳቸው ፡ ቢቃናላቸው ፡ ኖሮ ፡ ምር ጫቸው ፡ በሌላ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ በመረጡ ፡ ነበር ።

ከተጠየቁት ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ጥቂቶቹ ፡ በመንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ግፋ ፡ ቢል ፡ እስከ ፡ ሰባተኛ ፡ ክፍል ፡ የተማሩ ፡ ሲሆኑ ፡ አብዛኞቹ ፡ ግን ፡ የተማሩት ፡ በቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነው ። የሕግ ፡ ዕውቀትና ፡ ችሎታ ፡ ያገኙት ፡ ራሳ ቸው ፡ በማንበብና ፡ በሥራ ፡ ልምምድ ፡ ነው ።

በአዲስ ፡ አበባ ፡ በሐረርና ፡ በአሥመራ ፡ የሚገኙት ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ምንም ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ቦታቸው ፡ ይዘው ፡ ባይመጡ ፡ ልዩ ፡ ልዩዎች ፡ የሕግ ፡ መጻሕ ፍት ፡ አሏቸው ። አብዛኛዎቹ ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ እንዳላቸው ፡ ተናግረዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ መጻሕፍት ፡ የሏቸውም ። የማመልከቻ ፡ ማቅረቢያ ፡ ፎርም ፡ አብሮ ፡ በመያያዙ፡ ምክንያት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በነርሱ ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ የተወ ደደ ፡ ሆኑዋል ። በታላላቅ ፡ ከተማዎች ፡ አካባቢ ፡ በሚገኙ ፡ የገጠር ፡ ስፍራዎች ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሕጎቹን ፡ መጻሐፍት ፡ ማግኘት ፡ አይችሉም ። እነዚህም ፡ ራፖር ጸሐፊዎች ፡ የሚተማመኑት ፡ በእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ተገልብጠው ፡ በሚገኙ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በሚጠቀሱ ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮችና ፡ በጠበቆችም ፡ ምክር ፡ ነው ።

ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያላቸው ፡ "የሕግ ፡ ዕውቀት ፡" የክርክሩን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በሚገባው ፡ መንገድ ፡ መጻፍ ፡ ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ያለውን ፡ አንቀጽ ፡ ከሕጉ ፡ ውስጥ ፡ መጥቀስና ፡ በሚገኙበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጸመውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማወቅ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ራፖር ፡ ጸሐፊው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ ወይም ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ ሲጽፍ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ና ፡ ፪፻፳፫ ፡ ላይ ፡ የተመለከ ተው ፡ በማመልከቻም ፡ ላይ ፡ ተሟልቶ ፡ መገኘቱን ፡ ማረጋገጥ ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ማመልከቻ ፡ ሲጽፉ ፡ ሕላዊ ፡ ሕጉ ፡ ትርጉም ፡ ውስጥ ፡ አይገቡም ። የሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ብቻ ፡ ከተጠቀሰ ፡ በኋላ ፡ የተጠቀሰበትን ፡ ምክንያት ፡ ማወቅ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈንታ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙ ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ለአ ንድ ፡ ቀላል ፡ ጉዳይ ፡ ማመልከቻ ፡ እንዴት ፡ እንደሚጽፉ ፡ የሚያሳይ ፡ ምሳሌ ፡ ነው።

ከሳሽ ፡ ዘምሕረት ፡ በረከት ፡ አብ ፤
ተከሳሽ ፡ ግርማ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ የስድስት ፡ ብር ፡ ክስ ፤

በ፳፰/፩/፷፩ ፡ በተስማማነው ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ተከሳሽ ፡ ለችግሩ ፡ መውጫ ፡ የኢት ፡ $ 6 ፡ ተበድሮኝ ፡ በ/፫/፪/፷፩ ፡ ብድሩን ፡ ሊከፍለኝ ፡ ሶስት ፡ ጥይት ፡

መያዣ ፡ ሰጥቶኛል ። በተባለው ፡ ቀን ፡ የተበደረውን ፡ ገንዘብ ፡ አልከፍልም ፡ አለ ። ስለዚህ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪ሺ፭ ፡ መሠረት ፡ የተበደ ረኝን ፡ የኢ.ት ፡ ፲ ፡ ብር ፡ እንዲከፍለኝ ፡ ለዚህ ፡ ክስ ፡ ያወጣሁትን ፡ ሌላ ፡ ወጪ ፡ ጭምር ፡ ኪሣራዬን ፡ በሙሉ ፡ እንዲከፍለኝ ፡ ያደርጉልኝ ፡ ዘንድ ፡ አመለክታ ለሁ ። ያስያዘኝን ፡ ሦስት ፡ ጥይት ፡ ለመመለስ ፡ ፈቃደኛነቴንም ፡ እገልጻለሁ ። ተከሳሹ ፡ የብድሩን ፡ ውል ፡ ቢክድ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፪፻፳፫ ፡ መሠረት ፡ የውሉን ፡ ግልባጭ ፡ አቀርባለሁ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፺፱ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ያለኝ ፡ ማስረጃ ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ እገልጻለሁ ።

ፊርማ ፤ ዘምሕረት ፡ በረከት ፡ አብ ።

ጥቂቶች ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ስለማመልከቻ ፡ አጻጻፍ ፡ ጉዳይ ፡ የሚጠቀሙት ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ ተያይዞ ፡ በሚገኘው ፡ ፎርም ፡ ነው ። አስፈላጊውን ፡ ሕግ ፡ ለመጥቀስ ፡ ሲያስፈልግ ፡ በቃላቸው ፡ ያውቁታል ፡ ወይም ፡ ከሕጉ ፡ ውስጥ ፡ በማንበብ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አንዱ ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊ ፡ እንዳለው ፡ ከሕጉ ፡ ውስጥ ፡ አስፈላጊውን ፡ ማውጫ ፡ በማዘጋጀት ፡ ነው ። የሚከተለው ፡ ከፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ የተዘጋጀ ፡ ማውጫ ፡ ነው ። ማውጫው ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰበት ፡ ምክንያት ፡ ብዙዎቹ ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ያላቸውን ፡ ዕውቀት ፡ ስለ ሚያሳይ ፡ ነው ።

## ማውጫ ፤

## የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ።

| | | የሕጉ፡ቁጥር ፡ |
|---|---|---|
| 1. | አበዳሪ ፡ ገንዘቡን ፡ ሳያገኝ ፡ ሲቀር ፤ | 2005 |
| 2. | ምስክሩ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፤ | 2002 |
| 3. | ተከራይ ፡ ኪራይ ፡ አልከፍልም ፡ ሲል ፤ | 2945 |
| 4. | አንድ ፡ ሰው ፡ ሌላውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሲሰድበው ፤ | 480 ፤ 481 |
| 5. | ተከሳሽ ፡ በሐሰት ፡ ስለተከሰስሁ ፡ ካሣ ፡ ይገባኛል ፡ ሲል ፤ | 2028 ፤ 2090 |
| 6. | ባልና ፡ ሚስት ፡ ንብረታቸውን ፡ ሲጠይቁ ፤ | 652 ፤ 653 |
| 7. | ስለውክልና ፡ ሥልጣን ፤ | 2205 |
| 8. | ውክልናን ፡ ችላ ፡ ስለማለት ፤ | 2226 |
| 9. | ክሱን ፡ ስለማይቀጥል ፡ ሰው ፤ | 2028 |
| 10. | እኔ ፡ ርስት ፡ ይገባኛል ፡ ስል ፤ | 896 ፤ 996 ፤ 999 |
| 11. | ስለዕቁብ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፤ | 1911 |
| 12. | አዕምሮ ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ አቤቱታ ፡ ስለማቅረብ ፤ | 339 |
| 13. | ከሳሽ ፡ ማስረጃ ፡ የለኝም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስለአቀረብከው ፡ ክስ ፤ እምላለሁ ፡ ሲል ፤ | 2006 |
| 14. | ወሰን ፡ ስለመካድ ፤ | 1771 |
| 15. | ስለቤት ፡ ኪራይ ፤ | 2915 |

16. ዋሱ ፡ የባለዕዳው ፡ ንብረት ፡ አስቀድሞ ፡ ይሸጥ ፡ ብሎ ፤ ስለማመልከት ፤ 1934
17. ሁለት ፡ ሰዎች ፡ የጋብቻ ፡ ጽሑፍ ፡ ሳይኖራቸው ፡ በባልና ፤ ሚስትነት ፡ ሁኔታ ፡ ስለመኖር ፣ 699
18. አንደኛው ፡ ወገን ፡ አስቀድሞ ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳይሰጥ ፡ ሲቀር ፤ 2571
19. ሠራተኛ ፡ ከሥራ ፡ በሚሰናበትበት ፡ ጊዜ ፤ 2573 ፤ 2574
20. ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ እንደተከፈለ ፡ የሚቆጠርበት ፡ ሁኔታ ፤ 2024
21. የማስታወቂያ ፡ ጊዜና ፡ የካሣ ፡ መጠን ፤ 2571 ፤ 2524
22. ስለ ፡ ልዩ ፡ ውክልና ፤ 2205
23. በሌላ ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ ስለመጠቀም ፤ 2896
24. ዋሱ ፡ እኔ ፡ መክፈል ፡ የለብኝም ፡ ዋናው ፡ ባለዕዳ ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ፡ ሲል ፤ 1934
25. ስለ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፤ 681

ስለ ፡ ክስ ፡ መዝገብ ፡ ጉዳይ ፡ የተጻፈው ፡ ክፍል ፡ በሚነበብበት ፡ ጊዜ ፡ ይህንን ፡ ማውጫ ፡ መመልከት ፡ ያስፈልጋል ። ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሕጉን ፡ እንዴት ፡ እንደሚ ጠቀሙበት ፡ የሚያመለክት ፡ ትክክለኛ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ የሕጉን ፡ መሠረት ፡ የሚያመለክት ፡ ሳይሆን ፡ ሕጉን ፡ ለመጥቀስ ፡ ብቻ ፡ የሚረዳ ፡ ነው ። ጉዳዩን ፡ የሚመለከት ፡ ሁኔታ ፡ ሲፈጠር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ቁጥሩ ፡ ምን ፡ እንደሚል ፡ ሳይታይ ፡ የሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይጠቀሳል ።

በመጨረሻ ፡ መገንዘብ ፡ የሚያስፈልገው ፡ የክስ ፡ ማመልከቻና ፡ የመከላከያ ፡ መልስ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመቅረባቸው ፡ በፊት ፡ ፍሬ ፡ ነገሩንና ፡ የክር ክሩን ፡ ጭብጥ ፡ እንዲያውቁ ፡ የሚረዳቸው ፡ መሆኑን ፡ ነው ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ ራፖር፡ ጸሐፊዎች ፡ ተግባራቸውን ፡ በሚገባ ፡ ይፈጽማሉ ። የሕጉን ፡ ድንጋጌ ፡ ለመረዳትና ፡ ለመተርጐም ፡ በቂ ፡ ችሎታ ፡ ባይኖራቸውም ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ለተሟጋቾች ፡ በአነስተኛ ፡ ዋጋ ፡ ጠቃሚ ፡ የሆነ ፡ አገልግሎት ፡ ይሰጣሉ ።

<u>የፍርድ ፡ ቤት ፡ የአስተዳደር ፡ ሠራተኞች ።</u>

በየወረዳውና ፡ በየአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ በሚገኙበት ፡ ያሉት ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቶች፡ የሚቀጥራቸው፡ በማዕረግ ፡ የሚያሳድጋቸውና ፡ ከሥራ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ የሚያዘዋውራቸው ፡ አያሌ ፡ ሠራተኞች ፡ አሉ ።

በአዲስ ፡ አበባ ፡ የወንጀለኛና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ችሎት ፡ ባላቸው ፡ የወረዳ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከዳኛው ፡ በስተቀር ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ደመወዝ ፡ የሚከፍሏቸው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አምስት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ይገኛሉ ። ምንም፡ እንኳን፡ በየፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ የያንዳንዱ ፡ ሠራተኛ ፡ ሥራ ፡ ተመሳሳይና፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡ ቢባልም ፡ ለሠራተኞቹ ፡ ተለያይቶ ፡ የሚሰጣቸው ፡ ሥራ ፡ ይለ ያያል ። ሊኖሩ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ቀዋሚ ፡ ሠራተኞች ፡ ብዛት ፡ እንደሚከተለው ፡ ይሆናል ።

የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ የሚቆጣጠርና ፡ ክሱ ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት ፡ ማመልከቻው ፡ አስፈላጊውን ፡ ፎርም ፡ መከተሉን ፡ የሚመለከት ፡ ሬጅስት ራሩ ፡ ነው ። ሌላው ፡ ተግባሩ ፡ ደግሞ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፈቀደውን ፡ ትዕዛዝ ፡ መጻ ፍና ፡ ከሌሎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ ከመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ጋር ፡ የሚደረገ

ውን ፡ የደብዳቤ ፡ ግንኙነት ፡ ማካሄድ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ የመዝገብ ፡ ቤቶችን ፡ በሚገባ ፡ ለማቋቋም ፡ ኃላፊነት ፡ አለበት ። ይህ ፡ ሥራ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ ይጣመራል ።

የመዝገብ ፡ ቤቱን ፡ ሥራ ፡ የሚያካሂደው ፡ ሬጅስትራሩ ፡ ሳይሆን ፡ የተለየ ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ከሆነ ፡ እርሱም ፡ እንደአለቃው ፡ ያለ ፡ ችሎታ ፡ ብቻ ፡ ይኖረዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ልዩነቱ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከሥራ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ያለመዘዋወሩ ፡ ነው ። በመዝገብ ፡ ቤት ፡ የፋይሉ ፡ አያያዝ ፡ በየፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተለያየ ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያትና ፡ የመዝገቡንም ፡ አያያዝ ፡ የሚያውቅ ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ስለሌለ፡ እያንዳንዱን ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሠራተኛ ፡ በጣም ፡ ተፈላጊ ፡ ያደርገዋል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ እነዚህ ፡ ሠራተኞች ፡ አንድ ፡ ፋይል ፡ በደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ማግኘት ፡ እንችላለን ፡ ቢሉም ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሠራተኛው ፡ በራሱ ፡ ዘዴ ፡ ብቻ ፡ በሚሠራበት ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ፋይል ፡ ይጠፋል ።

ለሬጂስትራርነትና ፡ ለመዝገብ ፡ ቤትነት ፡ ሥራ ፡ ኃላፊ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ያላቸው ፡ ችሎታ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ የአማርኛ ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ ነው ። የቀድሞ ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ቢኖራቸው ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ብዙውን ፡ ፡ ጊዜ ፡ የጽሕፈት ፡ ሥራ ፡ ነው ። የሚከፈላቸውም ፡ ደመወዝ ፡ እንዳገልግሎታቸው ፡ መጠን ፡ በወር ፡ ከኢ.ት ፡ $ 65 ፡ እስከ ፡ የኢ.ት ፡ $ 100 ድረስ ፡ ይሆናል ።

ከነዚህ ፡ ከሁለት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሹማምንት ፡ በስተቀር ፡ የእርሱ ፡ ረዳት ፡ ሆነው ፡ የሚሠሩ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አሉ ። እነዚህንም ፡ ሠራተኞች ፡ የሚቀጥሯቸው ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቶችና ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሲሆኑ ፡ የሚቆጣጠራቸው ፡ ግን ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነው ። አንዱ ፡ ጸሐፊ ፡ የዳኛውን ፡ የዕለቱን ፡ አጀንዳ ፡ ለማዘጋጀትና ፡ ፍርድ ፡ ለማስፈጸም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚፈቅደውን ፡ ትዕዛዝ ፡ ለማስተላለፍ ፡ ኃላፊ ፡ ሲሆን ፡ ሌላው ፡ ጸሐፊ ፡ ደግሞ ፡ ለይግባኝ ፡ የሚጠየቀውን ፡ ግልባጭ ፡ ማዘጋጀትና ፡ የተፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ መዝገብ ፡ ማስገባት ፡ ነው ።

ተሟጋቾችን ፡ ተራቸው ፡ ሲደርስ ፡ መጥራት ፡ ብቻ ፡ ሥራቸው ፡ የሆነ ፡ በተጨማሪ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተላላኪዎችና ፡ ሌሎች ፡ ሠራተኞች ፡ አሉ ።

በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ "ደጅ ፡ ጠኝ ፡" የሚባሉ ፡ ሰዎች ፡ ይገኛሉ ። እነርሱም፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቀጠሩ ፡ ሳይሆኑ ፡ ወደፊት ፡ ቋሚ ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ጸሐፊዎችን ፡ የሚረዱ ፡ ናቸው ። ጥቂቶች ፡ ደጅ ፡ ጠኚዎች ፡ በሙሉ ፡ ጊዜ ፡ ሠራተኛነት ፡ ለመቀጠር ፡ ከስድስት ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ዓመታት ፡ ይወስድባቸዋል ።

ጸሐፊዎች ፡ እንዳገልግሎታቸው ፡ መጠን ፡ ከኢ.ት ፡ $ 40 ፡ እስከ ፡ የኢ.ት ፡ $ 100 ድረስ ፡ ደመወዝ ፡ ይከፈላቸዋል ። ስለዚህ ፡ ከሚቆጣጠሩዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ ያነሰ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያገኙት ፡ ሬጂስትራሮችና ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹሞች ፡ ጸሐፊዎችን ፡ የሚቆጣጠሩበት ፡ ጊዜ ፡ እንደነበረ ፡ ያደረግነው ፡ ምርመራ ፡ ያስረዳል ።

በተጨማሪ ፡ ደግሞ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያልቀጠራቸው ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴርና ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ገንዘብ ፡ ተቀባይ ፡ የሆኑ ፡ ሠራተኞች ፡ አሉ ። የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ገንዘብ ፡ ተቀባይ ፡ ተሟጋቾች ፡ ለዳኝነት ፡ የሚከፍሉትን ፡ ገንዘብ ፡ ይቀበላል ። የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀባይ ፡ ደግሞ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቱን ፡ ደንብ ፡ ተላልፎ ፡ መቀጫ ፡ የተጣለበትን ፡ ገንዘብ ፡ ይሰበስባል ። እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሠራተኞች ፡ የፍርድ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ማዛጋጃ ፡ ቤት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሚቀጥራቸው ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይበልጥ ፡ ደመወዝ ፡ ይከፍላቸዋል ።

ባንዳንዶች ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ ፍለጋ ፡ ምክንያት ፡ ሥራ ፡ እንዳይበደል ፡ በማሰብ ፡ ሠራተኞች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከሥራ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ይዘዋወራሉ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙ ፡ ሬጅስትራሮችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውጭ ፡ የሚዛወሩ ፡ አይመስልም ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውጪ ፡ የሚገኙት ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑት ፡ ሠራተኞች ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አይዛወሩም ።

በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ መብዛት ፡ ምክንያት ፡ ከሬጅስትራርና ፡ ከመዝገብ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ በታች ፡ የሚገኙት ፡ ሠራተኞች ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ በሚገኝ ፡ አራት ፡ ችሎት ፡ ባሉት ፡ በአንድ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አሉ ። ከእነዚህም ፡ ጸሐፊዎች ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ሲሆኑ ፡ ለአገልግሎታቸው ፡ ደመወዝ ፡ በወር፡ ከኢ.ት ፡ $ 50 ፡ እስከ ፡ የኢ.ት ፡ $ 60 ፡ ይከፈላቸዋል ። በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሠሩ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚሠሩ ፡ ተመሳሳይ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይልቅ ፡ የረዥም ፡ ጊዜ ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ሲኖራቸው ፡ በደመወዝ ፡ ግን ፡ አይበላለጡም ።

እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ ሠራተኞች ፡ ለመቅጠር ፡ ፈተና ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፡ በአቀጣጠር ፡ ረገድ ፡ ሌላ ፡ ተፈላጊ ፡ ነገር ፡ አለ ። የቤተ ፡ ሰብ ፡ መተሳሰርና ፡ በመንግሥት፡ ሥራ ፡ ማገልገል ፡ መጠነኛ ፡ ተጽዕኖ ፡ ስላለው ፡ ባንዳንድ ፡ ሥፍራ ፡ ከሚፈለገው ፡ ሠራተኛ ፡ በላይ ፡ ሠራተኞች ፡ እንዲኖሩ ፡ ምክንያት ፡ ሆኗል ። ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ቦታ ፡ ብቁ ፡ የሆኑ ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ባልነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ የጸሐፊነት ፡ ሥራ ፡ የተከበረና ፡ ደህና ፡ ደመወዝ ፡ የሚገኝበት ፡ ሥራ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ የጸሐፊነት ፡ ሥራ ፡ በጣም ፡ ተፈላጊ ፡ የነበረ ፡ ሲሆን ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ በጣም ፡ ተፈላጊ ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ጸሐፊ ፡ ለመሆን ፡ የሚፈልጉት ፡ የሚተማመኑበት ፡ ሥራና ፡ ኋላም ፡ የጡረታ ፡ አበል ፡ ለማግኘት ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ሰዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የደመወዝ ፡ እድገትና ፡ ከፍተኛ ፡ የሚያስከብር ፡ ሥራ ፡ ሳይፈልጉ ፡ ዝቅተኛ ፡ ደመወዝ ፡ እያገኙ ፡ በሚቻለው ፡ አኳኋን ፡ እየኖሩ ፡ ዕድሜአቸውን ፡ ለመግፋት ፡ የሚሹ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

## ጠበቆች ።

### ትርጉም ፡

"ጠበቃ ፡" በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግም ፡ ውስጥ ፡ "ነገረ ፡ ፈጅ፡" የሚለው ፡ በማናቸውም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ወይም ፡ ድንጋጌ ፡ ውስጥ ፡ ትርጉም ፡ የተሰጠው ፡ ቃል ፡ አይደለም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ስለጠበቆች ፡ በመዝገብ ፡ መግባት ፡ የወጣ ፡ የ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ደንብ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በጥብቅና ፡ ቆመው ፡ ስለሚነጋገሩ ፡ የሕግ ፡ ጠበቆች ፡ ፈቃድ ፡ ስለመስጠትና ፡ ስለጠበቆችም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አጠባበቅ ፡ ጉዳይ ፡ ደንግጓል ። በዚህ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ማናቸውም ፡ ድንጋጌ ፡ "ጠበቃ"፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ አልተጠቀመበትም ። ነገር ፡ ግን፡ ስለጠበቆች ፡ በመዝገብ ፡ መግባት ፡ የወጣ ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ደንብ፡ "በጥብቅና ፡ መነጋገር ፡" ለተባለው ፡ እንደሚከተለው ፡ መግለጫ ፡ ሰጥቷል ።

"በጥብቅና ፡ መነጋገር ፡ ማለት ፡ የሕግ ፡ አማካሪ ፡ ሆኖ ፡ በደንበኛ ፡ ሥራው ፤

ሀ) በፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ ስለሌላው ፡ ሰው ፡ የሚከራከር ፡ የሚሟገት ፡ ማመልከቻ ፡ የሚያቀርብ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የሕግ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፤

ለ) ሕጋዊ ፡ ክርክርን ፡ በሚነካ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ስለሌላ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ማናቸውንም ፡ ጽሑፍ ፡ የሚጽፍና ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ የሚያደራጅ ፤

ሐ) የሕግ ፡ ምክርን ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፡ ማለት ፡ ነው ።”

በክፍል ፡ “ለ” የተሰጠው ፡ መግለጫ ፡ በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለሚሟገቱ ፡ ተከራካሪዎች ፡ ማመልከቻ ፡ የሚጽፉትን ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ይመለከታል ። ስለሆነም ፡ በተለምዶ ፡ በሕግ ፡ የታወቁ ፡ “ጠበቆች” ፡ ሆነው ፡ አይገመቱም ።

በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፪ሺህ፩፻፶፱ ፡ ጠበቆች ፡ ነበሩ ። ግማሾቹ ፡ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሲሠሩ ፡ ስድሳ ፡ አንድ ፡ በኤርትራ ፡ ዘጠና ፡ በሐረርጌ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ይነጋገሩ ፡ ነበር ። ከእነዚህም ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ አርባ ፡ አምስቱ ፡ ያህል ፡ ጥብቅና ፡ የሚቆሙት ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሲሆን ፡ ከመቶው ፡ ሠላሳ ፡ ሰባቱ ፡ ያህል ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ከመቶ ፡ አሥሩ ፡ ግን ፡ በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነበር ።[166]

ለጠበቆች ፡ በጥብቅና ፡ እንዲነጋገሩ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጣቸው ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሲሆን ፡ እንደጠባያቸውና ፡ እንደችሎታቸው ፡ መጠን ፡ የሚነጋገሩበትን ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ደረጃ ፡ የሚወስነው ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ነው ።[167] ስለጠበቆች ፡ መዝገብ ፡ መግባት ፡ የወጣው ፡ የ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ደንብ ፤ ጠበቆች ፡ ችሎታቸው ፡ የሚመጥንበትን ፡ ፈተና ፡ እንዲወስዱ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሊያስገድዳቸው ፡ ወይም ፡ ያለፈተና ፡ ስለችሎታቸው ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ፡ በማለት ፡ ደንግጓል።[168]

ዳግመኛ ፡ በነዚህ ፡ ድንጋጌዎች ፡ መሠረት ፡ የተመዘገቡ ፡ ጠበቆች ፡ እንዲነጋገሩበት ፡ በተፈቀደላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ደረጃ ፡ መሠረት ፡ የተተመነውን ፡ የዓመት ፡ ግብር ፡ መክፈል ፡ ይኖርባቸዋል ። ጠበቃው ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲነጋገር ፡ በተፈቀደለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዓመት ፡ የሚከፈለውም ፡ ግብር ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ ይጨምራል ።

በዚሁ ፡ ደንብ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲ ፡ መሠረት ፡ “የጠበቆች ፡ የዲሲፕሊን ፡ ጉባዔ ፡” ተቋቁሟል ። ጉባዔውም ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትር ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ የወከለው ፡ ሰው ፡ የሚሾማቸው ፡ አምስት ፡ ሰዎች ፡ ይገኙበታል ። የጉባዔውም ፡ ተግባር ፡ የጠበቆችን ፡ ጠባ

---

166. ዓመታዊ ፡ የእስታቲስቲክ ፡ መጽሔት ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ፲፱፻፷ ። የእስታቲስቲክስ ፡ ጠቅላይ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገጽ ፡ ፪፻፲ ።

167. “የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ይዞ ፡ በሥራው ፡ ምክንያት ፡ ለመንግሥት ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ ከሚነጋገር፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ስሙ ፡ በመዝገብ ፡ ያልገባ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በጥብቅና ፡ አይነጋገርም ።”
ስሙ ፡ በመዝገብ ፡ ቢገባም ፡ “በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ እንዳይነጋገር ፡ በተወሰኑት፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አይነጋገርም ።”ስለ ፡ ጠበቆች ፡ መዝገብ ፡ መግባት ፡ የወጣ ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ደንብ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷፯ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አሥራ ፡ አንደኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲፩ ።

168. ስለጠበቆች ፡ በመዝገብ ፡ መግባት ፡ የወጣው ፡ የ፲፱፻፵፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ደንብ ፡ አንቀጽ ፡ ፭ ፡ (አላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷፫ ፡ የተጠቀሰው) ፡ “የጥብቅና ፡ ሥራውን ፡ በሚገባ ፡ ለመሥራት፡ የሚያስችለው ፡ አስፈላጊ ፡ ዕውቀትና ፡ ትምህርት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ለመረዳት ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትር ፡ ወይም ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ ማንኛውም ፡ በጥብቅና ፡ መዝገብ ፡ የተመዘገበውን ፡ ወይም ፡ በመዝገብ ፡ እንዲገባ ፡ ማመልከቻ ፡ ያቀረበውን ፡ ሰው ፡ በየጊዜው ፡ ተገቢነት ፡ ያለው፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ፈተና ፡ እንዲፈተን ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ።” ይላል ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ፈተና ፡ የሚሰጠው ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ ለሚያመለክቱና ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ ኖሮአቸው ፡ ደረጃቸውን ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ ለሚሹ ፡ አመልካቾች ፡ ነው ። ሆኖም ፡ በቅርቡ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ እንዲሠሩ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ፈቅዶላቸዋል ።

ይና ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ መመርመር ፡ ነው ። ጉባዔውም ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ሰውዬው፡ "በፍርድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ላይ ፡ እርዳታ ፡ ለመስጠት ፡ ጠባዩ ፡ ተስማሚ ፡" ሆኖ ካላገኘው ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃዱ ፡ እንዲሰረዝ ፡ ወይም ፡ ከጥብቅና ፡ ሥራ ፡ እንዲታገድ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ለማሳሰብ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

በአንቀጽ ፡ ፩ ፡ መሠረት ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጠበቃው ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ተግባር ፡ መፈጸሙን ፡ ካመነ ፡ ጠበቃውን ፡ ከጥብቅና ፡ ሥራው ፡ ለማገድ ፡ ይችላል ፤ ስለ ሆነም ፡ ጉዳዩን ፡ እንዲመረምር ፡ ለጠበቆች ፡ ዲሲፕሊን ፡ ጉባዔ ፡ መምራት ፡ አለበት ። ጉባዔው ፡ ነገሩን ፡ መመርመር ፡ ወይም ፡ አለመመርመር ፡ እንዳለበት ፡ በግልጽ ፡ አልተነገረም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የጉባዔው ፡ ተግባር ፡ ምናልባት ፡ በጉባዔው ፡ አነሳሽነት ፡ ምርመራ ፡ ተደርጎ ፡ ለሚኒስትሩ ፡ ሀሳብ ፡ እንደሚቀርበው ፡ ሁሉ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጥበት ፡ ጉባዔው ፡ የተላከውን ፡ ጉዳይ ፡ መርምሮ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሀሳቡን ፡ ማቅረብ ፡ ይኖርበታል ።

በጠበቃ ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ ሌላው ፡ መቆጣጠር ፡ ደግሞ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠበቃው ፡ ሲያጠፋ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ እንዳይነጋገር ፡ ለማድረግ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፪፻፶ ፡ ብር ፡ ድረስ ፡ ለመቅጣት ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ ነው ።[169] ይህ ፡ ሥልጣን ፡ በደንቡ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠበቃውን ፡ መቅጣቱ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ከተገለጸለት ፡ በኋላ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በጠበቃው ፡ ላይ ፡ እንደመሰለው ፡ ከሚወስደው ፡ እርምጃ ፡ ሌላ ፡ ነው ።[170]

የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፕሬዚዳንቶች ፡ ወይም ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኞች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፹፮ ፡ መሠረት ፡ ጠበቆችን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ለማስጠበቅና ፡ ለመቆጣጠር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቷቸዋል ።[171] ዳኞች ፡ ጠበቆችን ፡ የሚቀጡበት ፡ የተወሰነ ፡ ሁኔታና ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ቅጣት ፡ እንደሚወሰኑ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፹፮ ፡ ስለተገለጸ ፡ ዳኞች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጠበቆች ፡ ሲያጠፉ ፡ በቀላል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ብቻ ፡ ይቀጧቸዋል ። በዚሁ ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ጠበቆችን ፡ ከሥራቸው ፡ ለማገድ ፡ ዳኞች ፡ አለን፡ የሚሉትን ፡ ሥልጣን ፡ የሚጠቀሙበት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ ያውም ፡ ብርቱ ፡ በሆነ ፡ ጥፋት ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

በአባሎቹ ፡ ላይ ፡ የዲሲፕሊን ፡ እርምጃ ፡ ለመውሰድ ፡ የሚችል ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ በኢትዮጵያ ፡ የለም ።[172] ሆኖም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ የተባለ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ አለ ። የዚህም ፡ ማኅበር ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡

169. ስለጠበቆች ፡ በመዝገብ ፡ መግባት ፡ የወጣው ፡ የ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ደንብ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፪፳፫ ፡ የተጠቀሰ ፡ ቁጥር ፡ ፳ ።

170. ከዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ፱ ፡ (፪) ።

171. "የማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱንና ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ለማስከበር ፡ ማናቸውንም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ እርምጃ ፡ ሊወስድ ፡ ይችላል ። ይህንንም ፡ ለማስፈጸም ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ችሎት ፡ ክብር ፡ ወይም፡ ለዳኝነቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መልካም ፡ አመራር ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ ጠባይ ፡ የሚያሳየውን ፡ ማናቸውንም ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ በችሎቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ ተቃራኒ ፡ ተግባር ፡ በሠራበት ፡ ጊዜ ፡ በያዘው ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ሊወስንበት ፡ ይችላል ፡" የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹፮ ።

172. በፌዴሬሽን ፡ ጊዜ ፡ ኤርትራ ፡ በሁሉም ፡ ጠበቆች ፡ ላይ ፡ የዲሲፕሊን ፡ መቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የጠበቆች ፡ ማህበር ፡ ነበራት ፤ አንድነቱ ፡ ከተመሠረተ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፡ ማህበሩ ፡ በዲስፕሊን ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተወስዷል ።

ሲሆን ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ቅርንጫፎች ፡ አሉት ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የማኅበረተኝነት ፡ ገንዘብ ፡ እየከፈሉ ፡ በስብሰባውም ፡ የሚገኙ ፡ ስድሳ ፡ ማኅበረተኞች ፡ አሉት ። ከማኅበረተኞቹ ፡ አንዱ ፡ እንደገለጹት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደተመለከተው ፡ ማኅበሩ ፡ ለማኅበረተኞቹ ፡ ከሚያበረክተው ፡ የመረዳጃ ፡ አገልግሎት ፡ ሌላ ፡ በየጊዜው ፡ እየተሰበሰበ ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ሙያ ፡ ችግሮች ፡ ይወያያል ፤ እነዚህም ፡ ችግሮች ፡ እርምጃ ፡ እንዲወሰድባቸው ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይቀርባሉ ። በማኅበሩ ፡ አሳሳቢነት ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሁለት ፡ ችግሮችን ፡ በመመርመር ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። ከነዚሁም ፡ አንዱ ፡ ዳኞች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በጣም ፡ የመጫን ፡ ሁኔታ ፡ ያሳያሉ ፡ ለጠበቆች ፡ የመናገር ፡ ዕድል ፡ አይሰጡም ፡ እንዲያውም ፡ በጠቅላላው ፡ ለሕግ ፡ ሙያ ፡ አክብሮት ፡ የላቸውም ፡ የሚለውን ፡ የማኅበሩን ፡ አቤቱታ ፡ ነው ። ሌላው ፡ የማኅበሩ ፡ ቅሬታ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ገንዘብ ፡ ለሌለው ፡ ተከሳሽ ፡ ቆሞ ፡ እንዲነጋገር ፡ መታዘዙ ፡ በጥብቅና ፡ ሙያ ፡ ላይ ፡ ሸክም ፡ ሆኗል ፡ የሚል ፡ ነው ። ማኅበሩ ፡ ጠበቆች ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አገልግሎት ፡ መከፈል ፡ ይገባቸዋል ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ አለው ።

ማኅበሩ ፡ የሚደርሰውን ፡ የጠበቆች ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ተግባር ፡ እርምጃ ፡ እንዲወስድበት ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይመራል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ጠበቆች ፡ መካከል ፡ እላይ ፡ የተነገረውን፡ የጠበቆች ፡ ተግባር ፡ ያወሳ ፡ አልነበረም ። ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ጠበቆች ፡ እንደተገኘው ፡ ማኅበሩ ፡ እንደ ፡ እድር ፡ ያለ ፡[173] ለመረዳዳት ፡ የተቋቋመ ፡ ሲሆን ፡ ጠበቆች ፡ ሲታመሙ ፡ በማስታመም ፤ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ሲሞት ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ለቀብር ፡ አስፈላጊውን ፡ እርዳታ ፡ በማድረግ ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ ችግር ፡ ሲገጥማቸው ፡ ለጠበቆች ፡ ዋስ ፡ በመሆን ፡ የሚያገለግል ፡ ነው ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ ጥያቄ ፡ ከተደረገላቸው ፡ ጠበቆች ፡ መካከል ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ የሆኑ ፡ ጥቂቶች ፡ ብቻ ፡ ሲሆኑ ፡ የቀሩት ፡ ግን ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ካለመሆናቸውም ፡ ሌላ ፡ ስለማኅበሩ ፡ ተግባርና ፡ አቋም ፡ ምንም ፡ የማያውቁ ፡ ናቸው ። ጥቂቶቹ ፡ እንዲያውም ፡ ስለማኅበሩ ፡ መቋቋም ፡ አልሰሙም ።

ስለማኅበሩ ፡ የሰሙ ፡ ወይም ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ የነበሩ ፡ ጠበቆች ፡ ማኅበሩ ፡ ስለ ፡ አባሎቹ ፡ ደህንነት ፡ አብልጦ ፡ በማሰብ ፡ በፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ረገድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስላሉት ፡ የጊዜው ፡ ችግሮች ፡ በቂ ፡ ሥራ ፡ አላሠራም ፡ ይላሉ ። እነርሱም ፡ ማኅበሩ ፡ የዳኝነት ፡ አመራር ፡ እንዲሻሻልና ፡ የሕግ ፡ ሙያም ፡ እንዲከበር ፡ ለማድረግና ፡ ለመርዳት ፡ከፍ ፡ ያለ ፡ ችሎታ ፡ እንዳለው ፡ ያስባሉ ።

ስለዚህ ፡ በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚነጋገሩት ፡ ጠበቆች ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ የሚያስገኘው ፡ መተሳሰብና ፡ የሥራ ፡ ጓደኝነት ፡ የሚያተርፈው ፡ የወንድማማችነት ስሜት ፡ የላቸውም ። አብዛኛውንም ፡ ጊዜ ፡ በሥራቸው ፡ ብቻቸውን ፡ የተሰማሩ ፡ ስለሚመስላቸው ፡ ከደንበኞቻቸውና ፡ ከሌሎች ፡ ጠበቆች ፡ ጋር ፡ የሚያስተሳስሯቸውን ፡ አስፈላጊ ፡ ደንቦች ፡ የማወቅ ፡ ዕድል ፡ የላቸውም ።

በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ጠበቆች ፡ በጥብቅና ፡ የሚነጋገሩበት ፡ የአሁኑ ፡ ሁኔታ እነዚህን ፡ ዓላማዎች ፡ ለማሟላት ፡ አያስችልም ፤ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞችና ፡ የተሚጋቾችና ፡ የራሳቸው ፡ የጠበቆቹም ፡ ሁኔታ ፡ ለመሻሻሉ ፡ ዕንቅፋት ፡ ሆኗል ። በሙያ ፡ ረገድ ፡ ታማኝነት ፡ ባለመኖሩ ፡ የተነሳ ፡ በጠቅላላው ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ላይ፡

173. እድሮች ፡ በጠቅላላው ፡ እነጋገር ፡ የመቃብር ፡ መረዳጃ ፡ ማህበሮች ፡ ናቸው ።

በተሰማሩት ፡ ማለት ፡ በጠበቆች ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ በተሟጋቾችና ፡ በዳኞች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ አለመከባበር ፡ የመሻሻል ፡ መንፈስ ፡ እንዳያሳይ ፡ የማድረግ ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጥላቻ ፡ በመረዳዳት ፡ መንፈስ ፡ እስከተተካ ፡ ድረስ ፡ ተገቢው ፡ ዝንባሌና ፡ ታማኝነት ፡ መኖሩ ፡ ያጠራጥራል ።

በከፍተኛው፡ ፍርድ፡ቤት ፡ ለመነጋገር ፡ ፈቃድ ፡ ያላቸው ፡ ጠበቆች ፡ ምንም ፡ እንኳ፡ አዘውትረው ፡ ወደ ፡ አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢሄዱም ፡ ወደ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ብቅ ፡ አይሉም ። እንደዚሁም ፡ በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የሚቆሙት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አይቆሙም ። በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ የሚቆሙበት ፡ ጉዳይ ፡ ሊኖራቸው ፡ ይችላል ። እነዚህ ፡ የተሻለ ፡ ላይ ፡ ችሎታ ፡ አላቸው ፡ የሚባሉት ፡ ጠበቆች ፡ በወረዳና ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚኖራቸው ፡ ተጽዕኖ ፡ ጠቃሚ ፡ ቢሆንም ፡ ወደ ፡ በታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መሄድን ፡ እንደ ፡ ችግር ፡ ስለሚቆጥሩት ፡ ለመነጋገር ፡ ከተፈቀደላቸው ፡ በጣም፡ ከፍ ፡ ካለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አለመለየትን ፡ የሚመርጡ ፡ ይመስላሉ ። በነርሱ ፡ አስተያየት ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ችግሮች ፡ መፍትሔ ፡ የሚፈልግላቸው ፡ መሆናቸው ፡ ቀርቶ ፡ ችላ ፡ የሚባሉ ፡ ናቸው ።[174]

“ተሟጋቾች ፡ ወይም ፡ ጠበቆች ፡ በሕግ ፡ ውክልና ፡ ሙያ ፡ ላይ ፡ ከተሰማሩት፡ ውስጥ ፡ በአንድ ፡ ክፍል ፡ የሚመደቡ ፡ ናቸው ። ሌላው ፡ ዓይነት ፡ ሕጋዊ ፡ እንደ ራሴ ፡ ደግሞ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ “ወኪል ፡” ወይም ፡ በተለምዶ ፡ አነጋገር ፡ “ነገረ ፡ ፈጅ ፡” ይባላል ። እንደነዚህ ፡ ያሉትን ፡ ሙያተኞች፡ ስለ ፡ ጠበቆች ፡ በመዝገብ ፡ መግባት ፡ የወጣው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ደንብ ፡ ስለማይመለከታቸው ፡ ፈቃድ ፡ ለማግኘት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መከተል ፡ አያስፈልጋቸውም ።

ወኪሎች ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ እላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ በሁለት ፡ ይከፈላሉ ። አንዱ ፡ ዓይነት ፡ ለንግድ ፡ ማኅበሮችና ፡ ለመንግሥት ፡ ተወክለው ፡ የሚሠሩ ፡ የሆኑ ፡ ናቸው ። ለግል ፡ ሰዎች ፡ ተወክለው ፡ አይነጋገሩም ።

ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ወኪሎች ፡ ደግሞ ፡ ሙያቸው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መነጋገር ፡ ያልሆነ ፡ ናቸው ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ለቅርብ ፡ ዘመድ ፡ ተወክለው ፡ ለቤተ ፡ ሰብ ፡ መነጋገር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ነገረ ፡ ፈጆች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ እንዲከራከርለት ፡ ለመወከል ፡ የነበረው ፡ መብት፡ ቅርስ ፡ ናቸው ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ መብት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአንቀጽ ፡ ፶፰ ፡ እንደ ተመለከተው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ እንዲነጋገርለት ፡ መወከል ፡ የሚችለው ፡ ፈቃድ ፡ ያለውን ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ ባልን ፡ ወይም ፡ ሚስትን ፡ ወንድምን ፡ ልጅን ፡ አባትን ፡ ወይም ፡ አሳዳጊን ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ ተወስኗል ። ለቤተ ፡ ዘመድ ፡

174. ይህ ፡ አመዳደብ ፡ በአሥመራ ፡ ያለ ፡ አይመስልም ። በቂ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ጠበቃ ፡ በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቆማል ። ብዙ ፡ ጊዜም ፡ በወረዳና ፡ ባውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንኳ ፡ ይከራከራል ። በነዚያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መከራከር ፡ ግን ፡ ተመሳሳይ ፡ በሆኑ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የመከራከርን ፡ ያህል ፡ አያስቸግርም ። የአሥመራ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የአዲስ ፡ አበባዎቹን ፡ ያህል ፡ በሥራ ፡ ብዛት ፡ ያልተጣበቡ ፡ ከመሆናቸውም ፡ ሌላ ፡ በአያያዝም ፡ ቢሆን ፡ ከአዲስ ፡ አበባዎቹ ፡ የተሻለ ፡ ሥርዓት ፡ አላቸው ።

የሚነጋገሩ ፡ ወኪሎች ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀበሉ ፡ አይፈቀድላቸውም ።[175]

አንድ ፡ ሰው ፡ የፈቀደውን ፡ እንዳይወክል ፡ የተወሰነበት ፡ ምክንያት ፡ የዳኝነት፡ አሠራር ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ በጥብቅና ፡ ሙያ ፡ ብቻ ፡ የተሠማሩ ፡ ሰዎች ፡ የሚነጋገሩበትን ፡ የሥራ ፡ መስክ ፡ ለማስፋፋት ፡ በማሰብ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ በአንቀጽ ፡ ፶፰ ፡ ለውክልና ፡ ወሰን ፡ የተደረገበት ፡ ምክንያት ፡ የጥብቅናን ፡ ተግባር ፡ ለጠበቆች ፡ ብቻ ፡ ለማድረግ ፡ ጠበቆች ፡ ያላቸው ፡ ፍላጐት ፡ መሆን ፡ አለበት ። ወኪሎች ፡ አንዳች ፡ ወሰን ፡ ሳይደረግ ፡ እንዲከራከሩ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ እንደሆነ ፡ መክፈልና ፡ አለመክፈላቸውን ፡ የማወቂያ ፡ ዘዴ ፡ ስለማይኖር ፡ ጠበቆች ፡ የሚከፍሉትን ፡ ግብር ፡ ሳይከፍሉ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመጠቀም ፡ እድል ፡ ያገኛሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሚሠራበት ፡ ቢሆንም ፡ በፓርላማ ፡ ያልጸደቀበት ፡ አንዱ ፡ ምክንያት ፡ የሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ በልማድ ፡ በሚሠራበት ፡ ውክልና ፡ ላይ ፡ ስላደረገው ፡ ወሰን ፡ አንዳንድ ፡ አባሎች ፡ ባላቸው ፡ ተቃውሞ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ሆኖም ፡ ይኸው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ በውክልና ፡ ላይ ፡ ያደረገው ፡ ወሰን ፡ በአሠራር ፡ ሁልጊዜ ፡ የተጠበቀ ፡ አይደለም ።

## ጠበቆች ፤ የጥብቅና ፡ ሥራ ።

በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚነጋገሩ ፡ ጠበቆች ፡ ብቸኞች ፡ ናቸው ። በጠቅላላው ፡ የጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የላቸውም ፤ ባለጉዳዮችንም ፡ ተቀብለው ፡ የሚያነጋግሩት ፡ በመኖሪያ ፡ ቤታቸው ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመቅረባቸው ፡ በፊት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚነጋገሩት ፡ ጠበቆች ፡ የሚሚገቱበት ፡ ጉዳይ ፡ ተደጋግሞ ፡ የሚመጣ ፡ ጉዳይ ፡ ስለሆነ ፡[176] በየዕለቱ ፡ የሚነጋገሩት ፡ ጉዳይ ፡ ያው ፡ በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ለማዘጋጀት ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ጊዜ ፡ ከባለ ፡ ጉዳዩ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ለመረዳት ፡ አስፈላጊውን ፡ የአቤቱታ ፡ ረቂቅ ፡ ለመጻፍና ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ እስኪገለብጡ ፡ ድረስ ፡ መጠበቅ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ተደጋግሞ ፡ ለሚመጣው ፡ ጉዳይ ፡ ዝግጅት ፡ ከሁለት ፡ ሰዓት ፡ የሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ አይወስድባቸውም ። ከዚሁም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛውን ፡ የሚያጠፉት ፡ ጠበቃውና ፡ ባለ ፡ ጉዳዩ ፡ ሲገናኙ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜአቸው ፡ እንደሆነ ፡ ለጠበቃው ፡ ስለሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በመነጋገር ፡ ነው ።

በመሠረቱ ፡ ለጠበቃው ፡ የሚከፈለው ፡ አበል ፡ በሁለት ፡ መንገድ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ክርክሩ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ርስት ፡ ለማስመለስ ፡ እንደሆነ ፡ ጠበቃው ፡ ከሚያስመልሰው ፡ ነገር ፡ የተወሰነ ፡ እጅ ፡ ማግኘት ፡ ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ ከመቶ ፡ ሀያ ፡ እስከ፡ ሰላሳ ፡ የሚደርስ ፡ ይሆናል ። በጣም ፡ የተለመደው ፡ የጠበቃ ፡ ክፍያ ፡ ግን ፡ ለመነሻ ፡ የሚሆን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥቶት ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ቀጠሮ ፡ መቅረቢያ ፡ አነስ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ መክፈል ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ የአከፋፈል ፡ ዘዴ ፡

175. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ (ለ) ።

176. የተመረመሩትን ፡ ክሶች ፡ መዛግብት ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ የያዘውን ፡ የዚህን ፡ ጽሑፍ ፡ ተጨማሪ ፡ ክፍል ፡ ይመለከቷል ። የተለመዱ ፡ ተብለው ፡ እዚህ ፡ የተጠቀሱት ፡ ጉዳዮች ፡ የስድብ ፡ የስም ፡ ማጥፋትና ፡ ያላግባብ ፡ በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ መግባት ፡ ክሶች ፡ ናቸው ። በርግጥ ፡ ውርስን ፡ የሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። ግን ፡ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በሌሎች ፡ ሰፋፊ ፡ ከተሞች ፡ የሚገኙ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በገጠር ፡ ያሉትን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ያህል ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ክሶች ፡ አይቀርቡላቸውም ።

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ስለተሟጋቾች ፡ በሚናገረው ፡ ክፍል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደሚገለ
ጸው ፡ ሁሉ ፡ ነገሩ ፡ ቶሎ ፡ ከፍጻሜ ፡ እንዲደርስ ፡ የሚያበረታታ ፡ አይደለም ፤ ምክን
ያቱም ፡ ነገሩ ፡ እየተጎተተ ፡ ሲሄድ ፡ ጠበቃው ፡ በየጊዜው ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡
ስለሚያስችለው ፡ ነው ።

ሆኖም ፡ ሊያስከትለው ፡ የሚችለው ፡ ጉዳት ፡ ከጠፋ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የአከፋ
ፈል ፡ ዘዴ ፡ በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ለሚገኙት ፡ ጠበቆችና ፡ ተሟጋቾች ፡ ተስ
ማሚ ፡ ነው ። ተሟጋቹ ፡ አብዛኛውንም ፡ ጊዜ ፡ ለጠበቃ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚከፍ
ለው ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ በእጁ ፡ አይገኝም ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ጠበቃው ፡ ሙግቱ፡
እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ የገንዘቡን ፡ ክፍያ ፡ መጠበቅ ፡ አይችልም ። አብዛኛዎቹ ፡ ፍርድ ፡
ቤት ፡ የቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ደግሞ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ክርክር ፡ ከመደረጉ ፡ በፊት ፡
ወይም ፡ ከአንድ ፡ ሁለት ፡ ቀጠሮ ፡ በኋላ ፡ ያለ ፡ ጠበቃ ፡ እርዳታ ፡ ይፈጸማሉ ። ይህ ፡
ሲሆን ፡ ለማናቸውም ፡ እንደዚህ ፡ ላሉት ፡ ጉዳዮች ፡ ጠበቃው ፡ አስቀድሞ ፡ ለባለጉ
ዳዩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አጥፍቶ ፡ ይሆናል ። ባለጉዳዩ ፡ ጠበቃውን ፡ ሳይማከር ፡ በጉን ፡
የተገላገለ ፡ እንደሆነ ፡ ተፈልጎ ፡ ስለማይገኝና ፡ ጠበቃውም ፡ ገንዘቡን ፡ ለመቀበል ፡
የሚደርስበት ፡ ችግር ፡ ከሚፈልገው ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ ስለሆነ ፡ የድካሙን ፡
ዋጋ ፡ እንዳጣ ፡ ይቀራል ።

ጠበቃው ፡ ለመኖር ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ገቢ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ማግኘት ፡ አለበት ።
የሚቀጠርበትም ፡ ነገር ፡ እንዳጋጣሚ ፡ በዕድል ፡ የሚገኝ ፡ ነው ። ከተጠየቁት ፡ አብዛ
ኛዎቹ ፡ ጠበቆች ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለትና ፡ ሶስት ፡ ነገረተኞች ፡ ብቻ ፡ እንደነበራቸው
ገልጸዋል ።

በኢትዮጵያ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚነጋገሩ ፡ ጠበቆች ፡ ከሙቶ ፡ ሰማንያውን፡
ያህል ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀጠሮ ፡ ጊዜ ፡ ተራቸውን ፡ በመጠበቅና ፡ ከሙቶ ፡ አስ
ሩን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በዳኛ ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ በመነጋገር ፡ የቀረውን ፡
ከሙቶ ፡ አሥሩን ፡ ለጉዳዩ ፡ በመዘጋጀት ፡ ጊዜያቸውን ፡ ያሳልፋሉ ። ስለዚህ ፡ ጥቅም ፡
ባለው ፡ ሥራ ፡ የሚያውሉት ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ስለሆነ ፡ ለመኖሪያ ፡ በቂ ፡ ገቢ ፡ ለማግ
ኘት ፡ ለዚህ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ መጠየቅ ፡ ይኖርባቸዋል ። ይህም ፡
ማለት ፡ በአሁኑ ፡ የአሠራር ፡ መንገድ ፡ ጠበቆች ፡ በከንቱ ፡ ለሚያጠፉት ፡ ጊዜ ፡ ባለ
ጉዳዮች ፡ እንዲከፍሉ ፡ ያስገድዳቸዋል ።

ጠበቆች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረቡ ፡ ቁጥር ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፈላቸው ፡ ለሚያደር
ገው ፡ ለአሁኑ ፡ የአበል ፡ አከፋፈል ፡ ዘዴ ፡ አንዱ ፡ ምክንያት ፡ የአሁኑ ፡ የዳኝነት ፡
ሥራ ፡ አመራር ፡ ጠበቆች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጊዜያቸውን ፡ በከንቱ ፡ እንዲያሳልፉ ፡ ማድ
ረጉ ፡ ነው ። ጠበቃው ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ መዘጋጀትም ፡ ሆነ ፡ ከሌላው ፡ ወገን ፡ ጋር ፡ ከስ
ምምነት ፡ ለመድረስ ፡ ሲል ፡ የሚያጠፋው ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ በመሆኑ ፡ ባለጉ
ዳዩ ፡ እንደትልቅ ፡ ነገር ፡ አድርጎ ፡ የሚቆጥረው ፡ ጠበቃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀጠሮ
ው ፡ ሰዓት ፡ በመቅረብ ፡ የሚሰጠውን ፡ አገልግሎት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡
ጠበቃው ፡ ባለጉዳዩን ፡ የሚያገኘው ፡ በቀጠሮ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ጠበቆች ፡ ከሰዓት ፡ በፊት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በአራት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ለሁ
ለት ፡ ወይም ፡ ለሦስት ፡ ጉዳዮች ፡ ቆመው ፡ እንደሚነጋገሩ ፡ ገልጸዋል ። ከሰዓት ፡ በኋላ ፡
አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ችሎት ፡ ባይኖርም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚቀርቡ ፡ ተናግረዋል ።
ለሦስት ፡ ወይም ፡ አራት ፡ ጉዳዮች ፡ ለመቆም ፡ በቀን ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ በጣም ፡
ንቁና ፡ ሁልጊዜ ፡ ዝግጁ ፡ መሆን ፡ አለበት ። አንደኛ ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ያለው ፡ ቀጠሮ ፡
ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲሆንለት ፡ መሞከር ፡ አለበት ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ፡
እንደማይሳካለት ፡ ሁሉ ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ ካልቻለ ፡ ፋይሉ ፡ እርሱ ፡ በሚፈልገው ፡
ሰዓት ፡ እንዲቀርብለት ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ ነገሩን ፡ እንዲያቆዩ

ለት ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ወይም ፡ ከዳኛው ፡ ጋር ፡ መስማማት ፡ ይኖርበታል። የጠበቃው ፡ ገቢ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚቀርብበት ፡ መጠን ፡ ስለሚወሰን ፡ ለኑሮው ፡ አስፈ ላጊውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ መተባበር ፡ ማግኘት ፡ አለበት ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ቀጠሮ ፡ የሚሰጠው ፡ በተወሰነ ፡ ሰዓት ፡ ሳይሆን ፡ በቀን ፡ ስለሆነ ፡ ጠበቃው ፡ በግምት ፡ እንኳ ፡ በስንት ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ እንደሚጠራ ፡ አያውቀውም ። ነገሩ ፡ በሌለበት ፡ የተጠራ ፡ እንደሆነ ፡ ለሌላ ፡ ሰዓት ፡ እንዲያውም ፡ ለሌላ ፡ ቀን ፡ ይተላለ ፋል ። ባለጉዳዮቹ ፡ በጠበቃቸው ፡ አለመቅረብ ፡ ምክንያት ፡ ቀጠሮ ፡ ስለሚጠይቁ ፡ ይህ ፡ በቀጠሮ ፡ መተላለፍ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጅ ፡ ሆኗል ። ምንም ፡ ጠበ ቃው ፡ በዚያው ፡ ዕለት ፡ የሚቀርብ ፡ መሆኑን ፡ ባለጉዳዩ ፡ ለዳኛው ፡ ቢያረጋግጥለ ትም ፡ ጉዳዩ ፡ ለሌላ ፡ ቀን ፡ ስለሚቀጠር ፡ የባለጉዳዮችም ፡ ጊዜ ፡ በከንቱ ፡ ይባክናል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ጠበቃው ፡ ቢቀርብ ፡ ኖሮ ፡ ሊያገኝ ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ያጣል ።

ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ጠበቆች ፡ ለማናቸውም ፡ ነገር ፡ ጥብቅና ፡ ቆመው ፡ የሚነጋገሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጸዋል ። ለተለየ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እንነጋገራለን፡ ያሉት ፡ ግን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ የሚነጋገሩ ፡ ናቸው ። ሁለት ፡ ጠበቆች ለወንጀል ፡ ጉዳይ ፡ የሚቆሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ተናግረዋል ። እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ጠበቆች፡ በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በስድብ ፡ በድብደባና ፡ በስም ፡ ማጥፋት ፡ በግል ፡ ከሳሾች ፡ በሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ጥብቅና ፡ ቆመው ፡ ለከሳሽና ፡ ለተከሳሽ ፡ የሚነጋገሩ ፡ ናቸው ። በሌላ ፡ ዓይነት ፡ የወንጀል ፡ ክሶች ፡ ግን ፡ ለከሳሹ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ስለሚከራከርለትና፡ ተከሳሾቹ ፡ ጠበቃ ፡ ማቆም ፡ ስለማይችሉ ፡ የጠበቃ ፡ እርዳታ ፡ አያገኙም ።

ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ጠበቆች ፡ መካከል ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎችን ፡ ያለእነርሱ ፡ ቁጥጥር ፡ የክስ ፡ ማመልከቻ ፡ የሚያስጽፉ ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ሆኖም ፡ ከተ ጠየቁት ፡ መካከል ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ጠበቆች ፡ የአቤቱታውን ፡ ማመልከቻ ፡ ረቂቁን ፡ ካዘጋጁ ፡ በኋላ ፡ የሚገለብጡላቸው ፡ ወይም ፡ ቃሉን ፡ ተቀብለው ፡ የሚጽፉላቸው ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጸዋል ። ግማሾቹ ፡ ግን ፡ ማመልከቻውን ፡ ራሳቸው ፡ የሚጽፉ ፡ መሆናቸውን ፡ ተናግረዋል ። የቀሩት ፡ ከፍ ፡ ባሉት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚነጋገሩት ፡ ጠበቆች ፡ ግን ፡ ረቂቅ ፡ አውጥተው ፡ ጠበቃው ፡ ከተስማማ በት ፡ በኋላ ፡ ማመልከቻውን ፡ የሚጽፉላቸው ፡ ጸሐፊዎችና ፡ ረዳቶች ፡ አሏቸው ።

ከተጠየቁት ፡ ጠበቆች ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ላይ ፡ የተቃውሞ ፡ አስተያየት ፡ ያሰሙት ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። አብዛኛዎቹ ፡ "ጥሩ ፡ አገልግሎት ፡ ያበረክ ታሉ ፡" ብለዋል ። አያሌ ፡ ባለጉዳዮች ፡ ጠበቃ ፡ የሚገዙት ፡ ማመልከቻቸውን ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊ ፡ ከጻፈላቸው ፡ በኋላ ፡ ስለሆነ ፡ ጠበቆችም ፡ ከራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ የተለማመዱ ፡ በመሆናቸው ፡ ስለራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ችሎታ ፡ ለመናገር ፡ የሚያስችል ፡ መሠረት ፡ አላቸው ።

ስለዚህ ፡ በጠበቆች ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፡ በጠበቆችና ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ መካ ከል ፡ መግባባትና ፡ ስምምነት ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ነው ።

## የጠበቆች ፡ መሠረታዊ ፡ ችሎታ ።

በአዲስ ፡ አበባና ፡ በሐረር ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ጠበቆች ፡ ከሁለት ፡ በስተቀር ፡ የመጻፍና ፡ የማንበብ ፡ ችሎታ ፡ አላቸው ።[177] ከእነርሱም ፡ ከመቶ ፡ ሃምሳው ፡

177. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ጠበቆች ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ በሐረር ፡ ነበር ። እነርሱም ፡ ከጣሊያን ፡ ወረራ ፡ በፊትም ፡ ጠበቆች ፡ ነበሩ ። በረጅም ፡ ጊዜ ፡ የሕግ ፡ ሙያ ፡ አባልነታቸው ፡ ምክንያት ፡ በጥብቅናቸው፡ እንዲቀጥሉ ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ልዩ ፡ ፈቃድ ፡ ተሰጥቶአቸዋል ፤ በአዲስ ፡ አበባም ፡ ሆነ ፡ በአሥ መራ ፡ መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ ለማያውቁ ፡ ጠበቆች ፡ ጥያቄ ፡ አላቀረብንም ።

ያህሉ ፡ የአማርኛ ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ ሲኖራቸው ፡ ከመቶ ፡ ሠላሣው ፡ ያህሉ ፡ ደግሞ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ በተጨማሪም ፡ ከሁለተኛ ፡ እስከ ፡ ስምንተኛ ፡ ክፍል ፡ ድረስ ፡ ደንበኛ ፡ ትምህርት ፡ ነበራቸው ። የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ትምህርት ፡ አላቸው ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከሚገኙት ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ጠበቆች ፡ ከመቶ ፡ አሥራ ፡ ስምንቱ ፡ ያህል ፡ ዩኒቨርሲቲው ፡ የሚሰጠውን ፡ የሕግ ፡ ሰርቲፊኬት ፡ ወይም ፡ ዲፕሎማ ፡ ኮርስ ፡ በመውሰድ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ወይም ፡ የወሰዱ ፡ ናቸው። የሕግ ፡ ሰርቲፊኬትና ፡ ዲፕሎማ ፡ ፕሮግራሞች ፡ አዲሶቹን ፡ ሕጎች ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ከተሰማሩት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ለማስተዋወቅ ፡ የታቀዱ ፡ መሠረታዊ ፡ የማታ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ፕሮግራሞች ፡ ናቸው ። በሰርቲፊኬት ፡ ደረጃ ፡ የሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ በጣም ፡ መሠረታዊ ፡ ነው ። የዲፕሎማው ፡ ትምህርት ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የሚሰጥ ፡ ሲሆን ፡ ወደዚሁ ፡ ፕሮግራም ፡ ለመግባት ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

በአሥመራ ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ስምንት ፡ ጠበቆች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ትምህርት ፡ የለውም ። ሆኖም ፡ በአማርኛና ፡ በግዕዝ ትምህርት ፡ በጣም ፡ የገፋ ፡ ነው ። ሦስቱ ፡ የኢጣልያን ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ ሲኖራቸው ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ ከላሳል ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ከኤክስቴንሺን ፡ ኮርስ ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ የተቀበለ ፡ ነው ። የቀሩት ፡ ግን ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ እስከ ፡ ስድስተኛ ፡ ክፍል ፡ ተምረዋል ።

የሚያስገርመው ፡ ነገር ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተጠየቁት ፡ በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በጥብቅና ፡ ከሚቆሙት ፡ ጠበቆች ፡ መካከል ፡ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ በመንግሥት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ያከናወኑ ፡ አለመኖራቸው ፡ ነው ።

ስለዚህ፡ ጠበቆች ፡ ከትምህርት ፡ ችሎታቸው ፡ ማነስ ፡ የተነሣ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞችም ፡ ሆነ ፡ ከተሟጋቾች ፡ ተገቢውን ፡ አክብሮት ፡ አያገኙም ። የሌላውን ፡ ሰው፡ ጉዳይ ፡ ለማከናወን ፡ የተለያየ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ወይም ፡ አለን ፡ ብለው ፡ የሚገምቱ ፡ ሲሆኑ ፡ በተፈጥሮ ፡ ብልሆችና ፡ የፍርድ ፡ ቤትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ያስተማሩ ፡ ናቸው ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ተደጋግመው ፡ ለሚመጡላቸው ፡ ጉዳዮች ፡ እምብዛም ፡ የሕላዌ ፡ ሕግ ፡ ዕውቀት ፡ አያስፈልጋቸውም ። በተጨማሪም ፡ በጥብቅና ፡ ቆመው ፡ የሚነጋገሩባቸው ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዳኞች ፡ ከእነርሱ ፡ ይበልጥ ፡ ሕጉን ፡ ካለማወቃቸውም ፡ በላይ ፡ በትምህርትም ፡ ከእነርሱ ፡ ያንሱ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አይበልጡም ፤ በሕግ ፡ ዕውቀት ፡ ረገድ ፡ ዳኞች ፡ ከጠበቆች ፡ የሚለዩበት ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የረዥም ፡ ጊዜ ፡ የአስተዳደር ፡ ልምምድ ፡ ያላቸው ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ጠበቆች ፡ የሚኖሩት ፡ በብልጠት ፡ ሲሆን ፡ ብዙዎች ፡ የዕለት ፡ እንጀራቸውን ፡ የሚያገኙት ፡ ያለአንዳች ፡ ትምህርት ፡ ነው ። በሕግ ፡ ተግባር ፡ የተሠማሩበት ፡ አኳኋንና ፡ ለኑሯቸው ፡ አሁን ፡ ገንዘብ ፡ የሚያገኙበት ፡ መንገድ ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ በብቸኛነት ፡ መኖራቸውን ፡ ያመለክታል ። ከተጠየቁት ፡ ጠበቆች ፡ ከመቶ ፡ ሀያ ፡ አምስቱ ፡ ያህል ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ የጀመሩት ፡ በራሳቸው ፡ ጉዳይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ ከተሟገቱ ፡ በኋላ ፡ መሆኑን ፡ ገልጸዋል ። አብዛኛውንም ፡ ጊዜ ፡ ክርክሩ ፡ አባት ፡ ወይም ሌላ ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ ሞቶባቸው ፡ በርስት ፡ ውርስ ፡ ምክንያት ፡ ከዘመድ ፡ ጋር ፡ ባጋጠማቸው ፡ ክርክር ፡ ነው ፤ ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ጠበቆች ፡ ከመቶ ፡ አርባው ፡ ያህል ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ የጀመሩት ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ተቀጥረው ፡ ሲሠሩ ፡ የሙግት ፡ ልምድ ፡ ስላገኙ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ጠበቆች ፡ የሕግ ፡ ጠበቆች ፡ ከመሆናቸው ፡ በፊት ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊ ፡ ሆነው ፡ የሠሩ ፡ ናቸው ። ከተጠየቁት ፡ ጠበቆች ፡ መካ

ከል ፡ ሁለቱ ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ከመጀመራቸው ፡ በፊት ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ነበሩ ።[178] አንዱ ፡ ጠበቃ ፡ ደግሞ ፡ የፖሊስ ፡ ሕግ ፡ አስከባሪ ፡ የነበረ ፡ ሲሆን ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ። በተጨማሪም ፡ ከጠበቆቹ ፡ መካከል ፡ ሁለቱ ፡ በየጊዜው ፡ ገንዘብ ፡ አልከፍ ልም ፡ ያሉትን ፡ ዕቁብተኞች ፡ ገንዘብ ፡ ለማስከፈል ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመመላለስ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ የተላመዱ ፡ የዕቁብ ፡ ዳኞች ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ።

ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ጠበቆች ፡ ከመቶ ፡ አርባው ፡ በጥብቅና ፡ ተግባር ፡ ለመሰማራት ፡ የሚያስችላቸው ፡ አንዳች ፡ የተለየ ፡ ልምድ ፡ እንዳላቸው ፡ አልገለጹም ።[179] ስለነዚህም ፡ ሰዎች ፡ ለመናገር ፡ አይቻልም ። ይሠሩ ፡ የነበረውም ፡ ሥራ ፡ በኩባንያ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በዝቅተኛ ፡ ደረጃ ፡ ጸሐፊነት ፡ በፖሊስ ፡ ሥራ ፡ በአነስተኛ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ በግብርናና ፡ እንደዚህ ፡ በመሳሰሉ ፡ ሥራዎች ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ሁለት ፡ ጠበቆች ፡ አባቶቻቸው ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንደነበሩ ፡ አውስተዋል ። ሆኖም ፡ በጠቅላላው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ የሚጀምሩት ፡ በቀድሞ ፡ ሥራቸው ፡ ላይ ፡ ከሚያገኙት ፡ ገንዘብ ፡ የበለጠ ፡ ለማግኘት ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ በገቢ ፡ በኩል ፡ ከሚገኘው ፡ እድገት ፡ ሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከቀድሞ ፡ ሥራቸው ፡ ጋር ፡ ሲወዳደር ፡ አስደሳች ፡ ኑሮን ፡ ያበረክታሉ ፤ ከእነርሱም ፡ መካከል ፡ ከመቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስቱ ፡ ያህል ፡ አሥር ፡ ዓመታት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ያነሰ ፡ ዘመን ፡ በጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የቆዩ ፡ ሲሆኑ ፡ ከመቶ ፡ ሠላሳ ፡ አምስቱ ፡ ያህል ፡ ደግሞ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ ያነሰ ፡ ጊዜ ፡ ሠርተዋል ።

በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አካባቢ ፡ እንደሚታየው ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ብዙ ፡ በዕድሜ ፡ የገፉ ፡ ጠበቆች ፡ ያሉ ፡ አይመስልም ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ ከጣልያን ፡ ወረራ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ ጠበቆች ፡ ትምህርት ፡ ስላልነበራቸው ፡ ወይም ፡ ከጥንቱ ፡ ልማዳዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ የተላመዱ ፡ በመሆናቸው ፡ ስለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ በ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ካቋቋመው ፡ ከአዲሱ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ አቋም ፡ ጋር ፡ ሊላመዱ ፡ ስላልቻሉ ፡ ይሆናል ።

አዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ በጣም ፡ የሚሠራባቸው ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ጠበቆች ፡ ስለነዚህ ፡ ሕጋጋት ፡ በመጠኑም ፡ ቢሆን ፡ ማወቅ ፡ ይኖርባቸዋል ። አለበለዚያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በጥብቅና ፡ ቆመው ፡ መነጋገር ፡ አይችሉም ፤ ምናልባት ፡ የተሰጠው ፡ ምሳሌ ፡ ለወጣት ፡ ጠበቆች ፡ መብዛት ፡ ሌላው ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ የማይችሉ ፡ ጠበቆች ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ በሐረር ፡ የሚገኙ ፡ ሲሆን ፡ ምናልባትም ፡ በሌሎች ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ሳይኖሩ ፡ አይቀሩም ። ሆኖም ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ለመሥራት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ይሆንባቸዋል ።

---

178. ይህንን ፡ ሲያዩት ፡ ምክንያት ፡ አልባ ፡ የሆነውን ፡ የሥራ ፡ መቀየር ፡ ምክንያት ፡ ሲገልጡ ፡ አንድ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ እንዲህ ፡ ብለዋል ። "በድሮ ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ በበቅሎ ፡ ሲሰግሩ ፡ ተሟጋቾች ፡ ፍትኅን ፡ እየለመኑ ፡ ይከተሏቸው ፡ ነበር ። ጠበቆችም ፡ ጠመንጃዎቻቸውን ፡ አንግተው ፡ ከዳኞቹ ፡ በቅሎ ፡ ጐን ፡ በመራመድ ፡ ዳኞችን ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ጠበቆች ፡ መኪና ፡ ሲነዱ ፡ እኛ ፡ እግረኞች ፡ ነን ።"

179. በጠቅላላው ፡ እነጋገር ፡ የአሥመራ ፡ ጠበቆች ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ የጀመሩት ፡ ከሥር ፡ ጀምር ፡ ጠበቃ ፡ በመሆን ፡ ነው ። በርግጥ ፡ ብዙዎቹ ፡ በኢጣሊያ ፡ ሕግ ፡ ዲግሪ ፡ ያላቸው ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ናቸው ። ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ በእንግሊዝ ፡ አስተዳደር ፡ ጊዜ ፡ በእንግሊዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ውስጥ ፡ የሰለጠኑ ፡ ናቸው ። ጥቂቶቹ ፡ ከሌሎች ፡ ጠበቆች ፡ ጋር ፡ በመሥራት ፡ ራሳቸውን ፡ በማስተማርና ፡ በማለማመድ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የደረሱ ፡ ናቸው ። በአሥመራ ፡ የሕግ ፡ ሙያ ፡ በመካከለኛ ፡ ዕድሜ ፡ ላይ ፡ የሚጀመር ፡ ሥራ ፡ አይመስልም ።

በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚነጋገሩት ፡ ጠበቆች ፡ ደንበኞቻቸው ፡ ወደ ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ከመምጣታቸው ፡ በፊት ፡ ስለአዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ ምንም ፡ አያውቁም ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ሰጥተዋል ። ጠበቆቹ፡ ጥብቅና፡ ለሚቆሙላቸው ፡ የሚሰጡት ፡ ከፍተኛ፡ ግምት ፡ ደንበኞቻቸው ፡ ግፉ ፡ ቢል ፡ የአዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ መኖር ፡ ማወቃቸውን ፡ ብቻ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አብዛኞዎቹ ፡ ጠበቆች ፡ እንደሚሉት ፡ ደንበኞቻቸው ፡ ከል ማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ይልቅ ፡ አዲሶቹን ፡ ሕጎች ፡ እንደሚመርጡ ፡ ይገምታሉ ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ እንደጠበቆቹ ፡ አስተያየት ፡ የባለጉዳዮቹ ፡ አስተሳሰብ ፡ ወይም፡ ዝንባሌ ፡ እላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ቢገመትም ፡ ይህ ፡ ላይሆን ፡ የማይችልበትም ፡ ምክ ንያት ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ። የጠበቆቹን ፡ አስተያየት ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ የማያሰኘው ፡ አንዱ ፡ ምክንያት ፡ ጠበቆች ፡ በጠቅላላው ፡ ስለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ተቃውሞ ፡ ከማሰ ማት ፡ ስለሚቆጠቡ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሌሎችንም ፡ ቅሬታ ፡ ለመናገር ፡ አይፈቅ ዱም ፡ ይሆናል ። ሌላው ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ተሟጋቾች ፡ ጠበቆችን ስለሚ ንቁ ፡ በጠበቆችና ፡ በባለጉዳዮች ፡ መካከል ፡ በግልጽ ፡ የመነጋገር ፡ ሁኔታ ፡ ስለሌለ ፡ ነው ።

ተሟጋቾች ፡ ለዳኞች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አክብሮት ፡ እንዳላቸው ፡ ጠበቆች ፡ ቢገምቱም ፡ አክብሮት ፡ የሚያሳዩት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ መሆኑንና ፡ ይህም ፡ በእርግጥ ፡ ዳኛውን ፡ ለማክበር ፡ ሳይሆን ፡ ከፍርሃት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ሰጥተዋል ።[180] ምንም ፡ እንኳ ፡ ጠበቆች ፡ ስለራሳቸው ፡ ያላቸው ፡ ከፍተኛ ፡ አስተያየት ፡ ከአነጋገራቸው ፡ ሊታወቅ ፡ ቢቻልም ፡ አብዛኞቹ ፡ ተሟጋቾች ፡ ለዳ ኛው ፡ የሚሰጡት ፡ አክብሮት ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ እስኪወጡ ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ጠበቆቹ ፡ እንደሚሉት ፡ ከሆነ ፡ ዳኞች ፡ ችሎታ ፡ የሌላቸውና ፡ እምነትም ፡ የሚጎድላቸው ፡ ናቸው ፡ በመባል ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ በተሟጋቾች ፡ ዘንድ ፡ በን ቀት ፡ የሚታዩ ፡ ናቸው ።

እያሌ ፡ ጠበቆች ፡ እንደሚገምቱት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ ለማሻሻል፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ በተለይም ፡ ዳኞች ፡ የበለጠ ፡ ትምህርት ፡ ያስፈልጋቸ ዋል ።

ብዙዎቹ ፡ ተሟጋቾች ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ በበለጠ ፡ እንዲሻሻል ፡ በቅድሚያ ፡ ጉቦና ፡ ነገር ፡ መንተት ፡ መቅረት ፡ አለባቸው ፡ ሲሉ ፡ ይህንን ፡ ያወሱ ፡ ጠበቆች ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ከሌላው ፡ ችግር ፡ ይልቅ ፡ ጠበቆች ፡ የትምህርትን ፡ ነገር ፡ ይበልጥ ፡ ያሰቡበት ፡ ምክንያት ፡ የጉቦ ፡ ጉዳይ ፡ ስሜትን ፡ የሚነካ ፡ በመሆኑ ፡ ማናቸ ውም ፡ ሰው ፡ በቀላሉ ፡ ሊያጋንነው ፡ ስለሚችል ፡ እንዲሁም ፡ የነገር ፡ መጐተት ፡ በቀ ጥታ ፡ የሚሰማቸውና ፡ የሚታያቸው ፡ ተሟጋቾች ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀ ርም ።

በተጨማሪም ፡ ደግሞ ፡ ጉቦ ፡ ከባለ ፡ ጉዳዩ ፡ ለዳኛ ፡ የሚሰጠው ፡ በጠበቃው ፡ አማካይነት ፡ መሆኑ ፡ ይነገራል ። እንዲያውም ፡ በብዙ ፡ ቀጠሮ ፡ ምክንያት ፡ ነገር ፡ ሲጎተት ፡ ለጠበቃው ፡ ከሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ዳኛውም ፡ ድርሻ ፡ እንዳለው፡ የሚያሳይ ፡ አንዳንድ ፡ ማስረጃ ፡ አይጠፋም ።

180. አንድ ፡ ጠበቃ ፡ "ተሟጋቾቹ ፡ ዳኞችን ፡ ያከብራሉን ?" ተብሎ ፡ ለቀረበለት ፡ ጥያቄ ፡ "በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹ ፡ መሠረት ፡ ዳኞች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሳሉ ፡ ተገ ቢውን ፡ ክብር ፡ ያልሰጧቸውን ፡ ወገኖች ፡ ሊቀጡ ፡ ይችላሉ ፡ "ሲል ፡ መልሷል ።
በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙ ፡ ፲፮ ፡ ዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ቀርቦላቸዋል ። ከነዚህም ፡ ፲ቱ ፡ የአውራ ጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ።

ስለዚህ ፡ የአሁኑ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ያለበት ፡ የዕድገት ፡ ደረጃ ፡ ለጠበቆች ፡ የተስማማቸው ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። አዲሱ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ተሟጋቾችን ፡ ስለሚያደናግራቸው ፡ በሚፈጠረው ፡ ግርግር ፡ የሚጠቀሙት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጠበቆች ፡ ናቸው ።

## ዳኞች ።[181]

ከዳኞች ፡ ጋር ፡ የተደረጉት ፡ ጥያቄና ፡ መልሶች ፡ የሕግ ፡ ችሎታቸውን ፡ ለመፈተን ፡ የታቀዱ ፡ አልነበሩም ፤ የተጠየቁት ፡ ጥያቄዎች ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዳኞች ፡ እንዴት ፡ ዓይነት ፡ ሰዎች ፡ እንደሆኑ ፡ ስለሥራቸው ፡ በሕብረተሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ስላላቸው ፡ ቦታና ፡ ከፍተኛ ፡ ሥፍራ ፡ ይዘው ፡ ስለሚገኙበት ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ እንደሚያስቡ ፡ ለማወቅ ፡ የታቀዱ ፡ ነበሩ ።

### የሕይወት ፡ ታሪካቸው ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሚገኙ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ ከመካከለኛ ፡ የኤኮኖሚና ፡ የሶሻል ፡ ደረጃ ፡ ተነስተው ፡ አሁን ፡ ያሉበት ፡ ቦታ ፡ የደረሱ ፡ ናቸው ።

የተጠየቁት ፡ ዳኞች ፡ ማዕከላዊ ፡ ዕድሜ ፡ ዓርባ ፡ አምስት ፡ ነበር ፡ ይህም ፡ ማለት ፡ እነዚህ ፡ ዳኞች ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ ደረጃ ፡ አሁን ፡ ካለበት፡ ደረጃ ፡ ዝቅተኛ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ እና ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከሕዝቡ ፡ ዕድሜአቸው ፡ ከ፳፬ ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ ከሆኑት ፡ መደበኛ ፡ ትምህርት ፡ ከሚያገኙት ፡ ከመቶ ፡ ሦስት ፡ ከሚሆኑት ፡ ያነሰ ፡ የትምህርት ፡ ዕድል ፡ ያገኙ ፡ በነበረበት ፡ በ፲፱፻፹፰ ፡ ዓ፡ም፡ ገደማ ፡ ላይ ፡ ዕድሜአቸው ፡ ለትምህርት ፡ ደርሶ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።[182]

በቤተ ፡ ክህነት ፡ ከሚሰጠው ፡ የአማርኛ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ትምህርት ፡ ገፋ ፡ ቢልም ፡ ከግዕዝ ፡ ቋንቋ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። በቤተክህነት ፡ የሚሰጠው ፡ ትምህርት ፡ መንፈሳዊ ፡ ምንባቦችን ፡ ደጋግሞ ፡ ማጥናትና ፡ በቃል ፡ መውጣት ፡ ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ የሚወስደው ፡ መሠረታዊ ፡ ጊዜ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነው ።[183] ከኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውጪ ፡ የሚገኙት ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዳኞች ፡ በግምት ፡ ሁሉም ፡ ያላቸው ፡ የቤት ፡ ክህነት ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

181. በአዲስ ፡ አበባ ፡ አካባቢ ፡ ለሚገኙ ፡ ማለት ፡ ከሰበታ ፡ ከገነት ፡ ከፍቼ ፡ ከአምቦ ፡ ከአቃቂና ፡ ከደብረ ፡ ዘይት ፡ የተውጣጡ ፡ ስምንት ፡ ዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ቀርቦላቸዋል ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ነበር ። በሐረርም ፡ ለሦስት ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞችና ፡ ለሁለት ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ ቀርቦላቸው ፡ ነበር ። ለዓለማያ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛና ፡ በኮምቦልቻ ፡ የሚገኙት ፡ ሁለት ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞችም ፡ ተጠይቀው ፡ ነበር ። በአሥመራም ፡ ለ፲፫ ፡ ዳኞች ፡ ጥያቄ ፡ አቅርበናል ። ከነዚህም ፡ ስምንቱ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ነበሩ ።

182. በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ብዛቱ ፡ ሦስት ፡ በመቶ ፡ የሚሆነው ፡ ዕድሜው ፡ ፳፬ ፡ እና ፡ ከዚያም ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ (የትምህርት ፡ ሚኒስቴርን ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርት ፡ በሚከተሉ) ፡ በመንግሥት ፡ በግልና ፡ በሚሲዮን ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ የተለየ ፡ ሙያን ፡ በሚያስተምሩ ፡ እንደ ፡ እርሻ ፡ ንግድ ፡ የጤና ፡ ትምህርትና ፡ የመምህራን ፡ ማሠልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። ከነዚህም ፡ ከሰማኒያ፡ በመቶው ፡ በላይ ፡ ከአንደኛ ፡ እስከ ፡ ስድስተኛ ፡ ባሉት ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ።
ቁጥሩ ፡ የተወሰደውም ፡ ሆነ ፡ የተጻፈው ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ እና ፡ በ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከወጡት ፡ የኢትዮጵያ፡ እስታቲስቲክ ፡ መጽሔቶች ፡ ላይ ፡ ነው ። ጠቅላይ ፡ የእስታቲስቲክ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ም አዲስ ፡ አበባ ፡ ገጽ ፡ ፻፺፯ ፡ ተከታዮቹ ።

183. ኤስ ፡ ዲ ፡ ሚሲንግ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶፱ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፰ ፡ የተጠቀሰ ።

መደበኛ ፡ ትምህርት ፡ ለማግኘት ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆንና ፡ ኃላፊነት ፡ ያለባቸው ፡ ብዙ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ ክፍት ፡ ሲሆኑ ፡ በመንግሥት ፡ ሥራ፡ ላይ ፡ የተገኘ ፡ ልምድ ፡ የመደበኛ ፡ ትምህርትን ፡ ሥፍራ ፡ ይወስዳል ። እነዚህ ፡ በኋላ፡ ዳኞች ፡ ሊሆኑ ፡ የቻሉት ፡ ሰዎች ፡ አማርኛ ፡ የማንበብና ፡ የመጻፍ ፡ ችሎታ ፡ ስለነበራቸው ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ወይም ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በቢሮ ፡ ሠራተኛነት ፡ ለመቀጠር ፡ ቻሉ ። ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ አገልግሎት ፡ በኋላ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚሰጠውን ፡ ፈተና ፡ ለመውሰድ ፡ ወሰኑ ፤ ወይም ፡ በየበላዮቻቸው ፡ ዕርዳታ ፡ ፈተናውን ፡ ሳይወስዱ ፡ ዳኞች ፡ ሆኑ ።

በትክክል ፡ የታወቀና ፡ የተጻፈ ፡ የአስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሳይሆን ፡ ከዕለት ፡ ሥራ ፡ የተገኘ ፡ ልምድና ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የግል ፡ ትውውቅ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነበት ፡ የአስተዳደር ፡ አቋም ፡ ውስጥ ፡ የእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ለመመረጥ ፡ በጠቅላላው ፡ አሠራር ፡ ውስጥ ፡ ከአሥራ ፡ አምስት ፡ ወይም፡ ሃያ ፡ ዓመት ፡ የበለጠ ፡ ልምድ ፡ ሊያስፈልገው ፡ አይችልም ። ከተጠየቁትም ፡ ዳኞች ፡ አብዛኞቹ ፡ በተለይ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ሆነው ፡ ከሠሩ ፡ በኋላ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ የሆኑት ፡ የነበራቸው ፡ ይኸው ፡ በልማድ ፡ ያከማቹት ፡ ዕውቀት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የወረዳ ፡ ዳኞች ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሌላም ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ረጅም ፡ የአገልግሎት ፡ ዘመን ፡ ያላቸው ፡ መሆኑ ፡ የተለመደ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ዳኞች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ፡ የአንድ ፡ ወረዳ ፡ ወይም ፡ አውራጃ ፡ ገዥ ፡ ጸሐፊ ፡ ሆነው ፡ ያገለገሉ ፡ ናቸው ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ዳኞች ፡ ሆነው ፡ እንዲሾሙ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ገዥዎቹ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሐሳብ ፡ ያቀርቡላቸዋል ። ከሌላ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወደ ፡ ፍርድ፡ ሚኒስቴር ፡ በዳኝነት ፡ መዛወር ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ አገልግሎትና ፡ ታማኝነት ፡ የሚሰጥ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በችሎታ ፡ ማጣት ፡ ሳይሆን ፡ በግል ፡ ምክንያት ፡ ካለበት ፡ ቦታ፡ ሊያድግ ፡ ያልቻለን ፡ ሰው ፡ ከአካባቢው ፡ የማውጫያ ፡ ዘዴ ፡ ነው ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ የሚገኙ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ የአሁኑን ፡ ቦታቸውን ፡ ከመያዛቸው፡ በፊት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከከተማይቱ ፡ ውጪ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ይዘው ፡ የነበሩ ፡ ቢሆንም ፡ በርከት ፡ ያለውን ፡ ጊዜአቸውን ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ መንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሲያገለግሉ ፡ ያሳለፉ ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ። ዳኞች ፡ ከሆኑም ፡ በኋላ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውጪ ፡ አይዛወሩም ።

ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ወጣ ፡ ብለው ፡ የሚገኙ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ዳኞች ፡ ወንድሞቻቸው ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡ መዛወር ፡ ያጋጠማቸው ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ዳኞች ፡ ከተማይቱ ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ዳኞች ፡ ይበልጥ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ ሥፍራዎች ፡ ተመድበው ፡ በብዙ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያገለገሉ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ተጠግተው ፡ መሥራታቸውን ፡ እንደማዕረግና ፡ ደረጃ ፡ መሻሻል ፡ ይቆጥሩታል ። ከእንደእነዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ዳኞች ፡ አብዛኞቹ ፡ የኋላ ፡ ኋላ ፡ ከፍተኛ ፡ ደመወዝና ፡ የትምህርት ፡ ዕድል ፡ ወደሚገኝበት ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ለመዛወር ፡ በተስፋ ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ።

በጣም ፡ ሩቅ ፡ በሆኑ ፡ የገጠር ፡ ሥፍራዎች ፡ የሚገኙ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዳኞች ፡ ከትልልቅ ፡ ከተማዎች ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ እንዲሠሩ ፡ የተደረገ ፡ ሲሆን ፡ ለውጥም፡ ሲያገኙ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በዚያው ፡ በተወለዱበት ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ እንደወረዳ ፡ ዳኞችና ፡ ዝቅተኛ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ሆነው ፡ ይዛወራሉ ።

ስለዚህ ፡ የወረዳ ፡ ዳኞች ፡ በለመዱት ፡ አካባቢ ፡ እንዲሠሩ ፡ የተደረገ ፡ ስለሆነ ፡ ገጠር፣ ባሉትና ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ዳኞች ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ የሥፍራ ፡ መለዋወጥ ፡ ያለ ፡ አይመስልም ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ በከተማ ፡ ያለ ፡ የሥራ ቦታ ፡ ባላገር ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ የሥራ ፡ ቦታ ፡ ይበልጥ ፡ ተፈላጊ ፡ በመሆኑ ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ክፍት ፡ የሥራ ፡ ቦታዎች ፡ ስለማይገኙ ፡ ያሉትን ፡ ስፍራዎች ፡ ለመያዝ ፡ ውድድሩ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ከተጠየቁት ፡ የአውራጃ ፡ ግዛት ፡ ዳኞች ፡ ከአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ የሚያንሱት ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ ከመሆናቸው ፡ በፊት ፡ የወረዳ ፡ ዳኞች ፡ እንደነበሩ ፡ ታውቋል ። በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ መሾም ፡ በከፍተኛ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የወረዳ ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ ለመሾም ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ ለተሰጠ ፡ መልካም ፡ አገልግሎት ፡ የሚከፈል ፡ ዋጋ ፡ ነው ።

አንድ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ሕይወቱን ፡ ያሳለፈው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ ውስጥ ፡ በመቶ ፡ አለቃነት ፡ ነበር ። የጡረታ ፡ ዕድሜው ፡ ሲደርስ ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ አስተዳደር ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሾም ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሐሳብ ፡ አቀረበ ፤ ፍርድ ፡ ሚኒስቴርም ፡ ሰውዬውን ፡ ፈተና ፡ ሳይሰጥ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ አድርጎ ፡ ሾመው ፤ ምክንያቱም ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ እንዳይሾም ፡ ክብሩ ፡ ስለሚቀንስና ፡ ደመወዙም ፡ ከቀድሞ ፡ ዝቅ ፡ የሚል፣ ስለሆነ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ኤርትራ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ ስትቀላቀል ፡ የኤርትራ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ ብዙዎቹ ፡ የዚህ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ በአውራጃና ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ዳኞች ፡ ሆነው ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ። ከጣልያን ፡ ወረራ ፡ በፊት ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ፡ቤት፡ ዳኝነት ፡ ደረጃ፡የነበረውና፣ የጦርነቱንም ፡ ጊዜ ፡ በአርበኝነት ፡ ያሳለፈ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ባለሟል ፡ ሆኖ ፡ ያገለገለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከሦስት ፡ ዓመት በፊት ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ ተሹሟል ።

በአዲስ ፡ አበባና ፡ በአሥመራ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውጪ ፡ የመጡ ፡ ብዙ ፡ ዳኞች ፡ ይገኛሉ ። ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚሠሩና ፡ ለዳኝነት ፡ ሥራም ፡ አስፈላጊ ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በብዛት ፡ የተጠራቀሙ ፡ እነዚህ ፡ ከተሞች ፡ ውስጥ ፡ በመሆኑ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በአነስተኛይቱ ፡ በሐረር ፡ ከተማ፣ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ዳኞች ፡ አሁን ፡ ከያዙት ፡ ሥፍራ ፡ ለመድረስ ፡ የበቁት ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ በባላገር ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በሰጣቸው ፡ ቦታዎች ፡ በማገልገል ፡ በደረጃ ፡ ራሳቸውን ፡ እያሻሻሉ ፡ ከሔዱ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

እንደደንብ ፡ ሆኖ ፡ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በአሥመራ ፡ የሚገኙት ፡ ዳኞች ፡ ለዳኝነት ፡ ከተሾሙ ፡ በኋላ ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ገጠር ፡ በፍጹም ፡ ተዛውረው ፡ አያውቁም፤ በጠቅላላው ፡ በገጠርና ፡ በከተማ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የዳኞች ፡ መለዋወጥ ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ይመስላል ። ስለዚህ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞችም ፡ እንደ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ሹመታቸውን ፡ ያገኙት ፡ ለመንግሥት ፡ በቅንነትና ፡ በታማኝነት ፡ ለሰጡት ፡ አገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ስለአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት፣ ዳኞች ፡ ሌላ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የመንግሥት ፡ ወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለፍርድ፣ ሚኒስቴር ፡ የሚያቀርበው ፡ ድጋፌ ፡ አሳብ ፡ ዕውቀታቸውንና ፡ የሕግ ፡ ችሎታቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚቆጠር ፡ ለብዙዎቹ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ የሚሰጠው ፡ ፈተና ፡ ለነሱ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም ።

የዳኝነት ፡ ቦታዎችን ፡ ስለ ፡ መሙላት ፡ ያለው ፡ ችግር ።

በኢትዮጵያ ፡ ዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ በግምት ፡ ፩ሺ፭፻ ፡ የሚሆኑ ፡ ዳኞች ፡ ይገኛሉ ። እላይ ፡ በዳኞች ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ግልፅ ፡ ሆኖ ፡ እንዳገኘ ነው ፡ እነዚህን ፡ የዳኝነት ፡ ቦታዎች ፡ ለመሙላት ፡ አስፈላጊ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ በቂ ዳኞች ፡ የሉም ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከቤተክህነቱ ፡ ትምህርት ፡ በላይ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ዳኞች ፡ ለመሆን ፡ አይፈልጉም ።

ያሁኑ ፡ ሁኔታ ፡ ሊፈጠር ፡ የቻለው ፡ ምናልባት ፡ በሁለቱም ፡ ምክንያቶች ፡ የተ ነሣ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ኢትዮጵያ ፡ በደንብ ፡ የተማሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሏ ትም ። አንድ ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ በሚደረስበት ፡ ጊዜ ፡ ዳኛ ፡ የመሆን ፡ ነገር ፡ በልዩ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ፈጽሞ ፡ አይታሰብም ።

በጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የሚገኝ ፡ የአንድ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ደመወዝ ፡ በወር ፡ ፹ ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ ነው ። አዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ በኑሮ ፡ ውድነት የተነሣ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ እስከ ፡ ፻፳[184] ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ። ምንም፡ እንኳን ፡ ይህ ፡ ከማዕከላዊ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የዓመት ፡ ገቢ ፡ የበለጠ ፡ ቢሆንም ፡ ከአን ደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አስተማሪ ፡ ከጋራዥ ፡ ሠራተኛ ፡ ከባንክ ፡ ቤት ፡ ጸሐ ፊና ፡ ከአንድ ፡ ፋብሪካ ፡ ሠራተኛ ፡ ደመወዝ ፡ እንኳን ፡ ያነሰ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ እላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሞያዎች ፡ የበለጠ ፡ ኃላፊነትና ፡ ክብር ፡ ቢኖረውም ፤ ለዳኞች ፡ የሚከፈላቸው ፡ ደመወዝ ፡ የገቢ ያቸውን ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ሰዎች ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ እንዲ መርጡ ፡ አያደርጋቸውም ።

ከአንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ትምህርታቸውን ፡ አጠናቀው ፡ የሚ ወጡ ፡ ወጣቶች ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ እንዳይፈልጉ ፡ ከሚያደርጓቸው ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ደግሞ ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ዳኞች ፡ ሆነው ፡ የተመረጡት ፡ ሰዎች ፡ ከዚያው ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ በጸሐፊነት ፡ ያገለግሉ ፡ የነበሩና ፡ ምንም ፡ ደንበኛ ፡ ትምህርት ፡ ያላገኙ ፡ ሰዎች ፡ መሆናቸው ፡ ነው ። በእርግጥ ፡ አንድ ፡ የስምንተኛ ፡ ክፍል ፡ ያጠናቀቀ ፡ ሰው ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ አነስተኛ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ የሚሠሩትን ፡ ሥራ ፡ መምረጥ ፡ ለኅብረ ፡ ሰቡ ፡ አስፈላጊ ፡ አይሆንም ፡ የሚል ፡ አስተ ያየት ፡ አላቸው ፡ ።

በደንብ ፡ የተዘጋጀ ፡ የሕግ ፡ ሞያ ፡ ባለመኖሩና ፡ ጠበቆችም ፡ ዳኞች ፡ ለመሆን ፡ ስለማይፈልጉ ፡ በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ የዳኝነት ፡ ክፍት ፡ ቦታዎች ለመሙላት ፡ በፍርድ ፡ ሥራ ፡ በቂ ፡ ልምድ ፡ ባላቸው ፡ ሠራተኞች ፡ ላይ ፡ ዕምነትን ፡ መጣል ፡ ግዴታ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ከተጠየቁት ፡ ፴፪ ፡ ዳኞች ፡ መካከል ፡ ዳኞች ፡ ከመ ሆናቸው ፡ በፊት ፡ ጠበቆች ፡ የነበሩት ፡ ሁለት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

ጠበቆችን ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዳኞች ፡ እንዲሆኑ ፡ ማድረግ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞችን ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ያደርገዋል ። ዳኞች ፡ ከጠቅላላው፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ ጋር ፡ የረጅም ፡ ጊዜ ፡ መተሳሰር ፡ ያላቸው ፡ በመሆኑ ፡ ስለቅ ንጅቱ ፡ ሊሰጡት ፡ የማይችሉትን ፡ ነፃ ፡ አስተያየትም ፡ ለማግኘትም ፡ ያስችላል ።

184. ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ሠራተኞች ፡ ጋር ፡ ከተደረገ ፡ ውይይት ፡ የተገኘ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ጠበቆች ፡ ከሚያገኙት ፡ ገቢያቸው ፡ እንዲቀነስባቸው ፡ አይፈልጉም ። (ዳኞች ፡ የሚሆኑ ፡ አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ በገንዘብ ፡ በኩል ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ናቸው) ።

ስለዚህ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውጭ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ በደመወዝ ፡ በኩል ፡ ለመሳብ ፡ ስለማይችልና ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የሚገኙበት ፡ ከፍርድ ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ በሞላ ፡ ጐደል ፡ ነፃ ፡ የሆነ ፡ ሞያ ፡ ባለመኖሩ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን ፡ የሚሠሩት ፡ መደበኛ ፡ ትምህርት ፡ የሌላቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በፍ ርድ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ በቂ ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ስለሥራቸው ፡ አንድ ፡ የቢሮ ፡ ሠራተኛ ፡ ስለሥራው ፡ ከሚያስበው ፡ የተሻለ ፡ የማያስቡ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

## ዳኞች ፡ በኅብረ ፡ ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ስላላቸው ፡ ተግባር ።

ለዳኞች ፡ ከቀረቡት ፡ ጥያቄዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ ስለሥራቸው ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ ለማወቅ ፡ የታቀዱ ፡ ነበሩ ። ዳኞች ፡ በኅብረ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ ያላቸው ፡ "ተግባር" ፡ ምን ፡ እንደሆነና ፡ ባለፉት ፡ ጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥም ፡ በተለይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የተጻፉ ፡ ሕጎች ፡ ታውጀው ፡ ከወጡ ፡ ወዲህ ፡ በዳ ኞች ፡ ተግባር ፡ ረገድ ፡ ለውጥ ፡ ተደርጓል ፡ ብለው ፡ ያስቡ ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ ሙከራ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ። ዳኞች ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኅብረ ፡ ሰቡ ፡ ያላቸውን ፡ አቋም ፡ ማለት ፡ በደረጃ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥና ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ስላላቸው ፡ ክብርና ፡ ክርክሮችን ፡ ለመወሰን ፡ ባላቸው ፡ ሥልጣን ፡ ረገድ ፡ ከአሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ መቶ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኢጣልያን ፡ ወረራ ፡ ድረስ ፡ ከነበረው ፡ ከ"ጥንቱ"፡ ጊዜ ፡ ዳኛ ፡ አቋም ፡ ጋር ፡ እንዲያወዳድሩ ፡ የሚያደርጉ ፡ ጥያቄዎችም ፡ ቀርበው ፡ ነበር ።

ሕዝቡ ፡ ስለዳኞች ፡ ያለውን ፡ አስተያየትና ፡ ዝንባሌ ፡ ራሳቸው ፡ ዳኞቹ ፡ ያው ቁታል ። በትክክል ፡ የማይፈርዱና ፡ ስለ ፡ ሕጉም ፡ ምንም ፡ የማያውቁ ፡ ናቸው ፡ እየተ ባሉ ፡ መታማታቸውንም ፡ በደንብ ፡ ያውቃሉ ። እነሱ ፡ ግን ፡ ከተሚጋቾች ፡ ጉቦ ፡ እየተቀበሉ ፡ ኑሮአቸውን ፡ በማሟላት ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ያስገደዳቸው ፡ የኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ የሥራቸውን ፡ ታላቅነት ፡ አለመረዳት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ በፍርድ ፡ ጉድለት ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ኃላፊነት ፡ ከራሳቸው ፡ ያወርዳሉ ።

ዳኞች ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ስለታማኝነታቸው ፡ የሚያስቡትን ፡ ከማወቃቸውም ፡ ሌላ ፡ በቅርቡ ፡ የታወጁት ፡ ሕጎች ፡ በሞያቸው ፡ ብቁ ፡ ሆነው ፡ ያለመገኘትን ፡ ስሜት፡ አሳድሮባቸዋል ። የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ አዲስ ፡ የወጡትን ፡ ሕጎች ፡ ለማወ ቅና ፡ በትክክል ፡ እየተረጐሙ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚያቅታቸው ፡ መሆኑን ፡ ያውቃሉ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሳሉ ፡ በተለይም ፡ በሚያውቁት ፡ ሕግ ፡ እንደምንም ፡ አድርገው ፡ ለመሥራት ፡ ቢችሉም ፤ አዲስ ፡ የወጡትን ፡ የተወሳ ሰቡ ፡ ሕጎች ፡ በደንብ ፡ አውቀው ፡ የማያውቁትንና ፡ በሙሉ ፡ ልብ ፡ የማይቀበሉትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ እየተከተሉ ፡ እንዲሠሩ ፡ ከያዙት ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ የሚጠበቅ ፡ ነገር ፡ ነው ።

እላይ ፡ እንዳየነው ፤ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ዳኞች ፡ ከፊታቸው ፡ ለሚቀር ቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ቆራጭ ፡ ፈላጮች ፡ እነሱ ፡ ነበሩ ። አሁን ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ባለጉዳይ ፡ ሊጠቅሳቸው ፡ በሚችል ፡ በደንብ ፡ በተጻፉ ፡ ሕጎች ፡ መመራት ፡ አለባቸው ። እነሆ ፡ ዳኛ ፡ ድሮ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጌታ ፡ በመሆን ፡ የነበረውን ፡ ነፃነት ፡ አሁን በመንፈጉ ፡ ቀድሞ ፡ የነበረው ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ኃይሉን ፡ አጥቷል ፤ በዚህም ፡ የተነሳ ፡ ክብሩ ፡ እንደተቀነሰ ፡ ይሰማዋል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የዳኛ ፡ ኃይል ፡ ከችሎቱ ፡ እንደማ

ያልፍ ፡ ሁሉም ፡ ያውቀዋል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ ዳኞች ፡ በቀበሌው ፡ የደረጃ ፡ ባለመሬቶች ፡ አይደሉም ። ከአካባቢው ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ በጥቅም ፡ እንዳይተሳሰሩ ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ እየተዘዋወሩ ፡ እንዲሠሩ ፡ ይደረጋል ። ለምሳሌ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙ ፡ ዳኞች ፡ በሚዳኙባቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አካባቢ ፡ አይኖሩም ። በተጨማሪም ፡ በጥብቅ ፡ የተሳሰሩ ፡ ግለ ፡ ሰዎች ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሊደረጁ ፡ አይችሉም ። ስለዚህ ፡ ዳኛው ፡ በአካባቢው ፡ ከሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ መተሳሰር ፡ ስለሌለው ፡ ከሌላ ፡ ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ የተለየ ፡ አይደለም ፡ ማለት፡ ነው ።

አብዛኞቹ ፡ ዳኞች ፡ ድሮ ፡ ከነበራቸው ፡ ደረጃ ፡ ክብርና ፡ ሥልጣን ፡ ዝቅ ፡ በማለታቸው ፡ ሥራቸውን ፡ እንደገንዘብ ፡ ማግኛ ፡ ዘዴ ፡ ብቻ ፡ ይቆጥሩታል ።

በዳኞቹ ፡ በኩል ፡ በሥራቸው ፡ ብቁ ፡ ሆነው ፡ ያለመገኘትን ፡ ስሜት ፡ ሊያሳድርባቸው ፡ የቻለው ፡ ሌላው ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ የሚያደርገው ፡ ቁጥጥር ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ዳኞቹ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ላይ ፡ መጠነኛ ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ቢኖራቸውም ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሬጅስትራሮችና ፡ ተላላኪዎች ፡ እንኳን ፡ ዋናው ፡ ታዛዥነታቸው ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነው ። አንድ ፡ ባለጉዳይ ፡ በአንድ ፡ ዳኛ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ካልተስማማው ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አቤቱታውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ፡ ይህም ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚደረግ ፡ ነው ። በዚሁም ፡ አቤቱታ ፡ መሠረት ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወደ ፡ ተጠቀሰው ፡ ዳኛ ፡ ተቆጣጣሪዎቹን ፡ ልኮ ፡ የፍርዱን ፡ መዝገብ ፡ መርምረው ፡ ዳኛው ፡ ሕጉን ፡ እንዴት ፡ እንደተረጐመው ፡ በመመልከት ፡ ስለፍርዱ ፡ ትክክለኛነት ፡ ሪፖርት ፡ እንዲያቀርቡለት ፡ ያደርጋል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ሚኒስቴሩ ፡ የዳኛውን ፡ ፍርድ፡ ለመገልበጥ ፡ ባይችልም ፡ የተቆጣጣሪውን ፡ ራፖር ፡ በዳኛው ፡ የሥራ ፡ ዕድገትና ፡ ያለውንም ፡ ሥፍራ ፡ ይዞ ፡ በመቆየት ፡ ባለው ፡ ዕድል ፡ ላይ ፡ ውጤት ፡ ይኖረዋል ። አንድ ፡ ዳኛ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ሲናገሩ ፡ ተቆጣጣሪው ፡ ባልታወቀ ፡ ጊዜ ፡ መጥቶ ፡ አንድ ፡ ፋይል ፡ እንዲቀርብለት ፡ ይጠይቅና ፡ ካነበበ ፡ በኋላ ፡ ምርመራው ፡ እንዲደረግ ፡ ስለተደረገበት ፡ ምክንያት ፡ ሳይናገር ፡ ይመለሳል ፤ ሲሉ ፡ ገልጸዋል ። ስለዚህ ፡ ጥንት ፡ ዳኛ ፡ መሆን ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደነበረ ፡ የሚያስታውስ ፡ ወይም ፡ ወሰን ፡ ስላልነበረው ፡ የዳኛ ፡ ሥልጣን ፡ የሰማ ፡ የዘመኑ ፡ ዳኛ ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ በጠንካራ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ ጥንት ፡ የነበረው ፡ ሥልጣኑ ፡ የተቀነሰበት ፡ ይመስለዋል ። ዳኛው ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ድሮ ፡ ከሕዝቡ ፡ የነበረውን ፡ ክብር ፡ ሲያጣ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ አዲስ ፡ የታወጁትን ፡ ሕጎች ፡ ባለማወቁ ፡ የቀረቡለትን ፡ ጉዳዮች ፡ ለመወሰን ፡ ብቁ ፡ ሆኖ ፡ አልተገኘም ። የፍርድ ፡ ሚኒስቴርም ፡ የሚያደርገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ስለሚቆጣጠረው ፡ እንደማንኛውም ፡ ሌላ ፡ የቢሮ ፡ ሠራተኛ ፡ የመቆጠር ፡ ስሜት ፡ አሳድሮበታል ።

## ዳኞች ፡ በችሎት ፡ ላይ ።

ከተጠየቁት ፡ የወረዳ ፡ ዳኞች ፡ አብዛኞቹ ፡ በቀን ፡ ሃያ ፡ ክሶችን ፡ የሚሰሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጸዋል ። አብዛኛውም ፡ ጊዜ ፡ ችሎት ፡ የሚቀመጡት ፡ ከጧቱ ፡ ፫ ፡ ሰዓት ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ቀኑ ፡ ፲ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ የሚሰሙ ፡ ክሶች ፡ ካሉ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ለትንሽ ፡ ሰዓቶች ፡ ያህል ፡ ተቀምጠው ፡ ይዳኛሉ ። ዳኞች ፡ በቀን ፡ ሃያ ፡ ክሶችን ፡ ይሰማሉ ፡ ማለት ፡ በመጨረሻም ፡ ይህንኑ ፡ ያህል ፡ ጉዳይ ፡ ይወስናሉ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። እንደተመለከትነው ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሰዓት ፡ በፊት የሚወስነው ፡ ከአምስት ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ የሚደርሱ ፡ ክርክሮችን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ ግን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ ይተላለፋሉ ።

ከወረዳ ፡ ዳኞች ፡ ይልቅ ፡ በቀን ፡ አነስተኛ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚሰሙት ፡ የአውራጃ ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ። ይኽ ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ምናልባት ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ደረጃ፡ የሚደርሱት ፡ ጉዳዮች ፡ ከፍተኛ ፡ የገንዘብ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ክርክር ፡ ስለሆኑና ፡ ነገሩ ፡ የሚመለከታቸውን ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ እንዲያስቡበት ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ይሆናል ።

ክርክሩን ፡ የሚመሩት ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ። ጭብጡን ፡ እንዲያወጡ ፡ በተሚጋቾች ፡ ወይም ፡ በጠበቆቻቸው ፡ ላይ ፡ አይተማመኑም ፡ አብዛኛውንም ፡ ጊዜ ፡ ለምስክሮችና ፡ ለተሚጋቾቹ ፡ ጥያቄ ፡ የሚያቀርቡት ፡ ራሳቸው ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ። የምስክር ፡ ቃል ፡ በጽሑፍ ፡ በማስፈርም ፡ ዳኞች ፡ እንደ ፡ ቃል ፡ ተቀባይ ፡ ሆነው ፡ ይሠራሉ ። በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ችሎት ፡ የሚሰየሙት ፡ ዳኞች ፡ ሶስት ፡ ናቸው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ እነዚህ ፡ ዳኞች ፡ አንድን ፡ ክርክር ፡ የሚሰሙት ፡ በአንድነት ፡ ሆነው ፡ መሆን ፡ ቢገባውም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሶስቱም ፡ ዳኞች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሶስት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮችን ፡ ይሰማሉ ። እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ በእርግጥ ፡ በችሎቱ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ግርግር ፡ እንደሚፈጥር ፡ አይጠረጠርም ።

ዳኞች ፡ የነገረተኞቹን ፡ ቁጥር ፡ ለመቀነስ ፡ አንዳችም ፡ ጥረት ፡ የሚያደርጉ ፡ አይመስልም ። እነሱ ፡ የሚያዩት ፡ ከአንድ ፡ በኩል ፡ የተከመሩትን ፡ ፋይሎች ፡ እያነሱ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ በመከመር ፡ በየቀኑ ፡ በያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉትን ፡ አነስተኛ ፡ መሻሻል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ምናልባትም ፡ የዚህ ፡ አስተሳሰብ ፡ መነሾው ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ምስክሮቻቸውንና ፡ ማስረጃዎቻቸውን ፡ በሚገባ ፡ አሟልተው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ፍ/ ቤት ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ለማድረግና ፡ ተሚጋቾችም ፡ ክርክራቸውን ፡ በተቀነባበረ ፡ ሁኔታ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ እንዳለባቸው ፡ በማግባባቱ ፡ ረገድ ፡ የሚፈጠረው ፡ ችግር ፡ ነው ።

## <u>ዳኞች ፡ ስለጠበቆች ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፤</u>

ከተጠየቁት ፡ ዳኞች ፡ አብዛኞቹ ፡ ጠበቆች ፡ ከአዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ ስላልተለማመዱ ፡ ሕጉን ፡ በመተርጎምና ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ረገድ ፡ አጥጋቢ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ አይችሉም ፤ የሚል ፡ አስተያየት ፡ አላቸው ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በክርክራቸው ፡ ውስጥ ፡ አግባብ ፡ የሌላቸውን ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ይጠቅሳሉ ፤ ይባላል ። በተጨማሪም ፡ ጠበቆች ፡ በጠቅላላው ፡ የነገሩን ፡ ጭብጦች ፡ አስተካክለው ፡ አያቀርቡም ፡ የሚል ፡ የዳኞች ፡ አስተያየት ፡ አለ ።

ለነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጉድለቶች ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ጠበቆች ፡ ደንበኛ ፡ ትምህርት ፡ የሌላቸው ፡ በመሆናቸውና ፡ የሚከራከሩለትንም ፡ ወገን ፡ ጉዳይ ፡ ፍሬ፡ ነገሩንና ፡ ክርክሩን ፡ በትክክል ፡ በማቅረብ ፡ ፈንታ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ የመርታት ፡ ጉጉት ፡ ስለሚያድርባቸው ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ዳኞች ፡ አስተያየታቸውን ፡ ሰጥተዋል ።

በተጨማሪም ፡ ዳኞች ፡ እንደሚሉት ፡ ጠበቆች ፡ ስለጉዳዩ ፡ ከደንበኞቻቸው ፡ ጋር ፡ ካለመመካከራቸውም ፡ በላይ ፡ አብዛኛውንም ፡ ጊዜ ፡ ክርክሩ ፡ በእርቅ ፡ ወይም በሌላ ፡ መልክ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ እንዲያልቅ ፡ የሚያስችሉትን ፡ አንዳንድ ፡ አስፈላጊ ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ከደንበኞቻቸው ፡ ይደብቃሉ ። እነዚሁም ፡ ዳኞች ፡ ጠበቆቹ፡ ለደንበኞቻቸው ፡ አንዳችም ፡ ኃላፊነት ፡ የማይሰማቸውና ፡ ብዙዎችም ፡ ነገረተኞች ፡ መረታት ፡ የሚደርስባቸው ፡ በጠበቆቻቸው ፡ ገንዘብ ፡ መውደድ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ይናገራሉ ።

ዳኞች ፣ ጠበቆች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በሚያሳዩት ፡ ጠባይ ፡ ላይ ፡ የበላይ ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ ተግባር ፡ እንዳላቸው ፡ አድርገው ፡ ይገምታሉ ። የሕግ ፡ ችሎታቸው ፡ ከጠበቆቹ ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ ከመናገራቸውም ፡ በላይ ፡ በሕግ ፡ ሞያ ፡ የተሰማሩት ፡ ሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ ያልታረሙና ፡ ኃላፊነታቸውንም ፡ የማያውቁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማለት ፡ የገበያ ፡ ቦታ ፡ አለመሆኑ ፡ ተደጋግሞ ፡ እንዲነገራቸው ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ መሆናቸ ውንም ፡ ጭምር ፡ ይናገራሉ ።

እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አስተያየት ፡ የአብዛኞዎቹ ፡ ዳኞች ፡ አስተያየት ፡ ቢሆ ንም ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ባሳየው ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ቅጣት ፡ መወሰናቸውን ፡ የተናገሩ ፡ ዳኞች ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ሆኖም ፡ ብዙ ፡ ዳኞች ፡ ጠበቆች ከመልካም ፡ ጠባይ ፡ ውጭ ፡ ሲሄዱ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የሚሰጣቸው ፡ መሆኑን ፡ ገልጸዋል ።

በጠባይ ፡ ጉድለት ፡ የዲሲፕሊን ፡ እርምጃ ፡ በጠበቆች ፡ ላይ ፡ የሚወሰደው ፡ አን ዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ክርክሩን ፡ የሚመራው ፡ ራሱ ፡ ዳኛው ፡ በመሆኑ ፡ ይሆ ናል ። ተሚጋቾችንና ፡ ምስክሮችን ፡ የሚጠይቀው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ዳኛው ፡ ሲሆን ፤ ጥያቄም ፡ በማይጠየቅበት ፡ ጊዜም ፡ ጥያቄው ፡ እንዴት ፡ እንደሚጠየቅ ፡ ለጠ በቃው ፡ የሚነግረው ፡ እሱው ፡ ነው ። ዳኞች ፡ የነገረተኞች ፡ በችሎት ፡ ውስጥ ፡ እርስ፡ በርስ ፡ መወዛገብ ፡ የሚያሰለቻቸው ፡ በመሆኑ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ያቋርጧቸዋል ። ስለ ዚህ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ብዙ ፡ በመናገር ፡ ራሱን ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ ለማስገባት ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ። በዳኞች ፡ አስተያየት ፡ ጠበቆች ፡ ብዙ ፡ በመለፍለፍና፡ በመቀባጠር ፡ ተሚጋቾች ፡ ሁሉ ፡ የጠበቃ ፡ እርዳታ ፡ እንደሚያስፈልጋቸው ፡ በማሳ መን ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ትከሻ ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። የሚያሳዝነው ፡ ነገር ፡ በችሎት ፡ ጊዜ ፡ በዳኞችና ፡ በጠበቆች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ትምህርት ፡ ሊያ ገኝ ፡ የሚችልበት ፡ የኃሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ አለመኖሩ ፡ ነው ። ባጭሩ ፡ ዳኞችና ፡ ጠበ ቆች ፡ በኅብረት ፡ አይሠሩም ።

## ዳኞችና ፡ ሌሎች ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ።

ዳኞች ፡ የሚያነቧቸው ፡ የአቤቱታ ፡ ማመልከቻዎች ፡ በግምት ፡ ሁሉም ፡ የሚጻ ፉት ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሕጉን ፡ ጠን ቅቀው ፡ ባያውቁም ፡ ለተሚጋቾች ፡ ጠቃሚ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጡ ፡ መሆናቸውን ፡ ሁሉም ፡ ዳኞች ፡ ተስማምተውበታል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ ዳኞች ፡ የፍርድ ፡ ቤቶቻቸውን ፡ ሠራተኞች ፡ ለመቆጣጠር ፡ ቢችሉም ፡ ሬጅስትራሮችንና ፡ የመዝገብ ፡ ቤት ፡ ፀሐፊዎችን ፡ በመቆጣጠር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አያጠፉም ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሥራቸው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ የሚነግራቸው ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለሆነ ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ ከዳኞች ፡ ቁጥጥር ፡ ውጭ ፡ የሚ ሠሩ ፡ ናቸው ።

በፋይል ፡ አከፋፈትና ፡ ባለጉዳዮችን ፡ በማስተናበር ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ የሚገቡ ፡ ዳኞች ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። እንዳንዱ ፡ ሠራተኛ ፡ የራሱን ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ፡ ለብቻው ፡ ይተዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ ቅሬታ ፡ የሚሰማው ፡ ማን ኛውም ፡ ባለጉዳይ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሄዶ ፡ አቤቱታውን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሠራተኛ ፡ በግል ፡ ኃላፊነቱ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለሆነ ፡ በዳ ኞችና ፡ በሌሎቹ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ መካከል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥርጣሬና ፡ ያለ መተማመን ፡ ይታያል ።

## ዳኞችና ፡ ተሚጋቾች ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ ከተጠየቁት ፡ ዳኞች ፡ ብዙዎቹ ፡ ለነገረተኞች ፡ የሚያዝኑ ፡ መሆናቸውን ፡ ቢገልጹም ፡ በሪፖርቱ ፡ የተገኘው ፡ የፍትሕ ፡ መዛባት ፡ እንደሚያሳየው ፡ ብዙ ፡ ዳኞች ፡ ተማጋቾችን ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ የሚያጉላሉ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ።

እንደዳኞቹ ፡ አስተሳሰብ ፡ ተሚጋቾች ፡ በክርክራቸው ፡ ላይ ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ እንዲጠቀስላቸው ፡ ይፈልጋሉ ። ተሚጋቾች ፡ የባህል ፡ ደንቦችን ፡ ጠቅሰው ፡ ይከራከሩ ፡ እንደሆን ፡ ቢጠየቁ ፡ ዳኞቹ ፡ የመገረም ፡ መልክ ፡ አሳይተዋል ። አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ በጽሑፍ ፡ ከወጡት ፡ ሕጎች ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ እንዲዳኙ ፡ ይፈልጋሉ ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ለአንዳንድ ፡ ዳኞች ፡ የክህዲነት ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ ሆኖ ፡ ተገኝቷል ። ይሁን ፡ እንጅ ፡ ተሚጋቾቹ ፡ ዳኞች ፡ ፊት ፡ የሚቀርቡት ፡ መጀመሪያ ፡ ከራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከጠበቆችና ፡ ከሬጅስትራሮች ፡ ጋር ፡ ከተነጋገሩ ፡ በኋላ ፡ ስለሆነ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ተሚጋቾች ፡ ስለሕጎቹ ፡ በእርግጥ ፡ ምን ፡ አስተያየት ፡ እንዳላቸው ፡ ሊያውቁ ፡ አይችሉም ።

## ዳኞችና ፡ ድሆች ፡ በወንጀል ፡ ተከሳሾች ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ የ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሀረት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፪ ፡ መሠረት ፡ በወንጀል ፡ የተከሰሱ ፡ ድሆች ፡ ሰዎች ፡ ነፃ ፡ የጠበቃ ፡ እርዳታ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ ቢኖራቸውም ፡ በወንጀል ፡ ከሚከሰሱት ፡ ድሆች ፡ ሰዎች ፡ በጣም ፡ ብዙዎቹ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቱን ፡ እርዳታ ፡ አያገኙም ።

አንቀጽ ፡ ፶፪ ፡ በሚገባ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳይውል ፡ ካደረጉት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ ዳኞች ፡ ስለወንጀል ፡ ክስ ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ለችግረኞች ፡ የወንጀል ፡ ተከሳሾች ፡ ነፃ ፡ የጠበቃ ፡ እርዳታ ፡ እንዲሰጡ ፡ የሚያዝዛቸው ፡ መሆኑን ፡ ቢያውቁም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የነሱ ፡ አስተያየት ፡ ማስረጃው ፡ ራሱ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ትክክለኛ ፡ ፍትሕን ፡ ሊያስገኝ ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ ነው ። አንድ ፡ ተከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ ባይኖረውም ፡ እውነቱን ፡ ለማግኘትና ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ለመቀበል ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ ጠበቃ ፡ ካለው ፡ ተከሳሽ ፡ እኩል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ።

ዳኛው ፡ የጠበቃ ፡ እርዳታን ፡ በሚያዝዝበት ፡ ጊዜ ፡ የሚከተለው ፡ የተወሰነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የለም ። ዳኛው ፡ ለዚህ ፡ ተግባር ፡ የሚመርጠው ፡ በአካባቢው ፡ የሚገኘውን ፡ ማንኛውንም ፡ ጠበቃ ፡ ነው ። ለሁሉም ፡ በወንጀል ፡ ለተከሰሱ ፡ ሰዎች ፡ ጠበቃ ፡ ለማቆም ፡ የማይቻል ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ዳኞች ፡ የጠበቃ ፡ እርዳታ ፡ ማዘዝ ፡ ያለባቸው ፡ በምን ፡ በምን ፡ ጊዜ ፡ እንደሆነ ፡ አያውቁም ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ግልጽ፡ የሆነ ፡ አመራር ፡ (ፖሊሲ) ፡ ቢኖር ፡ ለዳኞችና ፡ ለድሆች ፡ ተከሳሾች ፡ ታላቅ ፡ እርዳታ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

## ዳኞች ፡ ማጠቃለያ ።

ዳኞች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በሥራ ፡ የተገኘ ፡ ልምድ ፡ ያላቸውና ፡ አነስተኛ ፡ መደበኛ ፡ ትምህርት ፡ ያገኙ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። የተጻፉ ፡ ሕጎች ፡ ከመታወጃቸው ፡ በፊት ፡ የነዚህ ፡ ዳኞች ፡ ችሎታ ፡ በቂ ፡ የነበረ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። አሁን ፡ ግን ፡ ሕዝቡ ፡ ሕጎቹን ፡ በቀላሉ ፡ ለማግኘት ፡ በመቻሉና ፡ እነዚሁም ፡ ሕጎች ፡ የተወሳሰቡ ፡ በመሆናቸው ፡ ዳኞች ፡ በጣም ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ አክብሮት ፡ ከሕዝቡ ፡ ለማግኘት ፡ ትምህርት ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኗል ።

## ተሚጋቾች ።[185]

አንድ ፡ ሰው ፡ የፍርድን ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ የሚቋቋመው ፡ ባለው ፡ ሀብት ፡ መጠን ፡ ነው ። ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉ ፡ መሀይምናን ፡ ድሆችና ፡ ኃብታሞች ፡ ተሚጋቾች ፡ ወደ ፡ ዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚቀርቡት ፡ በተለያዩ ፡ መንገዶች ፡ ነው ። እነዚህም ፡ የተለያዩ ፡ አቀራረቦች ፡ በድሆች ፡ በጠበቆች ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎችና ፡ በሌሎች ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ላይ ፡ የተለያዩ ፡ የተሚጋች ፡ ዝንባሌዎችን ፡ ይፈጥራሉ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ከሳሽ ፡ ወይም ፡ ተከሳሽ ፡ ሆኖ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ መጀመሪያ ፡ የሚያደርገው ፡ የክስ ፡ ወይም ፡ የመከላከያ ፡ ማመልከቻውን ፡ አስጽፎ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሥርዐት ፡ እላይ ፡ ስለራፖር ፡ ፀሐፊዎች ፡ በሚናገረው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ተገልጧል ።

### ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉ ፡ ተሚጋቾች ።

ከተጠየቁት ፡ ተሚጋቾች ፡ ግማሽ ፡ የሚሆኑት ፡ የአቤቱታ ፡ ማመልከቻቸውን ፡ የሚያስጽፉት ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ። ይህም ፡ ክፍል ፡ መሀይምናንና ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉትን ፡ ተሚጋቾች ፡ ይጨምራል ። ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ከሚያውቁት ፡ ተሚጋቾች ፡ ፴፭ ፡ በመቶ ፡ (ሰላሳ ፡ አምስት ፡ በመቶው) ፡ የክስ ፡ ወይም የመከላከያ ፡ ማመልከቻውን ፡ የሚያስጽፉት ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ሲሆን ፡ ይኸንኑ ፡ ያህል ፡ የሚሆኑት ፡ ደግሞ ፡ አቤቱታቸውን ፡ የሚጽፉት ፡ ራሳቸው ፡ መሆናቸውን ፡ ከተደረገላቸው ፡ ጥያቄዎች ፡ ለመረዳት ፡ ችለናል ። ለቀሩት ፡ ግን ፡ ማመልከቻቸውን ፡ የሚጽፉላቸው ፡ ጠበቆች ፡ ናቸው ።

የራሳቸውን ፡ ማመልከቻ ፡ በሚጽፉ ፡ ተሚጋቾችና ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ በሚያስጽፉት ፡ መካከል ፡ በመሠረቱ ፡ እምብዛም ፡ ልዩነት ፡ የለም ። ሆኖም ፡ በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ከኋለኞቹ ፡ ይበልጥ ፡ ስለሕጉ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸው ፡ መሆኑን፡ ይናገራሉ ። ግን ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ስለሕግ ፡ ዕውቀት ፡ አለን ፡ ሲሉ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚፈጸም ፡ እናውቃለን ፡ ማለታቸው ፡ እንጅ ፡ ስለተጻፈው ፡ ሕግ ፡ ዕውቀት ፡ አለን ፡ ማለታቸው ፡ አይደለም ። እነዚህ ፡ ስለሕግ ፡ እናውቃለን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ያሳለፉ ፡ በመሆናቸው ፡ ያላቸውን ፡ ዕውቀት ፡ ያገኙት ፡ በልማድ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አሁንም ፡ አንድ ፡ ማመልከቻ ፡ በሚጻፍበት ፡ ጊዜ ፡ በሌላው ፡ ቦታ ፡ እንኳ ፡ ባይሆን ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ እንዲጠቀሱ ፡ አስፈላጊ ፡ ይሆናል፤ ካልተጠቀሱ ፡ ግን ፡ ማመልከቻው ፡ ተቀባይነት ፡ አይኖረውም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ዳኞችንና ፡ ሬጅስትራሩን ፡ ለማስደሰት ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመጥቀስ፡ ቢቻልም ፡ አግባብ ፡ ያለውን ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ገልጦ ፡ ማየት ፡ ወይም ፡ አንዳንድ ፡ የተለመዱ ፡ በቃል ፡ የተጠኑ ፡ ቁጥሮችን ፡ መጥቀስ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ መጠየቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ተሚጋቾች ፡ ከአሁን ፡ በፊት ፡ የገጠሟቸውን ፡ ክርክሮች ፡ ፋይሎች ፡ የሚያስቀምጡት ፡ ራሳቸው ፡ በመሆናቸውና ፡ አብዛኞቹም ፡ ተሚጋቾች ፡ ደጋግመው ፡ የሚያጋጥሟቸው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ጉዳዮች ፡ ስለሆኑ ፡ አንድ ፡ ተሚጋች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመ

185. በአዲስ ፡ አበባ ፡ በአውራጃና ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ ለሚከራከሩ ፡ ፻፰ ፡ ተከራካሪዎች ፡ ጥያቄ ፡ አቅርበን ፡ ነበር ።

መላለስ ፡ የነገሩን ፡ ሁኔታና ፡ አጻጻፍ ፡ ስለሚያጠና ፡ እየተደጋገመ ፡ በሚያጋጥመው ፡ ሙግት  የራፖር ፡ ጸሐፊ ፡ እርዳታ ፡ ሳያስፈልገው ፡ ይችላል ።

የራሳቸውን ፡ ማመልከቻዎች ፡ የሚጽፉት ፡ ተሚጋቾች ፡ ጉዳያቸውን ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ለመግፋት ፡ የሚያስችል ፡ የሕግ ፡ ችሎታ ፡ እንዳላቸው ፡ በኩራት ፡ ይናገራሉ ። አብዛኞዎቹ ፡ ሙግትን ፡ በጣም ፡ ይወዳሉ ። አንድ ፡ ልብስ ፡ ሰፊ ፡ ተሚጋች ፡ የራሱን ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ገዝቶ ፡ በትርፍ ፡ ጊዜው ፡ የሚያነብ ፡ መሆኑን ፡ ገልጿል ። አንድ ፡ ጡረታ ፡ የወጣ ፡ ወታደር ፡ ደግሞ ፡ ሙግት ፡ ለማዳመጥ ፡ ብቻ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሄድ ፡ መሆኑን ፡ አስረድቷል ።

ይሁን ፡ እንጅ ፡ የራሳቸውን ፡ ማመልከቻ ፡ የሚጽፉ ፡ ብዙ ፡ ተሚጋቾች ፡ ከሕጉ ፡ መጽሐፎች ፡ መኖር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ያለማወቃቸውን ፡ ገልጸዋል ። ቢሆንም፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በመመላለሳቸው ፡ ባገኙት ፡ የተወሰነ ፡ የሕግ ፡ ችሎታ ፡ እንኳን ፡ ከራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሚሻሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ያምኑበታል።

ስለሕጎቹ ፡ ሰምተው ፡ የማያውቁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የራሳቸውን ፡ ማመልከቻዎች ፡ የሚጽፉ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ አይጠፉም ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ማመልከቻውን ፡ ለማርቀቅ ፡ እርዳታ ፡ ሳያስፈልጋቸው ፡ አይቀርም ፡ ይሆናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በከፍተኛ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚገኙ ፡ በመሆናቸውና ፡ ምናልባት ፡ ከራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ የተለመደ ፡ ዕውቀት ፡ ይልቅ ፡ በራሳቸው ፡ የተፈጥሮ ፡ ችሎታ ፡ ላይ ፡ መመካት ፡ የተሻለ ፡ መስሎ ፡ ይታያቸው ፡ ይሆናል ።

የማንበብና ፡ የመጻፍ ፡ ችሎታ ፡ እያላቸው ፡ ማመልከቻቸውን ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከሚያስጽፉ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንዳቸውም ፡ ስለሕጉ ፡ የሚያውቁት ፡ ነገር፡ አለመኖሩን ፡ ከጥያቄው ፡ መልስ ፡ ለመረዳት ፡ ችለናል ። እንዲያውም ፡ በጣም ፡ በርከት ፡ ያሉት ፡ ስለተጻፉት ፡ ሕጎች ፡ መኖር ፡ እንኳን ፡ የሚያውቁ ፡ አለመሆናቸውን ፡ ገልጸዋል ። ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉ ፡ ሆነው ፡ ማመልከቻቸውን ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከሚያስጽፉት ፡ ሰዎች ፡ ግማሽ ፡ የሚሆኑት ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ በፍጹም ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ የማያውቁ ፡ ሲሆኑ ፡ ሌሎቹ ፡ አብዛኞቹ ፡ ደግሞ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የመጡ ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ማመልከቻቸውን ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሚያስጽፉት ፡ ተሚጋቾች ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ የራሳቸውን ፡ ማመልከቻ ፡ የሚጽፉት ፡ ሰዎች ፡ ከሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ እኩል ፡ የትምህርት ፡ ደረጃ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። በትምህርት ፡ የገፉ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ ማመልከቻቸውን ፡ ለማስጻፍ ፡ ወደ ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሚሄዱበት ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመመላለስ፡ ብቻ ፡ ሊገኝ ፡ ስለሚችለው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ባላቸው ፡ ዕውቀት ፡ ስለ ማይተማመኑ ፡ ይመስላል ።

እነዚህ ፡ ተሚጋቾች ፡ የሚያጋጥሙአቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ሙግቱ ፡ ሲጀመር ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ የአዋቂ ፡ እርዳታ ፡ አስፈልጎ ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ ራሱን ፡ እንዲችል ፡ የሚያደርግ ፡ ልዩነት ፡ የላቸውም ። ሁለቱም ፡ ክፍሎች ፡ የሚገኙባቸው ፡ ሙግቶች ፡ አስቸጋሪነታቸው ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ።

ከተጠየቁት ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ከሚችሉት ፡ ተሚጋቾች ፡ አንድ ፡ ሦስተኛ ፡ የሚሆኑት ፡ ማመልከቻቸውን ፡ የሚያስጽፉት ፡ በጠበቃዎች ፡ ሲሆን ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች፡ የሚገኙባቸው ፡ ሙግቶች ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ግምት ፡ የያዙ ፡ ናቸው ። ሙግታቸውን ፡ ሲጀምሩ ፡ ጠበቃ ፡ የቀጠሩና ፡ ጉዳያቸው ፡ ባውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ፡ ተሚጋቾች ፡ ቁጥራቸው ፡ ያልተመጣጠነ ፡ ነው ። ሌሎቹ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የደሞዝ ፡

ደረጃ ፡ ያላቸው ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉ ፡ ተሚጋቾች ፡ ገና ፡ ከመጀመሪያው ፡ ጠበቃ ፡ ከመቅጠራቸውም ፡ ሌላ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቶቹ ፡ አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተመላለሱ ፡ በመሆናቸው ፡ ባለፉት ፡ ጊዜያት ፡ ሙግታቸውን ፡ ሁሉ ፡ ያካሄዱት ፡ በጠበቃ ፡ እርዳታ ፡ እንደነበር ፡ ለማወቅ ፡ አያዳግትም ። ይህም ፡ ማለት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅምን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መምጣት ፡ የሚያዘወትሩና ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ ችሎታቸውም ፡ ዕውነተኛውን ፡ ነገር ፡ የሚያውቁ ፡ የተለዩ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የራሳቸውን ፡ ማመልከቻ ፡ ከሚጽፉት ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ የተሻለ ፡ ዕውቀት ፡ ቢኖራቸውም ፡ ለሙግታቸው ፡ ጠበቃ ፡ በመቅጠር ፡ አስቀድመው ፡ ጥንቃቄ ፡ መውሰድን ፡ ይመርጣሉ ።

ሌሎች ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉ ፡ በሙግታቸው ፡ መጀመሪያ ፡ ጠበቃ ፡ የሚቀጥሩ ፡ በቀላሉ ፡ የሚታወቁ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አሠራር ፡ ልምምድ፡ የሌላቸው ፡ ሆነው ፡ ይገኛሉ ። ስለ ፡ ሕጎቹ ፡ መኖር ፡ ከማወቃቸው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ የሚያውቁት ፡ ነገር ፡ አለመኖሩን ፡ አልካዱም ።

እነዚህን ፡ ከሙግታቸው ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ጠበቃ ፡ የሚቀጥሩትን ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ሰዎች ፡ ስናወዳድራቸው ፡ አንድ ፡ መደምደሚያ ፡ ላይ ፡ ልንደርስ ፡ እንችላለን ። ይኸውም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ጠበቃ ፡ የሚቀጥረው ፡ ስለሕጉ ፡ ዕውቀት ፡ ኖሮት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የዕውቀቱን ፡ ልክ ፡ ሲገምተው ፡ ካበለሙያው ፡ ጠበቃ ፡ ጋር ፡ የሚወዳደር ፡ አለመሆኑን ፡ የተረዳ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ሕግና ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ የማያውቅ ፡ መሆኑን ፡ የሚያምን ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ማስተዋል ፡ ያለብን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በመጀመሪያ ፡ ማመልከቻውን ፡ በጠበቃ ፡ ያላስጻፈ ፡ እንደሆነ ፡ በኋላ ፡ ጠበቃ ፡ አይቀጥርም ፡ ለማለት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ነው ። እንደእውነቱ ፡ ከሆነ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ተሚጋቾች ፡ በሙግታቸው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ እክል ፡ ካላጋጠማቸው ፡ በስተቀር ፡ ጠበቃ ፡ አይቀጥሩም ። ይህም ፡ መሀይምናንም ፡ ሆኑ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ የሚያደርጉት ፡ ነው ።

<u>መሃይምናን ፡ ተሚጋቾች ።</u>

ለመሃይምናን ፡ ተሚጋቾች ፡ ማመልከቻቸውን ፡ የሚጽፍላቸው ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊ ፡ ነው ። የቃል ፡ ጥያቄ ፡ ከተደረገላቸው ፡ መሃይምናን ፡ ተሚጋቾች ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ሦስተኛ ፡ ለሚሆኑት ፡ ማመልከቻቸውን ፡ የጻፉላቸው ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ናቸው ። ወደ ፡ አንድ ፡ ስድስተኛ ፡ ገደማ ፡ ለሚጠጉት ፡ ማመልከቻቸው ፡ በጠበቆች ፡ የተጻፉ ፡ ሲሆን ፤ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ ማመልከቻቸውን ፡ ጓደኞች ፡ ወይም ፤ በግል ፡ ከሳሽ ፡ የቀረቡ ፡ ጉዳዮች ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፤ ፖሊስ ፡ ጽፎላቸዋል ። የቃል ፡ ጥያቄ፡ ከተደረገላቸው ፡ ተሚጋቾች ፡ ውስጥ ፡ ብዙዎቹ ፡ ስለ ፡ ሕጎቹ ፡ ሰምተው ፡ የማያውቁ ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፡ መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ እንደሚችሉት ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዘውትረው ፡ ያልመጡ ፡ ናቸው ።

መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ አለመቻላቸው ፡ የሀብታቸው ፡ አነስተኛነትና ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ረገድ ፡ በቂ ፡ ልምድ ፡ የሌላቸው ፡ መሆኑ ፡ መጻፍና ፡ ማንበብ፡ ከሚችሉት ፡ ነገረተኞች ፡ ይልቅ ፡ እነዚህን ፡ በበለጠ ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ ጥለዋቸዋል ።

ሆኖም ፡ በሙግቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ የራፖር ፡ ጸሐፊ ፡ መኖር ፡ ይህንን ፡ ልዩነት ፡ ያስተካክላል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ መሃይምናኑ ፡ ተሚጋቾች ፡ ወደ ፡ ራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ዘንድ ፡ የሚሄዱት ፡ ያለፈቃዳቸው ፡ ቢሆንም ፤ ይህን ፡ ማድረጋቸው ፡ መጠ

ነኛ ፡ ጥቅምን ፡ አላስገኘላቸውም ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ። አንደኛ ፤ ራፖር ፡ ጸሐፊ ዎች ፡ ቢያንስ ፡ ከሕጉ ፡ ጋር ፡ በቅጡ ፡ ሳይለማመዱ ፡ የራሳቸውን ፡ ማመልከቻ ፡ ከሚ ጽፉት ፡ ነገረተኞች ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ አቤቱታ ፡ የመጻፍ ፡ ችሎታ ፡ አላቸው ። ሁለ ተኛ ፤ ራፖር ፡ ጸሐፊዎቹ ፡ ለተሟጋቾች ፡ በነጻ ፡ የሚለግሱት ፡ የሕግ ፡ ምክር ፡ ከጠበ ቆች ፡ ከሚገኘው ፡ እኩል ፡ ሲሆን ፤ በተለይም ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ከሚሟገቱት ፡ ማን በብና ፡ መጻፍ ፡ ከሚችሉት ፡ ነገረተኞች ፡ ሀሳብ ፡ በርግጥ ፡ የተሻለ ፡ ነው ።

ለመሃይሙም ፡ ሆነ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ለሚችለው ፡ ተሟጋች ፡ መርታቱን ፡ ወይም ፡ መረታቱን ፡ የሚወስነው ፡ ያለው ፡ የገንዘብ ፡ መጠን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ መኖር ፡ የተነሳ ፡ የሚፈጠረውንም ፡ የማስተካከል ፡ ተጽዕኖ ፡ የሚያጠፋው ፡ ይሆናል ። ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉት ፡ ነገረተኞች ፡ ከመሃይም ናኑ ፡ የበለጠ ፡ ገንዘብ ፡ ሳይኖራቸው ፡ ስለማይቀር ፡ ሀብትና ፡ የትምህርት ፡ ችሎታ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ የአሸናፊነትን ፡ ዕድል ፡ ያጐናጽፉቸዋል ። ገንዘብ ፤ ለአንድ ፡ ተሟ ጋች ፡ ከጸሐፊዎች ፡ ከዳኞችና ፡ ከፖሊሶች ፡ ጋር ፡ በመግባባት ፡ በነገሩ ፡ በጣም ፡ እን ዲገፋበት ፡ ኃይል ፡ ይሰጠዋል ።

## ተሟጋቾች ፡ ስለጠበቆች ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ።

አቤቱታቸውን ፡ ራሳቸው ፡ የጻፉ ፡ ተሟጋቾች ፡ በሙግታቸው ፡ መጨረሻ ፡ ላይ፡ ጠበቆችን ፡ አልቀጠሩም ። ማመልከቻቸውን ፡ በራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ ያስጻፉትም ፡ ማን በብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉት ፡ ነገረተኞችም ፡ ቢሆኑ ፡ ሙግታቸው ፡ ከተጀመረ ፡ በኋላ ፡ ጠበቆችን ፡ የመቅጠር ፡ ፍላጐት ፡ አላሳዩም ። ስለዚህም ፤ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚች ሉት ፡ ተሟጋቾች ፡ ጠበቃ ፡ ቢቀጥሩም ፡ እንኳን ፡ በሙግታቸው ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ነው ።

በመሃይምናን ፡ ነገረተኞች ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ሁኔታ ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ፈጽሞ ፡ የተለየ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ጉዳያቸው ፡ እንደተጀመረ ፡ ጠበቆችን ፡ የቀ ጠሩት ፡ መሃይምናን ፡ ተሟጋቾች ፡ ቁጥር ፡ አነስተኛ ፡ ቢሆን ፡ (በመቶ ፡ አሥራ ፡ ስድ ስቱ ፡ ብቻ) ፡ ከሁለት ፡ ሦስተኛ ፡ በላይ ፡ የሚሆኑት ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ በተደረገላቸው ፡ ጊዜ ፡ ባለጠበቆች ፡ ነበሩ ።

ሙግታቸውን ፡ ያለጠበቃ ፡ የጀመሩት ፡ መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ የሚችሉትና ፡ መሃ ይምናን ፡ ተሟጋቾች ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ ጉዳዩ ፡ የጠበቆችን ፡ እርዳታ ፡ በሚያስፈልግ ፡ አኳኋን ፡ የተወሳሰበ ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ ነው ። ለምን ፡ ጠበቆችን ፡ ሳትቀጥሩ ፡ ቀራችሁ ፡ ለሚለው ፡ ጥያቄ ፤ "ጉዳዩ ፡ ቀላል ፡ ነው ። እኔው ፡ እራሴ ፡ ልፈ ጽመው ፡ እችላለሁ ፤" የሚለው ፡ መልስ ፡ የበዛ ፡ ነበር ። መሃይምናን ፡ ተሟጋቾች ፡ ጠበቆችን ፡ ለመቅጠር ፡ ያላቸው ፡ ዝንባሌ ፡ ሙግታቸው ፡ ከተጋመሰ ፡ በኋላ ፡ መሆኑ፡ በሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። አንደኛ ፤ መሃይምናን ፡ ተሟ ጋቾች ፡ ችግር ፡ በተፈጠረ ፡ ጊዜ ፡ በሕግ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ ስለ ማይኖራቸውና ፤ ሁለተኛ ፤ የጉዳያቸውን ፡ የተወሳሰበ ፡ ሁኔታ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ በትክክል ፡ ለመገመት ፡ ያላቸው ፡ ችሎታ ፡ መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ ከሚችሉት ፡ ነገረተ ኞች ፡ ያነሰ ፡ በመሆኑ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። "ለራሴ ፡ ራሴ ፡ እበቃለሁ ፤" የሚለው ፡ ከመሃይምናን ፡ ተሟጋቾች ፡ የሚሰነዘረው ፡ አነጋገር ፡ ጭብጦቹን ፡ ጠለቅ ፡ ብሎ ፡ ካለመመልከት ፡ የመነጨ ፡ አስተሳሰብ ፡ መሆኑ ፡ የሚታመን ፡ ነው ።

ከተሟጋቾች ፡ በሙሉ ፡ አንድ ፡ ሦስተኛ ፡ የሚሆኑት ፡ ጠበቃ ፡ የመቅጠር ፡ ፍላ ጐት ፡ የነበራቸው ፡ ወይም ፡ የቃል ፡ ጥያቄው ፡ በተደረገላቸው ፡ ጊዜ ፡ ጠበቃ ፡ የነበራ

ቸው ፡ ናቸው ። ይኸም ፤ ብዙዎች ፡ ተሚጋቾች ፡ በጠበቆች ፡ ላይ ፡ ከሰነዘሩት ፡ አስተያየት ፡ ጋር ፡ ሲነፃጸር ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ነው ። ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ተሚጋቾች ፡ ውስጥ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ የነበራቸው ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ። ለዚህም ፡ ምክንያቱ ፡ በነገረ ፡ ፈጅ ፡ ማቆም ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፶፰ ፡ መሠረት ፡ የሚደረገው ፡ ቁጥጥር ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ተሚጋቾች ፡ እንደሚሉት ፡ ተጨማሪ ፡ ዋጋን ፡ መጠየቅ ፡ ይችሉ ፡ ዘንድ ፡ ጠበቆች ፡ ነገርን ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ይጐትቱታል ። ይኸንንም ፡ ለማድረግ ፡ ከሚጠቀሙባቸው ፡ ዘዴዎች ፡ አንዱ ፡ ተሚጋቾች ፡ እንደሚሉት ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ በሚያቀርባቸው ፡ አቤቱታዎች ፡ ላይ ፡ ጥቃቅን ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መቃወሚያዎችን ፡ መፍጠር ፡ ነው ። በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ስሕተት ፡ መታረም ፡ የሚያስፈልገው ፡ ከሆነ ፡ ማመልከቻውን ፡ እንደገና ፡ ለመጻፍ ፡ ጉዳዩ ፡ በቀጠሮ ፡ ይተላለፋል ። ከዚያ ፡ በኋላም ፡ መቃወሚያውን ፡ ያቀረበው ፡ ጠበቃ ፡ በጉዳዩ ፡ መተላለፍ ፡ የተነሳ ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቃል ። ተሚጋቾች ፡ እንደሚሉት ፤ አንዳንድ ፡ ጠበቆች ፡ ጉዳዩን ፡ በቀጠሮ ፡ መጐተት ፡ ይመቻቸው ፡ ዘንድ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ሳይዘጋጁ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይመጣሉ ። ሌሎችም ፡ ከጉዳዩ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ በሌለው ፡ ሙግት ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜን ፡ ስለሚያጠፉ ፡ የቀረው ፡ ጉዳይ ፡ ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ ይተላለፋል ።

ሌሎች ፡ ተሚጋቾች ፡ ደግሞ ፤ ጠበቆች ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ደንበኞች ፡ ስላሏቸው ፡ ቀጠሯቸው ፡ ሲደራረብ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ክርክራቸውን ፡ ያስተላልፋሉ ፡ ወይም ፡ ጨርሶ ፡ ሳይቀርቡም ፡ ይውላሉ ፡ ብለዋል ። የቃል ፡ ጥያቄ ፡ የተደረገላቸው ፡ አያሌ ፡ ተሚጋቾች ፡ የቀን ፡ ሠራተኞች ፡ ስለሆኑ ፡ ያንድ ፡ ጠበቃ ፡ በቀጠሮ ፡ አለመቅረብ ፡ በገቢያቸው ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ኪሣራን ፡ ያስከትላል ።

ዳግም ፤ ጠበቆች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ በጉቦ ፡ ተደልለው ፡ ምስጢርን ፡ ስለሚያባክኑ ፡ ወይም ፡ ጉዳዩን ፡ "ስለሚተዉት ፡" ሊታመኑ ፡ አይገባም ፡ እስከማለት ፡ የደረሱ ፡ ተሚጋቾች ፡ ተገኝተዋል ። ተሚጋቾች ፡ ሁሉ ፡ እንደሚሉት ፡ ጠበቆች ፡ ክርክሮችን ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ለመፈጸም ፡ ፈጽሞ ፡ የማይሞክሩ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ ተስፋ ፡ የሌላቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ ገንዘብን ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ ያደርጋሉ ። እንዲያውም ፡ አንዳንድ ፡ ተሚጋቾች ፡ እንደተናገሩት ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ በአንዳቸው ፡ ወገን፡ከተቀጠረ ፡ በኋላ ፡ ሌላው ፡ ወገን፡ ጉዳዩን ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ለመጨረስ ፡ ፍላጐት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ሲገልጽ ፡ ደንበኛቸው ፡ የእርቁን ፡ ድርድር ፡ እንዳይቀበል ፡ ይገፋፉታል ።

ተሚጋቾች ፡ ስለጠበቆች ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ በደንብ ፡ ለመግለጽ ፡ ያመች፡ ዘንድ ፤ "በጠቅላላው ፡ ስለ ፡ ጠበቆች ፡ ምን ፡ ያስባሉ ?" ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ነገረተኞቹ ፡ የሰጧቸውን ፡ አንዳንድ ፡ መልሶች ፡ መጥቀስ ፡ ይረዳል ፤

"ጠበቆች ፡ ነገርን ፡ እንዳያጓትቱና ፡ ከደንበኞቻቸውም ፡ ገንዘብን ፡ ከመግፈፍ ፡ እንዲታገዱ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ እንዲቆጣጠራቸው ፡ ያስፈልጋል ።"

"ጠበቆች ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ገንዘብን ፡ ይቀበላሉ ።"

"ጠበቆች ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ችሎታ ፡ የላቸውም ።"

"የጥብቅና ፡ ሙያ ፡ መጥፎ ፡ ስምን ፡ አትርፎአል ። እንደ ፡ ክብር ፡ ሙያ ፡ በመታየትም ፡ ፋንታ ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ተቆጥሯል ።"

የቃል ፡ ጥያቄ ፡ ከተደረገላቸው ፡ ተሚጋቾች ፡ ውስጥ ፡ ጠበቆችን ፡ የሚያመሰግነው ፡ አስተያየት ፡ የተሰነዘረው ፡ "በጠበቃዬ ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ አለኝ ፡" በም

ትል ፡ በአንዲት ፡ ወይዘሮ ፡ ሲሆን ፤ "ጠበቃዬ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ትጉህ ፡ ነው ፤" ብላለች ።

ጠበቆችን ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ካልተቃወሙት ፡ ወገን ፡ የተሰጠው ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ ደግሞ ፤ "ጠበቆች ፡ ሕጉን ፡ ስለሚያውቁ ፡ ጉዳዮቻችንን ፡ እንሰጣቸዋለን ፤" የሚል ፡ ነው ። አንድ ፡ ተሟጋች ፡ በጠበቆች ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየትና ፡ ተሟጋቾችም ፡ ለምን ፡ እንደሚቀጥሯቸው ፡ ትክክለኛ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ እንደሚከተለው ፡ አጠቃልሎታል ፤ "ጠበቆችን ፡ አላምናቸውም ፤ ጠበቃ ፡ እንዲኖረኝ ፡ ያደረግሁበትም ፡ ምክንያት ፡ ዳኞች ፡ እነሱን ፡ ስለሚሰሟቸው ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፤ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጠበቃዬ ፡ እኔ ፡ የማልፈቅደውን ፡ ነገር ፡ በተናገረ ፡ ቁጥር ፡ እሱን ፡ ማረም፡ አዘወትራለሁ" ።

በጠበቆችና ፡ በደንበኞቻቸው ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ደንበኞች ፡ በጠበቆቻቸው ፡ ላይ ፡ ባላቸው ፡ ጥርጣሬ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ ጠበቆችም ፡ ለደንበኞቻቸው ፡ ዕውነተኛ ፡ ሆነው ፡ አለመገኘታቸው ፡ የሚነቀፍ ፡ ነው ። ተሟጋቾች ፡ በጠበቆች ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ ከላይ ፡ የተዘረዘረው ፡ ዓይነት ፡ ሲሆን ፡ ጠበቆችን ፡ ለምን ፡ ይቀጥራሉ ፡ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ይከተላል ። ለዚህም ፡ መልሱ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሊታወስ ፡ የሚገባው ፡ መሃይምናኑ ፡ ተሟጋቾች ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ከሚችሉት ፡ ተሟጋቾች ፡ በይበልጥ ፡ ጠበቆች ፡ የሚቀጥሩ ፡ መሆናቸው ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ጉዳያቸውን ፡ ለማቅረብ ፡ በጣም ፡ የሚቸገሩ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ እንደሌላቸው ፡ የሚናገሩና ፡ ከፍርድ ፡ ቤትም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ ያላቸው ፡ ልምድ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ የሆነ ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ መሃይሙ ፡ ተሟጋች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ረዳት ፡ የሌለው ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተደጋገመ ፡ በመሆኑ ፡ መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ የሚችለው ፡ ሰው ፡ በቀላሉ ፡ ሊረዳው ፡ የሚችል ፡ ቢሆንም ፤ መጻፍና ፡ ማንበብ ፡ የማይችለው ፡ ሰው ፡ የሚሰጡትን ፡ አያሌ ፡ ወረቀቶች ፡ (ጽሑፎች) ፡ እንደምን ፡ እንደሚይዛቸው ፡ ሊያውቅ ፡ አይችልም ። ስለዚህም ፤ ተሟጋች ፡ ሁኔታውን ፡ ተረድቶ ፡ ምን ፡ እንደተወሰነበትና ፡ ምን ፡ እንደሚጠበቅበት ፡ እንዲያውቅ ፡ ጠበቆች ፡ ይቀጠራል ።

ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ተሟጋች ፡ ጠበቃ ፡ የቀጠርኩት ፡ ጠበቃው ፡ "ሕጉን ፡ ስለሚያውቀው ፡ ነው ፡" ብሎ ፡ በሚናገርበት ፡ ጊዜ ፤ በእርግጥ ፡ የሚገልጸው ፡ ጠበቃው ፡ ማንበብ ፡ መቻሉንና ፡ ከዳኞቹና ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ የተላመደ ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሥራውም ፡ ይኸንኑ ፡ ዕውቀቱን ፡ ለደንበኛው ፡ ማካፈል ፡ ነው ። ተሟጋች ፡ የሚገኝበት ፡ ይህ ፡ ያልተስተካከለ ፡ ግንኙነት ፡ ማለትም ፡ ጠበቃው ፡ ሙግቱን ፡ ለግል ፡ ጥቅሙ ፡ ማስፋፊያ ፡ ሊያደርገው ፡ ሲሞክር ፡ ተሟጋቹ ፡ በጠበቃው ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ እንዲገኝ ፡ የሚያደርግበት ፡ ሁኔታ ፡ ተሟጋቾች ፡ የገለጹትን ፡ የመሰለ ፡ በሕጉ ፡ ሙያ ፡ ላይ ፡ የተፈጠረው ፡ የእምነት ፡ ማጣት ፡ ሁኔታ ፡ እያደገ ፡ እንዲሄድ ፡ ያደርገዋል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ከላይ ፡ የተገለጸው ፡ በጠበቃና ፡ በደንበኛው ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ የሚገኝ ፡ ባይሆንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ጠበቆች ፡ በደንበኞቻቸው ፡ ዕውቀት ፡ ማነስ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ይጠቀማሉ ።

በሕግ ፡ ሙያ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ዝቅተኛ ፡ ግምት ፡ በሙግቶች ፡ ውስጥ ፡ ሁልጊዜ ፡ ተሸናፊ ፡ ወገን ፡ ከመኖሩ ፡ ጉዳይ ፡ ጋር ፡ ሊዛመድም ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ተሟጋች ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ከተረታ ፡ ጥፋተኛ ፡ የሚያደርገው ፡ ጠበቃውን ፡ ነው ።

## ተሚጋቾች ፡ በፍርድ ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ።

ተሚጋቾች ፡ በአሁኑ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቅንጅት ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ ማወቅ ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፡ በፍርዱ ፡ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ መሻሻል ፡ መደረግ ፡ ያስፈልገዋል ፡ ብለው ፡ እንደሚያስቡና ፡ ስለዳኞችም ፡ ያላቸውን ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፡ እንዲሰጡ ፡ ተጠይቀው ፡ ነበር ።

ብዙዎቹ ፡ የሰጡት ፡ የማሻሻያ ፡ ሃሳብ ፡ ክርክሮች ፡ ከአሁኑ ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ በቶሎ ፡ ይወሰኑ ፡ የሚለው ፡ ነው ። አብዛኞቹ ፡ ተሚጋቾች ፡ ዳኞች ፡ አንድን ፡ ጉዳይ ፡ በሚያዩበት ፡ ጊዜ ፡ አያሌ ፡ ቀጠሮዎችን ፡ ይሰጣሉ ፡ ይላሉ ። ሌሎች ፡ አስተያየቶች ፡ ደግሞ ፡ ጉቦ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ በኩል ፡ ጨርሶ ፡ እንዲጠፋ ፡ የሚያሳስቡና ፡ የዐቃብያነ ፡ ሕጉም ፡ ችሎታ ፡ እንዲሻሻል ፡ የሚጠይቁ ፡ ናቸው ።

አንዳንድ ፡ ተሚጋቾችም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፍርዳቸውን ፡ የሚያስፈጽሙበት ፡ ሥልጣን ፡ ከፍ ፡ እንዲልና ፡ ያላቸውንም ፡ ሥልጣን ፡ ውጤት ፡ በሚሰጥ ፡ አኳኋን ፡ እንዲጠቀሙበት ፡ አሳስበዋል ። በዚህ ፡ በኩል ፡ ስላለው ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ላይ ፡ የተሰነዘሩት ፡ ብዙዎቹ ፡ ቅሬታዎች ፤ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ የፍርድ ፡ ባለዕዳዎችን ፡ ፈልጐ ፡ በማግኘትና ፡ ካገኙዋቸውም ፡ በኋላ ፡ አስገድዶ ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ በማቅረብ ፡ ረገድ ፡ ያላቸውን ፡ የችሎታ ፡ ማነስ ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። የተገቢውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትዕዛዝ ፡ ለማግኘት ፡ የፍርድ ፡ ባለገንዘቦች ፡ መከተል ፡ ያለባቸው ፡ የተራዘመ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትም ፡ ሌላ ፡ የቅሬታ ፡ ምክንያት ፡ ሆንዋል ።

ተሚጋቾች ፡ ከሰነዘርዋቸው ፡ ሌሎች ፡ አስተያየቶችና ፡ ሂሶች ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፤

—"አዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ ጥሩ ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ በማይታመኑ ፡ የሕዝብ ፡ አገልጋዮች ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ምክንያት ፡ በሚገባ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋሉም ።"

—"ፖሊሶች ፡ ወንጀለኞችን ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ሸንጐ ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸው ።"

—"በማመልከቻዎች ፡ ውስጥ ፡ በሚፈጸሙ ፡ በአንዳንድ ፡ ቀላል ፡ ስኅተቶች ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ቤቶች ፡ ፋይሎችን ፡ መዝጋት ፡ የለባቸውም ፤ ይህ ፡ ሁኔታ ፡ ለድሆች ፡ ነገረተኞች ፡ ከፍተኛ ፡ የገንዘብ ፡ ችግርን ፡ የሚፈጥር ፡ ነው ። "

—"ዳኞች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በጊዜው ፡ መገኘት ፡ ይገባቸዋል ።"

—"ለዳኞች ፡ ጉቦ ፡ ለመስጠት ፡ በቂ ፡ ሀብት ፡ እንዲኖረኝ ፡ ያስፈልጋል ፡ ወይም፡ ዳኞች ፡ ጉቦ ፡ መብላትን ፡ ማቆም ፡ ይኖርባቸዋል ።"

በፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ቤቶች ፡ የሚገኙትን ፡ ፋይሎች ፡ በመመርመር ፡ የክርክሮች ፡ መጓተት ፡ እውነት ፡ መሆኑን ፡ በግልጽ ፡ መረዳት ፡ ይቻላል ። ምርጫው ፡ አንድን ፡ ጉዳይ ፡ በሙሉ ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ መወሰን ፡ ወይም ፡ ከሰዓት ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጉዳዮችን ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ መመርመር ፡ ነው ። ምርጫው ፡ በመጨረሻ ፡ በተገለጸው ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ያተኰረ ፡ ሲሆን ፤ ተሚጋቾች ፡ ተስማሚ ፡ ሆኖ ፡ አላገኙትም ። ሆኖም ፡ ክርክሮች ፡ ያለቀጠሮ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰሙ ፡ ቢደረግ ፡ ጉዳያቸው ፡ ተራ ፡ እስኪደርሰው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ስለሚቆይ ፡ ተሚጋቾች ፡ ምን ፡ አስተያየት ፡ እንዳላቸው ፡ ለማወቅ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ።

## ተሚጋቾች ፡ ስለዳኞች ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ።

በዳኞች ፡ ላይ ፡ አስተያየታቸውን ፡ እንዲሰጡ ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ተሚጋቾች ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ሦስተኛዎቹ ፡ ስለዳኞች ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ በጣም ፡ መጥፎ ፡ ነው ። ዳኞች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሳሉ ፡ የሚከበሩ ፡ ቢሆኑም ፡ በተሚጋቾች ፡ ዘንድ ፡ እንደደንቆሮዎች ፡ ጉቦኞችና ፡ እንዲያውም ፡ ጨካኞች ፡ ሆነው ፡ መታየታቸው ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

በተሚጋቾች ፡ ዘንድ ፡ ለዳኞች ፡ ስም ፡ መጥፋት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፤ የዳኞች ፡ ጉቦ ፡ መቀበል ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።[186] ሌሎቹ ፡ ዳኞች ፡ የሚነቀፉባቸው ፡ ምክንያቶች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በቅልጥፍና ፡ አለመሥራታቸውና ፡ የድሆችን ፡ ችግር ፡ በመረዳት ፡ ረገድ ፡ የሚያሳዩትን ፡ ልበ-ድንጋይነትን ፡ ይጨምራል ። በዳኞች ፡ ላይ ፡ መጥፎ ፡ አስተያየት ፡ ያልሰጡት ፡ ወገኖች ፡ ሲተቹ ፡ "ምንም ፡ አይሉ፡" "የዳኞች ፡ ችሎታ ፡ በመሻሻል ፡ ላይ ፡ ነው ፤" ወይም ፡ "በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተሾሙ ፡ ስለሆኑ ፡ ቢሳሳቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቀጣቸዋል ፡" ብለዋል ።

ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉ ፡ ተሚጋቾች ፡ የመሃይምናን ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ ያህል ፡ በዳኞቹ ፡ ላይ ፡ ነቀፌታቸውን ፡ ለመሰንዘር ፡ አልቃጡም ። እንዲያውም ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ ከሚችሉት ፡ ተሚጋቾች ፡ ብዙዎቹ ፡ ስለ ዳኞች ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ ገለልተኛ ፡ ነው ።

መሃይምናን ፡ ተሚጋቾች ፡ ስሜታቸውን ፡ በግልጽ ፡ ከመግለጻቸውም ፡ ሌላ ፡ በዳኞች ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ በጠቅላላው ፡ መጥፎ ፡ ነው ። ዳኞችን ፡ የሚያዋርድ ፡ አስተያየት ፡ ከሰጡት ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎቹ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበው ፡ የማያውቁ ፡ ናቸው ። የአስተያየታቸው ፡ አብዛኛው ፡ ክፍል ፤ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ከተደረገ ፡ ውይይት ፡ የተገኘ ፡ ለመሆኑ ፡ ይህ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችሉት ፡ ተሚጋቾች ፡ በዳኞች ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ ልዝብ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ችግር ፡ ከመሃይምናኑ ፡ ተሚጋቾች ፡ ይልቅ ፡ እነዚህኞቹ ፡ የበለጠ ፡ ለመረዳት ፡ በመቻላቸው ፡ ይሆናል ። በተጨማሪም ፡ አንድ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ከመሃይም ፡ ይልቅ ፡ አዘውትሮ ፡ ከመንግሥት ፡ መ/ቤቶችና ፡ ከሥራቸው ፡ ጋር ፡ በሚያደርገው ፡ ግንኙነት ፡ በልምምድ ፡ ያገኘው ፡ ትምህርት ፡ ለዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ልዝብ ፡ አስተያየት ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። እንዲያውም ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችለው ፡ ተሚጋች ፡ በዳኞቹ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ቅሬታ ፡ አይኖረውም ። ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችለው ፡ ሰው ፡ የዳኝነቱን ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ ለመቋቋም ፡ የሚያስችለው ፡ ገንዘብና ፡ ብልጠት ፡ ካለው ፡ እራሱን ፡ ሊጠብቅ ፡ ይችላል ።

## የዘመኑና ፡ የጥንቱ ፡ ተሚጋቾች ።

ተሚጋቾች ፡ አዲሱን ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቅንጅት ፡ ከኢጣልያ ፡ ወረራ ፡ በፊት ፡ ከነበረው ፡ "ከጥንቱ ፡" ቅንጅት ፡ ጋር ፡ ሲያወዳድሩት ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ አስተያየት ፡

186. የሚከተሉት ፡ ተሚጋቾች ፡ የሰጡአቸው ፡ አስተያየቶች ፡ ናቸው ። "ዋስ ፡ መጥራት ፡ ያስፈለገኝ ፡ እንደሆነ ፡ ለዳኛው ፡ ጉቦ ፡ ካልሰጠሁት ፡ በቀር ፡ ያቀረብኩትን ፡ ሰው ፡ አይቀበለኝም ። ጉቦም ፡ ካልሰጠሁ ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ መግባቴ ፡ አይቀርም ።" "እዚህ ፡ ላለው ፡ ዳኛ ፡ ለጾም ፡ ፍሪ ፡ ሁለት ፡ በጐች ፡ ወስጃለሁ ።" "የዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ የሚሄድበት ፡ የኔ ፡ ባላጋራ ፡ መኪና ፡ ነው ።"

እንዳላቸውም ፡ ለማወቅ ፡ ሙከራ ፡ ተደርጐ ፡ ነበር ። ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎቹ ፡ ከ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ የሙግት ፡ ሁኔታ ፡ ለመገንዘብ ፡ ዕድሜአቸው ፡ የማይፈቅድላቸው ፡ በመሆኑ ፡ ስለጥንቱ ፡ ቅንጅት ፡ ከተሰጠው ፡ አስተያየት ፡ አብዛኛው ፡ በይባላል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የዘመኑንና ፡ የጥንቱን ፡ ለማወዳደር ፡ ያህል ፡ የአሁኑ ፡ ዝንባሌያቸው ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

በልማዳዊ ፡ ሕግና ፡ ባሁኖቹ ፡ ሕጐች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ አለመግባባት ፡ ለማወቅ ፡ ተሚጋቾች ፡ ለቀረበላቸው ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ አልፈቀዱም ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ተሚጋቾች ፡ ውስጥ ፡ አዲሶችን ፡ ሕጐች ፡ ተረድቶ ፡ ከልማዳዊው ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ የማወዳደር ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ምናልባት ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ ባለመኖሩ ፡ ነበር ። የአዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ በብዛት ፡ ልማድን ፡ የተከተሉ ፡ መሆን ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግና ፡ በአዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ መካከል ፡ ቀዋሚ ፡ አለመስማማትን ፡ ለማውጣት ፡ ያልተቻለበት ፡ ምክንያት ፡ ሊሆንም ፡ ይችላል ። ቢሆንም ፤ ለጠሉት ፡ ለውጥ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ አዲሱ ፡ ሕግ ፡ መሆኑን ፡ ቢያውቁም ፡ ክርክርን ፡ በማካሄድ ፡ ረገድ ፡ በቀድሞውና ፡ በአዲሱ ፡ ሕግ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ልዩነት ፡ በጣም ፡ እንዳስቆጣቸው ፡ ግልጽ ፡ ነበር ።

ተሚጋቾች ፡ የሚከተሉትን ፡ አስተያየቶች ፡ ሰጥተዋል ፡-

"ልማዳዊው ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ፈጣን ፡ ነበር ። ይኸኛው ፡ ዝግተኛ ፡ ነው።" "አዲሱ ፡ ሕግ ፡ ርስት ፡ እንዲመዘገብና ፡ ከማዘጋጃ ፡ ቤትም ፡ ሰነድ ፡ መቀበል ፡ አስፈላጊ ፡ እንደሆነ ፡ ይናገራል ። በድሮው ፡ ሕግ ፡ አንድ ፡ ቀላድ ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ አባትና ፡ እናት ፡ እርስት ፡ መሆኑን ፡ የቀበሌው ፡ ዳኛ ፡ ያረጋግጣል ፤ የኔ ፡ ነው ፡ ባይ ፡ ቢነሣ ፡ መብቱን ፡ ማረጋገጥ ፡ ያለበት ፡ በቀበሌው ፡ ዳኛ ፡ እንጂ ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ አልነበረም ።" "የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፻፰ ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ ሊሟገቱ ፡ የሚችሉትን ፡ ለአንዳንድ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ ወስኗል ። በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ተሚጋች ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቆሞ ፡ የሚከራከርለትን ፡ ማንኛውንም ፡ ሰው ፡ ሊመርጥ ፡ ይችላል ።" ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ አግባብ ፡ ሊኖረው ፡ የሚችልባቸው ፡ የርስት ፡ ውርስ ፡ ክርክሮች ፡ በታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙ ፡ የወረዳና ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ አይበዙም ። በነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚሰሙ ፡ ክሶች ፡ ቀዋሚ ፡ የሆነ ፡ እነርሱን ፡ የሚመለከት ፡ ልዩ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ የሌላቸው ፡ ይሆናሉ ።

ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ዕዳውን ፡ አልከፍልም ፡ ሲል ፡ ሌላውን ፡ ሲያቆስል ፡ ወይም ፡ ሲሰርቅ ፡ በየትም ፡ ቦታ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋለው ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ ተጐጂው ፡ ወገን ፡ ለጉዳቱ ፡ ካሣ ፡ ማግኘት ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ የሚታየው ፡ ልዩነት ፡ የተጐጂውን ፡ ሰው ፡ መብት ፡ አጠባበቅ ፡ ሥነ-ሥርዓት ፡ ላይ ፡ ይመስላል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ በከተማ ፡ የሚኖር ፡ ተሚጋች ፡ በአካባቢው ፡ የሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ከየቀበሌያቸው ፡ ያመጡትን ፡ የተለየ ፡ ልማድ ፡ እያየ ፡ የራሱ ፡ ቀበሌ ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ ይኖረዋል ፡ ብሎ ፡ የሚገምት ፡ አይመስልም ። በከተማ ፡ ተወልዶ ፡ ያደገ ፡ ከ"ልማዳዊ ፡ ደንቦች ፡" ጋር ፡ ምንም ፡ ግንኙነት ፡ ላይኖረው ፡ ይችላል ። በመጨረሻም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከቤተሰብ ፡ ግንኙነት ፡ ውጭ ፡ የሚነሱትን ፡ ክርክሮች ፡ ቀና ፡ መስሎ ፡ በታያቸው ፡ መንገድ ፡ የመጨረስ ፡ ልምድ ፡ አላቸው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ። በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ክርክሩን ፡ ወደ ፡ አባት ፡ ሽማግሌዎች ፡ እንደመውሰድ ፡ ያለው ፡ ልማዳዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውጤቱ ፡ ያልተሳካ ፡ እንደሆን ፡ ነገሩ ፡ የመንግሥት ፡ ሹም ፡ ወደሆነው ፡ ዳኛ ፡ ይወሰዳል ። ኢትዮጵያውያን ፡ እስከ ፡ ዙፋን ፡ ችሎት ፡ ድረስ ፡ ይግባኝ ፡ ለመውሰድ ፡ ያላቸው ፡ ከፍተኛ ፡ ፍላጐት ፡ በየቀበሌ

ዎቻቸው ፡ በሚነሱት ፡ ክርክሮች ፡ ላይ ፡ ለሥፍራው ፡ ባይተዋር ፡ የሆኑ ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔ ፡
መስጠታቸውን ፡ የማይቃወሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ያሳያል ።

ስለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ ተሚጋቾች ፡ ክርክሮቻቸው ፡ የሚሰሙት ፡ በዘ
መናዊ ፡ ፍ/ቤቶች ፡ ውስጥና ፡ በባይትዋር ፡ ዳኞች ፡ በመሆኑ ፡ ምንም ፡ ቅር ፡ አልተሰ
ኙም ፤ መለስ ፡ ብለውም ፡ በቀበሌያቸው ፡ በዛፍ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ፍትሕ ፡ ይሰጥበት ፡ የነበ
ረውን ፡ ጊዜ ፡ አላስታወሱም ። ቢሆንም ፡ የጥንቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጊዜን ፡ ቆጣቢ ፡
በመሆኑ ፡ ከትዝታ ፡ ጋር ፡ ተመራጭነት ፡ ነበረው ።

እንደተሚጋቾቹ ፡ አስተሳሰብ ፡ አብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ ክርክሮቻቸውን ፡ ለቀበ
ሌው ፡ ሽማግሎች ፡ ከማቅረብ ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ፍ/ቤት ፡ ማምጣቱን ፡ ይመርጣሉ ።
ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ተሚጋቾች ፡ ከመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስቱ ፡ ለክርክሮቻቸው ፡ ውሳኔ
ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ለሽማግሎች ፡ አቅርበው ፡ የሞከሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጸዋል ፤ ቢሆ
ንም ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሙከራዎች ፡ ልማዳዊው ፡ ቅንጅት ፡ ውሳኔዎቱን ፡ ለማስፈጸም ፡ ካለ
መቻሉ ፡ የተነሳ ፡ ሳይሳኩ ፡ ቀርተዋል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለሽምግልናው ፡ አለመሳካት ፡
ምክንያት ፡ ከተሚጋቾቹ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የስምምነቱን ፡ ውል ፡ አለማክበሩ ፡
ነው ። "ዛሬ ፡ እኮ ፡ ደህና ፡ ሽማግሌ ፡ የለም" ፡ እና ፡ "ሽማግሌዎች ፡ ሁሉ ፡ አድሎ ፡ ያበ
ዛሉ" ፡ ወይም ፡ "ሽማግሌዎች ፡ ጊዜያቸውን ፡ ሽምግልና ፡ በማየት ፡ ከሚያሳልፉ ፡
ይልቅ ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘትን ፡ ይመርጣሉ ፡" በማለት ፡ ጥቂቶቹ ፡ ተሚ
ጋቾች ፡ ይህን ፡ ዓይነቱን ፡ ለውሉ ፡ መፍረስ ፡ ኃላፊነቱን ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ ላይ ፡ ጥለው
ታል ። እንዲያውም ፡ ብዙዎቹ ፡ ተከራካሪዎች ፡ "ሽማግሌዎች ፡ የማይታመኑ ፡ ናቸው ፤"
ብለዋል ።

የሽማግሌዎቹ ፡ ውሳኔ ፡ አስገዳጅነት ፡ የሌለውና ፡ እንዲሁም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡
ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ክርክሮቻቸውን ፡ በልማድ ፡ መሠረት ፡ ለመጨረስ ፡
ቢችሉ ፡ ኖሮ ፡ ይደሰቱ ፡ እንደነበር ፡ አብዛኞቹ ፡ ተሚጋቾች ፡ ተናግረዋል ። አንድ ፡
ተሚጋች ፡ "ክርክሮችን ፡ በተፋጠነ ፡ ሁኔታ ፡ ስለሚቆርጥ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ የልማ
ድን ፡ ሥርዓት ፡ ይወዳሉ ፤ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡
ሊውል ፡ ስለሚችል ፡ ፍ/ቤቶችን ፡ ይመርጣሉ ።" ብሏል ። ይህም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ክር
ክሩን ፡ ወደ ፡ ፍ/ቤት ፡ ለመውሰድ ፡ ወይም ፡ ላለመውሰድ ፡ በሚያስብበት ፡ ጊዜ ፡
ውሳኔውን ፡ ከማድረጉ ፡ በፊት ፡ የሚያወጣና ፡ የሚያወርደውን ፡ ሀሳብ ፡ አጠቃልሎ ፡
ይዟል ።

በታሪክ ፡ ጸሐፊዎችና ፡ ጥንት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በደረሱ ፡ የአውሮፓ ፡ መንገደኞች ፡
አስተያየት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሙግት ፡ ይወዳሉ ። ለነርሱ ፡ ሙግት ፡ የመደሰቻ ፡ ዓይ
ነት ፡ ነበር ። የጥንቱ ፡ ዓይነት ፡ ሙግት ፡ ማለትም ፡ ክርክሮች ፡ በቀረቡበት ፡ ዕለት ፡
ውሳኔአቸው ፡ ይሰጥ ፡ የነበረበት ፡ ጊዜ ፤ ተሚጋቾች ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ ሲቀርቡ ፡ ምን ፡
ማድረግ ፡ እንደሚገባቸው ፡ ያውቁ ፡ የነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ዳኞችም ፡ የተፈሩና ፡ የታፈሩ ፡
የቀበሌው ፡ ሰዎች ፡ የነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ በርግጥ ፡ አስደሳች ፡ ጊዜ ፡ ማሳለፊያ ፡ የነበረ ፡
ሊሆን ፡ ይችላል ።

አሁን ፡ ግን ፡ ሙግት ፡ የመደሰቻ ፡ ዓይነት ፡ እንዳልሆነ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ተሚጋ
ቾቹ ፡ የአሁኑ ፡ ሙግት ፡ ድሮ ፡ የነበረውን ፡ የሚያስደስት ፡ ለዛ ፡ ያጣበት ፡ ምክንያት ፡
ዕምነት ፡ በመጥፋቱ ፤ ጊዜ ፡ መውሰዱና ፡ ክርክሩ ፡ በሚነካቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡
በቅርብ ፡ መተዋወቅ ፡ ባለመኖሩ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይገምታሉ ። ስለዚህ ፡ ስለአዲሱ ፡
ቅንጅት ፡ የሰጡት ፡ አስተያየቶች ፡ ሕጉ ፡ በመሠረቱ ፡ ጥሩ ፡ አይደለም ፡ የሚሉ ፡ ሳይ
ሆኑ ፡ ቅንጅቱ ፡ የራሱን ፡ ደንብ ፡ ተከትሎ ፡ መሥራት ፡ አልቻለም ፡ የሚሉ ፡ ናቸው ።

ተሚጋቾቹ ፡ የተረዱት ፡ ጉድለት ፡ በቅንጅቱ ፡ ውስጥ ፡ በርግጥ ፡ ያለ ፡ ቢሆንም ፡ ለትክክ ለኛና ፡ ለተቀላጠፈ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ እንደተጣለ ፡ ተገንዝበውታል ።

## የአጥቢያ ፡ ዳኞች ።

ከወረዳ ፡ ፍ/ቤቶች ፡ በታች ፡ "የአጥቢያ ፡ ዳኛ" የሚባል ፡ የፍርድ ፡ ባለሥልጣን ፡ አለ ። እሱም ፡ ስለ ፡ አጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡[187] በወጣው ፡ አዋጅ ፡ መሠ ረት ፡ የተሾመ ፡ ሰው ፡ ነው ። ይህ ፡ አዋጅ ፡ "በተወሰነላቸው ፡ አጥቢያ ፡ የሚነሳውን፡ ክርክር ፡ በዕርቅ ፡" የሚጨርሱ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በማናቸውም ፡ ቀበሌ ፡ እንዲ ሾሙ ፡ ያዝዛል ።

ዳኛው ፡ በሥረ ፡ ነገር ፡ ክርክር ፡ ስላለው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ረገድ ፡ የሚያ የው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክር ፡ በገንዘብ ፡ ከሃያ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ የማይ በልጥ ፡ እንዲሆንና ፡ እንዲሁም ፡ የሚቀርብለት ፡ የወንጀል ፡ ክርክር ፡ ከአሥራ ፡ አም ስት ፡ ብር ፡ መቀጮ ፡ በላይ ፡ የሚያስቀጣ ፡ እንዳይሆን ፡ አዋጁ ፡ ወስኗል ። የግዛት ፡ ሥልጣኑም ፡ ስፋት ፡ አምሳ ፡ ጋሻ ፡ ያህል ፡ በሚሆነው ፡ አጥቢያ ፡ ወይም ፡ ቀበሌ ፡ ላይ ፡ ነው ። ዳኛው ፡ በሚያስችልበት ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ "እማኞች" ፡ መያዝ ፡ ሲኖር በት ፡ ከሚሰጠውም ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊወሰድ ፡ ይቻላል ።

እነዚህ ፡ ዳኞች ፡ የሚሾሙት ፡ በሁለት ፡ መንገድ ፡ ነበር ። በቀበሌው ፡ አንድ ፡ መልከኛ ፡ ካለ ፡ (መልከኛ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ርስት ፡ ያለው ፡ የመንግሥት ፡ ሹምና ፡ የአካባቢው ፡ የመንግሥት ፡ ግብር ፡ ሰብሳቢ ፡ ነው) ፡ አጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ ይሆናል ። መልከኛ ፡ በሌለበት ፡ ሥፍራ ፡ የአውራጃው ፡ የወረዳውና ፡ የምክትል ፡ ወረዳው ፡ ፍ/ቤቶች ፡ ፕሬዚዳንቶችና ፡ ምክትል፡ ፕሬዚዳንቶች ፡ ካገር ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ በቀበሌው ፡ ከሚገኙት ፡ ባለርስቶች ፡ መካከል ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞችን ፡ ይመርጣሉ ።[188]

እነዚህ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ የሚያገኙት ፡ ገንዘብ ፡ ተሚጋቾች ፡ ለዳኝነት ፡ ከሚ ከፍሉት ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ ነበር ። ቢሆንም ፡ የ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ የፍትሐብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በፍትሐብሔር ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ የማይናገር ፡ ስለሆነ ፡ የሚቀርቡላቸው ፡ ጉዳዮችና ፡ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ የሚያገኙት ፡ ገቢ ፡ በጣም ፡ እንደተቀነሰባቸው ፡ ብዙዎች ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ አመልክተዋል ። ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ተስማምተው ፡ ነገራቸውን ፡ ለአጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ የአቀረቡ ፡ እንደሆነ ፡ የአጥቢያው ፡ ዳኛ፡ በነገሩ ፡ ላይ ፡ የፍትሐብሔር ፡ የዳኝነት ፡ ሥል ጣን ፡ እንዲኖረውና ፡ የሚሰጠውም ፡ ውሳኔ ፡ አስገዳጅ ፡ ሆኖ ፡ የቀበሌው ፡ ወረዳ ፡ ፍ/ቤት ፡ እንዲያስፈጽመው ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ቢፈቅድም ፡ የተለወጠ ፡ ነገር ፡ የለም ።[189]

ግን ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ የክሱ ፡ ምክንያት ፡ ከሃያ ፡ አም ስት ፡ ብር ፡ በታች ፡ የሆነውን ፡ እንደዕቁብና ፡ በአነስተኛ ፡ ብድሮች ፡ ምክንያት ፡ የሚ

187. በ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ አጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ሹመት ፡ የወጣ ፡ አዋጅ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ስድስተኛ ፡ ዓመት ፡ ቁጥር ፡ ፲ ።

188. ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፮—፯ ፤ በአሁኑ ፡ አሠራር ፡ ግን ፡ መልከኛው ፡ የመሾም ፡ ሥልጣኑንም ፡ ቢሆን ፡ ለሌላ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ።

189. በኩኒ ፡ ወረዳና ፡ በጨርጨር ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ስለርሻ ፡ መሬት ፡ ክርክር ፡ ጥናት ፡ (በእንግሊዝኛ) ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፤ አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ።

ነሱትንም ፡ ክርክሮች ፡ በአንደኛው ፡ ወገን ፡ አመልካችነት ፡ ብቻ ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ የሚያዩ ፡ ይመስላል ።

የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ አፊሴል ፡ የሆነ ፡ የወንጀል ፡ ዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አሁንም ፡ አላቸው ። ይህም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ የተ ሰጣቸው ፡ ነው ። በዚያ ፡ ቁጥር ፡ መሠረት ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ሥራ ፡ በመሠረቱ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ከሚናገረው ፡ ጋር ፡ ተመ ሳሳይ ፡ ነው ። ተቀዳሚ ፡ ሥራው ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ የሚታረቁበትን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ ካልተሳካ ፡ የአሥራ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጥ ይችላል ። የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ የሚሰሟቸው ፡ ክሶች ፡ መዝገብ ፡ ዝርዝር ፡ እንዲይዙ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ ያዛል ።

በአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ፊት ፡ ክስ ፡ የሚጀመረው ፡ የተጻፈ ፡ ማመልከቻ ፡ በማቅረብ ፡ ነው ። ጥቂቶቹ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ ሲሰጡ ፡ ሕጐችን ፡ የሚጠቅሱ ፡ መሆናቸውን ፡ ቢገልጹም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ የተሰጣቸው ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ሳይጠቅሱ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ የሚያስችላቸው ፡ ይመስላል ፤ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ደንብን ፡ በመተላ ለፍ ፡ ምክንያት ፡ በሚነሱ ፡ ክርክሮች ፡ ተሟጋቾቹን ፡ ወገኖች ፡ ለማስታረቅ ፡ ይሞክራሉ፤ ይህ ፡ ካልተሳካና ፡ ጥፋተኛነት ፡ ከተረጋገጠ ፡ የአጥቢያው ፡ ዳኛ ፡ ባጥፊው ፡ ላይ ፡ የአሥራ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ እንዲጥል ፡ በቁጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ ተፈቅዶለታል ።

ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በወር ፡ ውስጥ ፡ ከሦስት ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ክሶች ፡ እንደሚቀርቡላቸው ፡ አመልክተዋል ። ይሰሟቸው ፡ ከነበሩት፡ክርክሮች፡ አብዛኞቹ ፡ በተለይም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገሮች ፡ አሁን ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚሰሟቸው ፡ እንደሆኑ ፡ አብዛኞቹ ፡ ያጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ አመልክተዋል ። ጥቃቅን ፡ የወንጀል ፡ ነገሮችን ፡ እንኳ ፡ ከአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ አሳልፎ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፡ ዝንባሌ ፡ መኖሩንም ፡ ያጥቢያ ፡ ዳኞቹ ፡ ገልጸዋል ።

አብዛኛው ፡ ያጥቢያው ፡ ዳኛ ፡ ሥራ ፡ የሚውለው ፡ "ባጥቢያው" ፡ ላይ ፡ የፍ ርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ትዕዛዝ ፡ በማስፈጸም ፡ ነው ። ስለ ዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ ለሚፈልጉ ፡ ሰዎችና ፡ በምስክርነት ፡ ለሚፈለጉ ፡ ሰዎች ፡ የመጥሪያ ፡ ወረቀት ፡ መስጠት ፡ የርሱ ፡ ኀላፊነት ፡ ነው ፤ ለፍርድ ፡ አፈጻጸም፡ ጉዳይ ፡ መሬትን ፡ ይገምታል ፡ ድንበሮችን ፡ ይከልላል ፡ አንዳንዴም ፡ ወንጀለኞችን ፡ ይዞ ፡ ለቀበሌው ፡ ፖሊስ ፡ ማስረከብ ፡ ይኖርበታል ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ እንደገንዘብ ፡ ሚኒ ስቴር ፡ ላሉ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍሎች ፡ ግብር ፡ በመሰብሰብ ፡ በወኪልነት ፡ ይሠራል ።

ቀደም ፡ ሲል ፡ እንደተነገረው ፡ አጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ጥንት ፡ ይከፈሉ ፡ የነበሩት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክር ፡ ተሟጋቾች ፡ ለዳኝነት ፡ ከከፈሉት ፡ ገቢ ፡ ላይ ፡ ነበር ። ለዳኝነት ፡ ይከፈል ፡ የነበረው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በክሱ ፡ ምክንያት ፡ በሆነው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ተገምቶ ፡ የሚከፈል ፡ ነበር ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከተነፈጋቸው ፡ ወዲህ ፡ ግን ፤ ገቢያ ቸው ፡ በወንጀል ፡ ሙግት ፡ ምክንያት ፡ ተሟጋቾች ፡ በሚከፍሉት ፡ አነስተኛ ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ተወስኖአል ። አንድ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ ከዚህ ፡ ውጭ ፡ ለሚፈጽመው ፡ ሥራ ፡ የማይከፈል ፡ ስለሆነ ፡ ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ ያጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በዚህ ፡ ከመማረራቸ ውም ፡ ሌላ ፡ በጠቅላላው ፡ ለሥራቸው ፡ ፍቅር ፡ የላቸውም ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ደመወዝ ፡ የማይከፈላቸው ፡ ቢሆኑም ፡ ምስክርን ፡ ወይም ፡ ወንጀለኛን ፡ ሳያቀርቡ ፡ ሲቀሩ ፡ ወይም፡ በመሬት ፡ አገማመት ፡ ላይ ፡ የተሳሳቱ ፡ እንደሆነ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተጠር ተው ፡ ይወቀሳሉ ።

ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በሙሉ ፡ ሥራቸውን ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ ቢያንስ ፡ የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓመት ፡ ምህረቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ይዘው ፡ የቆዩ ፡ ናቸው ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በመጀመሪያ ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተመረጡ ፡ ወይም ፡ የነርሱ ፡ ተወላጆች ፡ ናቸው ። አሁን ፡ አጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ የሆኑ ፡ ጥቂት ፡ ባላባቶች ፡ (ባለርስቶች) ፡ ከ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ በፊትም ፡ ካሁኑ ፡ ሥራቸው ፡ ጋር ፡ ይመሳሳሰል ፡ የነበረ ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ እንደነበር ፡ አስረድተዋል ።

"የአጥቢያ ፡ ዳኞች" ፡ የተሾሙት ፡ ለጥቃቅን ፡ ክርክሮች ፡ ሕጋዊ ፡ ውሳኔን ፡ በመስጠት ፡ ብዙዎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እነዚህን ፡ ክርክሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፡ ሲሉ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ እንዳይጓዙ ፡ ለምቾታቸው ፡ ታስቦ ፡ ነው ። አንድ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ በራሱ ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ ጠንካራ ፡ አቋም ፡ ስለሚኖረው ፡ የሚሰጠው፡ ውሳኔ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ነበረው ።

ሆኖም ፡ አዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ ይህን ፡ አቅጣጫ ፡ የለወጡት ፡ ይመስላል ። ራሱ ፡ ውሳኔዎችን ፡ በመስጠት ፡ ፋንታ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኛው ፡ የዋናው ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ቅንጅት ፡ መሣሪያ ፡ እንደሆነ ፡ ቆጥሮታል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የሚሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ በማስፈጸም ፡ ረገድና ፡ በሩቅ ፡ ሥፍራ ፡ የሚኖሩ ፡ ምስክሮችን ፡ በማቅረብ ፡ ረገድ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ወኪል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አሁንም ፡ የሚሠራው ፡ የርሱ ፡ ባል ሆነ ፡ በሌሎች ፡ ሥልጣን ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

በአዲስ ፡ አበባና ፡ በሐረር ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ የሉም ። በአሥመራ ፡ ግን ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ደመወዝ ፡ የሚከፍላቸው ፡ ብዙ ፡ የአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ አሉ ። እነዚህ ፡ ያጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ ሥራቸውን ፡ በውርስ ፡ ያገኙ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት፡ አማካይነት፡ ለሥራው ፡ የተመረጡ ፡ ሲሆኑ ፤ በሥራቸውም ፡ በጣም ፡ ትጉሆች ፡ ናቸው ። የክርክራቸውም ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ የ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ በወሰነው ፡ የዳኝነት፡ ሥልጣን ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ሆኖ ፡ ከሃያ ፡ እስከ ፡ ሰላሣ ፡ የሚሆኑ ፡ የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ በየሳምንቱ ፡ ከያጥቢያዎቻቸው ፡ ይቀርቡላቸዋል ።

እነዚህ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከዳኝነት ፡ ሥራቸው ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ተግባር ፡ አላቸው ። የመንግሥት ፡ ማስታወቂያዎችን ፡ ለሕዝቡ ፡ ይናገራሉ ፡ ንብረትን ፡ ይመዘግባሉ ፡ ስለሕዝብ ፡ ጤና ፡ አጠባበቅ ፡ መግለጫዎችን ፡ ይሰጣሉ ፡ የሕዝብ ፡ ዕድገት ፡ ፕሮግራሞችንም ፡ ያቋቁማሉ ።

የሚቀርቡላቸውን ፡ ክሶች ፡ የሚሰሙት ፡ የጽሑፍ ፡ ማመልከቻ ፡ ከቀረበላቸው ፡ በኋላ ፡ ሲሆን ፡ የሚከተሉት ፡ ግን ፡ ልማዳዊውን ፡ የሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ ዋና ፡ ሕግ ፡ ነው ። አሁንም ፡ ተግባራቸው ፡ የሚቻል ፡ ከሆነ ፡ ተሟጋቾችን ፡ ማስታረቅ ፡ ነው ። እንደ ፡ አዲስ ፡ አበባዎቹ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሳይሆን ፡ ለአሥመራ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሚቀርቡት ፡ ክርክሮች ፡ ቁጥር ፡ አነስተኛነት ፡ አንጻር ፡ ሲታይ ፡ እነዚህ ፡ ያጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ውጤት ፡ ያለው ፡ ነው ።

ከነዚህም ፡ ዋናው ፡ የተጣሉት ፡ ወገኖች ፡ ከመረጧቸው ፡ ሽማግሌዎች ፡ (አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ ሁለት ፡ ሽማግሌዎች ፡ መርጦ)፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የተስማሙበት ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ሆኖ ፡ ለማስታረቅ ፡ እንዲሞክሩ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለሽማግሌዎች ፡ የሚቀርቡት ፡ ነገሮች ፡ በቤተሰብ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የሚነሱ ፡ ክርክሮች ፡ ቢሆኑም ፡ ከቀላል ፡ ስድብ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ርስትና ፡ ነፍስ ፡ ግዳይ ፡ ክርክሮች ፡ ድረስ ፡ ባሉት ፡ በማንኛውም ፡ ጠቦች ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

ጥንት ፡ የሽማግሌዎች ፡ ውሳኔ ፡ አስገዳጅነት ፡ ነበረው ፤ ዛሬም ፡ ቢሆን ፡ በየባላገሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የሚሰጡት ፡ ውሳኔ ፡ ትልቅ ፡ ተሰሚነት ፡ አለው ። በነርሱ ፡ አማካይነት ፡ የተደረሰበት ፡ስምምነት ፡ እንደሕግ ፡ ስለሚከበር ፡ ስምምነቱ ፡ ከሚያስከትለው ፡ ግዴታ ፡ ማምለጥ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። አሁን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሰዎች ፡ ነገራቸውን ፡ ለሽማግሌዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቢያቀርቡም ፡ ተሰሚነታቸው ፡ በተለይም ፡ በከተሞች ፡ ውስጥ ፡ ተቀንሷል ። ቢሆንም ፡ በታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ውስጥ ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበላቸው ፡ ተሟጋቾች ፡ አብዛኞቹ ፡ የሽማግሌዎች ፡ ጠቃሚነት ፡ ጊዜው ፡ ያለፈበት ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ይላሉ ። እነዚሁ ፡ ሰዎች ፡ በተጨማሪ ፡ ሲናገሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ እንደማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለኑሮአቸው ፡ መሥራትን ፡ ይወዳሉ፤ ደመወዝ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ የሙሉ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ፤ ለሚሠሩትም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለሽምግልናም ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ ገንዘብ ፡ ይፈልጋሉ ፡ ብለዋል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ለውሳኔአቸው ፡ ተፈጻሚነት ፡ ለማስገኘት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ለመጠቀም ፡ ስለማይቻል ፡ ውሳኔአቸው ፡ በተሟጋቾች ፡ ላይ ፡ አስገዳጅነት ፡ የለውም ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ አለ ። ስለዚህ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አንድን ፡ ነገር፡ እንዲያደርግ ፡ ወይም ፡ እንዳያደርግ ፡ መገደድ ፡ አለበት ፡ ብለው ፡ ሲያስቡ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሄድን ፡ ይመርጣሉ ።

ወደ ፡ ወንጀል ፡ ክስ ፡ የሚያመሩ ፡ ክርክሮች ፡ ላይ ፡ ሽምግልና ፡ ለመሳካት ፡ ያለው ፡ ዕድል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ዕድል ፡ ያነሰ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተበዳዩ ፡ ወይም ፡ ተጐጅው ፡ ወገን ፡ ሽማግሌዎች ፡ በነገሩ ፡ ለመግባት ፡ ዕድል ፡ ከማግኘታቸው ፡ በፊት ፡ ጉዳዩን ፡ ለፖሊስ ፡ ወይም ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀርባል ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ክርክሩ ፡ በደንበኛው ፡ ሥርዓት ፡ መካሄድ ፡ ከቀጠለ ፡ ወዲያ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ እየከረረ ፡ ስለሚሄድ፡የሽማግሌዎቹ፡ በነገሩ ፡ መግባት ፡ አስቸጋሪ ፡ ይሆናል ። ግን ፡ አስቸጋሪ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የማይቻል ፡ ነገር ፡ እንደማይሆን ፡ ግልጽ ፡ ነው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረበና ፡ በራሱ ፡ አነሳሽነት ፡ ባንድ ፡ በንብረት ፡ መድፈር ፡ የወንጀል ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ጣልቃ ፡ ገብቶ ፡ ክርክሩ ፡ ቀበሌውን ፡ አጥብቆ ፡ የሚመለከት ፡ በመሆኑ ፡ እዚያው ፡ መታየት ፡ ስላለበት ፡ ዳኛው ፡ ውሳኔ ፡ እንዳይሰጥበት ፡ አመለከተ ። ከብዙ ፡ ጭቅጭቅና ፡ ዳኛውና ፡ ሽማግሌው ፡ ክርክራቸውን ፡ እንዳይቀጥሉ ፡ ሁለቱንም ፡ ወገኖች ፡ ከመከሯቸው ፡ በኋላ ፡ ሳይወዱ ፡ ወደቀበሌአቸው ፡ ለመመለስ ፡ ተስማሙ ።

በሽማግሌዎች ፡ ዘንድ ፡ የክርክሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቋሚ ፡ የሆነ ፡ ቅጽ ፡ የለውም ። አንደኛው ፡ ወገን ፡ የሚለው ፡ ሳይሰማ ፡ ለብቻው ፡ ተወስዶ ፡ ይጠየቃል ። የምስክሮች ፡ ቃል ፡ ካስፈለገም ፡ ራሳቸው ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ምስክሮቹን ፡ አምጥተው ፡ ይሰማሉ ። በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ባለጉዳዮቹና ፡ ምስክሮቹ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ እሑድ ፡ ቀን ፡ በሚደረግ ፡ ስብሰባ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ፊት ፡ አብረው ፡ ቀርበው ፡ ክርክራቸውን ፡ ያሰማሉ ።

ሽምግልናው ፡ ለምሳሌ ፡ ገንዘብ ፡ ተበድሮ ፡ ለተበዳሪው ፡ መልሶ ፡ መክፈል ፡ ባቃተው ፡ ሰው ፡ አነሳሽነት ፡ ይጀመራል ። ተበዳሪው ፡ ሁለት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይመርጥና ፡ አበዳሪው ፡ እንዳይከሰው ፡ ይለምኑለት ፡ ዘንድ ፡ ይልካል ። ሽማግሌዎቹ ፡ ሥራቸው ፡ የተሳካላቸው ፡ እንደሆነ ፡ ገንዘቡ ፡ የሚከፈልበትን ፡ ሁኔታ ፡ ለመወሰን ፡ ሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ ያገናኟቸዋል ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በሽማግሌዎች ፡ አማካይነት ፡ የተደረገ ፡ ስምምነት ፡ በጽሑፍ ፡ ይሠፍርና ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ይፈርሙበታል ። ከዚያም ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ስምምነ

ቱን ፡ ባለማክበሩ ፡ ክርክር ፡ ከተጀመረ ፡ ሰነዱ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ የጽሑፍ ፡ ስምምነቶችም ፡ በዳኞች ፡ ዘንድ ፡ የተከበሩ ፡ ናቸው ።

ሽማግሌዎች ፡ በወሰን ፡ ጭቅጭቅ ፡ በእጅ ፡ እልፊት ፡ ውዝፍ ፡ እዳን ፡ ባለመክፈል ፡ በቤተሰብ ፡ ውስጥ ፡ በሚነሱ ፡ ብጥብጦች ፡ በስድብና ፡ ስም ፡ በማጥፋት ፡ በመሳሰሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ወረዳና ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡትን ፡ አብዛኛዎቹን ፡ ክርክሮች ፡ ለመጨረስ ፡ ይሞክራሉ ።

ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከስምምነቱ ፡ ለመድረስ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ የሚከተሉት ፡ ደንብ ፡ ራሳቸው ፡ ርቱዕ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሚያምኑበት ፡ መንገድ ፡ ነው ። ጥቂቶቹ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ደህና ፡ ስምምነት ፡ ለመድረስ ፡ ሲሞክሩ ፡ ሕግ ፡ መጥቀሳቸውን ፡ ቢያስረዱም ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የሚገለገሉት ፡ በልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ መሆኑን ፡ ተናግረዋል ፤ ይህንኑ ፡ ሕግ ፡ አንደኛው ፡ ሽማግሌ ፡ በሚከተለው ፡ ዓይነት ፡ ይገልጹታል ፦

“ልማዳዊው ፡ ሕግ ፡ በሕዝቡ ፡ የሕሊና ፡ ፍርድ ፡ (ግምት) ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። የሕጉም ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ ተበዳዩ ፡ ተገቢውን ፡ ካሳ ፡ ማግኘት ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ነው ። የመነጨውም ፡ ሕዝባችን ፡ ካለው ፡ የፍትሕና ፡ የትክክለኛነት ፡ ስሜት ፡ ነው ።”

እንደ ፡ ዕቁብና ፡ እድር ፡ ያሉ ፡ በፈቃደኝነት ፡ የተቋቋሙ ፡ ማህበሮች ፡ በመካከላቸው ፡ የሚነሱትን ፡ ክርክሮች ፡ የሚወስኑ ፡ “ዳኞች” ፡ አሏቸው ። እነዚህ ፡ “ዳኞች” ፡ የተከበሩና ፡ ጽኑ ፡ መሠረት ፡ ያላቸው ፡ የቀበሌው ፡ ማህበሮች ፡ መሪዎች ፡ ናቸው ። ከማህበሩ ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ቢሆንም ፡ በማህበረተኞቹ ፡ መካከል ፡ ለሚነሳው ፡ ለማንኛውም ፡ ክርክር ፡ ዳኞቹ ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣሉ ። አንድ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ እነዚህ ፡ ማህበሮች ፡ ወደፊት ፡ በጣም ፡ ኃይል ፡ እያገኙ ፡ ስለሚሄዱ ፡ በማህበሮቻቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚነሱትን ፡ ክርክሮች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በአካባቢው ፡ የሚነሱትን ፡ በመሠረቱ ፡ ለወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡትን ፡ ቀላል ፡ ክርክሮችንም ፡ ጭምር ፡ መወሰን ፡ የሚችሉበት ፡ ጊዜ ፡ እንደሚመጣ ፡ ያምናሉ ።

## <u>የፍርድን ፡ ሥራ ፡ ለማሻሻል ፡ የቀረበ ፡ ኦፊሴላዊ ፡ ሐሳብ ።</u>

በቅርቡ ፡ በአስተዳደር ፡ ረገድ ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ ለማሻሻል ፡ የታቀደ ፡ ዓላማ ፡ ቢኖርም ፡ በሕግ ፡ አውጪው ፡ ወይም ፡ በአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ በኩል ፡ የተወሰደ ፡ እርምጃ ፡ የለም ። በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ለማሻሻል ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እርምጃ ፡ መውሰድ ፡ እንደሚቻል ፡ ለማሻሻያ ፡ ከቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ልንረዳ ፡ እንችላለን ።

የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፩ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

“ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዳኞችን ፡ ይሾማል ። እነርሱም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጠባይና ፡ መልካም ፡ ስም ፡ ያላቸው ፡ በሚሠሩበትም ፡ ሕግ ፡ በቂ ፡ ልምድና ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ እንዲሆኑ ፡ ያስፈልጋል ። ለሹመት ፡ የሚታጩበት ፡ የሚሾሙበት ፡ የሹመት ፡ እድገት ፡ የሚያገኙበት ፡ ከሥራ ፡ የሚወገዱበት ፡ ከሥራ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ የሚዘዋወሩበትና ፡ ትተው ፡ የሚያርፉበት ፡ ሁኔታ ፡ በሕግ ፡ ይወሰናል ።”

በቅርቡ ፡ ቅንጅቱን ፡ ለማሻሻል ፡ የተደረገው ፡ ሙከራ ፡ አንድ ፡ እጩ ፡ ዳኛ ፡ ለመሆን ፡ በቂ ፡ የሚያደርገውን ፡ ነገር ፡ ዝርዝር ፡ ሁኔታ ፡ የሚገልጽና ፡ ስለዳኞች ፡ አመራረጥም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሥርዓት ፡ የሚያቋቁም ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ የሚመለከት ፡ የተለየ ፡ ሕግ ፡ በማውጣት ፡ ላይ ፡ የታለመ ፡ ነበር ።

በ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሕጉ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እንደ ሆነ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴርን ፡ ጠየቀ ።[190] ለፓርላማው ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ ሥቱ ፡ የዚህን ፡ "ልዩ ፡ ሕግ" ፡ ጉዳይ ፡ የሚያጠና ፡ የዳኝነት ፡ ኮሚሽን ፡ ሾሙ ።[191] ኰሚቴው ፡ ስለዳኞች ፡ ሹመት ፡ ረቂቅ ፡ የሕግ ፡ ሐሳብ ፡ ቢያቀርብም ፡ ባልታወቀ ፡ ምክንያት ፡ ረቂቁ ፡ ለፓርላማ ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀረ ።

በኰሚቴው ፡ የተዘጋጀ ፡ ምንም ፡ ረቂቅ ፡ ባለመቅረቡ ፡ ጥቂት ፡ የፓርላማው ፡ አባሎች ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ራሳቸው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ አዘጋጁ ። በረቂቁም ፡ ላይ ፡ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ ጥቂት ፡ ከተነጋገሩበት ፡ በኋላ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ያንን ፡ አርእስተ ፡ ጉዳይ ፡ የያዘ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፡ ስላመለከቱ ፡ ጉዳዩ ፡ እዚያው ፡ ላይ ፡ ቆመ ።[192] በጉዳዩ ፡ ያሰቡበት ፡ የፓርላማ ፡ አባሎች ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አለ ፡ ያሉትን ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ተስማሙ ። ሕጉ ፡ በፍጥነት ፡ ካልቀረበ ፡ ግን ፡ ፓርላማ ፡ የራሱን ፡ ሕግ ፡ ያሳልፋል ፡ (ያወጣል) ፤ አሉ ።[193] እስካሁን ፡ የጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ረቂቅ ፡ ለፓርላማ ፡ ካለመቅረቡም ፡ ሌላ ፡ በዚሁ ፡ አርእስተ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የወጣ ፡ የተለየ ፡ ሕግም ፡ የለም ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ ፓርላማውም ፡ በራሱ ፡ ረቂቅ ፡ በኩልም ፡ የወሰደው ፡ ምንም ፡ እርምጃ ፡ የለም ። የፍርድን ፡ ሥራ ፡ ለማሻሻል ፡ ለሚወጣው ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ መምሪያ ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሾሙት ፡ ኮሚሲዮን ፡ ሥራ ፡ በአጀንዳው ፡ ላይ ፡ በሚከተለው ፡ ዓይነት ፡ ተመልክቷል ።

"፩/ የዳኞች ፡ ጠቅላላ ፡ ሁኔታ ።

ኰሚቴው ፡ ጥሩ ፡ የሕግ ፡ ትምህርትና ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ የረጅም ፡ ጊዜ ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ለዳኝነት ፡ የሚመረጡበትን ፡ መንገድ ፡ ይነጋገርበታል ። እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ታማኞችና ፡ ለሥራቸው ፡ ብቁ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። ሰዎቹ ፡ በምንም ፡ የማይደለሉና ፡ ለስማቸው ፡ አጥብቀው ፡ በማሰብ ፡ በንጹሕ ፡ ሕሊና ፡ የሚፈርዱ ፡ ለያንዳንዱ ፡ የሚገባውን ፡ የሚሰጡ ፡ መሆንም ፡ ይኖርባቸዋል ።

፪/ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣንና ፡ ቅልጥፍና ።

የቀለጠፈ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የሚኖርበትን ፡ መንገድ ፡ ለማግኘት ፡ ኰሚቴው ፡ በያንዳንዱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ ይነጋገራል ። በተጨማሪም ፡ ኰሚቴው ስለሚቀነሱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ ስለይግባኝም ፡ መቀነስ ፡ በተጨማሪ ፡ ይነጋገራል ።

፫/ ፍትህን ፡ የሚፃረሩ ፡ ሥራዎችን ፡ ስለማስወገድ ።

ኰሚቴው ፡ ጉቦና ፡ ፍትህን ፡ የሚያዛቡ ፡ ተግባሮች ፡ የሚወገዱበትን ፡ መንገድ፡ ያጠናል ፤ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ፍትህ ፡ በቀለጠፈ ፡ ሁኔታ ፡ በሚሰጥበት ፡ ዘዴ ፡ ላይም ፡ የበኩሉን ፡ አስተያየት ፡ ያቀርባል ።"[194]

190. አ ፡ ባንቲዋሉ ፡ አላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፪፰፫ ፡ የተጠቀሰ ፡ ገጽ ፡ ፺፭ ።
191. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፺፯ ።
192. ከዚያው ።
193. ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፺፱ ።
194. ከዚያው ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ።

በኰሚቴው ፡ የቀረበው ፡ ዋናው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አፈ ፡ ንጉሡ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ የሕግ ፡ መምሪያው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ያሉበት ፡ አንድ ፡ ቀዋሚ ፡ የዳኝነት ፡ ኰሚሲዮን ፡ እንዲቋቋም ፡ ያሳስባል ። የዚህ ፡ ቀዋሚ ፡ የዳኝነት ፡ ኰሚሲዮን ፡ ተግባር ፡ የአውራጃ ፡ የከፍተኛንና ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዳኞችን ፡ መርጦ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይሾማቸው ፡ ዘንድ ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረብና ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ላይም ፡ አጉል ፡ ተግባር ፡ ሲፈጽም ፡ ነገሩን ፡ መርምሮ ፡ የደረሰበት ፡ እንደሆነ ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በኩል ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መግለጫ ፡ ማቅረብ ፡ ነው ። የወረዳ ፡ ፍ/ቤት ፡ ዳኞች ፡ በነዚህ ፡ አንቀጾች ፡ የተገለሉ ፡ ቢሆንም ፡ አንድ ፡ ተከታይ ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ በሕዝብ ፡ ድምጽ ፡ እንዲመረጡ ፡ አሳስቧል ።

ከዋናው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚው ፡ ቁጥር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

"ክፍ ፡ ያለ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ ብቁና ፡ ቀልጣፋ ፡ ዳኛ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ኰሚቴው ፡ ካላረጋገጠለት ፡ በቀር ፡ የማንንም ፡ ሰው ፡ የዳኝነት ፡ ሹመት ፡ አናጸናም ።"[195]

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ዳኞቹ ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ አቅራቢነት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይሾማሉ ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባቀረበው ፡ የስም ፡ ዝርዝር ፡ ላይ ፡ የሌሎችን ፡ ተመራጮች ፡ ስም ፡ ለመጨመር ፡ ሥልጣን ፡ ሲኖራቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ እንደዚህ ፡ ማድረጋቸው ፡ ተረጋግጧል ። በቁጥር ፡ ፻፲፩ ፡ መሠረት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተሰጠው ፡ "የመሾም ፡" ሥልጣን ፡ የቀረበለትን ፡ ከማጽደቅ ፡ እንዲያልፍ ፡ የሚያደርገው ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ዋናው ፡ የሕግ ፡ ረቂቅ ፡ "(ዳኞች) ፡ ለሹመት ፡ የሚታጩበት ፡ የሚሾሙበት ፡ የሹመት ፡ እድገት ፡ የሚያገኙበት ፡ ከሥራ ፡ የሚወገዱበት ፡ ከሥራ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ የሚዛወሩበትና ፡ ሥራ ፡ ትተው ፡ የሚያርፉበት ፡ ሁኔታ ፡ በሕግ ፡ ይወሰናል ።"[196] በማለት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ስለዳኞች ፡ ለሚወስነው ፡ ሕግ ፡ ተፈፃሚነትን ፡ በሰጠው፡ ነበር ።

ዋናው ፡ ረቂቅ ፡ ቀድሞ ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ብቻ ፡ ተይዞ ፡ የነበረውን ፡ የዲሲፕሊን ፡ ሥልጣን ፡ ለአውራጃና ፡ ለወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፕሬዚዳንቶች ፡ ሰጥቷቸዋል ። አንድ ፡ ዳኛ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ጠባዩን ፡ እንዲያሻሽል ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከተሰጠው ፡ በኋላ ፡ ጉድለቱን ፡ ሳያርም ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ነገሩን ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ አስተላልፎ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስትሩም ፡ ነገሩን ፡ ለቋሚው ፡ የዳኝነት ፡ ኰሚሲዮን ፡ እንዲመራው ፡ ረቂቁ ፡ ያዝዛል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኰሚሲዮኑም ፡ የዳኛውን ፡ ጥፋተኛነት ፡ ለመመርመርና ፡ የሚወስደውንም ፡ እርምጃ ፡ ለመወሰን ፡ ሥልጣን ፡ ይኖረዋል ። ኰሚሲዮኑ ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጠው ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ ሲሆን ፡ አስተያየቱን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያጸናው ፡ ዘንድ ፡ ያስተላልፋል ።

በዋናው ፡ ረቂቅ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሊወጡ ፡ የነበሩት ፡ "ደንቦች" በግልጽ ፡ የተዘረዘሩ ፡ ኃላፊነቶችን ፡ ለሰብሳቢ ፡ ዳኞች ፡ ይሰጣል ።

፭/ በልዩ ፡ ልዩዎች ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሥራ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ማከፋፈልን ፤

195. እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፻፷፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ ከአ ፡ ባንቲዋሉ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የድንጋጌው ፡ ረቂቅ ፡ ቁጥር ፡ ፬ ፤ የረቂቁ ፡ ሕግ ፡ ይኸኛው ፡ ክፍል ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ሲተረጐም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ያላገለገለ ፡ ሰው ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ አይሆንም ፡ ማለት ፡ ነው ።

196. የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፻፲፩ ።

፪/ ፍርድ ፡ ቤቱና ፡ መዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሥራቸው ፡ በቅልጥፍና ፡ ስለሚያካሄዱበት ፡ መንገድ ፤

፫/ በሥልጣኑ ፡ ሥር ፡ በሚገኙ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ለሚቀርበው ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ለሚመለከት ፡ አቤቱታ ፡ ባፋጣኝ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፤

፬/ የጠባይ ፡ ጉድለትን ፡ ያሳዩ ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ ችሎታ ፡ ማነስ ፡ ምክንያት ፡ ተግባራቸውን ፡ በሚገባ ፡ ለመፈጸም ፡ ያልቻሉትን ፡ ዳኞች ፡ ለኮሚሲዮኑ ፤ ዐቃብያነ ፡ ሕግ ፡ ሲሆኑ ፡ ግን ፡ ለሚኒስትሩ ፡ ማስታወቅ ፤

፭/ ሥራቸውን ፡ በሚገባ ፡ ለማካሄድ ፡ ይችሉ ፡ ዘንድ ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍትንና ፡ በየጊዜው ፡ የሚወጡትን ፡ ሕጐች ፡ እንዲሁም ፡ የጽሕፈት ፡ መሣሪያዎችን ፡ ለየፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መላክ ፤

፮/ በሕመም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ የዳኞችና ፡ የዐቃብያነ ፡ ሕጐች ፡ እጥረት፡ ሲኖር ፡ ይህንኑ ፡ ለሚኒስትሩ ፡ መግለጥ ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በነዚሁ ፡ ደንቦች ፡ መሠረት ፡ የመዝገብ ፡ ቤቱ ፡ ሹምና ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሠራተኞች ፡ በሙሉ ፡ በየፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ሊሆኑ ፡ ነበር ።[197]

በተጨማሪም ፡ ደንቦቹ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዳኞችን ፡ ሲሾም ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር አቅራቢነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በኮሚሲዮኑ ፡ አሳሳቢነትም ፡ ጭምር ፡ እንዲሆን ፡ ወስነው ፡ ነበር ።[198]

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ለተደጋገሙት ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ጉድለቶች ፡ በደንቡ ፡ ውስጥ ፡ የተለየ ፡ ግምት ፡ ተሰጥቷቸው ነበር ።

ማንኛውም ፡ ዳኛ ፡

(ሀ) አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ አንድን ፡ ክርክር ፡ ውሳኔ ፡ ሳይሰጥ ፡ ማዘግየት ፡ የለበትም ፤

(ለ) በቂ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረት ፡ የለበትም ፤

(ሐ) የኢትዮጵያን ፡ ሕጐች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከማዋል ፡ ቸል ፡ ማለት ፡ የለበትም ፤

(መ) ትክክለኛውን ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የሚተናኰል ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ማድረግ ፡ የለበትም ።

(ሠ) በአንድ ፡ ክርክር ፡ አያያዝ ፡ ረገድ ፡ ከአስተዳደር ፡ ባለሥልጣን ፡ ለሚተላለፍለት ፡ ትዕዛዝ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ግምት ፡ መስጠት ፡ የለበትም ፤

(ረ) ለጠበቆች ፡ ለምስክሮችና ፡ ለተከራካሪዎቹ ፡ ተገቢውን ፡ አክብሮት ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

(ሰ) በሐኪም ፡ በተረጋገጠለት ፡ ብርቱ ፡ በሽታ ፡ ምክንያት ፡ ሳይሆን ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ለመቅረት ፡ ሲሻ ፡ አስቀድሞ ፡ ከሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ፈቃድ ፡ ማግኘት ፡ አለበት ።[199]

---

197. በረቂቁ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ የሚወጣው ፡ ደንብ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ አ ፡ ባንቲዋሉ ፡ እላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፻፷፫ ፡ የተጠቀሰ ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ።

198. ከዚያው ፡ የደንቦቹ ፡ ረቂቅ ፡ ቁጥር ፡ ፬ ።

199. ከዚያው ፡ የደንቦቹ ፡ ረቂቅ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ።

## ማሻሻያ ፡ ሐሳቦች ።

የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ለማሻሻል ፡ የቀረበው ፡ አንዱ ፡ ሐሳብ ፡ ዳኞችን ፡ ከሥራ ፡ የማገድና ፡ የጠባይ ፡ ጉዳይን ፡ የመከታተል ፡ ሥልጣን ፡ ተገቢ ፡ ችሎታ ፡ ላላቸው ፡ የሕግ ፡ ሰዎችና ፡ ዳኞች ፡ ለሚገኙበት ፡ ኮሚቴ ፡ መስጠት ፡ መሆኑን ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ አይተናል ። ቢሆንም ፡ ይህንን ፡ ሐሳብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋሉ ፡ ዛሬ ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ረገድ ፡ በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ችግሮች ፡ በሙሉ ፡ ሊያስወግድ ፡ እንደማይችል ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ዋናው ፡ ችግር ፡ በወር ፡ ሰማንያ ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ ሃምሣ ፡ ብር ፡ እያገኙ ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኝነት ፡ ለማገልገል ፡ ፈቃደኞች ፡ የሆኑ ፡ በቂ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ እጥረት ፡ ነው ። አንድ ፡ የዳኝነት ፡ ኮሚሲዮን ፡ በቂ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ እንዲያመለክቱ ፡ ሊያስገድዳቸው ፡ መቻሉ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው።

ለብዙዎቹ ፡ የዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ችግር ፡ የመጀመሪያው ፡ መፍትሔ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ የሚታሰበው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የዓመት ፡ ባጀት ፡ ውስጥ ፡ በርከት ፡ ያለውን ፡ ክፍል ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ መስጠት ፡ ነው ። ይህ ፡ ቢደረግ ፡ ለዳኞችና ፡ ለሌሎች ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደመወዝ ፡ ለመክፈል ፡ ከመቻሉም ፡ በላይ ፡ የዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ አቀማመጥ ፡ የተሻለ ፡ መልክ ፡ ይኖረው ፡ ነበር ።

ከፍተኛ ፡ ደመወዝ ፡ ዳኞችና ፡ ሌሎች ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ አሁን ፡ በሚያገኙት ፡ ገቢ ፡ ምክንያት ፡ የሚፈጠረውን ፡ ጉልህ ፡ የገንዘብ ፡ እጥረት ፡ ከልዩ ፡ ምንጮች ፡ በጉቦም ፡ ጭምር ፡ ለሟሟላት ፡ ያላቸውን ፡ ፍላጐት ፡ ምናልባት ፡ ያስወግደው፡ ይሆናል ። የፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ ሕንፃ ፡ መሻሻል ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሠራተኞች ፡ በሥራቸው፡ ላይ ፡ የበለጠ ፡ ኩራትን ፡ ሳያሳድርባቸው ፡ አይቀርም ። ቢሆንም ፡ ለሚቀርቡት ፡ የማሻሻያ ፡ ሐሳቦች ፡ ለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የሚውል ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ከመንግሥት ፡ እንደማይገኝ ፡ መገንዘብ ፡ ያስፈልጋል ። እንግዲህ ፡ ጥያቄው ፡ ባለው ፡ ገንዘብ ፡ ሁኔታውን ፡ ለማሻሻል ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል ? የሚል ፡ ነው ።

መሻሻልን ፡ የሚፈልጉ ፡ ሦስት ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ አሉ ። አንደኛ ፡ በእያንዳንዱ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ የሚሰጥበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተፋጠነና ፡ የቀለጠፈ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ሁለተኛው ፡ መሻሻልን ፡ የሚፈልገው ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ ዋናውን ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋልን ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ሕጐቹ ፡ በተሻለ ፡ መንገድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ለማድረግ ፡ እንዴት ፡ ይቻላል ? የአሁንስ ፡ ዋና ፡ ሕግ ፡ እንዴት ፡ የዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ፍላጐት ፡ እንዲያረካ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻላል ? ሦስተኛ ፡ በዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ረገድ ፡ ጠቃሚ ፡ ሂስና ፡ ሀሳቦችን ፡ ሊሰነዝር ፡ የሚችል ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ክፍል ፡ የለም ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ክፍሎች ፡ ተቋቁመው ፡ ጠቅላላውን ፡ ቅንጅት ፡ ሊጠቀሙ ፡ በሚችሉበት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሊታሰብበት ፡ ይገባል ።

### ሥነ ፡ ሥርዓት ።

እያንዳንዱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ክርክር ፡ በየደረጃው ፡ እየተቀባበሉ ፡ ለማካሄድ ፡ የተመደቡ ፡ ብዙ ፡ ሠራተኞች ፡ አሉት ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ ሠራተኛ ፡ የለውም ፡ ብለን ፡ የገመትን ፡ እንደሆነ ፡ ከዳኛው ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ተራው፡ ተላላኪ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ እያንዳንዱ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኛ ፡ የሚሠራው ፡ ለርሱ፡ የተመደበ ፡ አስፈላጊ ፡ ሥራ ፡ አለው ። ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ብዙዎች ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራ

ተኞች ፡ ዳኞችም ፡ ጭምር ፡ የሥራ ፡ ፍቅር ፡ እንደሌላቸው ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ከሚገባ ቸው ፡ በላይ ፡ ይሠራሉ ፤ ደመወዛቸው ፡ አነስተኛ ፡ ነው ፡ ይበሳጫሉም ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ሥራቸውን ፡ በሚገባ ፡ አይሠሩም ፤ የፍርድ ፡ ቤትም ፡ ሥራ ፡ እንደሚገባው ፡ አይካሄድም ።

እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በሥራቸው ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ አስተሳሰብ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ለማድ ረግ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ። ለምሳሌ ፡ ባለሥልጣኖች ፤ ለነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የሙያ ፡ (ሥራ) ፡ ማህበሮችን ፡ አቋቁመው ፡ ሥራቸውን ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ እትሞ ችን ፡ በየጊዜው ፡ እያወጡ ፡ ለነዚህ ፡ ሰዎች ፡ እንዲያድሉ ፡ ሊያደርጉ ፡ ይችላሉ ። የፍ ርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የነዚህን ፡ ሰዎች ፡ ሞራል ፡ በሚያዳብሩት ፡ ዘዴዎች ፡ ላይ ፡ በበለጠ ፡ ማተኮር ፡ አለበት ። በተለያዩ ፡ አጥቢያዎች ፡ የሚገኙ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሠራተኞች ፡ በየጊዜው ፡ ተገናኝተው ፡ ለሁሉም ፡ የጋራ ፡ በሆነ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ መወያየት ፡ መንፈ ሳቸውን ፡ ሊያነቃቃው ፡ ይችላል ።

ቀጥሎም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚሠሩባቸው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ በድጋሚ ፡ እንዲ ታዩ ፡ ያሻል ፤ ለምሳሌም ፡ ያህል ፡ በየቀኑ ፡ ብዙ ፡ ክርክሮችን ፡ በመጠኑ ፡ መስማት ፡ ይሻላል ፡ ወይስ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ሳያቋርጡ ፡ አንድን ፡ ክርክር ፡ ብቻ ፡ መስማት ፡ ይሻላል ? ቀጠሮአቸው ፡ ሲደርስ ፡ ለክርክራቸው ፡ ውሳኔ ፡ ወዲያውኑ ፡ እንደሚሰጥ ፡ ቢረ ጋገጥላቸው ፡ ተሟጋቾች ፡ ክሳቸው ፡ እስከሚሰማበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ለመጠበቅ ፡ ፈቃደኞች ፡ ይሆናሉን ? ለሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉዳዮችና ፡ ለሙሉ ፡ ችሎት ፡ የተ ለያዩ ፡ ቀናትን ፡ በመወሰን ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የአሠራር ፡ ዘዴ ፡ ለመፍጠር ፡ ይቻል ፡ ይሆ ናል ፤ ይህም ፡ ዳኞቹ ፡ በሌላ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የተነሳውን ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ክርክር ፡ ዓይቶ ፡ ለመወሰን ፡ ሲሉ ፡ የያዙትን ፡ ክስ ፡ ለመቅጠር ፡ የሚገፋፉቸውን ፡ ነገር ፡ ስለሚያ ስወግደው ፡ ተሟጋቾች ፡ ጉዳያቸው ፡ ሳይቋረጥ ፡ እንዲሰማላቸው ፡ ያደርግላቸዋል ። የአ ንድ ፡ ክርክር ፡ ሳይቋረጥ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ መሰማት ፡ ባለ ፡ ጉዳዮቹ ፡ የሚጠይቁ ትን ፡ ዳኝነት ፡ ባፋጣኝ ፡ ለማግኘት ፡ ያስችላቸዋል ። ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ክርክር ፡ ውሳኔ ፡ ሳያገኝ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ አይቆይም ። ክርክሮችን ፡ ነጣጥሎ ፡ በየዓይነታቸው ፡ እንዲ ሰሙ ፡ ሲባል ፡ የተሰነዘረው ፡ ሀሳብ ፡ አሁን ፡ በጥቃቅን ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ክርክር ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መጥተው ፡ ጉዳያቸው ፡ ከመሰማቱ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ረዘም ያለ ፡ ክርክር ፡ እስኪያልቅ ፡ ድረስ ፡ መጠበቅ ፡ ለሚገደዱ ፡ ባለጉዳዮችም ፡ አንድ ፡ እር ዳታ ፡ ነው ። በርግጥ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባለጉዳዮቹን ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ነገራቸው ፡ በሙሉ ፡ እንዲሰማ ፡ ለክርክሩ ፡ ተዘጋጅተው ፡ እንዲመጡ ፡ ለማድረግ ፡ ባለው ፡ ችሎታ ፡ ላይ ፡ የተደገፈ ፡ ነው ፤ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ለውሳኔ ፡ የሚረዱትን ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ይዘው ፡ በማይቀርቡ ፡ ባለጉዳዮች ፡ ጠበቆችና ፡ ምስክሮች ፡ ላይ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የጠበቀ ፡ እርምጃ ፡ እንደሚወስዱ ፡ በግልጽ ፡ ማስታወቅ ፡ ይኖርባ ቸዋል ።

ለዚህ ፡ አባሪ ፡ በሆነው ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ እንደተገለጠው ፡ ብዙ ፡ ክርክሮች ፡ በተ ለይም ፡ በግል ፡ አቤት ፡ ባዮች ፡ የሚቀርቡት ፡ በከሳሽ ፡ በተከታታይ ፡ ቀጠሮ ፡ አለመ ቅረብ ፡ ምክንያት ፡ መዝገባቸው ፡ ተዘግቷል ። ከሳሽ ፡ ነገሩን ፡ ላለመቀጠል ፡ ያደረገ ውን ፡ ውሳኔ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ማሳወቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተሰረዙት ፡ ክሶች ፡ የሚሰሙበትን ፡ ቀን ፡ በመወሰን ፡ በቀጠሮውም ፡ ቀን ፡ በመጥራት ፡ የሚያባክ ነውን ፡ ጊዜ ፡ ይቀንስለታል ። ከሳሽ ፡ ደጋግሞ ፡ ሳይቀርብ ፡ ሲቀር ፡ ነገሩን ፡ ትቶታል ፡ ብሎ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲገምት ፡ ከማስገደድ ፡ ይልቅ ፡ ተከራካሪዎች ፡ ክርክራቸውን፡ ላለመቀጠል ፡ ሲሹ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያስታውቁ ፡ ማድረግ ፡ ይገባል ። የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ደንብ ፡ ወጥቶ ፡ ለባለጉዳዮችም ፡ ክሳቸውን ፡ ሲጀምሩ ፡ የደንቡን ፡

መኖር ፡ ለማስታወቅ ፡ ይቻላል ። ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ ሳይቀርቡ ፡ ሲቀሩም ፡ ቅጣት ፡ ለመወሰንም ፡ ይቻላል ።

ሌላው ፡ መፍትሔ ፡ የሚፈልገው ፡ ችግር ፡ ደግሞ ፡ በቦታ ፡ ጥበት ፡ ምክንያት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የተፈጠረው ፡ ግርግር ፡ ነው ። ሰፋ ፡ ያሉ ፡ ክፍሎች ፡ እስኪገኙ ፡ ድረስ ፡ መተፋፈግ ፡ ሊወገድ ፡ የሚችለው ፡ ጉዳይ ፡ ሳይኖራቸው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መጥተው ፡ ቦታ ፡ የሚይዙትን ፡ ሰዎች ፡ በማስወጣት ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊይዝ ፡ የሚችለው ፡ ሰዎች ፡ ቁጥር ፡ ተወስኖ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሠራተኞች ፡ ይህንኑ ፡ እንዲያስፈጽሙ ፡ በማድረግ ፡ ነው ። ለዐቃብያነ ፡ ሕጐች ፡ ሁሉ ፡ ተገቢ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ከተሰጣቸው ፡ በኋላ ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ ክርክሮቹ ፡ መዘጋጀታቸውን ፡ ሳያረጋግጡ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲቀጣቸው ፡ ያስፈልጋል ። ከመዘጋጀታቸው ፡ በፊት ፡ ተሚጋቹ ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ ያምን ፡ ወይም ፡ አያምን ፡ እንደሆነ ፡ የመጠበቅ ፡ልምዳቸውን ፡ መለወጥ ፡ ይኖርባቸዋል ። ዐቃብያነ ፡ ሕጐች ፡ የአንድን ፡ ተካሳሽ ፡ መልስ ፡ ነገሩ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ከመሰማቱ ፡ በፊት ፡ በቀላሉ ፡ ለማወቅ ፡ ይችላሉ ።

በወንጀል ፡ ነገሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጠበቃ ፡ የሚያቆምላቸው ፡ ድሆች ፡ ተከሳሾች ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ለአንድ ፡ ተከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ እንዲቆምለት ፡ ሲደረግ፡ ለሌላው ፡ ደሀ ፡ ተከሳሽ ፡ የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ እርዳታ ፡ የማይደረግበት ፡ ልዩ ፡ ምክንያት፡ ያለ ፡ አይመስልም ። ጥያቄ ፡ የቀረበላቸው ፡ ዳኞች ለድሆቹ ፡ ተከሳሾች ፡ ጠበቃ ፡ የሚያዙላቸው ፡ በምን ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ሲገኝ ፡ እንደሆነ ፡ እርግጠኞች ፡ አይደሉም ። ድሆች ፡ ተከሳሾች ፡ የሚገኙባቸው፡ ብዙ ፡ የወንጀል ፡ ነገሮች ፡ መኖራቸው ፡ ሲታወቅ፡ ዳኞቹ ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ምሕረቱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥር ፡ ፶፪ ፡ ትዕዛዝ ፡ በቀላሉ ፡ ችላ ፡ ይሉታል ። ነፃ ፡ ጥብቅና ፡ ለድሆች ፡ ተከሳሾች ፡ ስለሚሰጥበት ፡ ሁኔታ ፡ ደንብ ፡ ወጥቶ ፡ ዳኞች ፡ እንዲሰሩበት ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ። በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ድሆች ፡ ተከሳሾችን ፡ በመርዳት ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ችግር ፡ ለመቋቋም ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፡ ሕጉ ፡ የዚህ፡ ዓይነቱን ፡ ርዳታ ፡ ለብርቱ ፡ ወንጀሎች ፡ እንዲወስነው ፡ ይገባል ።

ዳኞች ፡ በፍርድ ፡ ቤቶቻቸው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ሠራተኞች ፡ በመቆጣጠር፡ ረገድ ፡ የበለጠ ፡ ሥልጣን ፡ ሊሰጣቸው ፡ ይገባል ። በፍርድ ፡ ቤቶቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ለሚካሄደው ፡ ሥራና ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶቹም ፡ ቀልጣፋ ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ ተቀዳሚ ፡ ኃላፊነት ፡ ያለባቸው ፡ መሆኑን ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሊገልጽላቸው ፡ ይችላል ።

በፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ አቋምና ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ላላቸው ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ በኩልም ፡ መሻሻል ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ ያሀል ፡ በገጠር ፡ ያሉት ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተሠሩት ፡ ከሚያገለግሉት ፡ ሕዝብ ፡ ርቀው ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ለመስማት ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ካላቸው ፡ ነገሮች ፡ ጥቂቶቹ ፡ ለወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሊሰጡ ፡ ይችላሉ ። አለዚያም ፡ አንዳንድ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡ በየአጥቢያቸው ፡ በሚገኙት ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እየዞሩ ፡ ሊዳኙ ፡ ይችላሉ ። ዳኞች ፡ በሌላ ፡ ቦታ ፡ ብቻቸውን ፡ እየተሰየሙ ፡ የሥራ ፡ ድቅናቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ ተግተው ፡ ሲሠሩ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አንድን ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ ሦስት ፡ ዳኞች ፡ መሰየማቸው ፡ የሰው ፡ ጉልበት ፡ መባከን ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ባንዳንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንደሚደረገው ፡ ሦስቱም ፡ ዳኞች ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ክርክሮችን ፡ሲሰሙ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ችሎቱ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የጐደለው ፡ ይሆናል ። ዳኞች ፡ ተነጣጥለው ፡ ለየብቻቸው ፡ እንዲያስችሉ ፡ ማድረግ ፡ ወይም ፡ ለዚህ ፡ በቂ ፡ ሥራ ፡ ከሌለ ፡ አንዳንዶቹን ፡ ዳኞች ፡ በዚያ ፡ ያለውን ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፡ ለማቃለል ፡ ይረዱ ፡

ዘንድ ወደ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መላክ ፡ ይገባል ። የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሥረ ፡
ነገር ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ካላቸው ፡ ሥልጣን ፡ ጥቂቱን ፡ ያጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ እንዲወስ
ዱት ፡ በማድረግ ፡ በሰፋፊ ፡ ከተሞች ፡ የሚገኙ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ከባድ ፡
ሥራ ፡ ለማቃለል ፡ ይቻላል ። እነዚህ ፡ ያጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ የሚመረጡት ፡ በሕብረ ፡
ሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ያላቸው ፡ አቋም ፡ በሚገባ ፡ እየታየ ፡ ከሆነና ፡ ሰዎችን ፡ በፍትሐ ፡
ብሔርም ፡ ሆነ ፡ በወንጀል ፡ ነገር ፡ አስገድዶ ፡ የማቅረብና ፡ የሚሰጡትንም ፡ ውሳኔ ፡
የማስፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ ከተሰጣቸው ፡ አሁን ፡ ለወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚቀርቡት
ክሶች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ሦስተኛውን ፡ ያህል ፡ ለመቀነስ ፡ ይችላሉ ። የቀላል ፡ ብድር ፤
የስድብና ፡ የስም ፡ ማጥፋት ፡ ነገሮች ፡ እንዲሁም ፡ አነስተኛ ፡ እጅ ፡ እልፊቶች ፡ የመ
ጀመሪያ ፡ ተግባሩ ፤ በነገረተኞቹ ፡ መካከል ፡ እርቅን ለማውረድ ፡ መሞከር ፡ ወደሆ
ነው ፡ ወደ ፡ አጥቢያ ፡ ዳኛው ፡ ሊመሩ ፡ ይቻላል ። የሥረ ፡ ነገር ፡ ክርክራቸው ፡ በዚህ፡
ዳኛ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የሆነ ፡ ክርክሮች ፡ ሁሉ ፡ ለርሱ ፡ እንዲቀርቡ ፡ መደረግ ፡ አለ
በት ። በነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሠራበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ለዳኞቹ ፡ አያያዝ ፡ ያመ
ች ፡ ዘንድ ፡ እስከዚህም ፡ የጠበቀ ፡ እንዲሆን ፡ አያሻም ። ለዳኛው ፡ መቅረብ ፡ የሚያስ
ፈልገው ፡ የፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ሐተታና ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ብቻ ፡
ቢሆን ፡ ይበቃል። ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉትን ፡ ጥቃቅን ፡ ክርክሮች ፡ ለመ
ወሰን ፡ ይረዳቸው ፡ ዘንድ ፡ የተለየ ፡ ሕግ ፡ ለማርቀቅም ፡ ይቻላል ።

<u>ዋና ፡ ሕግ ።</u>

ሕጐች ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ የማይሰጣቸውና ፡ በትክክልም ፡ የማይሰራባቸው፡
መሆኑን ፡ የመረመርናቸው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ ያስረዳሉ ። ሆኖም ፡ ሕጉን ፡
ለመረዳት ፡ አለመቻል ፡ በተለይም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ የፍትህ ፡ መጓደልን ፡
ማስከተሉ ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ።

በወንጀል ፡ ጉዳዮች ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አንዳንዶችን ፡ ድር
ጊቶች ፡ ከሌላው ፡ ለይቶ ፡ እንደ ፡ ወንጀል ፡ የመቁጠር ፡ ሥልጣን ፡ ከተሰጠው ፡ ቅጣት
መከተሉ ፡ ስለማይቀር ፡ አንድን ፡ ድርጊት ፡ ወንጀል ፡ ነው ፡ ከመባሉ ፡ በፊት ፡ ተሟል
ተው ፡ መገኘት ፡ ያለባቸው ፡ ነገሮች ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ካለመቻል ፡ የተነሳ ፡ ፍትህ ፡
ሊጓደል ፡ ይችላል ።

ይህን ፡ ሁኔታ ለማሻሻል ፡ በዝቅተኛ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ስለሚሰሙት ፡
ወንጀሎች ፡ የሚናገሩት ፡ የሕግ ፡ ክፍሎች ፡ በሙሉ ፡ ተለቅመው ፡ ከተጠናቀሩ ፡ በኋላ
ለዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዳኞች ፡ ጠበቆችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ ማደል ፡ ያስፈልጋል ።
እነዚህ ፡ አነስተኛ ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ ዳኞቹን ፡ አግባብ ፡ ያለውን ፡ ጭብጥ ፡ በመመ
ርመር ፡ ረገድ ፡ ይረዷቸው ፡ ዘንድ ፡ መግለጫዎችንና ፡ ምሳሌዎችን ፡ መያዝ ፡ አለባ
ቸው ። በነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ባሉ ፡ አርእስተ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ የበላይ ፡ ፍርድ ፡
ቤቶች ፡ የሰጧቸው ፡ ውሳኔዎችም ፡ በጠቅላላ ፡ ለዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፡
መላክ ፡ አለባቸው ።

ሕጐቹን ፡ በትክክል ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በርግጥ ፡ ትምህርት ፡ አስፈላጊ ፡
ነው ። ግን ፡ ትምህርት ፡ ሊያገኙ ፡ የሚችሉት ፡ ዳኞች ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ስለሆኑ ፡
ይህ ፡ መምሪያ ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ቢወጣ ፡ በገጠር ፡ ለሚገኙ ፡ ዳኞችም ፡ ለመድረስ፡
ስለሚችል ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ በመጠኑ ፡ ሊያሻ
ሽለው ፡ ይችላል ።

የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ጉዳይ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴርን ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ጠበቆች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ በመተቸት ፡ ረገድ ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ የሕግ ፡ ባለሙያዎች ፡ የሚሠሩትን ፡ ሥራ ፡ አይሠሩም ። ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ ከውጭ ፡ ሆነው ፡ ወዲያውም ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ የውስጥ ፡ ሥራ ፡ በቅርብ ፡ የሚያውቁ ፡ ነፃ ፡ የሆኑ ፡ ተመልካቾች ፡ የሉትም ። የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጠበቆችን ፡ ሰብስቦ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ካጠናቸው ፡ በኋላ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ለማሻሻል ፡ የሚረዱ ፡ ሀሳቦችን ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ኃላፊነት ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

ዳኞችና ፡ ጠበቆች ፡ የዳኝነቱ ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ ምሰሶዎች ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ በጠቅላላው ፡ የሥራ ፡ አካሄድ ፡ ላይ ፡ መጠነኛ ፡ ቁጥጥር ፡ ለማድረግ ፡ የሚችሉ ፡ መሆናቸው ፡ ይሰማቸው ፡ ዘንድ ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በየጊዜው ፡ ውይይቶችንና ፡ ስብሰባዎችን ፡ ሊያዘጋጅላቸው ፡ ይገባል ።

## ተጨማሪ ፩

## ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ጉዳዮችና ፡ አያያዛቸው ።

### መግቢያ ።

በአንድ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚገኙት ፡ ፋይሎች ፡ በቡድን ፡ በተከፋፈሉ ፡ በሕግ ፡ ተማሪዎች ፡ ተመርምረዋል ። በወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ (ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ "ወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት" ፡ ተብሎ፡ የሚጠራው)፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ አንድ ፡ ሃያኛው፡ ጉዳይ ፡ በዳይጀስት ፡ (Digest)፡ መልክ ፡ ተዘጋጅቷል ። ከዚሁ ፡ ዓመተ ፡ ምህረት ፡ ውስጥ ፡ መናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ አሥረኛው ፡ ጉዳይ ፡ በዳይጀስት ፡ መልክ ፡ ተዘጋጅቷል ። ስለዚህም ፡ የተሰሙት ፡ የፍርድ፡ ጉዳዮች ፡ ዓይነት ፡ ከመቶ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ የተገመቱት ፡ እጅ ፡ እንዳመጣሽ ፡ ከተመረጡ ፡ ጉዳዮች ፡ ስለሆነ ፡ እንደግምት ፡ መወሰድ ፡ አለባቸው ።

ሆኖም ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ባሉት ፡ ክፍሎች ፡ የተጠቀሱት ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ለአንባቢው ፡ የአንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ዓይነት ፡ ከመቶ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከመጥቀስ ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ መረጃ ፡ እንዲሰጡ ፡ የታቀዱ ፡ ናቸው ። በወረዳና ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መዝገብ ፡ ቤቶች ፡ ያሉትን ፡ ጉዳዮች ፡ መመርመር ፡ በበታች ፡ ፍርድ፡ ቤቶች ፡ ያሉትን ፡ ችግሮች ፡ ለይቶ ፡ ለማወቅ ፡ ይረዳል ።

"የተጠቀሱ ፡" "መሠረት ፡ የሆኑ ፡" ወይም ፡ "የተወሱ ፡" የተባሉት ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ የሚያመለክቱት ፡ ጠበቆች ፡ ጸሐፊዎች ፡ ወይም ፡ ተሟጋቾች ፡ በማመልከቻቸው ፡ ውስጥ ፡ የጠቀሷቸውን ፡ አንቀጾች ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ዳኞች ፡ ፍርድ ፡ በሚሰጡበት ፡ ጊዜ ፡ በአቤቱታዎች ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ትተው ፡ባልተገለጹ ፡ ምክንያቶች ፡ በመመራት ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚወስኑበት ፡ ጊዜ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ። የተደነገገው ፡ ሕግ ፡ በሚገባ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ባልዋለበት ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ማንኛውም ፡ በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚገኝ ጠበቃ ፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ ተሟጋች ፡ ሕጉን ፡ በሚገባ ፡ አያውቅም ፡ ለማለት ፡ ያስችላል ።

### የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኘው ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የሚያጠቃልለው ፡ ዘመናዊ ፡ የንግድና ፡ የመደብር ፡ ቦታን ፡ ዘመናዊ ፡ መኖሪያ ፡ ሠፈርንና ፡ የአገሬውን ፡ የመኖሪያና ፡ የገበያ ፡ ቦታ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ወደዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ከሚመነጩት ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ የተውጣጡ ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሁለት ፡ ችሎት ፡ አለው ፡- እነርሱም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔርና ፡ የወንጀል ፡ ሲሆኑ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አንዳንድ ፡ ዳኛ ፡ አላቸው ።

## የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ።

በወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረቡት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ በግምት ፡ ሰላሳ ፡ ዘጠኙ ፡ በመቶው ፡ የሚመለከቱት ፡ በግለሰቦች ፡ መካከል ፡ የተደረገ ፡ ብድርና ፡ ዱቤ ፡ አለመክፈልን ፡ ሲሆን ፡ አሥራ ፡ ሶስት ፡ በመቶው ፡ የሚመለከቱት ፡ ኪራይ ፡ አለ መክፈልን ፤ አሥራ ፡ ሁለት ፡ በመቶው ፡ ደግሞ ፡ በአሠሪዎችና ፡ በሠራተኞች ፡ መካ ከል ፡ በሚነሳው ፡ ጠብ ፡ በተለይም ፡ ሠራተኛው ፡ ከሥራ ፡ ሲሰናበት ፡ የሚከፈለውን ፡ ኪሳራ ፡ ባለመክፈል ፡ ሲሆን ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ በመቶው ፡ ደግሞ ፡ ታክስን ፡ ባለመክ ፈል ፡ የሚነሱ ፡ ክርክሮች ፡ ናቸው ። የቀሩት ፡ ሃያ ፡ በመቶው ፡ ደግሞ ፡ የሚመለከቱት፡ የዕቁብ ፡ ክፍያን ፡ ዋስትናን ፡ የልጅ ፡ ማሳደጊያን ፡ በንብረት ፡ ክፍያ ፡ የሚመጣው ፡ የጋብቻ ፡ ጠብ ፡ እንዲሁም ፡ ውሎችን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የማጽደቅን ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። በመጨረሻም ፡ ከቀረው ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ በመቶው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ክሶች ፡ የሚ መለከቱት ፡ የተሸጠን ፡ ዕቃ ፡ አለማስረከብንና ፡ በንብረት ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ ካሣን ፡ መጠየቅ ፡ ነው ። በወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ተደጋግመው ፡ እንደመጡበት ፡ ተራ ፡ ይብራራሉ ። የመጨረሻዎቹ ፡ ጉዳዮች ፡ ዓይ ነት ፡ ማለት ፡ የንብረት ፡ ጉዳትና ፡ የተሸጠ ፡ ዕቃን ፡ አለማስረከብ ፡ የሚመለከቱ ትን ፡ (በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ስለሆኑና ፡ ከነርሱም ፡ ጠቃ ሚ ፡ መደምደሚያ ፡ ለማግኘት ፡ ስለማይቻል) ፡ አንነጋገርባቸውም ።

## ከብድር ፡ የሚመነጩ ፡ ዕዳዎች ።

የአብዛኛዎቹ ፡ ዕዳዎች ፡ ምክንያቶች ፡ በግለ ፡ ሰቦች ፡ መካከል ፡ የተደረጉ ፡ ጥቃ ቅን ፡ ብድሮች ፡ ናቸው ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ መበደሩን ፡ ያምናል ፡ ወይንም ፡ በተጻፈው ፡ ውል ፡ ብድሩ ፡ ይረጋገጣል ፡ ወይንም ፡ ተከሳሹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለመቅ ረቡ ፡ በሌለበት ፡ ይበየንበታል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ክሱ ፡ የሚነሳው ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ሳይስማ ሙበት ፡ ሲቀሩ ፡ ነው ።

በእንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥ ፡ ዋናው ፡ የነገሩ ፡ ጭብጥ ፡ የፍሬ ፡ ነገር ፡ ጉዳይ ፡ ስለሆነ ፡ በምስክሮች ፡ ወይም ፡ በይሆናል ፡ ይረጋገጣል ። ምንም ፡ ያህል ፡ የሕግ ፡ መተርጐም ፡ ስለማያስፈልግ ፡ ጉዳዮቹ ፡ ሲመረመሩ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ የሚገኘው፡ ማመልከቻዎችን ፡ የጻፉት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ተሟጋቾች ፡ ወይም ፡ ዳኞች ፡ እምብዛም ፡ እንዳልደከሙበት ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። ዋናዎቹ ፡ ጥያቄዎች ፡ ብድር ፡ ነበር ፡ ወይ ? ካለስ ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ተከሳሹ ፡ ገንዘቡን ፡ ከፍሏል ፡ ወይ ? የሚ ሉት ፡ ስለሆኑ ፡ በማንም ፡ ዘንድ ፡ የሕግ ፡ መተርጐም ፡ እምብዛም ፡ አላስፈለገም ።

ይህን ፡ እላይ ፡ ያልነውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ አንድ ፡ ዓይነተኛ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ ወስደን ፡ በመጀመሪያ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፤ ቀጥሎም ፡ በማመልከቻዎችና ፡ በዳኛው ፡ ውሳ ኔዎች ፡ የተሰጡትን ፡ ቁጥሮች ፡ እንመርምር ።

ከሳሹ ፡ ጉዳዩን ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀረበው ፡ በጽሑፍ ፡ በተደረገ ፡ ውል ፡ መሠ ረት ፡ ያበደረውን ፡ ፩፻፴ ፡ ብር ፡ ተከሳሹ ፡ አልከፍልም ፡ ብሎኛል ፡ በማለት ፡ ነው ። ክሱ ፡ መጀመሪያ ፡ ሊሰማ ፡ በተቀጠረበት ፡ ቀን ፡ ተከሳሹ ፡ ስላልቀረበ ፡ ከሳሹ ፡ ለተ ከሳሹ ፡ መጥሪያና ፡ የክሱን ፡ ግልባጭ ፡ እንዲሰጠው ፡ ዳኛው ፡ አዘዘ ። ክሱ ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ በሚሰማበት ፡ ቀን ፡ ከሳሹም ፡ ተከሳሹም ፡ አልቀረቡም ። በመጨረሻም ፡ ክሱ ፡ ለሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሲሰማ ፡ ይኸውም ፡ ከሳሽ ፡ ክሱን ፡ በከፈተ ፡ በአራተኛው ፡ ወር ፡

ዳኛው ፡ ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ ለከሳሽ ፡ ፈረደለት ። ፍርዱ ፡ የተመሠረተው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፰ ፡ ፩ሺ፮፻፸፱ ፡ እና ፡ ፪ሺ፹፰ ፡ ላይ ፡ ነበር ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ብድርን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥሮች ፡ አጭር ፡ መግለጫ ፡ መስጠት ፡ ያስፈልጋል ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፬፻፸፩ ፡ "ብድር" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ሲተረጉም ፤ "የሚያልቅ ፡ ነገር ፡ ብድር ፡ ማለት ፡ ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ አበዳሪው ፡ ሌላውን ፡ ተበዳሪ ፡ ሰው ፡ የተበደረውን ፡ ነገር ፡ በዓይነቱ ፡ ለመመለስ ፡ ተገዳጅ ፡ በማድረግ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በማገልገል ፡ የሚያልቅ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ለተበዳሪው ፡ ለመስጠትና ፡ ሀብትነቱን ፡ ለማስተላለፍ ፡ የሚገደድበት ፡ ውል ፡ ነው ።" ይላል ።

ብድር ፡ "ውል ፡" ስለሆነ ፡ በጠቅላላው ፡ ውሎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ደንቦች ፡ የብድር ፡ ጉዳዮችንም ፡ ይመለከታሉ ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፮፻፸፮) ።

ቁጥር ፡ ፩ሺ፮፻፸፭ ፡ ውልን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይተረጉመዋል ፤

"ውል ፡ ማለት ፡ ንብረታቸውን ፡ የሚመለከቱ ፡ ግዴታዎችን ፡ ለማቋቋም ፡ ወይም ፡ ለመለወጥ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ ባላቸው ፡ ተወዳዳሪ ፡ ግንኙነት፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ ስምምነት ፡ ነው ።"

እላይ ፡ እንደ ፡ ምሳሌ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ጉዳይ ፡ ዓይነት ፡ ዳኞችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ በሚወስኑበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ዐቢይ ፡ መሠረተ ፡ ሀሳብ ፡ ማስታወስ ፡ እንዳለባቸው ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ "አንድ ፡ ሰው ፡ ለሌላው ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ማበደሩንና ፡ በውሉም ፡ መሠረት ፡ ተበዳሪው ፡ አልከፍልም ፡ ማለቱን ፡ ካረጋገጠ ፡ አበዳሪው ፡ ከተበዳሪው ፡ ገንዘቡን ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ አለው ።"

መሠረተ ፡ ሀሳቡ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ችግሩ ፡ ይህን ፡ ከሕጉ ፡ ቁጥሮች ፡ ጋር ፡ ማዛመድ ፡ ነው ። ለፍሬ ፡ ነገር ፡ ጭብጦች ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠት ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ለውሳኔው ፡ ሕጋዊ ፡ መሠረት ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

በያዝነው ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ውል ፡ መኖሩን ፡ ለማስረዳት ፡ የሚያስችለው ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፰ ፡ እንደ ፡ መሠረት ፡ ተወስዷል ፤

"(፩) የጽሑፍ ፡ ሰነድ ፡ በላዩ ፡ ስለሚገኘው ፡ የስምምነት ፡ ቃል ፡ እንዲሁም ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ስለተጻፈው ፡ ቀን ፡ በተፈራራሚዎቹ ፡ መካከል ፡ ሙሉ፡ እምነት ፡ የሚጣልበት ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ነው ።

"(፪) እንዲሁም ፡ በእንደራሴ ፡ በተፈጸሙላቸው ፡ ሰዎች ፡ በኩልና ፡ የተዋዋዮቹ ፡ ወገኖች ፡ ወራሾች ፡ በሆኑት ፡ ዘንድ ፡ ሙሉ ፡ እምነት ፡ የሚጣልበት ፡ በቂ ፡ ማስረጃነት ፡ አለው" ።

"በኛ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈ ፡ ውል ፡ ስለነበር ፡ በጽሑፍ ፡ በሰፈሩት ፡ ነገሮች ፡ ስምምነት ፡ ነበር" ፡ ለሚለው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ቁጥር ፡ አግባብ ፡ አለው ።

ቀጥሎ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፮፻፸፱ ፡ ነበር ። ይህም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

"ውል ፡ ተዋዋዮች ፡ በገቡባቸው ፡ ግዴታዎችና ፡ እነዚህም ፡ አስገዳጅ ፡ እንዲሆኑ ፡ የተስማሙበትን ፡ በሚገልጸው ፡ የፈቃድ ፡ መስጠት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።"

ፈቃድ ፡ መስጠት ፡ ለሕጋዊ ፡ ውል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፤ ሆኖም ፡ የፈቃድ መኖር ፡ ወይም ፡ አለመኖር ፡ የነገሩ ፡ ጭብጥ ፡ ስላልነበር ፡ የዚህ ፡ ቁጥር ፡ መጠቀስ ፡ ለጉዳዩ ፡ እምብዛም ፡ አግባብ ፡ የለውም ።

በመጨረሻም ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፳፰ ፡ ተጠቅሷል ።

"ማንም ፡ ሰው ፡ ከራሱ ፡ ጥፋት ፡ የተነሳ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ካደረሰ ፡ ላደረገው ፡ ጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ መክፈል ፡ አለበት" ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ደንብ ፡ የሚገኘው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ ሥር ፡ ነው ፤ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚደርስ ፡ አላፊነትና ፡ ያላግባብ ፡ ስለመበልጸግ ፡ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፴፯ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

"(፩) አንድ ፡ ሰው ፡ በአንድ ፡ ውል ፡ ምክንያት ፡ የመጣበትን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽም ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ለሆነ ፡ ነገር ፡ አላፊነት ፡ የሚያስከትልበትን ፡ ጥፋት ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ አይቆጠርበትም ።

(፪) እንዲህም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የውል ፡ አለመፈጸም ፡ ደንብ ፡ ብቻ ፡ ተፈጻሚ ፡ ይሆናል ።"

ይህ ፡ ከሆነ ፡ ሕጉ ፡ በጠቅላላ ፡ አገባቡ ፡ ካልተነበበ ፡ በስተቀር ፡ ይህ ፡ ቁጥር ፡ መሠረታዊ ፡ ሀሳብ ፡ ስለሚሰጥ ፡ ትክክለኛና ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ቢመስልም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፳፰ ፡ አሁን ፡ ለያዝነው ፡ ጉዳይ ፡ አግባብ ፡ የለውም ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያበደረውን ፡ ገንዘብ ፡ ተበዳሪው ፡ አልከፍልም ፡ ሲለው ፡ ገንዘቡን ፡ እንዲያገኝ ፡ የሚያስችለው ፡ ሕጋዊ ፡ መሠረት ፡ በውሳኔው ፡ ውስጥ ፡ አልተጠቀሰም ።

ስለ ፡ ውሎች ፡ ውጤትና ፡ (ቁጥር ፡ ሺ፯፻፳፫) ፡ ውልን ፡ አለመፈጸም ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ አልተጠቀሱም ። በዚህ ፡ ምትክ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በስህተት ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ የውል ፡ ግንኙነቶች ፡ አግባብ ፡ ያላቸው ፡ የሚመስሉ ፡ ሌሎች ፡ ቁጥሮች ፡ ተጠቅሰዋል ።

ከተመረመሩት ፡ የብድር ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፤

"በሕጉ ፡ አግባብ ፡ የተቋቋሙ ፡ ውሎች ፡ ባቋቋሚቻቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ሕግ ፡ ናቸው ።" የሚለውን ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፴፩ ፡ (፩)ን

ወይም

"(፩) ከተዋዋዮቹ ፡ አንዱ ፡ የውሉን ፡ ግዴታ ፡ ያልፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አጋጣሚ ፡ ሁኔታ ፡ ውሉን ፡ እንዲፈጽምለት ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላል ፤ ይህም ፡ ባይሆን ፡ የውሉን ፡ መፍረስ ፡ ራሱ ፡ ሊጠይቅ ፡ ወይም ፡ ሊገልጽ ፡ ይችላል ።

(፪) በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የውሉ ፡ አለመፈጸም ፡ ጉዳይ ፤ ጉዳት ፡ ስላደረሰበት ፡ የጉዳት ፡ ኪሣራ ፡ እንዲከፈለው ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ ይኖረዋል ።" የሚለውን ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፸፩ን ፤

ወይም ፡

"ተበዳሪው ፡ የተበደረውን ፡ ነገር ፡ በብዛቱና ፡ በዓይነቱ ፡ ልክ ፡ በውሉ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ለመመለስ ፡ ይገደዳል ።"

የሚለውን ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፬፻፸፪ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ን ፡ የጠቀሱ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።

ብድር ፡ መኖሩ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ተበዳሪው ፡ ያለበትን ፡ ዕዳ ፡ ላበዳሪው ፡ እንዲ ከፍል ፡ ይገደዳል ፡ የሚለውን ፡ አስተሳሰብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በይሆናል ፡ (በግምት) ፡ የተቀበሉት ፡ ይመስላል ።

ይህ ፡ ግምት ፡ በጣም ፡ ስር ፡ ስለሰደደ ፡ በማመልከቻዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚጠቀሱት ፡ ስለ ፡ ማመልከቻዎች ፡ ፎርምና ፡ በውስጣቸውም ፡ ስለሚሰፍሩ ፡ ነገ ሮች ፡ የሚናገሩት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ እና ፡ ፪፻፳፫ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። (ስለራፖር ፡ ጸሐፊዎች ፡ የተነገረውን ፡ ተመልከት) ።

የውል ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ በሕጉ ፡ ቁጥሮች ፡ በመጠ ቀም ፡ በተመሳሳይ ፡ ሁኔታ ፡ ተተርጉመዋል ። ከእንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ጉዳዮች ፡ ብዙዎቹ ፡ የሚመነጩት ፡ ከዕቁብ ፡ ማኅበሮች ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ማኅበሮች ፡ ገንዘብ ፡ መሰብሰቢያ ፡ ናቸው ። እያንዳንዱ ፡ ማኅበረተኛ ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ በየሳምንቱ ፡ ይሰጥና ፡ ዕጣ ፡ ይወጣል ። ዕጣው ፡ የደረሰው ፡ ሰው ፡ የተሰበሰበውን ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ ይወስዳል ። ሆኖም ፡ ሌሎች ፡ እቁብተኞች ፡ በሙሉ ፡ እስከደረሳቸው ፡ ድረስ ፡ ዳግመኛ ፡ ሊደርሰው ፡ አይችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ዕጣ ፡ የደረሰው ፡ ሰው ፡ የቀሩት ፡ እቁብተኞች ፡ በሙሉ ፡ እስ ኪደርሳቸው ፡ ድረስ ፡ በየሳምንቱ ፡ የሚደርስበትን ፡ ሳያቋርጥ ፡ መክፈል ፡ አለበት ። ከእንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ማኅበሮች ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ክሶች ፡ ሊፈጠሩ ፡ ይችላሉ ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉት ፡ ሁለት ፡ ምሳሌዎች ፡ የዕቁብ ፡ ዓይነተኛ ፡ ክሶች ፡ ናቸው ።

—ከሳሹ ፡ ዕጣ ፡ ስለወጣለት ፡ የዕቁብ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲሰጠው ፡ እቁብተኞቹን ፡ ከሰሳቸው ። መጥሪያ ፡ ስላልተሰጣቸው ፡ ተከሳሾቹ ፡ ክሱ ፡ መጀመሪያ ፡ በሚሰ ማበት ፡ ቀን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አልቀረቡም ። በሚቀጥለውም ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሾቹ ፡ አልተገኙም ፡ ሆኖም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የእቁብ ፡ ስምምነት ፡ መኖሩንና ፡ አሸናፊ ፡ ዕጣ ፡ የደረሰው ፡ መሆኑን ፡ ከሳሹን ፡ እንዲያስመሰክር ፡ አዘዘው ። በሚቀጥለው፡ ቀጠሮ ፡ ይኸውም ፡ ክሱ ፡ በተከፈተ ፡ በሦስተኛው ፡ ወር ፡ ተከሳሾቹ ፡ በሙሉ ፡ ቀርበው ፡ ስለነበር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለከሳሹ ፡ የሚደርሰውን ፡ ፲፰ ፡ ብር ፡ እንዲከ ፍሉ ፡ አዘዛቸው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ እና ፡ ፪፻፳፫ ፡ እንዲሁም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፪ ፡ ተጠቅሰዋል ።

—ተከሳሹ ፡ እቁብ ፡ ከደረሰው ፡ በኋላ ፡ የሳምንቱን ፡ ድርሻውን ፡ አልከፍልም ፡ አለ ። የቀሩት ፡ እቁብተኞች ፡ እሱንና ፡ ዋሶቹን ፡ የቀረበትን ፡ ፬፻፳ ፡ ብር ፡ እን ከፍሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረቧቸው ፡ ክሱ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በተሰማበት ፡ ዕለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለተከሳሹ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲደርሰው ፡ አዘዘ ። በሁለተኛው፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሹ ፡ የእቁብ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ለእቁብተኞቹ ፡ ለመቆም ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ እንዲያረጋግጥ ፡ ጠየቀ ። በሚቀጥለው ፡ ቀጠሮ ፡ ለነገረ ፡ ፈጁ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠበት ፡ ማስረጃ ፡ ቢቀርብም ፡ ተከሳሹ ፡ የውሉ ፡ ግልባጭ ፡ እን ዲሰጠው ፡ ስለጠየቀ ፡ ይህ ፡ ግልባጭ ፡ እስኪሰጠው ፡ ቀጠሮ ፡ ተደረገ ። በአራተ ኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሹ ፡ አለብህ ፡ የተባለው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲረጋገጥለት ፡ ጠየቀ፡ በአምስተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ከሳሹ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጠው ፡ አመለከተ ። ክሱ ፡ በተ ከፈተ ፡ በስድስተኛው ፡ ወር ፡ የጠየቁት ፡ ፬፻፳ ፡ ብር ፡ ለከሳሾቹ ፡ እንዲከፈላ ቸው ፡ ውሳኔ ፡ ተሰጠ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፭ ፡ ፪ሺ፳፰ ፡ እና ፡ ፩ሺ፱ ፻፳ እንዲሁም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ ፪፻፳፫ ፡ እና፡፯፪ ፡ ተጠቅሰዋል ።

እዚህም ፡ ላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ቁጥሮች ፡ ወደ ፡ ጉዳዩ ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ አይዘልቁም ። በዕቁብተኞቹ ፡ መካከል ፡ የተጻፈ ፡ የእቁብ ፡ ውል ፡ በሚገኝባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ

ከሳሾች ፡ ይበልጡን ፡ ጊዜ ፡ የጠቀሱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፭ን ፡ ነው ። ማኅበሩ ፡ የተቋቋመው ፡ በቃል ፡ ስምምነት ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ ይበልጥ ፡ የሚጠቅ ሰው ፡ ቁጥር ፡

"በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ደንቦች ፡ መሠረትና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ደንብ ፡ ላይ ፡ በተገለጸው ፡ ድንጋጌ ፡ ዓይ ነት ፡ በጽሑፍ ፡ በምስክር ፡ በሕሊና ፡ ግምት ፡ በተከራካሪው ፡ ወገን ፡ እም ነት ፡ ወይም ፡ በመሐላ ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ።" የሚለው ፡ ቁጥር፡ ፪ሺ፪ ፡ ነበር ።

ሆኖም ፡ በብድር ፡ ጉዳዮች ፡ እንዳየነው ፡ ገንዘብ ፡ ለማስመለስ ፡ መብት ፡ መሠ ረት ፡ የሚሰጥ ፡ ምንም ፡ ቁጥር ፡ አልተጠቀሰም ። ዋጋ ፡ ያለው ፡ የእቁብ ፡ ስምምነት ፡ መኖሩ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ከሳሹ ፡ ስምምነቱን ፡ ካላከበረው ፡ ሰው ፡ ገንዘቡን ፡ ወዲያውኑ፡ ለማስመለስ ፡ ይችላል ። በተጨማሪም ፡ "ከጥፋት" ፡ ስለሚመጣው ፡ ኪሣራ ፡ የሚ ያትተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፳፰ ፡ ለዚህ ፡ መብት ፡ መሠረት ፡ ሆኖ ፡ አንዳ ንድ ፡ ጊዜ ፡ ተጠቅሷል ፤ ከላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ የነገሩ ፡ ጭብጥ ፡ የውል ፡ ግዴ ታን ፡ ስላለመፈጸምና ፡ ስለሚከተለው ፡ ኪሣራ ፡ ሲሆን ፡ ይህን ፡ ቁጥር ፡ መጥቀስ ፡ ስህ ተት ፡ ነው ።

## <u>የቤት ፡ ኪራይ ።</u>

እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረቡት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ በብዛት ፡ ሁለተኛውን ፡ ደረጃ ፡ የያዘው ፡ የቤት ፡ ኪራይ ፡ አለመክ ፈል ፡ ጉዳይ ፡ ነበር ። የሚቀጥለው ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ተከሳሹ ፡ ባልተጻፈ ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ ለከሳሹ ፡ የሚገባውን ፡ የኢት፡ ፸፬ ፡ ብር ፡ የቤት ፡ ኪራይ ፡ ስላልከፈለ ፡ ተከሰሶ ፡ ክሱ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በተሰማ በት ፡ ዕለት ፡ ተከሳሹ ፡ ስላልቀረበ ፡ ከሳሹ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዘዘ ። በሁለተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሹ ፡ ስላልቀረበ ፡ ፭ ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ ተጣለበት ። በሦስተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ይኸውም ፡ ክሱ ፡ በተከፈተ ፡ በአራተኛ ፡ ወር ፡ ተከሳሽ ፡ በሌ ለበት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለከሳሽ ፡ ፈረደለት ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ እና ፡ ፪፻፳፫ ፡ በማመልከቻው ፡ ላይ ፡ ተጠቅሰዋል ።

በብድር ውሎች ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ የቤት ፡ ኪራይ ፡ ውሎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ልዩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ደንቦች ፡ አሉ ። ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፱፻፵፭ ፡ የነዚህን ፡ ውሎች ፡ አገባብ ፡ ሲወስን ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

"(፩) የአከራይና ፡ የተከራይ ፡ ውል ፡ ቤትን ፡ ከነዕቃው ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ባለክፍሎች ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ሕንፃ ፡ ወይም ፡ የሕንፃ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ለመከራየት ፡ ሲሆን ፡ የዚህ ፡ ክፍል ፡ ደንቦች ፡ ተፈጻሚዎች ፡ ይሆ ናሉ ።

(፪) በዚህ ፡ ሕግ ፡ አገልግሎት ፡ መስጠትን ፡ ስለሚመለከቱ ፡ ውሎች ፡ የተነገሩት ፡ ስለ ፡ ሆቴል ፡ ውል ፡ የተደነገጉት ፡ ደንቦች ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው። (ቁጥር ፡ ፪ሺ፮፻፶፫—፪ሺ፮፻፸፩) ።"

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፱፻፶፩ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

"(፩) የኪራይ ፡ ውል ፡ ለአንድ ፡ ወይም ፡ ለብዙ ፡ ዓመታት ፡ ተደርጎ ፡ እንደሆነ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ የውል ፡ ቃል ፡ ከሌለ ፡ በየሦስት ፡ ወር መጨረሻ ፡ የሚከፈል ፡ ይሆናል ።

(፪) ውሉ ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ለሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ላልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ተደርጎ ፡ እንደሆነ ፡ በየወሩ ፡ መጨረሻ ፡ የሚከፈል ፡ ይሆናል ።

(፫) በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ኪራዩ ፡ የውሉ ፡ ጊዜ ፡ ሲያልቅ ፡ (ሲያቆም) ፡ መከፈል ፡ አለበት ።"

የኪራዩ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ ተከራዩ ፡ ሳይከፍል ፡ ሲቀር ፡ ሁኔታው ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ የሚመለከተው ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፱፻፶፪ ፡ ነው ፤

"(፩) የኪራዩ ፡ መክፈያ ፡ ጊዜ ፡ ደርሶ ፡ ተከራዩ ፡ በተባለው ፡ ጊዜ ፡ ከመክፈል ፡ የዘገየ ፡ እንደሆነ ፡ የኪራዩ ፡ ውል ፡ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ ለሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ተደርጎ ፡ እንደሆነ ፤ አከራዩ ፡ የሠላሳ ፡ ቀን ፡ ጊዜ፡ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጥቶ ፡ ውሉ ፡ ለአነስተኛ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሆነም ፡ የአሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ሰጥቶ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ሳይከፍል ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ የሚፈርስ ፡ መሆኑን ፡ ለተከራዩ ፡ ሊያስታውቀው ፡ ይችላል ፡

(፪) የጊዜው ፡ መቆጠር ፡ የሚጀምረው ፡ ተከራዩ ፡ የአከራዩን ፡ ማስታወቂያ ፡ ከተቀበለበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ ነው ።

(፫) እነዚህን ፡ ጊዜዎች ፡ የሚያሳጥሩ ፡ ወይም ፡ ኪራዩ ፡ ባለመከፈሉ ፡ ምክንያት ፡ ወዲያው ፡ ውሉን ፡ የማፍረሱ ፡ መብት ፡ ለአከራዩ ፡ የሚሰጡ ፡ የውል ፡ ቃሎች ፡ ፈራሾች ፡ ናቸው ፡ (ዋጋ ፡ የላቸውም) ።"

የቤት ፡ ኪራይ ፡ አለመክፈልን ፡ የሚመለከቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ደንቦች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ሆኖም ፡ መታወስ ፡ ያለበት ፤ ኪራዩ ፡ ውል ፡ ስለሆነ ፡ ስለውሎች ፡ በጠቅላላው ፡ አፈጻጸም ፡ የሚቆጣጠሩት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደንቦች ፡ (ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፵—፩ሺ፯፻፸፪) ፡ የውል ፡ አለመፈጸም ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ (ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፸፩ — ፩ሺ፰፻፭) ፡ እና ፡ የውልን ፡ ጉዳይ ፡ ስለሚመለከት ፡ ማስረጃ ፡ (ቁጥር ፡ ፪ሺ፩ — ፪ሺ፲፱) ፡ የኪራይ ፡ ውልን ፡ ይመለከታሉ ።

ይህንን ፡ በማስታወስ ፡ በወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአብዛኛው ፡ በኪራይ ፡ ጉዳይ፡ ክርክሮች ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ እንመርምር ።

የቤት ፡ ኪራይ ፡ አለመክፈልን ፡ የሚመለከቱ ፡ በአብዛኞቹ ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ እና ፡ ፪፻፳፫ ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ በማመልከቻዎች ፡ ውስጥ ፡ መስፈር ፡ ስላለባቸው ፡ ነገሮች ፡ የሚናገሩ ፡ ናቸው ።

ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ እና ፡ ፪፻፳፫ ፡ ሌላ ፡ በተጨማሪ ፡ የተጠቀሱ ፡ ቁጥሮች ፡ ቢኖሩ ፡ ይበልጡን ፡ ጊዜ ፡ ተጨማሪው ፡ ቁጥር ፡ ስለ ፡ ጽሑፍ ፡ ማስረጃ ፡ በቂነት ፡ የሚመለከተው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፰ ፡ ነበር ።

እላይ ፡ ተጠቅሶ ፡ የነበረው ፡ የኪራዩን ፡ አገባብ ፡ የሚተረጉመው ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፱፻፵፰ ፡ ቀጥሎ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህም ፡ ቁጥር ፡ ቢሆን ፡ ገንዘብ ፡ ለማስመለስ ፡ መብት ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ መሠረት ፡ አይሰጥም።

በቅድሚያ ፡ ስምምነት ፡ ሳይኖር ፡ ኪራዩ ፡ የሚከፈልበት ፡ ጊዜ ፡ ከደረሰ ፤ ይህን ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከተው ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፱፻፶፩ ፡ እና ፡ ኪራይ ፡ አለመክፈል ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ የሚገልጸው ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፱፻፶፪ ፡ በተወሰዱት ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ አግባብ ፡ ያላቸው ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ እምብዛም ፡ አልተጠቀሱም፤ ውል ፡ አለመፈጸም ፡ የሚያስከትለውን ፡ ገንዘብ ፡ የማስመለስን ፡ መብት ፡ የሚመለከቱት ፡ ቁጥሮች ፡ (ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፹፩—፩ሺ፰፻፰) ፡ ፈጽሞ ፡ አልተጠቀሱም ።

ስለዚህ ፡ በኪራይ ፡ አለመክፈል ፡ ጉዳዮችና ፡ የብድርን ፡ ውል ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የወሰናቸው ፡ ጭብጦች ፡ በተከራካሪዎቹ ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ መኖሩንና ፡ መከፈል ፡ በሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ ተከፍሎ ፡ እንደሆን ፡ የሚጠይቁ ፡ ነበሩ ። ዋናው ፡ ጭብጥ ፡ የከሳሹ ፡ የማስመለስ ፡ መብት ፡ ሕጋዊ ፡ መሠረቱ ፡ ምንድ ነው ? የሚል ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠው ፡ ለዚህ ፡ ጭብጥ ፡ አግባብ ፡ በሌላቸው ፡ ቁጥሮች ፡ በመመራት ፡ ነው ።

## <u>የሥራን ፡ ውል ፡ ስለማቋረጥ ።</u>

ያሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ጉዳይ ፡ በወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀጥሎ ፡ በብዛት ፡ የተሰማው ፡ የክስ ፡ ዓይነት ፡ ነበር ።

ከነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ብዙዎች ፡ ከሥራ ፡ ለተወገዱ ፡ ሠራተኞች ፡ አሠሪው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ አለመስጠቱን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነበሩ ። ሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ ደግሞ ፡ የሚመለከቱት ፡ ደሞዝ ፡ አለመክፈልንና ፡ አሠሪው ፡ የሆስፒታል ፡ ወጪ ፡ ለመክፈል ፡ ያለበትን ፡ ኃላፊነት ፡ ነበር ።

በእነዚህም ፡ ጉዳዮች ፡ ቁጥሮች ፡ እንደተገኙ ፡ ከመጠቀሳቸው ፡ ሌላ ፡ ለማስመለስ ፡ መብት ፡ ሕጋዊ ፡ መሠረት ፡ በክስ ፡ ማመልከቻዎችም ፡ ሆነ ፡ በዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ አልተጠቀሱም ።

> አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ሆቴል፡ አለበቂ፡ ምክንያትና፡ አለማስታወቂያ ፡ ከሥራ ፡ ተወግጃለሁ ፡ በሚል ፡ ሠራተኛ ፡ ተከሷል ። አሠሪው ፡ ማስታወቂያ ፡ ስላልሰጠው ፡ ሠራተኛው ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ ደመወዝ ፡ ጠይቋል ፡ የሆቴሉ ፡ ባለቤት ፡ ያቀረበው ፡ መከላከያ ፡ ደግሞ ፡ ከሳሹ፡ ከሥራ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይቀር ፡ ስለነበር ፡ ከሥራ ፡ የተወገደው ፡ በበቂ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፤ የሚል ፡ ነበር ። የከሳሽ ፡ ጠበቃና ፡ ምስክሮች ፡ በቀጠሮዎች፡ ሁሉ ፡ ስላልተገኙ ፡ ከአሥራ ፡ አንድ ፡ ወርና ፡ ከሰባት ፡ ቀጠሮ ፡ በኋላ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሳሽ ፡ ከሥራ ፡ የተወገደው ፡ በበቂ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ተከሳሹ ፡ ሆቴል ፡ ምንም ፡ አይጠየቅም ፡ ሲል ፡ ፈርዷል ። የፍትሐ ፡ ብሔር ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷፪ ፡ እና ፡ ፪፻፷፫ ፡ እና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፪ ፡ ፪ሺ፭፻፸፩ ፡ እና ፡ ፪ሺ፭፻፸፫ ፡ ተጠቅሰዋል ።

የሥራ ፡ ውልን ፡ ማቋረጥ ፡ የሚመለከቱ ፡ ዋናዎቹ ፡ ደንቦች ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፭፻፷፰ — ፪ሺ፭፻፸፫ ፡ ናቸው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፭፻፷፰ ፡ በከፊል ፡ "ውሉን ፡ ቀሪ ፡ ለማድረግ ፡ አሠሪው ፡ ወይም ፡ ሠራተኛው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ አስቀድሞ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።" ይላል ። ቁጥር ፡ ፪ሺ፭፻፷፱ ፡ ደግሞ ፡ ለተለያዩ ፡ የቅጥር ፡ ሁኔታዎች ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ለመስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ጊዜ ፡ ያትታል ። አሠሪው ፡ ከፈለገ ፡ ሠራተኛው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ላልሞላ ፡ ጊዜ ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ሆነ ፡ ያንድ ፡ ወር ፡ ደመወዝ ፡ በመክፈል ፡ ወይም ፡ ሠራተኛው ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ ለበ

ለጠ ፡ ጊዜ ፡ ከሥራ ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ ደመወዝ ፡ በመክፈል ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ ማስታወቂያ ፡ ሳይሰጥ ፡ ሠራተኛውን ፡ ከሥራ ፡ ሊያሰናብተው ፡ ይችላል ።

የሥራ ፡ ውልን ፡ ስለማቋረጥ ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ የሚደጋገመው ፡ አቤቱታ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፭፻፸፭ ፡ የሚያዘው ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ አልተሰጠም ፡ ወይም ፡ በማስጠንቀቂያው ፡ ምትክ ፡ የሚሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ አልተከፈለም ፡ የሚል ፡ ነው ።

በእነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱት ፡ ቁጥሮች፡ በብድርና ፡ በኪራይ ፡ ጉዳዮች ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፭፻፸፭ን (ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት) ለማስመለስ መብት መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ጠቅሰዋል ፤ ጥቂቶቹ ፡ ደግሞ ፤ አለበቂ ፡ ምክንያት ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ለተቋረጠበት ፡ ሠራተኛ ፡ የሚከፈለውን ፡ ኪሣራ ፡ የሚወስነውን ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፭፻፸፫ን ጠቅሰዋል ። በተጨማሪ ፡ የተጠቀሱት ፡ በጠቅላላው ፡ ውል ፡ መኖሩን ፡ የሚያረጋግጡ ፡ ማስረጃዎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ቁጥሮች ፡ ናቸው ፡ (ቁጥር ፡ ፪ሺ፭ — ፪፲ሺ፱) ።

ሆኖም ፡ በተጠቀሱት ፡ ጉዳዮች ፡ በሙሉ ፡ አሠሪው ፡ ግዴታውን ፡ ለማስቀረት ፡ በሚሞክርበት ፡ ጊዜ ፡ ከባድ ፡ የሆኑ ፡ ግዴታዎች ፡ ስላልተፈጸሙልኝ ፡ ውሉን ፡ ለመሰረዝ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አለኝ ፡ በማለት ፡ የሚያቀርበውን ፡ መከላከያ ፡ የሚደግፍ ፡ ቁጥር ፡ አልተጠቀሰም ፡ (ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፭፻፸፱) ።

ማስጠንቀቂያ ፡ ባለመስጠትና ፡ አለበቂ ፡ ምክንያት ፡ ውልን ፡ ቀሪ ፡ በማድረግ ፡ ካሣ ፡ እንዲከፍሉ ፡ የተከሰሱ ፡ አሠሪዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚጠቀሙበት ፡ ብልሃት ፡ ከሳሽ ፡ ክሱን ፡ ለመተው ፡ ይገደዳል ፡ በሚል ፡ ተስፋ ፡ ነገሩን ፡ መጐተት ፡ ነው ።

የሚከተለው ፡ ለእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጉዳይ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ከሳሹ ፡ ለአንድ ፡ ኩባንያ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሠርቷል ። ማስጠንቀቂያ ፡ ወይም ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ ደመወዝ ፡ ሳይከፈለው ፡ ኩባንያው ፡ ከሥራ ፡ ስላስወገደው ፡ ከሳሹ ፡ አሠሪውን ፡ ከሰሰ ። ክሱ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በተሰማበት ፡ ዕለት ፡ የክስ ፡ ማመልከቻው ፡ ከሳሹ ፡ ይሠራ ፡ የነበረበትን ፡ ቦታ ፡ ስላልገለጸ ፡ የተሟላ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ተከሳሹ ፡ ስላመለከተ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ ተስተካክሎ ፡ እንዲጻፍ ፡ አዘዘ ። ክሱ ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሲሰማ ፡ የተከሳሽ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀረ ። በሦስተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሹ ፡ ለከሳሽ ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ በከፊል ፡ ከፍያለሁ ፡ ስላለ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተከሳሹ ፡ ኩባንያ ፡ የደሞዝ ፡ መክፈያ ፡ መዝገብ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ የተባለው ፡ እንዲረጋገጥ ፡ አዘዘ ። በሚቀጥሉት ፡ ሁለት ፡ ቀጠሮዎች ፡ ከሳሹ ፡ ስላልቀረበ ፡ ፋይሉ ፡ በተከፈተ ፡ በአሥራ ፡ አንደኛው ፡ ወር ፡ ተዘጋ ። የፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፴፪ ፡ እና ፡ ፪፻፴፫ ፡ እና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፵፫ ፣ ፪ሺ፭፻፸፫ ፡ እና ፡ ፪ሺ፭፻፸፬ ፡ ተጠቅሰዋል ።

ማስታወቂያ ፡ አለመስጠትና ፡ ካሣ ፡ መስጠትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ብዙ ፡ ሌሎች ፡ ጉዳዮችን ፡ ፋይል ፡ በተከፈተ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባልተገለጹ ፡ ምክንያቶች ፡ ዘግቷቸዋል ።

ያሠሪና ፡ የሠራተኞችን ፡ ግንኙነቶች ፡ የሚመለከቱት ፡ ሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ ስለ ፡ ደመወዝ ፡ አለመክፈል ፡ ነበሩ ። እነዚህ ፡ ክሶች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚመነጩት ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ከተደረጉ ፡ የሥራ ፡ ውሎች ፡ ሲሆን ፡ በመሠረቱ ፡ በእነዚህ ፡ ጉዳዮች፡ ላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ቁጥሮች ፡ በብድር ፡ ጉዳዮች ፡ የተጠቀሱት ፡ ቁጥሮች ፡ ናቸው ። ከእነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ በባለጉዳዮቹ ፡ በቀጠሮ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አለመቅረብ ፡ ምክንያት ፡ ፍጻሜ ፡ ያልደረሱ ፡ ናቸው ።

## ታክስ ፡ አለመክፈል ።

ታክስ ፡ አለመክፈልን ፡ የሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ በሌለበት ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ። ከእነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ብዙዎቹ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በወጣው ፡ በታክስ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የሥራ ፡ ግብርና ፡ የንግድ ፡ ታክስ ፡ ባለመክፈል ፡ የተነሱ ፡ ናቸው ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የታክስ ፡ ክሶች ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ባለመቅረቡ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውድቅ ፡ አድርጓቸዋል ። አንዳንዴም ፡ ለአምስት ፡ ወይም ፡ ለስድስት ፡ ወር ፡ ተከሳሹ ፡ ተፈልጎ ፡ ሳይገኝ ፡ ሲቀር ፡ ተከሳሹ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ያገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ክሱን ፡ እንደገና ፡ ለመክፈት ፡ ያለውን ፡ መብት በመጠበቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፋይሉን ፡ ይዘጋዋል ። እንዲሁም ፡ ተከሳሹ ፡ ሳይቀርብ ፡ በመቅረቱ ፡ ብዙ ፡ ቀጠሮዎች ፡ ከተሰጡ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ተከሳሹ ፡ ያለበትን ፡ የታክስ ፡ ዕዳ ፡ ከፍሎ ፡ በመገኘቱ ፡ ክሱ ፡ ውድቅ ፡ የሚሆንበት ፡ ጊዜ፡ አለ ።

## የልጅ ፡ ማሳደጊያና ፡ ሌሎች ፡ የቤተ ፡ ሰብ ፡ ችግሮች ።

የከተማ ፡ ኑሮ ፡ በልማዳዊው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ግንኙነቶች ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ፈተና ያስከትላል ። አባት ፡ የሌላቸውን ፡ ልጆች ፡ ማሳደጊያ ፡ የሚመለከቱት ፡ ክሶች ፡ መብዛት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ነዋሪዎች ፡ ልማዳዊ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ መቀራረብ ፡ አለመገኘቱን ፡ አጉልቶ ፡ ያሳያል ። እነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመነጩት ፡ ከተለያዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ ነው ። ሁለት ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌዎች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ተሰጥተዋል ።

> ተከሳሹ ፡ ሚስቱ ፡ ፍቺው ፡ ሲፈጸም ፡ ሊከፍላት ፡ የተስማሙበትን ፡ አልሰጥም ፡ አለ ። ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ በሁለት ፡ ተከታታይ ፡ ቀጠሮዎች ፡ ሳይቀርቡ ፡ ስለቀሩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱ ፡ በተከፈተ ፡ በሦስተኛው ፡ ወር ፡ ዘግቶታል ። ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ እና ፡ ፪፻፳፫ ፡ ጋር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፩ ፡ እና ፡ ፪ሺ፪ ፡ ተጠቅሰዋል ።

> ከሳሽዋ ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የነበራትን ፡ ሰው ፡ ከዚሁ፡ ግንኙነት ፡ የተወለዱትን ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ማሳደጊያ ፡ እንዲሰጣት ፡ ከሰሰችው ። ባለጉዳዮቹ ፡ ሳይቀርቡ ፡ ስለቀሩ ፡ ክሱ ፡ ከተከፈተ ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ተዘጋ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፪ ፡ እና ፡ ፪፻፳፫ ፡ እና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፪ ፤ ፪ሺ፳፯ ፡ እና ፡ ፲፻፹፩ ፡ ተጠቅሰው ፡ ነበር ።

የልጅ ፡ ማሳደጊያ ፡ ክሶች ፡ የሚመነጩባቸው ፡ ዋናዎቹ ፡ ሁኔታዎች ፡ በፍቺ ፡ ጊዜ ፡ የተደረጉት ፡ ስምምነቶች ፡ አልተከበሩም ፡ በማለት ፡ የሚቀርቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ናቸው ። በፍቺው ፡ ድርድር ፡ የተስማሙበትን ፡ ገንዘብ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ሳይከፍል ፡ በመቅረቱ ፡ በሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ የሚጠቀሱት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ቁጥሮች ፡ ውልን ፡ በጠቅላላው ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።

> ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ በሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ አማካይነት ፡ ተፋተዋል ። ባልየው ፡ በየወሩ፡ ፲፭ ፡ (አሥራ ፡ አምስት ፡ ብር) ፡ ለሚቀጥሉት ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡ ለሚስቱ ፡ ለመስጠት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ባሉበት ፡ በጽሑፍ ፡ ተስማምቷል ። ባልየው ፡ ይህንን ፡ ገንዘብ ፡ ለአሥራ ፡ አንድ ፡ ወራት ፡ ሳይከፍል ፡ በመቅረቱ ፡ ሚስቲቱ ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ያለበትን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበችው ። ቁጥር ፡ ፪ሺ፳፫ን ፡ በመመርኮዝ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በውሉ ፡ የተገለጸውን ፡ ገንዘብ፡ ተከሳሽ ፡ እንዲከፍል ፡ አዘዘ ።

ቁጥር ፡ ፩ሺ፳፰ ፡ የሚመለከተው ፡ "ጥፋት" ፡ የሚያስከትለውን ፡ ኪሳራ ፡ ስለ ሆነ ፡ አግባብ ፡ እንደሌለው ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

በተመሳሳይ ፡ ጉዳይ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፪ ፤ ፯፻፹፭ ፡ እና ፡ ፯፻ ፡ የው ሳኔው ፡ መሠረት ፡ ሆነዋል ። ቁጥር ፡ ፩ሺ፪ ፡ የሚናገረው ፡ ውል ፡ መኖሩን ፡ ለማስረ ዳት ፡ ስለሚቻልበት ፡ ዘዴ ፡ ነው ። ቁጥር ፡ ፯፻፹፭ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ከፍቺው ፡ በኋላ ፡ ሕጻናቱን ፡ ለማን ፡ እንደሚሰጡ ፡ የሚመሩበትን ፡ መሠረተ ፡ ሀሳብ ፡ የሚናገር ፡ ስለሆነ ፡ ስለ ፡ ገንዘብ ፡ መቀበል ፡ መብት ፡ በመጠኑ ፡ አግባብ ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል ።

ቁጥር ፡ ፯፻ ፡ የባልና ፡ ሚስትነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ አራት ፡ ምስክሮች ፡ ሊያስ ረዱ ፡ ይችላሉ ፡ ይላል ። በእንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ጉዳዮች ፡ የተጠቀሰው ፡ ሌላው ፡ ቁጥር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፺፱ ፡ ሲሆን ፡ "በከፊል ፡ የጋብቻው ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸ መበት ፡ ሥርዓት ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስና ፡ ይህ ፡ የሚያ ስከትለው ፡ ውጤት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ነው ፡" ይላል ። አንድ ፡ ዓይነት ፡ ግንኙነት ፡ መኖሩ ፡ ከተረጋገጠ ፡ የልጅ ፡ ማሳደግ ፡ ግዴታን ፡ ሊያስከትል ፡ ስለሚችል ፡ እነዚህ፡ ቁጥሮች ፡ ሊኖር ፡ የሚችለውን ፡ የገንዘብ ፡ መብት ፡ ሊያመለክቱ ፡ ይችላሉ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ቁጥሮች ፡ ብቻቸውን ፡ ገንዘብ ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አይሰጡም ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በመሠረቱ ፡ እነዚህ ፡ ክርክሮች ፡ በመጀመሪያ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መወሰን ፡ የለባቸውም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፳፰ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡

"(፩) ከመፋታት ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የሚነሳው ፡ ክርክር ፡ ለምርመራ ፡ የሚ ቀርበው ፡ የመፋታቱን ፡ ውሳኔ ፡ ለሰጡት ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ነው ።"

ከባልዋ ፡ ሳትፋታ ፡ ከቤቷ ፡ የተባረረችው ፡ ሚስት ፡ የግል ፡ ሀብቷንና ፡ ከግል ፡ ንብረታቸው ፡ ድርሻዋን ፡ ወይም ፡ ከጋብቻው ፡ የተገኙትን ፡ የልጆች ፡ ማሳደጊያ ፡ ልትጠይቅ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትመጣለች ። በዚህ ፡ ጥናት ፡ መሠ ረት ፡ እነዚህን ፡ ጉዳዮች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ይልካቸዋል ። የእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጉዳይ ፡ ማመልከቻዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚጠቅሳቸው ፡ ስለ ፡ ልጅ ፡ አጠባበቅ ፡ ውሳኔ ፡ የሚሆነውን ፡ የመሠረተ ፡ ሀሳብ ፡ መምሪያ ፡ የሚሰጠ ውን ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፹፩ንና ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፶፪ ፡ አንዳንድ ፡ ዓይነት ፡ ንብረቶችን ፡ "የጋራ ፡ ንብረቶች ፡" ብሎ ፡ የሚለየውን ፡ ነው ። እዚህም ፡ ውስጥ ፡ ቢሆን ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ መፋታት ፡ ሳይኖር ፡- ለመለያየት ፡ መስማማት ፡ ወይም ፡ በእርግጥም ፡ መለያየት ፡ ካለ ፡- ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ የጋብቻን ፡ ግንኙነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ እንዴት ፡ እን ደሚቆጣጠር ፡ ተሟጋቾች ፡ ጸሐፊዎችና ፡ ዳኞች ፡ አጣርተው ፡ አያውቁም ። በእንደ ዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጉዳዮች ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ በመጀመሪያ ፡ ጉዳዩን ፡ የማየት ፡ ሥል ጣን ፡ አላቸው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፳፭ ፡ በጋብቻ ፡ ጊዜ ፡ በባልና ፡ ሚስት ፡ መካከል ፡ የሚነሱትን ፡ ችግሮች ፡ መርምረው ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጡት ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ናቸው ፡ ይላል ።

## ተያገሮች ።

ብዙዎቹ ፡ የውል ፡ ጉዳዮች ፡- ብድርም ፡ ሆነ ፡ የሥራ ፡ አገልግሎት ፡ መስጠት ፡- ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ ለተስማሙት ፡ ሰዎች ፡ ዋስ ፡ የሚሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ የሚመ ለከቱ ፡ ናቸው ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ዋናው ፡ ባለ ፡ ዕዳ ፡ ግዴታውን ፡ ለመፈጸም ፡ ሳይ ችል ፡ ሲቀር ፡ ወይም ፡ ሊገኝ ፡ ካልቻለ ፡ ዋሱ ፡ ለከሳሹ ፡ ዕዳውን ፡ መክፈል ፡ አለበት ።

ተከሳሹ ፡ በጽሑፍ ፡ በሰፈረ ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ለከሳሽ ፡ የቤት ፡ አሽከር ፡ ተያዥ ፡ ነበር ፡ ስትል ፡ አመልክታለች ። አሽከርየው ፡ ከከሳሽ ፡ ቤት ፡ ገንዘብ ፡ ስለ

ሠረቀ ፡ ከሳሽ ፡ ተከሳሹን ፡ በ፺ ፡ ብር ፡ ከሳዋለች ። ከሁለት ፡ ቀጠሮ ፡ በኋላ ፡ ሁለ ቱም ፡ ወገኖች ፡ ሳይቀርቡ ፡ ስለቀሩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክሱን ፡ ሠርዞታል ። የተጠቀ ሰው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፲፯፻፳፫ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ከሳሹ ፡ የቤት ፡ ኪራይ ፡ አልተከፈለኝም ፡ ሲል ፡ ተከራዩንና ፡ ተያዡን ፡ ከሰሳ ቸው ፤ ለተከሳሽ ፡ መጥሪያ ፡ ተሰጥቶት ፡ አንድ ፡ ቀጠሮ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፤ የወ ረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ስላልነበረው ፡ ጉዳዩ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ወረዳ ፡ ተዛ ወረ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፰ ፡ እና ፡ ፪ሺ፱፻፶፰ ፡ ተጠቅሰዋል ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፰ ና ፡ ፪ሺ፱፻፶፰ ፡ የሚናገሩት ፡ በዋናው ፡ ውል ፡ ላይ ፡ ተያዡ ፡ ለባለ ፡ ዕዳው ፡ ተያዥ ፡ ለመሆኑ ፡ ሳይሆን ፡ የዋናውን ፡ ውል ፡ መመሥረት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለዋስትና ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፳፯ን ፡ የጠቀሱ ፡ ጉዳዮች ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ፤ ይህም ፡ ቁጥር ፡

> "ለግዴታው ፡ አፈጻጸም ፡ ዋስ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ባለ ፡ ዕዳው ፡ ግዴታውን ያልፈጸመ ፡ እንደሆነ ፤ ለባለ ፡ ገንዘቡ ፡ ይህን ፡ ግዴታ ፡ ሊፈጽም ፡ ይገደ ዳል ።" ይላል ።

ዋስትና፣አሁንም ፡ ሆነ ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ ሲወ ርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ ቋሚ ፡ ነገር ፡ ነው ። በ፲፱ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ አጋማሽ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የጐበኘ ፡ አንድ ፡ ተጓዥ ፡ "ዋስትና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕብረተ ፡ ሰብ ፡ ዋና ፡ ምሰሶ ፡ ነው ፤ አለሱ ፡ ማንኛውም ፡ የንግድ ፡ ወይም ፡ የገበያ ፡ መለዋወጥ ፡ አይፈ ጸምም ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ዕዳ ፡ ወለድና ፡ የንጉሡ ፡ ገቢ ፡ እንደሚከፈል ፡ የተረጋ ገጠ ፡ ነው ።" ሲል ፡ ጽፎአል ። (ሆትን ፡ ጂ ፡ ሲ ፡ <u>አቢሲኒያ ፡ ኤንድ ፡ ኢትስ ፡ ፒፕል</u> ፡- 1868 ፡ ገጽ ፡ 184) ።

ከዋስ ፡ የማስመለስ ፡ መብት ፡ የሚሰጡት ፡ የዘመናዊ ፡ ሕግ ፡ ደምቦች ፡ ተቀባይ ነት ፡ ያላገኙበት ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ አዕምሮ ፡ ውስጥ ፡ የአበ ዳሪ ፡ የተበዳሪና ፡ የዋስ ፡ ግንኙነቶች ፡ በጣም ፡ ሥር ፡ ስለሰደዱ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ዋናው ፡ የውል ፡ ግንኙነት ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ከተረጋገጠ ፡ ከዋሱ ፡ የማስመለስ ፡መብት፡ መኖሩ ፡ በግምት ፡ የተወሰደ ፡ ይመስላል ።

## <u>ውሎችን ፡ ማስመዝገብ ።</u>

በማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መብቶች ፡ የሚነካ ፡ ውል ፡ ሲፈ ጸም ፡ ተዋዋዮቹ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፳፫ ፡ መሠረት ፡ ውላቸውን፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ውል ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ሰው ፡ ማስመዝ ገብ ፡ ይኖርባቸዋል ።

—አመልካቾቹ ፡ ውል ፡ በመዋዋል ፡ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ላይ ፡ ፫፻ ፡ ብር ፡ ተበድሮአል ። በውሉ ፡ መሠረት ፡ አንደኛው ፡ አመልካች ፡ (አበዳሪው) ፡ የተበዳሪውን ፡ ቤት ፡ ለሦስት ፡ ዓመታት ፡ በይዞታው ፡ እንዲቆይ ፡ ተስማምተዋል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፳፫ ፡ መሠረት ፡ ውሉን ፡ አጸደቀው ።

—አንድ ፡ ሰው ፡ ቤቱን ፡ በ፳፻ ፡ ብር ፡ ወለድ ፡ አግድ ፡ ሊሰጥና ፡ የወሰደውን ፡ ፳፻ ብር ፡ ለገዢው ፡ ሲመልስ ፡ ቤቱ ፡ እንዲመለስለት ፡ ተስማሙ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፯፻፳፫ ፡ መሠረት ፡ ውሉን ፡ አጸደቀው ።

እነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ በፍጥነት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ ቀጠሮ ፡ ይፈጸማሉ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ከሚመለከቱ ፡ ሽያጮች ፡ ውስጥ ፡ ስንቱ ፡

ውል ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ በተሰጠው ፡ ሰው ፡ መመዝገባቸው ፡ ባይመረመርም ፡ ወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ጥቂቶች ፡ መመዝገባቸውን ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ።

## የባለጉዳዮች ፡ አለመቅረብ ።

በወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰሙትን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ ዓይነት ፡ ለማስረዳት ፡ ከተወሰዱት ፡ አንዳንድ ፡ ምሳሌዎች ፡ እንደታየው ፡ በባለ ፡ ጉዳዮቹ ፡ መታረቅ ፡ ወይም ፡ በከሳሽ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀጠሮ ፡ ቀን ፡ አለመቅረብ ፡ ምክንያት ፡ ፋይሎች ፡ ተዘግተዋል ። ከተመረመሩት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ ፷፭ ፡ በመቶው፡ ያህል ፡ በከሳሽ ፡ ጉዳዩን ፡ አጥብቆ ፡ አለመከታተል ፡ ምክንያት ፡ ተሠርዘዋል ።

አንድ ፡ ጉዳይ ፡ ለምን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ እንዳልደረሰ ፡ በመዝገቡ ፡ ውስጥ ፡ ስለማይገለጽ ፡ ምክንያቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ የምንችለው ፡ በግምት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ከሳሾች ፡ በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ጉዳይ ፡ ቢሆን ፡ ላይቀርቡ ፡ ስለሚችሉ ፡ ሳይቀርቡ ፡ የቀሩባቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ ዓይነት ፡ መመርመር ፡ ምንም ፡ ፍንጭ ፡ አይሰጥም ።

ሆኖም ፡ መጠኑ ፡ ትንሽ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብን ፡ በተለይም ፡ ፶ ፡ ብር ፡ ወይም ፡ ከ፶ ፡ ብር ፡ በታች ፡ የሆኑ ፡ የብድር ፡ ውሎችና ፡ የቤት ፡ ኪራዮችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ቶሎ ፡ ይቋረጣሉ ።

ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ፍጻሜ ፡ የማይደርሱት ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመነጩት ፡ ተከራካሪ ዎቹ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ካላቸው ፡ ግንኙነት ፡ ለምሳሌ ፡ በጋብቻ ፡ ወይም ፡ በዕቁብ ፡ ምክንያት ፡ ከሚነሱ ፡ ክሶች ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ የሚገኙ ፡ ግንኙነቶች ፡ ለጠብ ፡ ማብረጃ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ የተዘጋጁ ፡ ዘዴዎች ፡ ማለትም ፡ በጋብቻ ፡ በኩል ፡ አለመግባባትን ፡ የሚዳኙ ፡ ልማዳዊ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ዕቁብም ፡ በመጠኑ ፡ ፍርድ ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ "ዳኞች" ፡ አሏቸው ። በተጨማሪም ፡ ትንሽ ፡ ገንዘብ ፡ የማበደር ፡ ውል ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚመጣው፡ ቀድሞ ፡ ከነበረ ፡ ግንኙነት ፡ ነው ። አብዛኞቹ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የብድር ፡ ውሎች ፡ የሚደረጉት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በሚተዋወቁ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመገመት ፡ ይቻላል ። ስለዚህም ፡ አለመግባባታቸውን ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ እንዲያስወግዱ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ምናልባት ፡ ይመክሯቸው ፡ ይሆናል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ የከሳሾች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አለመቅረብ ፡ ምንም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚሰጠው ፡ ፍርድ ፡ የሚሻለው ፡ ዕርቅ ፡ ለመሆኑ ፡ አንድ ፡ ምልክት ፡ ቢሆንም ፡ እነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቆየታቸው ፡ አይካድም ። ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ክሱ ፡ በሚሰማበት ፡ እለት ፡ ከሳሹ፡ በማይቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ ከመሠረዙ ፡ በፊት ፡ በሁለት፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ያየው ፡ ይሆናል ። የጉዳዮችን ፡ ብዛት ፡ ስናይ ፡ የተቋረጡ ፡ ጉዳዮችን ፡ ማየት ፡ በርግጥ ፡ የፍርድ ፡ ቤትን ፡ ጊዜ ፡ ማባከን ፡ ነው ።

አንዳንድ ፡ የተቋረጡ ፡ ጉዳዮች ፡ የሚታዩት ፡ የክፍያው ፡ ጊዜ ፡ የደረሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማስከፈል ፡ ሳይሆን ፡ ዕዳውን ፡ አልከፍልም ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ለመቅጣት ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡

ተከሳሹ ፡ ከከሳሹ ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ተበድሮ ፡ ዕዳውን ፡ አልከፍልም ፡ አለ ። ከሳሹ ፡ ፋይሉን ፡ ለመክፈት ፡ ፩ ፡ ብር ፡ ከ፳ ፡ ወጪ ፡ አድርጐአል ። በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሹ ፡ አልቀረበም ። በሁለተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ሳይቀርቡ ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፡ ፋይሉ ፡ በተከፈተ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ክሱ ፡ ተሰርዟል ።

አንዳንድ ፡ ተሚጋቾች ፡ መስማማታቸውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቢያስታውቁም ፡ ይበልጡን ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የሚደረገው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለመቅረብ ፡ ነው ።

## <u>የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ መዘግየት ።</u>

ጉዳዮቹ ፡ መጀመሪያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረቡበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ተወሰኑበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃሉ ። ለያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጠው ፡ ቀጠሮ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ ጥቂት ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

ከተመረመሩት ፡ ጉዳዮች ፡ በጣም ፡ ረጅሙ ፡ ውሳኔ ፡ ለማግኘት ፡ ፳፱ ፡ ወራትና ፡ ፳፫ ፡ ቀጠሮ ፡ ፈጅቷል ። በጣም ፡ አጭሩ ፡ በአንድ ፡ ቀጠሮ ፡ ያለቀ ፡ ነው ። (በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፺፱፳፫ ፡ መሠረት ፡ ውል ፡ ለማጽደቅ ፡ የቀረበ ፡ ነበር) ። ክርክር ፡ ከተደረገባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ በጣም ፡ አጭሩ ፡ ለውሳኔ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ሲወስድ ፡ ነገሩን ፡ ለመፈጸም ፡ ሁለት ፡ ቀጠሮዎች ፡ አስፈልገዋል ።

በመሠረቱ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ከሌላው ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ይፈጃል ፡ ብሎ ፡ በዓይነት ፡ ለመለየት ፡ አይቻልም ። አንድ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ እንደሚፈጅ ፡ የሚወስኑት ፡ ዋናዎቹ ፡ ጉዳዮች ፡ የዳኛው ፡ ጉዳዩን ፡ በቶሎ ፡ ለመጨረስ ፡ ያለው ፡ ፍላጐት ፡ የባለጉዳዮቹ ፡ በቀጠሮ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብና ፡ የምስክሮች ፡ በቶሎ ፡ መገኘት ፡ ናቸው ። አንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ ከሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ የበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ እንደሚፈጁ ፡ ለመናገር ፡ ያዳግታል ። ሆኖም ፡ መዘግየትን ፡ የሚያመጡት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ በጣም ፡ ረጅም ፡ ሙግትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ይመስላሉ ።

ከዚህ ፡ የሚከተለው ፡ አንድ ፡ በጣም ፡ ጊዜ ፡ የፈጀ ፡ ጉዳይ ፡ ታሪክ ፡ ነው ።

ተከሳሹ ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ ከከሳሹ ፡ ጋር ፡ ተስማማ ። ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ ቤቱን ፡ ሳይሠራ ፡ ቀረ ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ኪሳራ ፡ ደርሶብኛል ፡ ብሎ ፡ ከሳሹ ፡ ቤት ፡ ሠሪውን ፡ ከሰሰው ። ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ተኩልና ፡ ከ፳፫ ፡ ቀጠሮ ፡ በኋላ ፡ ለከሳሽ ፡ ተፈረደለት ። ለእነዚህም ፡ ብዙ ፡ ቀጠሮዎች ፡ ምክንያት ፡ የሆኑ ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ። (፩) ተከሳሽ ፡ መጥሪያ ፡ ስላልደረሰው ፡ አልቀረበም ፤ (፪) ተከሳሹ ፡ ስላልቀረበ ፡ በድጋሚ ፡ መጥሪያ ፡ እንዲሰጠው ፡ ታዘዘ ፤ (፫) ዳኛው ፡ ክርክሩን ፡ ከመስማቱ ፡ በፊት ፡ ጉዳዩን ፡ ለመመርመር ፡ ፈለገ፤(፬) ተከሳሽ ፡ መከላከያውን ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ዳኛው፡ ጊዜ ፡ ሰጠው ፤ (፭) ዳኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አልተገኙም ፤ (፮) ተከሳሹ ፡ አልቀረበም ፤ (፯) ተከሳሹ ፡ መከላከያውን ፡ እንዲያቀርብ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ተሰጠው ፤ (፰) ከሳሹ ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ አልቀረበም ፤ (፱) ነገሩን ፡ ለመመርመር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ፈለገ ፤ (፲) ምንም ፡ ምክንያት ፡ አልተሰጠም ፤ (፲፩) ከሳሹ ፡ የሚያቀርበው፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ ነበረው ፤ (፲፪) ነገሩን ፡ በይበልጥ ፡ ለመመርመር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ አስፈለገው ፤ (፲፫) ከሳሹ ፡ የጠየቀውን ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ ስለለወጠ፡ ተከሳሹ ፡ አዲስ ፡ መከላከያ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ጊዜ ፡ ተሰጠው ፤ (፲፬) ተከሳሹ ፡ አልቀረበም ፤ (፲፭) ከሳሹ ፡ ለተከሳሹ ፡ መጥሪያ ፡ ስላልሰጠው ፡ መቀጫ ፡ ተጣለበት ፤ (፲፮) ተከሳሹ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ ጠየቀ ፤ (፲፯) ምንም ምክንያት ፡ አልተሰጠም ፤ (፲፰) ተከሳሹ ፡ መከላከያውን ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ታዘዘ ፤ (፲፱) ምስክሮች ፡ አልቀረቡም (፳) ምስክሮች ፡ አልቀረቡም ፤ (፳፩) ምስክሮች ፡ አልቀረቡም ፤ (፳፪) ምስክሮች ፡ አልቀረቡም ፤ (፳፫) ለከሳሽ ፡ ተፈረደለት ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የጉዳዩ ፡ በጣም ፡ መጎተት ፡ ከሳሹን ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ምሳሌ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለው ፡ ከሳሽ ፡ ሳይሆን ፡ ክርክሩን ፡ እንዲያቋርጥ ፡ ያደርገዋል ።

ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የፈጁ ፡ ጉዳዮች ፡ ጥቂቶች ሲሆኑ ፡ ከአምስት ፡ ወር ፡
እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የሚፈጁ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በእንደዚህ ፡ ያሉ ፡
ጉዳዮች ፡ ከአምስት ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ቀጠሮዎች ፡ ነበሩ ።

የከሳሹና ፡ የተከሳሹ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ የነበሩትን ፡ ባሕር ፡ ዛፎች ፡ ተከሳሹ ፡ ቆርጦ
ከሸጠ ፡ በኋላ ፡ ከሽያጩ ፡ ዋጋ ፡ ድርሻዬን ፡ አልሰጠኝም ፡ ብሎ ፡ ከሳሹ ፡ ክስ ፡ አቅር
ቦአል ። ከዘጠኝ ፡ ወርና ፡ ከዘጠኝ ፡ ቀጠሮዎች ፡ በኋላ ፡ ጉዳዩ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በአውራ
ጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ታይቶ ፡ ለተከሳሹ ፡ መፈረዱን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ደረሰበት ። ለዘ
ጠኙ ፡ ቀጠሮዎች ፡ ምክንያቶች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ፡ (፩) ተከሳሹ ፡ መጥሪያ ፡ አል
ደረሰውም ፡ (፪) ተከሳሹ ፡ መከላከያውን ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ተሰጠው ፡
(፫) ፡ ተከሳሹ ፡ መከላከያወን ፡ ስላላቀረበ ፡ መቀጫ ፡ ተጣለበት ፡ (፬) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡
ውሳኔውን ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ጊዜ ፡ አስፈለገው ፡ (፭) ጉዳዩ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በደንብ ፡
ስላልተመረመረ ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ አስፈለገ ፡ (፮) ባለ ፡ ጉዳዮቹ ፡ አልቀረቡም ፡
(፯) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔውን ፡ አላዘጋጀም ፡ (፰) አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠው ፡
ውሳኔ ፡ ለጉዳዩ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለተከሳሹ ፡ ፈረደ
ለት ።

አንድ ፡ ጉዳይ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ቀጠሮ ፡ ካስፈለገው ፡ ከስድስት ፡
ወር ፡ በላይ ፡ መፍጀቱ ፡ የተለመደ ፡ ይመስላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይበልጡን ፡ ጊዜ ፡ በስ
ድስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከሦስት ፡ የበለጡ ፡ ቀጠሮዎች ፡ ነበሩ ። በስድስት ፡ ወር ፡
ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡
ብቻ ፡ ሲሰሙ ፡ ሌሎች ፡ ስምንት ፡ ወይም ፡ ዘጠኝ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰሙበት ፡ ምክንያት ፡
ግልጽ ፡ አይደለም ። በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ የፈጁት ፡
ጉዳዮች ፡ አብዛኞቹ ፡ ምስክሮች ፡ የሚጠሩባቸው ፡ ወይም ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉድለት፡
ያለባቸው ፡ ነበሩ ።

በሁሉም ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ይሰማል ፡ ብለው ፡ ካሰ
ቡት ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ነገር ፡ ይሰማል ፡ ብለው ፡ ስለማይገምቱ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡
በደንብ ፡ አይዘጋጁም ። ስለዚህ ፡ በአንድ ፡ ቀጠሮ ፡ ከአንድ ፡ ጭብጥ ፡ በላይ ፡ የሚወ
ሰን ፡ አይመስልም ፡ ይህ ፡ ጭብጥ ፡ ከተወሰነ ፡ በኋላ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ
ለሚቀጥለው ፡ ክርክር ፡ ዝግጅት ፡ እንዲደረግ ፡ ያንድ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ይሰጣል ።

ያንድ ፡ ጉዳይ ፡ መዘግየት ፡ ጉዳዩ ፡ ለሚመለከተው ፡ ሁሉ ሸክም ፡ ነበር ። ከተ
መረመሩት ፡ ጉዳዮች ፡ ለመረዳት ፡ እንደተቻለው ፡ አንዱን ፡ ጉዳይ ፡ ለመወሰን ፡ የሚ
ያስፈልገውን ፡ የጊዜ ፡ መጠን ፡ የሚወስኑ ፡ ብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ። አንደኛው ፡
ምክንያት ፡ የዳኛው ፡ ፍላጐት ፡ ነው ። ዳኛው ፡ የባለ ፡ ጉዳዮቹን ፡ ነገር ፡ መጎተት ፡
በዝምታ ፡ ለማለፍ ፡ ካልፈለገ ፡ ጉዳዩን ፡ እንዲያፋጥን ፡ የሚከለክለው ፡ የለም ። ባልታ
ወቀ ፡ ምክንያት ፡ ዳኛው ፡ ስለ ፡ ነገር ፡ መጎተት ፡ ያለው ፡ አስተያየት ፡ እንደነገሩ ፡ ይለ
ዋወጣል ።

በዳኛው ፡ በኩል ፡ ካለው ፡ ጉድለት ፡ ሌላ ፡ ተሟጋቾቹ ፡ እራሳቸው ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡
በአስፈላጊው ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ እንዳያገኝ ፡ ሊያደርጉ ፡ ይችላሉ ። ይኸውም ፡
ባለመቅረብ ፡ ከቀረቡም ፡ በኋላ ፡ ጉዳያቸውን ፡ ባለማዘጋጀት ፡ ወይም ፡ ምስክሮቻ
ቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲመጡ ፡ ባለማግባባት ፡ ነው ።

ሌላው ፡ የመዘግየት ፡ ምክንያት ፡ የሚሆነው ፡ ክሱ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ከመሰ
ማቱ ፡ በፊት ፡ ለተከሳሾች ፡ መጥሪያ ፡ ፈጽሞ ፡ ስለማይደርሳቸው ፡ ነው ። በአብዛኞቹ፡

በተመረመሩት ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ክሱ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የተሰማው ፡ ተከሳሾች ፡ በሌሉበት ፡ ነው ። ይህ ፡ ነገር ፡ እያንዳንዱን ፡ ጉዳይ ፡ ከማዘግየቱም ፡ ሌላ ፡ በጠቅላላው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በክስ ፡ ብዛት ፡ እንዲጣበብ ፡ ያደርገዋል ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሌሎች ፡ ጉዳዮችን ፡ ለመስማት ፡ በቂ ፡ እርምጃ ፡ ለመውሰድ ፡ አይቻልም ።

በተጨማሪ ፡ ምስክሮች ፡ ክሱ ፡ ለመጀመሪያ ፡ በሚሰማበት ፡ ጊዜ ፡ በጭራሽ ፡ አይጠሩም ። ለዚህም ፡ ምክንያቱ ፡ ምናልባት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፵፮ ፡ እና ፡ ተከታታዮቹ ፡ "ክሱ ፡ መሰማት ፡ በሚጀምርበት ፡ ቀን ፡" ባለጉዳዮቹ ፡ እራሳቸው ፡ ቀርበው ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የሚቀርቡት ፡ መቃወሚያዎች ፡ "ውሳኔ ፡ እንዳያገኙና ፡ የነገሩ ፡ ጭብጥ ፡ እንዲታወቅ ፡" ስለሚሉ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። እላይ ፡ የተመለከትናቸው ፡ ምሳሌዎች ፡ ምስክሮችን ፡ በቶሎ ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ያስረዱናል ። ክሱ ፡ መሰማት ፡ በሚጀምርበት ፡ ቀን ፡ የምስክሮች ፡ መምጣት ፡ ባያስፈልግ ፡ እንኳን ፡ ለምስክርነት ፡ የሚፈለጉበት ፡ ጉዳይ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ መኖሩ ፡ ሊገለጽላቸው ፡ ይችላል ።

በወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚነሱ ፡ ጭብጦች ፡ ቀላል ፡ ስለሆኑ ፡ ለብዙዎቹ ፡ ጉዳዮች ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ክርክር ፡ መሰማት ፡ አስፈላጊነቱ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ። ምስክሮችና ፡ ባለጉዳዮች ፡ በሙሉ ፡ ክሱ ፡ መሰማት ፡ በሚጀምርበት ፡ ቀን ፡ ከተገኙ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉትን ፡ ጉዳዮች ፡ በአንድ ፡ ቀጠሮ ፡ ለመወሰን ፡ የሚቻል ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

## <u>የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፤ ጠበቆች ።</u>

ከወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመቶ ፡ አሥር ፡ የሚሆኑ ፡ ባለጉዳዮች ፡ በተመዘገቡ ፡ ጠበቆች ፡ ተወክለው ፡ ነበር ። ግማሽ ፡ የሚሆኑት ፡ ጠበቆች ፡ የተቀጠሩት ፡ በንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ እንደ ፡ እቁብ ፡ ባሉ ፡ ማኅበሮችና ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ነበር ። በግል ፡ ተሟጋቾች ፡ የተቀጠሩት ፡ ጠበቆች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በውክልና ፡ የሚቆሙት ፡ የክስ ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ ገንዘብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ ነበር ። አለማስጠንቀቂያ ፡ የሥራ ፡ ውል ፡ ተቋርጧል ፡ በሚሉት ፡ የአሠሪና ፡ የሠራተኛ ፡ ክሶችም ፡ ከሳሾች ፡ ጠበቃ ፡ ይቀጥራሉ ።

ከመቶ ፡ ሃያ ፡ በሚሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ ተካፋይ ፡ ሆነው ፡ ነበር ። ከእነዚህም ፡ ግማሾቹ ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ ያልተከፈለ ፡ ታክስ ፡ ለመቀበል ፡ በሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤቱን ፡ ወይም ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትን ፡ ሲወክሉ ፡ አንድ ፡ አራተኛ ፡ የሚሆኑት ፡ ደግሞ ፡ የዕቁብ ፡ ማኅበሮችን ፡ በብድር አለመከፈል ፡ ጉዳይ ፡ ባንኮችን ፡ በአሠሪና ፡ ሠራተኞች ፡ ጉዳይ ፡ ኩባንያዎችን ፡ ወክለዋል ። የቀሩት ፡ አንድ ፡ አራተኛዎቹ ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ በከሳሽ ፡ ወይም ፡ በተከሳሽ ፡ በኩል ፡ በመሆን ፡ ለግል ፡ ሰዎች ፡ ተከራክረዋል ። ስለዚህ ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካሉት ፡ የግል ፡ ተሟጋቾች ፡ በግምት ፡ ከመቶ ፡ አሥር ፡ የሚሆኑት ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ነበራቸው ፡ ማለት ፡ ነው ።

ለወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡ ፡ ጉዳዮች ፡ አነስተኛ ፡ ገንዘብን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ንብረትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ስለሆነ ፡ ጠበቃ ፡ መቅጠር ፡ አስፈላጊ ፡ አይመስልም ። በተጨማሪም ፡ ተሟጋቾች ፡ ስለጠበቆች ፡ ያላቸውን ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ በተግባር ፡ ማሳየታቸው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ተሟጋቾች ፡ ጠበቆችን ፡ ስለማያምኑ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ አይቀጥሯቸውም ።

## የወንጀል ፡ ክሶች ።

ለወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረቡት ፡ የወንጀል ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ሃያ፡ ሶስት ፡ የሚሆኑት ፡ የተለያዩ ፡ የሌብነት ፡ ወንጀሎችን ፡ ማለት ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ ሥርቆትን ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴፩) ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፯፻ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረቡትንና ፡ በቁጥር ፡ ፮፻፴ ፡ የተመለከተውን ፡ ዓይነት ፡ ሥርቆትና ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ሃብት ፡ ያላግባብ ፡ መገልገልን ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፵፩) ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።

ከመቶ ፡ አሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ የሚሆኑት ፡ ክሶች ፡ ደግሞ ፡ በአካል ፡ ላይ ፡ እርግጠኛ ፡ ጉዳትን ፡ የማድረስ ፡ ዛቻን ፡ ወይም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፴፱ንና፡ ፯፻፵፬ን ፡ ተላልፎ ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ማድረስን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፹፫ ፡ መሠረት ፡ የሚቀርቡት ፡ የስድብና ፡ የማዋረድ ፡ ክሶች ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ በመቶ ፡ ያህል ፡ ይሆናሉ ።

> "ተበዳዩን ፡ በቀጥታ ፡ በመናገር ፡ ወይም ፡ በአሽሙር ፡ የሰደበ ፡ ወይም ፡ ያዋረደ ፤ ለማዋረድ ፡ ምልክት ፡ የሰጠ ፤ ወይም ፡ የቃጣ ፤ ወይም ፡ ያንገላታ፤ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሌላ ፡ አደራረግ ፡ የተበዳዩን ፡ ክብር ፡ በመንካት ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፤ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ሳይታይ ፡ አድራጎቱ ፡ በጣም ፡ ቀላል ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ በደንብ ፡ መተላለፍ ፡ ሕግ ፡ መቀጣቱ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ ሳይታይ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ለማድረስ ፡ በሚችል ፡ ቀላል ፡ እሥራትና ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ በማይበልጥ ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ሊቀጣ ፡ ይችላል ። (ቁጥር ፡ ፯፻፺፭)"

ከመቶ ፡ አራት ፡ የሚሆኑት ፡ ደግሞ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፺፪ መሠረት ፡ የቀረቡ ፡ የዛቻ ፡ ክሶች ፡ ናቸው ።

> "ማንም ፡ ሰው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ድንጋጤና ፡ ሽብርን ፤ (ፍርሃትን ፡) በሚያደርስበት ፡ ሁኔታ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የሆነ ፡ አደጋ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስበት ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ የዛተበት ፡ እንደሆነ ፤
>
> በተበዳዩ ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ እሥራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፭፻ ፡ ብር ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ።"

በሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ የሚያደርስ ፡ ሰው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፺፫ን ፡ በመተላለፍ ፡ ሊከሰስ ፡ ይችላል ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረቡት ፡ ክሶች ፡ ከጠቅላላው ፡ የወንጀል ፡ ጉዳዮች ፡ ስምንት ፡ በመቶ ፡ ያህል ፡ ናቸው ።

የሰዎችን ፡ የአካል ፡ ደህንነት ፡ ስለመተናኰል ፤ ስድብና ማዋረድ ፤ ዛቻና ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ ክስ ፡ የሚቀርብባቸው ፡ በግል ፡ ከሳሽ ፡ አቤቱታ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚቀርቡት ፡ መቶ ፡ የወንጀል ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ያህሉ ፡ በግል ፡ ከሳሽ ፡ አቤቱታ ፡ ለፖሊስ ፡ ቀርበው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የደረሱ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከነዚህ ፡ የተረፉት ፡ ለወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረቡት ፡ የወንጀል ፡ ጉዳዮች ፡ ደግሞ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ለመልካም ፡ ጠባይ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆኑ ፡ አድራጎቶች ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፯፻፹፱) ፡ የሰዓት ፡ እላፊ ፡ ደንብ ፡ በሚጥሱ ፡ የምግብና ፡

የመጠጥ ፡ ቤቶች ፤ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፷፮) የትራፊክ ፡ ደንቦችን ፡ በመጣስና ፡ ሌላም ፡ እንደ ፡ ቁማር ፡ ጨዋታ ፡ ማሳሳት ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ በመድፈርና ፡ በሃሰት ፡ በመመስከር ፡ በሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች መካከል ፡ እኩል ፡ የተከፈሉ ፡ ናቸው ።

<u>ተከሳሹን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለማቅረብ ።</u>

እላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ወንጀል ፡ ሰርተዋል ፡ በመባል ፡ የተከሰሱ ፡ ሰዎች ፡ በሦስት ፡ መንገድ ፡ ሊያዙ ፡ ይቻላል ። በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትዕዛዝ ፡ መያዝ ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፵፱) ፤ እጅ ፡ ከፍንጅ ፡ በተፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ ምክንያት ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትዕዛዝ ፡ መያዝ ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፶—፶፩) ፡ ወይም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፳፰ ፡ መሠረት ፡ ፖሊስ ፡ የተጠረጠረውን ፡ ሰው ፡ ለጥያቄ ፡ ለመጥራት ፡ ይችላል ።

በተለይም ፡ በግል ፡ አመልካችነት ፡ በሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚሰራበት ፡ የተከሰሰውን ፡ ሰው ፡ ፖሊስ ፡ ጠርቶ ፡ ያስፈልጋል ፡ ብሎ ፡ ካመነበት ፡ ተከሳሹ ፡ ዋስ ፡ እንዲጠራ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። ተከሳሹ ፡ ዋስ ፡ ማቅረብ ፡ ቢያቅተው ፡ ክሱ ፡ እስከሚሰማበት ፡ ድረስ ፡ ፖሊስ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ያቆየዋል ። ተከሳሹን ፡ ፖሊስ ጣቢያ ፡ "መጥራት" በተግባር ፡ ላይ ፡ ሲውል ፡ በኃይል ፡ አስገድዶ ፡ ማቅረብ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ተከሳሹ ፡ በተላከበት ፡ የፖሊስ ፡ መጥሪያ ፡ መሠረት ፡ ያልቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ የመያዝ ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሰጠው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ መሠረት ፡ ፖሊስ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ይጠይቃል ።

> ተከሳሾቹ ፡ የከሳሽን ፡ ንብረት ፡ በማበላሸት ፡ ተከሰው ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ የበኩላቸውን ፡ ክርክር ፡ ቀርበው ፡ ለፖሊስ ፡ እንዲያስረዱ ፡ በከሳሹ ፡ በኩል ፡ መጥሪያ ፡ ተላከላቸው ። ተከሳሾቹ ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ስለአል ቀረቡ ፡ እንዲያዙ ፡ ፖሊስ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ፈቃድ ፡ ጠየቀ ።

የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ደንቦችን ፡ በመተላለፍ ፡ በመንግሥት ፡ ባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ ክስ ፡ ቀርቦባቸው ፡ በቀጠሮ ፡ ቀን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳይቀርቡ ፡ የሚቀሩ ፡ ሰዎችም ፡ እንዲያዙ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ ይሰጣል ።

> ተከሳሾቹ ፡ ፕላናቸውን ፡ ለማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሳያቀርቡ ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ ሠሩ ። ተከሳሾቹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ መጥሪያ ፡ ተልኮላቸው ፡ ለመቅረብ ፡ ፈቃደኞች ፡ ስለአልሆኑ ፡ እንዲያዙ ፡ ታዘዘ ።

በሥርቆት ፡ ወንጀል ፡ የተያዙ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ተከሳሾች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ና ፡ ፳ ፡ የተደነገገውን ፡ "የእጅ ፡ ከፍንጅ ፡ ወንጀል" ሲፈጽሙ ፡ በመገኘታቸው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፶ ፡ በተፈቀደው ፡ መሠረት ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትዕዛዝ ፡ የተያዙ ፡ ናቸው ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ና ፡ ፳ ፡ የተጠረጠሩ ፡ ሰዎችን ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ትዕዛዝ ፡ ለመያዝ ፡ ለፖሊስ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ሥልጣንን ፡ በግልጽ ፡ ይሰጣሉ ። አንድ ፡ ወንጀል ፡ "እጅ ፡ ከፍንጅ" ፡ ተፈጸመ ፡ የሚባለው ፡ ተከሳሹ ፡ ወንጀሉን ፡ በመፈጸም ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ሲገኝ ፡ ወንጀሉን ፡ እንደፈጸመ ፡ ወዲያውኑ ፡ የተያዘ ፡ ሲሆን ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፲፱) ፡

ወንጀሉ ፡ በተሠራበት ፡ ቦታ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፖሊስ ፡ የተጠራ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ የድረሱልኝ ፡ እሪታ ፡ የተሰማ ፡ እንደሆነ ፡ ነው። (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት፡ ቁጥር፡ ፳) ፡ ምናልባትም ፡ በሥርቆት ፡ ወንጀሎች ፡ ብዙዎቹ፡ ተጠርጣሪዎች ፡ የሚያዙት፡ እላይ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ቁጥሮች ፡ መሠረት ፡ ነው ። ከተመረመሩት ፡ መዛግብት፡ ውስጥ፡ ፖሊስ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ የመያዝ ፡ ፈቃድ ፡ የጠየቀባቸው ፡ ማመልከቻዎች ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፶፫) ። ስለዚህ ፡ ብዙዎቹ ፡ የወንጀል ፡ ተከሳሾች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡት ፡ "የእጅ ፡ ከፍንጅ" ወንጀል፡ ሲፈጽሙ ፡ ወይም ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ተይዘው ፡ አለዚያም ፡ የፖሊስን ፡ ጥሪ ፡ በማክበር ፡ ከቀረቡ ፡ በኋላ ፡ ይመስላል ።

## ስርቆት ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴ን ፡ በመተላለፍ ፡ የሚፈፀሙትን ፡ ወንጀሎች ፡ የማየት ፡ ሥልጣን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በአንደኛው፡ ሰንጠረዥ ፡ ለአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመስጠቱ ፡ በስርቆት ፡ ወንጀል ፡ ተይዘው ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ተጠርጣሪዎች ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ የተደነገገውን ፡ ለማሟላት ፡ ሲባል ፡ ብቻ ፡ ነው ።

> "(፩) ፡ ተከሳሹ ፡ በፖሊስ ፡ የተያዘ ፡ ወይም ፡ በቁጥር ፡ ፶፰ ፡ እንደተመለከተው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ተይዞ ፡ ለፖሊስ ፡ የተሰጠ ፡ እንደሆነ ፤ ከተያዘበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ከአርባ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ በማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ፡ ወይም ፡ የሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ ሁኔታዎችና ፡ መገናኛዎች ፡ በሚያመቹበት ፡ (በሚፈቅዱለት) ፡ መጠን ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ ፖሊሱ ፡ የተያዘውን ፡ ሰው ፡ በጣም ፡ አቅራቢያ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። የተያዘውን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማድረስ ፡ የሚፈጀው ፡ ጊዜ ፡ አይታሰብም ።
>
> (፪) ፡ ተከሳሹ ፡ የቀረበበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቁጥር ፡ ፶፱ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ማንኛውንም ፡ ትዕዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ።"

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፶፱ ፡ ተከሳሹ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ይቆይ ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ ወረቀት ፡ ይለቀቅ ፡ ብሎ፡ መወሰን ፡ አለበት ፤ በተጨማሪም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የምርመራውን ፡ ጊዜ ፡ ለእያንዳንዱ፡ የፖሊስ ፡ ጥያቄ ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ሊያረዝመው ፡ ይችላል ፡ ይላል ። በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፶፱ ፡ መሠረት ፡ በፖሊስ ፡ ጠያቂነት ፡ ተከሳሹን ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ አቆይቶ ፡ ምርመራውን ፡ ለመጨረስ ፡ የሚሰጠው ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከ፫ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቶቹን ፡ ጥያቄዎች ፡ በሙሉ ፡ ተቀብሏል ።

ተከሳሹ ፡ በግ ፡ ሰርቆ ፡ ሊሸጥ ፡ ሲሞክር ፡ ተያዘ ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረበና ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ መረጃዎችን ፡ ለማዘጋጀት ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ ተከሳሹ ፡ ለአምስት ፡ ቀን ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ጠየቀ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥያቄውን ፡ ተቀበለ ። ከአምስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ወንጀሉ ፡ ጉዳዩን ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ ወደ ፡ አለው ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መወሰዱ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተነገረው ።

በተጨማሪም ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ አንዳንድ ፡ ስርቆት ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ክሶችን ፡ የማየት ፡ ሥልጣን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንደኛ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ተሰጥቷል ። እነዚህም ፡ "ቀላል ፡ የሆነ ፡ የስርቆት ፡" (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴፩) ፡ እና ፡ "በሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ያለአገባብ ፡ ስለመገልገል ፡" (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፵፩) ፡ ክሶች ፡ ናቸው ።

"ቀላል ፡ የሆነ ፡ ስርቆት" ፡ በመሠረቱ ፡ የቅጣት ፡ ማቅለያ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ "ስርቆት" ፡ ነው ። አንድ ፡ "ስርቆት" ፡ በመባል ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር፡ ፮፻፴ ፡ መሠረት ፡ ሊቀጣ ፡ የሚችልን ፡ ወንጀልንና ፡ አንድ ፡ "ቀላል ፡ የሆነ ፡ ስርቆት" ነው ፡ ተብሎ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴፪ ፡ መሠረት ፡ ቀለል፡ ባለ ፡ ቅጣት  የሚቀጣ ፡ ወንጀል ፡ ልዩነታቸው ፡ በጣም ፡ ረቂቅ ፡ ነው ።

አንድን ፡ "ስርቆት" ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴፪ ፡ መሠረት ፡ "ቀላል ፡ የሆነ ፡ ስርቆት" ፡ ሊያሰኘው ፡ የሚችለው ፡ (፩) ፡ አድራጎቱ ፡ በችግር ፡ ወይም ፡ የሕሊና ፡ ኃይል ፡ በማጣት ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ (፪) የተሰረቀው ፡ ዕቃ ፡ ግምቱ ፡ አነስተኛ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ (፫) ፡ ወንጀለኛው ፡ ዕቃውን ፡ ወዲያውኑ ፡ ሊገለገልበት ፡ ወይም ፡ ሊያጠፋው ፡ አስቦ ፡ የሰረቀ ፡ እንደሆነና ፡ (፬) የስርቆቱ ፡ ተግባር ፡ የተፈጸመው ፡ አለአግባብ ፡ ብልጽግናን ፡ ለማግኘት ፡ ታስቦ ፡ መሆኑን ፡ የሚያሳይ ፡ አንዳችም ፡ አድራጎት ፡ የሌለ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ "የስርቆት" ፡ ወይም ፡ "ቀላል ፡ የሆነ ፡ የስርቆት" ፡ ክስ ፡ በማቅረብ ፡ የአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ምርጫ ፡ በግል ፡ ፈቃዱ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ እዚህ ፡ ውሳኔ፡ ላይ ፡ ለመድረስ ፡ የሚከተላቸው ፡ ምክንያቶች ፡ በመዛግብቱ ፡ ላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ግልጽ ፡ አይደሉም ። ቀላል ፡ በሆነ ፡ ሌብነት ፡ ነክ ፡ ስለሚከሰሱ ፡ ሰዎች ፡ ከሌብነት ፡ ክሶች ፡ የተውጣጡ ፡ ምሳሌዎች ፡ ከዚህ ፡ ይቀጥላሉ ።

> ተከሳሹ ፡ ከአደረበት ፡ ሆቴል ፡ አንድ ፡ የብርድ ፡ ልብስ ፡ ሰርቋል ፡ በመባል ፡ ተከስሶ ፡ ነበር ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴፩ ፡ ቀላል  የሆነ ፡ ስርቆት ፡ ተጠቅሶበት ፡ የ፲፫ ፡ ቀን ፡ እስራት ፡ ተፈረደበት ።
>
> ተከሳሹ  አንድ ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ሰብሮ ፡ በመግባት ፡ ዕቃ ፡ አንስቶ፡ ለማምለጥ ፡ ሲሞክር ፡ ተይዟል ፡ በመባል ፡ ክስ ፡ ቀረበበት ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፳፯ና ፡ ፮፻፴፩ ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ ስርቆት ፡ ሙከራ ፡ ተጠቅሶበት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በአቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ምስክሮች ፡ አለመቅረብ ፡ ምክንያት ፡ ከአሥር ፡ ወራትና ፡ ከስምንት ፡ ቀጠሮዎች ፡ በኋላ ፡ ተከሳሹ ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ እስራት ፡ እንዲቀጣ ፡ ተፈረደበት ።

የሚቀጥሉት ፡ ደግሞ ፡ ተከሳሹ ፡ በስርቆት ፡ ወንጀል ፡ የተከሰሰባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ።

> ተከሳሹ ፡ ልብሶች ፡ እንዲደርቁ ፡ ከተሰቀሉበት ፡ አጥር ፡ ላይ ፡ ሰርቋል ፡ በመባል ፡ ተከሰሰ ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ተከሳሹን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቅርቦ ፡ ለ፫፡ ቀን ፡ ተከሳሹ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይፈቅድለት ዘንድ ፡ ጠየቀ ። ጥያቄው ፡ ተፈቀደ ። ግን ፡ ነገሩ ፡ ወደ ፡ አውራጃው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ተላከ ። ተከሳሹ ፡ ለመስረቅ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ገብቷል ፡ በመባል ፡ ተከሰሰ ። በማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ አጭር ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ ከተፈቀደ ፡ በኋላ ፡ ነገሩ ፡ ወደ ፡ አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተላለፈ ።

በተሰረቀው ፡ ዕቃ ፡ ዋጋ ፡ አንጻር ፡ ሲታይ ፡ አላይ ፡ በተመለከቱት ፡ በ፪ቱ ፡ የክስ ምድቦች ፡ (ዓይነቶች) ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የፍሬ ፡ ነገር ፡ ሁኔታዎች ፡ ተመሳሳይ ፡ ናቸው። በ፪ቱ ፡ የክስ ፡ ምድቦች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በመጨረሻዎቹ ፡ ምሳሌዎች ፡ ውስጥ ፡ ተከሳሹ ፡ የሰረቀውን ፡ ዕቃ ፡ እራሱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሊጠቀምበት ፡ አስቦ ፡ አለ መሆኑ ፡ ፖሊሶች ፡ ማረጋገጣቸው ፡ ነው ።

ለዓይነት ፡ ከመረጥናቸው ፡ ምሳሌዎች ፡ እንደተረዳነው ፡ የፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ሁኔታ ፡ አንድን ፡ ወንጀል ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ ስርቆት ፡ መሆኑን ፡ ቢያመለክትም ፡ እንኳ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ወንጀሉን ፡ እንደ ፡ "ስርቆት" ፡ የመቁጠር ፡ ዝንባሌ ፡ ያለው ፡ ይመስላል ። በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ጉዳዩን ፡ ለማየት ፡ የሚቀርብለት ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ሆነ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ የመጠየቅ ፡ ዝንባሌ፡ ያላቸው ፡ አይመስልም ። በነዚህ ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ ጠበቃ ፡ ያላቸው ፡ ተከሳሾች ፡ ጥቂ ቶች ፡ ስለሆኑ ፡ የተከሳሹን ፡ ጥቅም ፡ የመጠበቁ ፡ ጉዳይ ፡ ለዳኛው ፡ የሚተው ፡ ነው ። የተከሳሹን ፡ ጥቅም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ያልጠበቀለት ፡ እንደሆነ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ በመ ሠረቱ ፡ ተመሳሳይ ፡ አድራጐትን ፡ ፈጽመው ፡ በተለያዩ ፡ ወንጀሎች ፡ በመከሰስ ፡ የተ ለያዩ ፡ ቅጣቶችን ፡ ለመቀበል ፡ ይችላሉ ።

## <u>የአካል ፡ ጉዳት ።</u>

አንድ ፡ ሰው ፡ በሌላው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ስለሚያደርሰው ፡ ጉዳት ፡ ክስ ፡ በወንጀ ለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፴፱ና ፡ ፭፻፵፩ ፡ መሠረት ፡ በግል ፡ ከሳሽ ፡ አቤቱታ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባል ። በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ አንድን ፡ ቁጥር ፡ ከሌላው ፡ ለይቶ ፡ ለመጥቀስ ፡ ሚዛን ፡ የሚሆነው ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ያልሆነ ፡ "የአካልና ፡ የጤና ፡ ጉዳት" ፡ ማድረስ ፡ የሚችል ፡ ሲሆን ፡ (ቁጥር ፡ ፭፻፴፱) ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ "ቀላል ፡ የሆኑ ፡ ሰንበሮች ፡ የደም ፡ መቋ ጠር ፡ ምልክቶች ፡ ወይም ፡ በቶሎ ፡ የሚያልፉ ፡ ስቃዮች ፡" ዓይነት ፡ ጉዳት ፡ በመኖሩ፡ ነው ። (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፵፩ ፡ (፪) ) ። በሁለቱ ፡ ወንጀሎች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ግልጽ ፡ አይደለም ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፵፩ ፡ (፪) ተጠቀሰው ፡ ወንጀል ፡ ከስ ምንት ፡ ቀን ፡ በማይበልጥ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ መቀጫ ፡ ይቀጣል ። እንግዲህ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ "ቀላል ፡ የሆኑ ፡ ሰንበሮችን ፡ ደም ፡ መቋጠር ፡ ምልክቶችን ፡ ወይም ፡ በቶሎ ፡ የሚያልፉ ፡ ስቃዮ ችን" ፡ አድርሷል ፡ በመባል ፡ ቢከሰስ ፡ ግፋ ፡ ቢል ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ እሥራት ፡ ሲቀጣ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ከባድ ፡ ያልሆኑ ፡ "የአካልና ፡ የጤና ፡ ጉዳት ፡" ያደ ረሰ ፡ ሰው ፡ ከአሥር ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡ በሚሆን ፡ የእሥራት ፡ ዘመን ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፭ሺ ፡ የኢት ፡ ብር ፡ በሚደርስ ፡ መቀጮ ፡ ሊቀጣ ፡ ይችላል ። እዚህ፡ የተመለከቱትን ፡ ሁለቱን ፡ የአካል ፡ ጉዳቶች ፡ ለመለየት ፡ የሚያስችል ፡ ሌላ ፡ ሕጋዊ ፡ መምሪያ ፡ የለም ፤ ሊኖርም ፡ አይችልም ፡ ይሆናል ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የተፈጠረው ፡ ችግር ፡ አንድ ፡ ድርጊት ፡ የተፈጸመው ፡ በት ክክል ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፴፱ ፡ ወይም ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፵፩ን ፡ በመተላለፍ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ካለ ማስቻሉም ፡ በላይ ፡ ብዙዎቹ ፡ ለዓይነት ፡ የመረጥናቸው ፡ ክሶች ፡ ሁለቱንም ፡ ቁጥ ሮች ፡ እንደጣሱ ፡ ሊቆጠሩ ፡ ይችሉ ፡ ነበር ።

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፵፩ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የአካልም ፡ ሆነ ፡ የጤንነት ፡ ጉዳት ፡ ካላስከተለ ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ይልቅ ፡ "ቀላል ፡ የሆኑ ፡ ሰንበሮ

ችን ፡ የደም ፡ መቋጠር ፡ ምልክቶችን ፡ ወይም ፡ በቶሎ ፡ የሚያልፉ ፡ ስቃዮችን” በአስ ከተለ ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ላይ ፡ አነስተኛ ፡ ቅጣት ፡ ስለሚወሰን ፡ የተጨማሪ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ ሆኖአል ። አነስተኛ ፡ ሰንበሮችን ፡ ያስከተለ ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ጉዳትን ፡ ካላስከተለ ፡ ድርጊቱ ፡ የበለጠ ፡ ቅጣት ፡ ሊወስንበት ፡ የሚገባ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። በእርግጥም ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ሆነ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አስተያየት ፡ ይኸው ፡ ይመስላል ።

ተከሳሹ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፴፱ን ፡ በመተላለፍ ፡ በግል ፡ አቤት ፡ ባይ ፡ ላይ ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ወንጀል ፡ ሠርቷል ፡ በመባል ፡ ተከሰሰ ። ተከሳሽ ፡ ከከሳሽ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ እንዲቀርብ ፡ የተጠራ ፡ መሆኑን ፡ ነግሮት ፡ ከሳሽ ፡ ጥሪውን ፡ ባለመቀበሉ ፡ ተከሳሽ ፡ ከሳሽን ፡ ለማነቅ ፡ ሞክሮ ፡ በጐረቤት ፡ ገላጋይነት ፡ ሊድን ፡ ቻለ ፡ ተባለ ። ተከሳሽ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ሲል ፡ ተከራከረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሁለት ፡ ወር ፡ ተኩልና ፡ ከሦስት ፡ ቀጠሮዎች ፡ በኋላ ፡ ፴ ፡ ብር ፡ መቀጮ፡ እንዲከፍል ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ እሥራት ፡ እንዲቀጣ ፡ ተፈረደበት ።

በዚህ ፡ ምሳሌ ፡ ውስጥ ፡ ከሳሽ ፡ ተከሳሽን ፡ ለማነቅ ፡ በሞከረበት ፡ ወቅት ፡ “ቀላል ፡ የሆኑ ፡ ሰንበሮችን ፡ የደም ፡ መቋጠር ፡ ምልክቶችን ፡ ወይም ፡ በቶሎ ፡ የሚያልፉ ፡ ስቃዮችን ፡” እንደደረሰበት ፡ ባይጠረጠርም ፡ በተከሳሽ ፡ ላይ ፡ የተጣለበት ፡ መቀጫ ፡ ለዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ወንጀል ፡ ከተደነገገው ፡ የበለጠ ፡ ነው ።

በግል ፡ አቤቱታ ፡ እንደሚቀርቡት ፡ የወንጀል ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ ብዙዎቹ ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ምክንያት ፡ የቀረቡ ፡ ክሶች ፡ በአቤት ፡ ባዮች ፡ በተከታታይ ፡ ቀጠሮ ፡ አለመቅረብ ፡ ምክንያት ፡ ፋይሎቹ ፡ ተዘግተዋል ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፴፰ን ፡ ወይም ፡ ፭፻፴፱ን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ በአቤት ፡ ባዮች ፡ አለመቅረብ፡ ምክንያት ፡ ፋይሎቻቸው ፡ ተዘግቷል ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ እንደዚህ ፡ ባሉት ፡ ክርክሮች፡ ከሳሾች ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረቡ ፡ በኋላ ፡ ምስክሮችን ፡ በመጥራት ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ወገን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብ ፡ በማድረግ ፡ የሚፈጠረው ፡ ውጣ ፡ ውረድ ፡ እያደር ፡ ያሰለቻቸው ፡ ይመስላል ።

ከሳሽ ፡ የመበቀል ፡ ፍላጐት ፡ ያለውም ፡ እንደሆነ ፡ ፖሊስ ፡ ተከሳሹን ፡ በመያዝ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ለፍርድ ፡ እስኪቀርብ ፡ ድረስ ፡ ለሁለት ፡ ወይም ፡ ለሦስት ፡ ሳምንታት ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ በማቆየት ፡ በሚወስደው ፡ እርምጃ ፡ ብቻ ፡ ሊረካ ፡ ይችላል ።

ሌላው ፡ የግል ፡ አቤት ፡ ባዮች ፡ ክሳቸውን ፡ እንዳይቀጥሉ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ነገር ፡ ቀጠሮው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በአንዳንድ ፡ ወር ፡ ልዩነት ፡ መቀጠሩ ፡ ነው ። በየቀጠሮው ፡ መሃከል ፡ ያለው ፡ የጊዜው ፡ ርዝመት ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ነገሩን ፡ ችላ ፡ እንዲሉት ፡ ጊዜ ፡ ይሰጣቸዋል ። ስለዚህ ፡ ነገሩ ፡ በተሟሟቀበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረቡ ፡ ክሶች ፡ ምናልባት ፡ እስከመጨረሻው ፡ ክርክራቸው ፡ አይቀጥልም ፡ ይሆናል ።

## በንብረት ፡ ላይ ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ብዙዎቹ ፡ በግል ፡ አቤት ፡ ባዮች ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ የሚሠራን ፡ ወንጀል ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። አንድ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ክስ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶ ፡ በሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡

ስለማድረግ ፡ በመጥቀስ ፡ የቀረበ ፡ ነበር ። በመሠረቱ ፡ ይህ ፡ ቁጥር ፡ የሚዳኘው ፡ "በሌላው ፡ ሰው ፡ ርስት ፡ (ባለቤትነት) ፡ በሰላማዊ ፡ ይዞታ ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡" የሚያስከትልን ፡ ድርጊት ፡ ነው ። (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶) ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ጥፋት ፡ ተደርጓል ፡ በማለት ፡ የሚነሱ ፡ ክሶች ፡ በግል ፡ አቤቱታ ፡ በወንጀለኛ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶፫ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀርባሉ ። ተመሳሳይ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ የከብት ፡ መንጋን ፡ በመልቀቅ ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ጥፋት ፡ በማድረስ ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፵፱) ፡ በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶፩) ፡ እና ፡ የወሰን ፡ ምልክቶችን ፡ በማዛወር ፡ ወይም ፡ በማንሣት ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶፪) ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ ይደነግጋሉ ። በእንደነዚህ ፡ ዓይነቶቹ ፡ ክሶች ፡ አንድ ፡ ሦስተኛው ፡ ያህል ፡ ከሳሹ ፡ በጥቂት ፡ ቀጠሮዎች ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ስለአቋረጠ ፡ ተሰርዘዋል ። የሚቀጥሉት ፡ ክሶች ፡ በሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ሁከት ፡ አድርሰዋል። በመባል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ።

ተከሳሽ ፡ የከሳሽ ፡ ንብረት ፡ ነው ፡ በተባለ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ሠርተሃል ፡ በመባል ፡ ተከሰሰ ። ተከሳሽ ፡ ቤቱን ፡ ለመሥራት ፡ ሲል ፡ ከሳሽ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ አጥር ፡ ከመስበሩም ፡ ሌላ ፡ ሰብሉንም ፡ አጥፍቶበታል ። ተከሳሽ ፡ የወንጀለኛ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶ ፡ እና ፡ ፮፻፶፫ን ፡ ተላልፎአል ፡ ተብሎ ፡ ተከሰሰ ። በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ ከሳሽም ፡ ሆነ ፡ ተከሳሽ ፡ አልቀረቡም ። በሚቀጥለው ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሹ ፡ ቀርቦ ፡ ለክሱ ፡ ምክንያት ፡ ለሆነው ፡ ድርጊት ፡ ኃላፊ ፡ አይደለሁም ፡ ሲል ፡ ተከራከረ ። በሶስተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሽ ፡ አልቀረበም ፡ ግን ፡ በአራተኛው ፡ ቀጠሮ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ቀርበው ፡ ነገራቸውን ፡ በመንደር ፡ ሽማግሌዎች ፡ ለመጨረስ ፡ መስማማታቸውንና ፡ የሽምግልናውንም ፡ ሁኔታ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚገልጹ ፡ መሆናቸውን ፡ አስረዱ ። ነገሩ ፡ ፍጻሜ ፡ ስላላገኘ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተመለሱ ። ተከሳሹ ፡ ለቤቱ ፡ መሠራት ፡ ኃላፊ ፡ ነው ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ እንዲያቀርብ ፡ ታዘዘ ። በስድስተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሽ ፡ አልቀረበም ፤ በሰባተኛው ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ሳይቀርቡ ፡ ቀሩ ። ፋይሉ ፡ ከተከፈተ ፡ ከስምንት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ በከሳሽ ፡ አለመቅረብ ፡ ምክንያት ፡ ተዘጋ ።

> ተከሳሽ ፡ ይጠጣ ፡ በነበረበት ፡ ቡና ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጥፋት ፡ አድርጓል ፡ በመባል ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶፫ ፡ ተጠቅሶበት ፡ ተከሰሰ ። ነገሩ ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ ተቀጠረ ። በመጀመሪያው ፡ የምስክሮች ፡ ቃል፡ ተሰማ ፤ በሁለተኛውና ፡ በሶስተኛው ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ሳይቀርቡ ፡ ቀሩ ። ፋይሉ ፡ ተዘጋ ።

## ክብርን ፡ ስለ ፡ መንካት ።

ብዙዎቹ ፡ በግል ፡ አቤቱታ ፡ የተነሱ ፡ ክሶች ፡ ክብር ፡ መንካትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነበሩ ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ክሶቹ ፡ የሚመለከቱት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፤ ፭፻፹፩ን ፡ በመተላለፍ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ "የስድብና ፡ የማዋረድ" ፡ ወንጀል ፡ ሲሆን፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ "ስምን ፡ ስለማጥፋትና ፡ በሐሰት ፡ ስለመወንጀል ፡" (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፹ ፡) ነው ። ዛቻ ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፶፪) ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፵፬) ፡ እና ፡ አስቦ ፡ የተደረገ ፡ ቀላል ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፴፱፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ከስም ፡ማጥፋትና ፡ ከስድብ ፡ ክሶች ፡ ጋር ፡ ተደርበው ፡ ይቀርባሉ። የሚቀጥሉት ፡ ለነዚህ ፡ ዓይነቶቹ ፡ ክሶች ፡ ሁለት ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ።

ተከሳሹ ፡ ከሳሿን ፡“ባሪያ” ፤ ብሎ ፡ በመሳደብና ፡ ሊገድላትም ፡ አስፈራርቷታል ፡ ተብሎ ፡ ተከሰሰ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፹፫ንና ፡ ፭፻፶፪ን ፡ ተላልፎአል ፡ በመባል ፡ ተከሰሰ ። በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሽ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ አለ ፤ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ መረጃዎቹን ፡ ስላላዘጋጀ ፡ ነገሩ ፡ ተቀጠረ ። በሁለተኛውና ፡ በሶስተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ ባለመቅረባቸው ፡ ፋይሉ ፡ ተዘጋ ።

ተከሳሹ ፡ ከሳሽን ፡ “ሌባ ፡” ብሎ ፡ በመጥራቱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፹፫ን ፡ ተላልፎአል ፡ በመባል ፡ ተከሰሰ ። በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሽ ፡ አልቀረበም ፤ በሁለተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ከጠበቃው ፡ ይመካከር ፡ ዘንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጠው ፡ ጠየቀ ፤ በሦስተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ምስክሮቹ ፡ ሳይቀርቡ ፡ ቀሩ ። በአራተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሽን ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘው ፡ ፴ ፡ የኢት ፡ ብር ፡ እንዲቀጣ ፡ በየነበት ።

ለዓይነት ፡ ከመረጥናቸው ፡ የስድብና ፡ የስም ፡ ማጥፋት ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ ሃምሳ ፡ በመቶ ፡ የሚሆኑት ፡ በአቤት ፡ ባዮች ፡ አለመቅረብ ፡ ምክንያት ፡ ፋይላቸው ፡ ተዘግቷል ። ይህም ፡ በግል ፡ አቤቱታ ፡ ተጀምረው ፡ በመካከሉ ፡ ከሚቋረጡት ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ፡ በብዛት ፡ ከፍተኛውን ፡ ደረጃ ፡ ይዞአል ። ክርክራቸው ፡ እስከ ፡ ፍርድ ፡ ድረስ ፡ ሳይዘልቅ ፡ በመካከሉ ፡ የሚቋረጠው ፡ የስድብና ፡ የስም ፡ ማጥፋት ክሶች ፡ ቁጥር ፡ በተለይ ፡ ከፍ ፡ ያለበት ፡ ምክንያት ፡ ከሌሎች ፡ በግል ፡ አቤቱታ ፡ ከሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ይልቅ ፡ ነገሩ ፡ በተሚሚቀበት ፡ ወቅት ፡ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ የሚቀርቡት ፡ የነዚህ ፡ዓይነቱ ፡ ወንጀሎች ፡ ስለሆኑና ፡ በኋላም ፡ ቶሎ ፡ ስለሚረሱ ፡ ነው ።

የቀሩት ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ሰላምን ፡ የሚያውኩ ፡ ድርጊቶች ፡ ስካርና ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤትን ፡ ደንቦችና ፡ የትራፊክ ፡ ሕጎችን ፡ መጣስ ፡ የሚመለከቱ ፡ ነበሩ ። ሌሎች ፡ እዚህ ፡ ምድብ ፡ ውስጥ ፡ የሚገቡ ፡ ክሶች ፡ ቅጣታቸው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፸፩ ፡ (፩) ፡ የተመለከተው ፡ ጥቂት ፡ የሥራ ፡ ፈትነት ወንጀሎች ፡ ናቸው ።

> “(፩) ሙሉ ፡ አካል ፡ እያለው ፡ መኖሪያ ፤ የተለምዶ ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ምግብ ፡ ለማግኘት ፡ የተረጋገጡ ፡ ወይም ፡ አሉ ፡ ለመባል ፡ የሚችሉ ፡ ለዚሁ ፡ አገልግሎት ፡ የሚረዱ ፡ ነገሮች ፡ ሳይኖሩት ፡ ሠርቶ ፡ ሊያገኝበት ፡ የሚችለውን ፡ ሥራ ፡ አልቀበልም ፡ በማለት ፡ የሥራ ፡ ፈትነትን ፡ የመጥፎ ፡ አካሄድ ፡ ዐመልን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ነቀፌታ ፡ ያለበትን ፡ የመጥፎ ፡ ዘዴ ፡ ወይም ፡ የለማኝነትን ፡ ኑሮ ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ልማድ ፡ አድርጎ ፡ የያዘና ፡ በዚህም ፡ ኑሮው ፡ ለሕዝብ ፡ ፀጥታ ፡ አደገኛ ፡ ሆኖ ፡ የሚታይ ፡ ሰው ፤ የነፃነት ፡ መወሰን ፡ ባለበት ፡ የግዴታ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ እስራት ፡ ይቀጣል ። (ቁጥር ፡ ፻፫)”

ሥራ ፡ ፈት ፡ በመባል ፡ በተከሰሰው ፡ ላይ ፡ ለማስፈረድ ፡ የሚደረገው ፡ ጥረት ፡ እምብዛም ፡ አይደለም ።-

ለምሳሌ ፡ ያህል ፡-

ተከሳሾቹ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ሕግ ፡ ቁጥር ፩፻፸፩ ፡ መሠረት ፡ አደገኛ ፡ በሆነ ፡ የሥራ ፡ ፈትነት ፡ ወንጀል ፡ ተከሰሰው ፡ ነበር ። በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ ተከሳሾቹ ፡ ጥፋተኞች ፡ አይደለንም ፡ ብለው ፡ ተከራከሩ ፤ ዐቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ምስክሮቹን ፡ ስላላቀረበ ፡ ነገሩ ፡ እንዲቀጠር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ጠየቀ ። በሁለተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ዐቃቤ ፡

ሕጉ ፡ ተከሳሾቹ ፡ ዋስ ፡ እንዲጠሩ ፡ አለዚያም ፡ ክርክሩ ፡ እስኪያበቃ ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንዲቆዩ ፡ ጠየቀ ። ተከሳሾቹ ፡ ዋስ ፡ ስላላገኙ ፡ በማረፊያ ፡ ቤት ፡ ቆዩ ፡ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ አራት ፡ ቀጠሮ ፡ ተቀጠረ ፤ በነዚህም ፡ ቀጠሮዎች ፡ ፖሊስ ፡ የተከሳሾቹን ፡ ጥፋተኝነት ፡ የሚያረጋግጡ ፡ ምስክሮች ፡ ሳያቀርብ ፡ ቀረ ። ፖሊስ ፡ የተባሉትን ፡ ምስክሮች ፡ ለማቅረብ ፡ ያልሞከረ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለደረሰበት ፡ ተከሳሾቹን ፡ በነፃ ፡ አሰናብቷቸዋል ።

የሕዝብን ፡ ፀጥታ ፡ በማወክ ፡ ከሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ የተለመዱት ፡ “ሰክሮ ፡ ወይም ፡ አዕምሮ ፡ የሚያናውጽ ፡ ነገር ፡ ቀምሶ ፡ ሕዝብን ፡ ማወክን ፡” (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፷፩ን) ፡ የሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ናቸው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የተጠረጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ዘወትር ፡ ወዲያውኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ የተደረገ ፡ ባይሆንም ፤ እንደሥራ ፡ ፈትነት ፡ ክሶች ፡ ሳይሆን ፡ በዚህ ፡ ቁጥር ፡ መሠረት ፡ የቀረቡ ፡ ክሶች ፡ ክርክራቸው ፡ እስከፍርድ ፡ ይዘልቃል ።

በአዲስ ፡ አበባ ፡ ብዙ ፡ ሆቴሎችና ፡ ቡና ፡ ቤቶች ፡ ስላሉ ፡ እነዚህን ፡ ድርጅቶች፡ የሚመለከቱ ፡ ጉዳዮችን ፡ በመዳኘት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከጊዜው ፡ ጥቂቱን ፡ ማጥፋት ፡ እንዳለበት ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

> ተከሳሿ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤትን ፡ የመጠጥ ፡ ቤት ፡ መዝጊያ ፡ ደንብ ፡ ተላልፋ ፡ ከምሽቱ ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ መጠጥ ፡ ስትሸጥ ፡ በመገኘቷ ፡ ተከሰሰች ። ለክሱ ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኗን ፡ አመነችና ፡ ፳ ፡ ብር ፡ ተቀጣች ።

የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ሊያደናቅፈው ፡ የሚችለው ፡ ችግር ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤትን ፡ ደንብ ፡ በመጣስ ፡ የተከሰሱ ፡ ሰዎች ፡ በተፈለጉ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አለመቅረባቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ችግር ፡ በችርቻሮ ፡ የሚሸጡ ፡ ሱቆችን ፡ ፈቃድ ፡ የጽዳትና ፡ የትራፊክ ፡ ደንቦችንና ፡ የመሳሰሉትን ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ባለማክበር ፡ በሚፈጸመው ፡ ወንጀል ፡ ምክንያት ፡ በሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ውስጥም ፡ አለ ።

በጠቅላላው ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ደንቦችን ፡ በመተላለፍ ፡ ምክንያት ፡ የሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ ሃያ ፡ ይሆናሉ ፤ ተከሳሾቹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ጥፋተኛነታቸውን ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ያምናሉ ። ቢሆንም ፡ ብዙ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ጊዜ ፡ በነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ባክኖአል ። ከዚህም ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣታቸውን ፡ ብቻ ፡ ለመክፈል ፡ በመጡ ፡ ሰዎች ፡ ተጣብቦ ፡ ነበር ። የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ደንቦች ፤ ተጥሰዋል ፡ ተብሎ ፡ በሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ ተከሳሽ ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ አምኖ ፡ ክርክሩን ፡ ለመቀጠል ፡ በማይፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ ስለነዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ክሶች ፡ አያያዝ ፡ ጉዳይ ፡ ሌላ ፡ ዘዴ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ አጀባቸው ፡ አነስተኛና ፡ በየቀኑም ፡ የሚሰሙት ፡ ክስ ፡ ቁጥር ፡ ያነሰ ፡ በሆነ ፡ ነበር ።

## ጠበቆች ፡ በወንጀል ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ።

እንደመረመርናቸው ፡ መዛግብት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ለወንጀል ፡ ተከሳሾች ፡ ጠበቆች ፡ እምብዛም ፡ አይቆሙም ። ከመረመርናቸው ፡ ፫፻፴፫ ፡ የወንጀል ፡ መዛግብት ፡ ውስጥ ፡ ለችግረኛ ፡ ተከሳሾች ፡ ጠበቃ ፡ የታዘዘላቸው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ሁለቱም ፡ ጠበቆች ፡ ለተከሳሾች ፡ እንዲቆሙላቸው ፡ የታዘዘው ፡ በግል ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ነበር ።

ከአንድ ፡ ክስ ፡ በስተቀር ፡ የተቀጠሩት ፡ ጠበቆች ፡ ሁሉ ፡ እንደስድብ ፡ ስም ፡ ማጥፋትና ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለማድረስ ፡ በመሳሰሉ ፡ በግል ፡ አቤቱታ ፡ በቀረቡ ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ ለተከሳሾች ፡ እንዲሟገቱ ፡ ነበር ።

ከአንድ ፡ ጠበቃ ፡ አገልግሎት ፡ የሚገኝ ፡ ጥቅም ፡ አለ ፡ የምንል ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ጥቅም ፡ ጠበቆች ፡ በተሟገቱባቸው ፡ ክርክሮች ፡ ውጤት ፡ ላይ ፡ አልታየም ። ጠበቆቹ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ እስከዚህም ፡ የጐላ ፡ ተጽዕኖ ፡ ያላቸው ፡ አይመስልም ። በመረጥናቸው ፡ ክሶች ፡ ጠበቆቹ ፡ ለደንበኞቻቸው ፡ የረቱላቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ቁጥር ፡ የተረቱባቸውን ፡ ያህል ፡ ነበር ።

ጠበቆች ፡ ያልቆሙባቸው ፡ ክሶች ፡ ጠበቆች ፡ ከቆሙባቸው ፡ ክሶች ፡ ይልቅ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጥባቸው ፡ ስለሚመስል ፡ የጠበቆች ፡ በክስ ፡ ውስጥ መኖር ፡ ለጉዳዩ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ በሚያስፈልገው ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ ለውጥ ፡ አሳይ ቷል ። ይህም ፡ በሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሳ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ጠበቆች ፡ ነገርን ፡ ለራሳቸው ፡ ጥቅም ፡ ሲሉ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ ያራዝማሉ ፡ የሚ ለው ፡ የዳኞችና ፡ የተሟጋቾች ፡ ጥርጣሬ ፡ አንደኛው ፡ ምክንያት ፡ ነው ። በየቀጠሮው ፡ የሚከፈሉ ፡ ስለሆነ ፡ ለነሱ ፡ ብዙ ፡ ቀጠሮ ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ጠበቆች ፡ ሲኖሩ ፡ ክርክሩ ፡ የሚራዘምበት ፡ ሁለተኛው ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ ጠበቃ ፡ ያቆሙት ፡ ወገኖች ፡ ጠበቃ ፡ ያስፈለጋቸው ፡ የሚሞግቷቸው ፡ ወገኖች ፡ በክ ርክሩ ፡ እስከመጨረሻው ፡ ለመግፋት ፡ አስበዋል ፡ ብለው ፡ ስላመኑ ፡ ነው ። ወይም ፡ ጠበቃ ፡ ያቆሙት ፡ ክርክሩን ፡ በመካከል ፡ ላለማቋረጥ ፡ ወስነው ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ጠበቆች ፡ በክርክሩ ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑባቸው ፡ ክሶች ፡ በርቀ ፡ ስምምነትም ፡ ሆነ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ አይፈጸሙም ።

## የወንጀል ፡ ይግባኞች ።

ከወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ እንደተገኘው ፡ በወንጀል ፡ ፍርዶች ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ የተጠየቀው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነበር። ይህም ፡ ብዙዎቹ ፡ ወረዳ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰሙት ፡ ወንጀሎች ፡ የሚወሰንባቸው ፡ ቅጣት ፡ አነስተኛ ፡ በመ ሆኑ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ምክንያት ፡ ከብዙዎቹ ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ተከሳሾች ፡ የአቅም ፡ ማጣት ፡ ጋር ፡ ተጣምሮ ፡ ይግባኝ ፡ ማለትን ፡ የማይቻል ፡ ጉዳይ ፡ ያደርገዋል ። ተደጋግሞ ፡ የተጣለው ፡ ቅጣት ፡ በ፲፭ ፡ ብር ፡ እና ፡ በ፴ ፡ ብር ፡ መካከል ፡ የሆነ ፡ መቀጫ ፡ ሲሆን ፡ ይግባኙ ፡ የሚፈጀው ፡ ገንዘብና ፡ ጊዜ ፡ ሲታሰብ ፡ ግን ፡ ከመቀጫው ፡ በጣም ፡ የበለጠ ፡ ይሆናል ።

## ስለወንጀል ፡ ክሶች ፡ መራዘም ፡ (መዘግየት) ።

የወንጀል ፡ ክሶች ፡ ውሳኔ ፡ ሳያገኙ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንዲጐተቱ ፡ የሚያደርጓ ቸው ፡ ምክንያቶች ፡ እነዚያው ፡ ብዙ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶችን ፡ ውሳኔ ፡ ሳያገኙ ፡ ካስፈላጊው ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ እንዲዘገዩ ፡ የሚያደርጓቸውና ፡ ሌሎችም ፡ ተጨማሪ ፡ ምክ ንያቶች ፡ ናቸው ።

በመጀመሪያ ፡ የባለጉዳዮቹ ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ አለመቅረብ ፡ ችግር ፡ አለ ። ፖሊሶች ፡ የወንጀል ፡ ተከሳሾችን ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ተከሳሾች ፡ ይልቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይዞ ፡ ማቅረብን ፡ በበለጠ ፡ ስለሚመርጡ ፡ የተከሳሾች ፡ አለመቅረብ ፡ በፍትሐ፡

ብሔር ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ የፈጠረውን ፡ ችግር ፡ ያህል ፡ በወንጀል ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ ባይፈጥርም ፡ በግል ፡ አቤቱታ ፡ በቀረቡ ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ የተከሳሽ ፡ በአንድ ፡ ወይም ሁለት ፡ ቀጠሮ ፡ አለመቅረብ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው ።

የወንጀል ፡ ክሶችን ፡ ከሚያዘገያቸው ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ የምስክሮች ፡ በተፈለጉበት ፡ ቀን ፡ አለመቅረብ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በወንጀል ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ ለመመስከር፡ ፈቃደኞች ፡ አይመስሉም ። ለዚህም ፡ ምክንያቱ ፡ ምስክርነታቸው ፡ ጥፋተኛ ፡ በመባል ፡ በሚፈረድበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤትና ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ከዚሁ ፡ ሰው ፡ የሚጠብቃቸውን ፡ የቂም ፡ በቀል ፡ በመፍራት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ምስክሮቹን ፡ በቀጠሮ ፡ ቀን ፡ እንዲገኙ ፡ ማድረግ ፡ የተሳናቸው መሆኑን ፡ በመዛግብቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ መግለጫዎች ፡ በተጨማሪ ፡ ይገልጣሉ ። ፖሊሶች ፡ እንቀርብም ፡ ባዮች ፡ ምስክሮችን ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ከታዘዙ ፡ በኋላም እንኳ ፡ እነዚህ ፡ ምስክሮች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በየቀጠሮው ፡ አይገኙም ።

ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ብሎ ፡ ቢከራከር ፡ በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ ማስረጃዎቹን ፡ ለማቅረብ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ስለማይዘጋጅ ፡ ለክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ መራዘም ፡ ምክንያት ፡ ሆኖአል ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አንዳንዴ ፡ የተከሳሾቹን ፡ ክርክር ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ በማዳመጥ ፡ ብቻ ፡ ከሰዓት ፡ በፊት ፡ ያለውን ፡ ጊዜ ፡ በሙሉ ፡ ያሳልፋል ። አንድ ፡ ተጠርጣሪ ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ ያመነም ፡ እንደሆነ ፡ ተገቢው ፡ ቅጣት እንዲወሰንበት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ይጠይቃል ። ግን ፡ ተከሳሽ ፡ ጥፋተኛ ፡ አይደለሁም ፡ ካለ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክርክሩን ፡ ለማሰናዳት ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ ነገሩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለወር ፡ ይቀጠራል ። ይህ ፡ ጊዜ ፡ ምናልባትም ፡ ለብዙዎች ፡ በግል፡ አቤቱታ ፡ ለቀረቡ ፡ ክሶች ፡ የመብረጃ ፡ ወቅት ፡ በመሆን ፡ ስለሚያገለግል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ሆነ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በወሩ ፡ ውስጥ ፡ ይታረቃሉ ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ያደርጉ ፡ ይሆናል ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የሚጠቀምበት ፡ የቀጠሮን ፡ ማራዘም ፡ ዘዴ፡ ተከሳሹ ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ የሚያምንበት ፡ ክርክር ፡ ከማሰናዳት ፡ ያድነዋል ። ግን ፡ የተከሳሽ ፡ ጥፋተኛነቱን ፡ ማመን ፡ ወይም ፡ አለማመን ፡ በሌላ ፡ በኩል የፍርድ፡ ቤቱንም ፡ ሆነ ፡ የተከሳሹን ፡ ጊዜ ፡ በመቆጠብ ፡ ዘዴ ፡ ሊያረጋግጥ ፡ ይችላል ።

በመጨረሻም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ እንደሚታየው ፡ ክሶች፡ በአፋጣኝ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲያገኙ ፡ ዳኛው ፡ ያለው ፡ ዝንባሌ ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ እስከ ፡ ፍርድ ፡ ድረስ በሚፈጀው ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ ተጽዕኖ ፡ አለው ። ዳኛው ፡ አለመዘጋጀትንና ፡ ሌሎችንም ፡ ጠበቆችና ፡ ተሟጋቾች ፡ የፍርዱን ፡ ቀን ፡ ለማስተላለፍ ፡ የሚጠቀሙባቸውን ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴዎች ፡ ችላ ፡ ለማለት ፡ ያለው ፡ ፈቃደኝነት ፡ የኋላ ፡ ኋላ ፡ የክርክሩን ፡ ዕድሜ ፡ የሚወስን ፡ ይሆናል ።

## የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ።

### መግቢያ ፦

በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኘው ፡ የመናገሻ ፡ አውራጃ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከከተማው ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ በሁሉም ፡ አቅጣጫ ፡ በሃምሳ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ርቀት ፡ ባለው ፡ ስፋት፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ሲኖረው ፡ በከተማው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ። ስለዚህ ፡ ከከተማው ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ ዙሪያውን ፡ በ፶ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ርቀት ፡ በሚገኘው ፡ ስፋት ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ በአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡

ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የሆነ ፡ ክስ ፡ ሲኖራቸው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ ክሳቸውን ፡ ማቅረብ ፡ ይኖርባቸዋል ። እንደዚሁም ፡ በዚህ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፍርድ ፡ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ የሚሰማው ፡ በመናገሻ አውራጃ ፡ ነው ።

በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ውስጥ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አለ ። የመናገሻ ፡ አውራጃ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመዝገብ ምርመራ ፡ የተመረጠበት፡ምክንያት ፡ ክርክሩ ፡ እዚያ ፡ የተካሄደ ፡ ክስ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በሚኖሩበት ፡ ከተማ፡ አካባቢ ፡ በሚገኝ ፡ ገጠር ፡ ውስጥ ፡ በወረዳና ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች የሚ ቀርቡትን ፡ ክሶች ፡ ዓይነት ፡ በመጠኑ ፡ ስለሚያመለክት ፡ ነው ። ይህም ፡ ከላይ ፡ የተ ጠቀሰው ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚመለከተው ፡ በሙሉ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ የሚ ነሳ ፡ ክርክርን ፡ ስለሆነ ፡ ለምርምሩ ፡ ጥሩ ፡ ሚዛንን ፡ ይሰጠዋል ተብሎ ፡ ተገምቷል ።

<u>የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ክስ ።</u>

የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ በገጠር ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ የመ ሬት ፡ ክርክር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ከሚሰማቸው ፡ ክሶች ፡ ከመቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ይሆናል። ከነዚህም ፡ ወደ ፡ ሁለት ፡ ሶስተኛ ፡ የሚጠጉት ፡ በልዩ ፡ ልዩ፡ ምክንያት ፡ የሚነሱ ፡ የውርስ ፡ መብቶችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነበሩ ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የውርስ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፰፻፺፮ ፡ መሠረት፡ "የወራሽነት ፡ ማስረጃ" ፡ መስጠትን ፡ ብቻ ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ ጉዳዮች ፡ አብዛኛ ውን ፡ ጊዜ ፡ የሚያከራክሩ ፡ አልነበሩም ።

> አመልካቾች ፡ ሳይናዘዝ ፡ የሞተው ፡ የአባታቸው ፡ ወራሾች ፡ መሆናቸው ፡ እንዲታወቅላቸው ፡ ጠየቁ ። በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ በነገሩ ፡ ያገባናል ፡ የሚሉ ፡ ወገኖች ፡ እንዳሉ ፡ ጥያቄአቸውን ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ በጋዜጣ ፡ ማስ ታወቂያ ፡ እንዲወጣ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዘዘ ። በሁለተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ማናቸ ውም ፡ ወገን ፡ ሳይቀርብ ፡ ቀረ ። በሶስተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ማስታወቂያው ፡ የወጣበትን ፡ ጋዜጣ ፡ ቅጂ ፡ ይዘው ፡ አመልካቾች ፡ ቀረቡ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያገባናል ፡ ባዮች ፡ ለመቅረብ ፡ ይችሉ ፡ ዘንድ ፡ ነገሩን ፡ በቀጠሮ ፡ አስተላ ለፈው ። በአራተኛው ፡ ቀጠሮ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የአመልካቾችን ፡ ወራሽነት የሚደግፉ ፡ ምስክሮችን ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ የውርስ ፡ ማስረጃውን ፡ ጥያቄ ፡ ተቀበለ ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፰፻፹፮ ፡ ፰፻፺፪ ፡ እና ፡ ፱፻፺፮ ፡ ተጠቅሰው ፡ ነበር ።

ሌላው ፡ ተደጋግሞ ፡ ለመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበው ፡ ክስ ፡ ደግሞ ፡ የመሬት ፡ ግዢንና ፡ ሽያጭን ፡ ውል ፡ የሚመለከት ፡ ነበር ። የዚህም ፡ ዓይነቱ፡ ክስ ፡ በመሬት ፡ ምክንያት ፡ ከሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ አንድ ፡ ስድስተኛው ፡ ነበር ።

> ከሳሽ ፡ በሽያጭ ፡ ውል ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ሜትር ፡ ካሬ ፡ ተብሎ ፡ የተጠቀሰውን ፡ መሬት ፡ ተከሳሽ ፡ ሸጦልኛል ፡ አለ ። መሬቱ ፡ ሰባ ፡ ስድ ስት ፡ ሺህ ፡ ሜትር ፡ ካሬ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ከሳሽ ፡ በገዛበት ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ያልተረከበው ፡ መሬት ፡ ዋጋ ፡ በገንዘብ ፡ እንዲመለስለት ፡ ጠየቀ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፫፻፲፩ን ፣ ፩ሺ፫፻፴፩ን ፡ ፩ሺ፫፻፳፫ን ፡ ፩ሺ፫፻፸፩ን ፡ ፩ሺ፫፻፸፫ን ፡ ፪ሺ፪፻፸፯ንና ፡ ፪ሺ፳፫ን ፡ በመጥቀስ ፡ በጥያቄው ፡ መሠረት ፡ ለከሳሽ ፡ ፈረደለት ።

የቀሩት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ "የመሬት ፡ ክርክሮች" ፡ በባለቤትነት ፡ (ባለሃብትነት) ፡ ላይ ፡ አለመስማማትንና ፡ በተለያዩ ፡ ምክንያቶች ፡ የመጡ ፡ የይዞታ ፡ መብቶችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ክሶች ፡ ነበሩ ።

<u>ለምሳሌ ፡</u>

ከሳሽ ፡ የአንድ ፡ ንብረት ፡ ባለሀብትነቱ ፡ እንዲታወቅለት ፡ ጠየቀ ። ያገባናል ፡ የሚሉ ፡ ወገኖች ፡ ይቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ ጥሪው ፡ በጋዜጣ ፡ እንዲታወጅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዘዘ ። አንድ ፡ ተከራካሪ ፡ ቀርቦ ፡ ከሶስተኛ ፡ ሰው ፡ በተዋዋለው ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ መሬቱ ፡ በይዞታው ፡ ሥር ፡ መሆኑን ፡ አመለከተ ። ግን ፡ የተከራካሪው ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ጊዜ ፡ ያለፈ ፡ መሆኑ ፡ ስለታወቀ ፡ የአመልካቹ ፡ የባለቤትነት ፡ መብት ፡ ተረጋገጠ ። ምንም የተጠቀሰ ፡ ሕግ ፡ አልነበረም ። ሌሎች ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሚሰሙ ጉዳዮች ፡ ብድር ፡ በወቅቱ ፡ አለመክፈልን ፡ በአሠሪና ፡ በሠራተኛ ፡ መካከል ፡ የሚነሱ ፡ ክርክሮችን ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ለሽያጭ ፡ ውል የማስመዝገብ ፡ ማመልከቻዎችንና ፡ የዋስትና ፡ ግዴታዎች ፡ እንዲፈጸሙ፡ መጠየቅን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነበሩ ። የጋብቻ ፡ ክርክሮችም ፡ ተሰምተዋል ። ከመጋባታቸው ፡ በፊት ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ያመጡትን ፡ ሀብት ፡ በሚፋቱበት ፡ ወቅት ፡ እኩል ፡ ለመካፈል ፡ ውል ፡ ገብተው ፡ ነበር ። ባልና ፡ ሚስት ፡ ሲፋቱ ፤ ባልየው ፡ ለሚስትየዋ ፡ የሚደርሳትን ፡ የንብረት ፡ ድርሻ ፡ ሳይሰጣት ፡ ቀረ ። ክርክሩ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ ዳኞች ፡ እንዲታይና ፡ ባልየውም ፡ ነገሩ ፡ በመታየት ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ለጊዜው ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ለሚስቱ ፡ እንዲሰጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዘዘ ። የአቤቱታው ፡ ማመልከቻ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷፫ንና ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፸፫ን ፡ ጠቅሷል ።

<u>ስለፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ መዘግየት ፡ ጉዳይ ።</u>

በዓመት ፡ ውስጥ ፡ የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ የሰማቸው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ በዚህኑ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰማቸውን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ ያህል ፡ አይበዙም ። በተጨማሪም ፡ በወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደሚገኙት፡ ሁለት ፡ ዳኞች ፡ ሳይሆን ፡ የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ የሥራው ፡ ብዛት ፡ የተከፈለባቸው፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስችሉ ፡ አራት ፡ ችሎቶች ፡ ሲኖሩት ፡ እያንዳንዱ ፡ ችሎትም ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ዳኞች ፡ አሉት ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ብዙዎቹ ፡ መናገሻ ፡ አውራጃ ፡ የሚቀርቡት ፡ አቤቱታዎች ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ሳይቀርብ ፡ ፍርድ ፡ የተሰጣቸውን ፡ የመሬት ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።

ስለዚህ ፡ የክሶች ፡ በብዛት ፡ መጠራቀም ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙት ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ እንደሆነው ፡ ሁሉ ፡ ለመናገሻ፡አውራጃው፡ አይደለም ። ግን ፡ የመሬት ፡ ክርክሮች ፡ በተለይም ፡ የውርስን ፡ የይዞታንና ፡ የባለቤትነትን ፡ መብት ፡ የሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ የብዙ ፡ ምስክሮችን ፡ ቃል ፡ መስማትንና ፡ ብዙ ፡ ሰነዶች ፡ ማቅረብን ፡ ይጠይቃሉ ። የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ክርክሩ ፡ ከሚነሳበት ፡ አካባቢ ፡ ርቆ ፡ ስለሚገኝ ፡ ምስክሮችና ፡ ተሟጋቾች ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ለመቅረብ ፡ ያዳግታቸዋል ።

ከሳሽ ፡ ምክንያቱ ፡ ባልተገለጸ ፡ ጉዳይ ፡ ከራሱ ፡ ከሆነው ፡ መሬት ፡ ከፍሎ ፡ ለተከሳሽ ፡ ለአሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በይዞታ ፡ ይሰጠዋል ። ከአሥራ ፡

አምስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከሳሽ ፡ ተከሳሽን ፡ መሬቱን ፡ እንዲመልስለት ፡ ቢጠይቀው ፡ መሬቱን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሰጠው ፡ በመሆኑ ፡ ተከሳሽ ፡ አሻፈረኝ ፡ አለ ። የቀጠሮዎቹ ፡ ሁኔታ ፡ እንደዚህ ፡ ነበር ። (፩) በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ የተከሳሽ ፡ ማመልከቻ ፡ ያልተስተካከለ ፡ በመሆኑ ፡ ነገሩ ፡ ተቀጠረ ፤ (፪) የሚቀርቡ ፡ ማስረጃዎች ፡ ስለነበሩ ፡ ነገሩ ፡ ዳግመኛ ፡ ተቀጠረ ፤ (፫) ከሳሽ ፤ ተከሳሽ ፡ ባቀረበው ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፡ መልሱን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ ጊዜ ፡ ጠየቀ ፤ (፬) ተከሳሽ ፤ ለከሳሽ ፡ ክርክር ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ጊዜ ፡ ጠየቀ ፤ (፭) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለፍርዱ ፡ ለማሰብ ፡ ጊዜ ፡ አስፈለገው ፤ (፮) ከሳሽ ፡ አልቀረበም ፤ (፯) ዳኞች ፡ አልሞሉም ፤ (፰) ፍርድ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክሮችን ፡ መቀበል ፡ ያስፈልጋል ፡ ተባለ ፤ (፱) የተፈለጉት ፡ ምስክሮች ፡ አልቀረቡም ፤ (፲) ከሳሽ ፡ አልቀረበም ፤ (፲፩) ተከሳሽ ፡ አልቀረበም ፤ (፪) የአንድ ፡ አስፈላጊ ፡ ሰነድ ፡ መቅረብ ፡ አስፈለገ ፤ (፲፫) መዝገቡ ፡ ከተከፈተ ፡ ከሰባት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ውሳኔ ፤ ተሰጠ ።

በትክክል ፡ ታስቦ ፡ የተሠራ ፡ ባይሆንም ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ምሳሌ ፡ የመሬት ፡ ክሶች ፡ የሚራዘሙባቸውን ፡ ምክንያቶች ፡ ያሳያል ።

የክሱ ፡ ማመልከቻ ፡ በደንብ ፡ የተጻፈ ፡ ቢሆንም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ያልታሰቡ ፡ ጭብጦች ፡ ተነስተዋል ። እነዚህም ፡ አዲስ ፡ ጭብጦች ፡ ለክርክር ፡ ሲቀርቡ ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተጨማሪ ፡ ምስክሮችንና ፡ ሰነዶችን ፡ ማቅረብ ፡ ያሻል ። ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ጉዳዩ ፡ ይዘገያል ። ድንገተኛ ፡ ጭብጥን ፡ በማቅረብና ፡ በማይቀርቡ ፡ ምስክሮች ፡ ምክንያት ፡ ከሚፈጠረው ፡ የክስ ፡ መዘግየት ፡ ሌላ ፡ ነገሩን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያቀረቡት ፡ ወገኖች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ጠበቃም ፡ ሆነ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ የሌላቸው ፡ ስለሆነ ፡ ክሳቸውን ፡ በሚገባ ፡ ለመቀጠል ፡ የተዘጋጁ ፡ አለመሆናቸውን ፡ እላይ ፡ ከተሰጠው ፡ ምሳሌ ፡ በግልጽ ፡ ለመረዳት ፡ ይቻላል ። አስፈላጊው ፡ ማስረጃ ፡ በጃቸው ፡ ቢኖርም ፡ እንኳን ፡ የአቀራረቡን ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ለይተው ፡ አያውቁትም ። ከዚህም ፡ የተነሳ ምስክሮቻቸውን እንዲቀርቡ ፡ ሳያስታውቋቸው ፡ ይቀራሉ ፤ አስፈላጊ ፡ ሰነዶችንም ፡ ማምጣትን ፡ ይዘነጋሉ ።

## ጠበቆችና ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ።

የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ክሳቸውን ፡ በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ የሚያቀርቡ ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ያላቸው ፡ ተሟጋቾች ፡ ቁጥር ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሳቸውን ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚያቀርቡት ፡ በጣም ፡ የበዛ ፡ ነው ።

በተለይም ፡ የክርክሩ ፡ ምክንያት ፡ መሬት ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ማቆሙ ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የመሬት ፡ ባለሀብትነት ፡ የቤተሰብ ፡ ጉዳይ ፡ በመሆኑ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። እንደሚታወሰው ፡ ሁሉ ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ በሕግ ፡ የሰው ፡ መብት ፡ ለተሰጣቸው ፡ ማኅበሮች ፡ ወይም ፡ ለመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በማይቆሙበት ፡ ጊዜ ፡ ሊወክሉ ፡ የሚችሉት ፡ ቤተሰቦቻቸውን ፡ መሆን ፡ ይኖርበታል ። ለድካማቸውም ፡ ዋጋ ፡ አይከፈላቸውም ። እነርሱም ፡ በቤተሰብ ፡ መተሳሰር ፡ ምክንያት ፡ ባለው ፡ ዝምድናና ፡ ራሳቸውም ፡ በክሱ ፡ የሚያገባቸው ፡ ስለሆነ ፡ ዘመዶቻቸውን ፡ ለመወከል ፡ ሁልጊዜ ፡ ፈቃደኞች ፡ ናቸው ።

ነገረ ፡ ፈጆች ፡ አቤቱታው ፡ ክርክርን ፡ በማያስከትል ፡ እንደ ፡ ወራሽነት ፡ መብትን ፡ ማሳወቅ ፡ ባሉ ፡ ጉዳዮችም ፡ ውስጥ ፡ መግባታቸውና ፡ እንዲሁም ፡ ጠበቆች ፡

የሚቆሙት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ክርክር ፡ ለሚያስፈልጋቸው ፡ ክሶች ፡ ከመሆኑ በቀር ፡ ሁለቱም ፡ ተሟጋቾችን ፡ የሚወክሉት ፡ በተመሳሰሉ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ነው ።

## የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኞች ።

ለመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ የሚቀርቡት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኞች ፡ የሚመጡት፡ በገጠር ፡ ከሚገኙት ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ በብዛት ፡ የመሬት ፡ ክርክሮች ፡ ሲሆኑ ፡ በ፲፱፻፷ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ከቀረቡት፡ ይግባኞች ፡ ውስጥ ፡ ስድሳ ፡ በመቶው ፡ የመሬት ፡ ክርክሮች ፡ ነበሩ ። በመሠረቱ ፡ እነዚህ ፡ ክርክሮች ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ናቸው ። እነርሱም ፡ በመሬት ፡ ውሎች ፡ ላይ ፡ የሚነሱ ክሶችና ፡ ይዞታን ፡ በማወክ ፡ የሚቀርቡ ፡ ክሶች ፡ ናቸው ።

አባት ፡ (ከሳሽ) ፡ ዛፍ ፡ እንዲተክልበትና ፡ ቤት፡ እንዲሰራበት ፡ ለልጁ ፡ (ተከሳሽ) ፡ መሬት ፡ ሰጠው ። አባት ፡ ይህንን ፡ መሬት ፡ ለልጁ ፡ የሰጠበት ፡ ምክንያት ፡ በሌላ ፡ የቤተሰብ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ አባትየው ፡ የልጁን ፡ እርዳታ ፡ ስለፈለገ ፡ ነበር ። ግን ፡ ልጁ ፡ አባቱ ፡ የሰጠውን ፡ መሬት ፡ ስላበላሸው ፡ መሬቱ ፡ እንዲመለስለት ፡ አባት ፡ ልጁን ፡ ከሰሰ ። የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለአባት ፡ ሲፈርድ ፡ የአውራጃውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ውሳኔ ፡ አፀና ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፩ሺ፬፻፳ ፡ ፩ሺ፩፻፸፮፡ ፩ሺ፩፻፸፯ ፡ እና ፡ ፩ሺ፩፻፹፱ ፡ እንዲሁም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥሮች ፡ ፪፻፵፬ ፡ ፫፻፵፰ ፡ ፬፻፲ ፡ እና ፡ ፪፻፷፫ ፡ ተጠቅሰው ፡ ነበር ።

ተሟጋቾቹ ፡ የቆየ ፡ ግንኙነት ፡ የሌላቸው ፡ እንደሆነ ፡ ክርክራቸው ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የኩታ ፡ ገጠም ፡ ርስቶችን ፡ ይዞታ ፡ መድፈርን ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

ተከሳሹ ፡ ሰብሎችን ፡ በከሳሽ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አብቅሎ ፡ ለገዛ ፡ ጥቅሙ ፡ ሸጦ ፡ ተጠቀመበት ፡ በመባል ፡ ተከሰሰ ። የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሽን ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘው ፡ ከሰብሉ ፡ ሺያጭ ፡ ያገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ ፈረደበት ። ተከሳሽ ፡ ይግባኝ ፡ ቢልም ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርዱን ፡ አፀናበት ።

የድንበሮች ፡ አለመወሰን ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ዓይነት ፡ ክርክሮች ፡ መነሾ ፡ ቢሆንም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ገብቷል ፡ በማለት ፡ የሚነሱ ፡ ክርክሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲቀርቡ ፡ ጭብጣቸው ፡ ባለሀብትነት ፡ ነበር ።

ነዋሪነቱ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሆነው ፡ ከሳሽ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ክልል ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ የባላገር ፡ ርስቱን ፡ ተከሳሹ ፡ ያላግባብ ፡ አረሰብኝ ፡ ሲል፡ አመለከተ ። ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ ክርክራቸውን ፡ ወደቀበሌው ፡ ያጥቢያ ፡ ዳኛ ፡ ወስደው ፡ ለነገሩ ፡ ትንሽ ፡ መፍትሔ ፡ አግኝተውለት ፡ ነበር ። ግን ፡ ተከሳሹ ፡ በስምምነታቸው ፡ ለመርጋት ፡ ስላልፈቀደ ፡ ከሳሽ ፡ ነገሩን ፡ ለወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቀረበ ።

ተከሳሽ ፡ የክሱ ፡ ምክንያት ፡ የሆነውን ፡ መሬት ፡ ሌላ ፡ ባለርስት ፡ ነኝ ፡ ባይ፡ሶስተኛ ፡ ሰው ፡ የሰጠው ፡ መሆኑንና ፡ የከሳሽንም ፡ ባለቤትነት ፡ የማያውቅለት ፡ መሆኑን ፡ አመለከተ ። ግን ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተባለው ፡ ሶስተኛው ፡ ሰው ፡ ቀርቦ ፡ እንዲመሰክር ፡ ሳያደርግ ፡ ለከሳሽ ፡ ፈረደለት ። ተከሳሽ ይግባኝ ፡ አለ ። አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሶስተኛውን ፡ ሰው ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ እንዲሰማ ፡ ከመምሪያ ፡ ጋር ፡ ክሱን ፡ መልሶ ፡ ላከለት ። ከሳሽ ፡ ይደግፈኛል ፡ ብሎ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፩ሺ፩፻፷፪ንና ፡ ፫ሺ፩፻፷፬ን ፡ ጠቅሷል ።

ከሞት ፡ በኋላ ፡ የሚደረግ ፡ የሀብት ፡ ክፍያ ፡ ያልተስተካከለ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረቡ ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ይግባኝ ፡ ተጠይቆባቸዋል ። ቢሆንም ፡ እነዚህ ፡ ይግባኞች ፡ እላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ የይግባኝ ፡ ዓይነቶች ፡ ጋር ፡ ሲወዳደሩ ፡ በቁጥር ፡ ያነሱ ፡ መሆናቸው ፡ ሳያስገርም ፡ አይቀርም ።

ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ሁለት ፡ ወንድማማቾች ፡ መሬት ፡ ገዙ ፤ ግን ፡ በገዙበት ፡ ጊዜ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መብት ፡ የሚያሳይ ፡ ሰነድ ፡ አልተዘጋጀም ፡ ነበር ። የመጀመሪያው ፡ ወንድም ፡ ሳይናዘዝ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ትቶ ፡ ሞተ ። ሁለተኛውም ፡ ሀብቱን ፡ በጠቅላላ ፡ ለሴት፡ ልጁ ፡ ትቶ ፡ ሞተ ። ከሳሽ ፦ ማለት ፡ ሳይናዘዝ ፡ የሞተው ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ መሬቱ ፡ የሁለቱ ፡ ወንድማማች ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ ስለነበረ ፡ ድርሻዋ ፡ እንዲሰጣት ፡ ክስ ፡ አቀረበች ።

ከሳሽን ፡ የሚደግፋት ፡ የጽሑፍ ፡ ሰነድ ፡ ባይኖራትም ፡ ወንድማማቾቹ ፡ በሕይወት ፡ ሳሉ ፡ መሬቱ ፡ የጋራ ፡ ንብረታቸው ፡ መሆኑን ፡ የሚያስረዱ ፡ ምስክሮች ፡ አቀረበች ። የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሳሽን ፡ በመደገፍ ፡ ፈረደ፤ ያውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ይህንኑ ፡ አጸና ። የተጠቀሱ ፡ የሕግ ፡ አንቀጾች፡ አልነበሩም ።

መሬት ፡ ነክ ፡ ያልሆኑ ፡ ይግባኞች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ብድርን ፡ የሥራ ፡ አገልግሎት ፡ መስጠት ፡ ውሎችን ፡ አለማክበርን ፡ ኪራይ ፡ አለመክፈልን ፡ ግብር ፡ አለማስገባትንና ፡ ከፍቺ ፡ በኋላ ፡ የሚደረግ  የሀብት ፡ ክፍያን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነበሩ ።

የብዙዎቹ ፡ ይግባኞች ፡ ምክንያት ፡ የበታቹ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ በደፈናው ፡ ትክክለኛ ፡ አይደለም ፡ ወይም ፡ ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ ለውሳኔው ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያመነበትን ፡ ማስረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቷል ፡ የሚል ፡ ነበር ።

በይግባኝ ፡ ላይ ፡ ከተሰጡት ፡ ሩብ ፡ ያህል ፡ የሚሆኑ ፡ ውሳኔዎች ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ውሳኔ ፡ የሚያሻሽሉ ፡ ነበሩ ። ብዙዎቹ ፡ የይግባኝ ፡ መዛግብት ፡ ክሱ ፡ ወደተጀመረበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ይኸው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳይሰማቸው ፡ የቀሩትን ፡ ምስክሮች ፡ ወይም ፡ ሳይቀበላቸው ፡ የቀሩትን ፡ ማስረጃዎች ፡ ጨምሮ ፡ ነገሩን ፡ እንደገና ፡ እንዲያየው ፡ ከመምሪያ ፡ ጋር ፡ ተመልሰዋል ።

ተከሳሹ ፡ የከሳሽን ፡ ቤት ፡ ቀለም ፡ ሊቀባ ፡ ተዋውሎ ፡ ለሥራው ፡ በቅድሚያ ፡ ገንዘብ ፡ ተከፍሎት ፡ ነበር ። ተከሳሽ ፡ ቤቱን ፡ በከፊል ፡ ቀብቶ ፡ ሥራውን ፡ ሳያጠናቅቅ ፡ ቀረ ። ከሳሽ ፡ በቅድሚያ ፡ የከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲመለስለት ፡ ተከሳሽን ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሰሰውና ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ተከሳሽን ፡ የወሰደውን ፡ ብር ፡ እንዲመልስ ፡ ሲፈርድበት ፡ አሥር ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ ጣለበት ። ተከሳሽ ፡ ለአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ አቀረበ ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ በቅድሚያ ፡ የተከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ ለተሠራው ፡ ሥራ ፡ ተመጣጣኝ ፡ ዋጋ ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ የከሳሽን ፡ ቤት ፡ ዐዋቂ ፡ እንዲመረምረው ፡ ሲል ፡ ከመምሪያ ፡ ጋር ፡ መዝገቡን ፡ ለወረዳው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ላከው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥሮች ፡ ፻፫ ፡ እና ፡ ፪፻፳፫ ፡ እንዲሁም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፩ ፡ ተጠቅሰው ፡ ነበር ።

ቁጥራቸው ፡ አነስተኛ ፡ የሆነ ፡ ክሶችን ፡ ብቻ ፡ (በመቶ ፡ አሥር) ፡ ወደ ፡ መጡበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሳይመልስ ፡ የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ፍርዳቸውን ፡ ገልብጧል ።

ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሕግ ፡ ሳይሆን ፡ የፍሬ ፡ ነገር ፡ ስህተት ፡ ተደርጓል ፡ ብለው ፡ ስለተከራከሩ ፡ ነው ። የፍሬ ፡ ነገር ፡ አለመስማማት ፡ ቢኖር ፡ የሚያስከትለውን ፡ አከራካሪ ፡ የፍሬ ፡ ነገር ፡ ጭብጥ ፡ ለማስረጃዎቹ ፡ አቅራቢያ ፡ በሆነው ፡ በመጀመሪያው ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማረጋገጡ ፡ ለባለጉዳዮቹ ፡ የቀና ፡ ይሆናል ። ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠው ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሚዛናዊ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ግልጽ ፡ የሕግ ፡ ሥህተቶችን ፡ በፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

> ይግባኝ ፡ ባዩ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ ተከሳሽ ፡ ነበር ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ፈረደበት ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ውሳኔ ፡ በመስጠት ፡ ፋንታ ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ መቀጮ ፡ እንዲከፍልና ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ እስር ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ፡ አዘዘ ። ተከሳሽ ፡ የተሻሻለውን ፡ የ፲፱፻፵፰ቱን ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቁጥሮች ፡ ፵፩ ፡ እና ፡ ፵፫ን ፡ በመጥቀስ ፡ ለአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ አለ ። የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ይግባኝ ፡ ባዩን ፡ በነፃ ፡ አሰናበተው ።

## ጠበቆችና ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ።

በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ከተሰሙት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኞች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ አሥራ ፡ አምስቱ ፡ ጠበቃ ፡ የቆመባቸው ፡ ነበሩ ። ይህም ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ በሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ደንበኞቻቸውን ፡ ከሚወክሉት ፡ የጠበቆች ፡ ቁጥር ፡ ጋር ፡ ሲወዳደር ፡ በጣም ፡ ብዙ ፡ ነው ።

ነገረ ፡ ፈጆች ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ክርክር ፡ እንዳላቸው ፡ ችሎታ ፡ ሁሉ ፡ ስለመሬት ፡ ክርክር ፡ የተለየ ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ባይመስልም ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ አባሎችን ፡ በመወከል ፡ ከመቶ ፡ በአሥራ ፡ ሶስቱ ፡ ላይ ፡ ቀርበዋል ። በይግባኝ ፡ ላይ ፡ ነገረ ፡ ፈጆች ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ ከሚጠየቅ ፡ ካሣ ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ብድር ፡ ክሶች ፡ ድረስ ፡ በማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ክርክሮች ፡ ውስጥ ፡ ገብተዋል ።

ስለዚህ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ባዮች ፡ ሩብ ፡ ያህል ፡ የሚሆኑት ፡ በቀጥታም ፡ ሆነ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ወኪል ፡ ነበራቸው ። በተጠናው ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይግባኝ ፡ ወደ ፡ መናገሻ ፡ አውራጃ ፡ የተወሰደባቸውን ፡ ክሶች ፡ የሚመስሉ ፡ ክርክሮች ፡ ጠበቃ ፡ የነበራቸው ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ በመቶው ፡ ብቻ ፡ ሲሆኑ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ የነበራቸው ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ያንሳሉ ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ በይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጠበቃን ፡ የሚያቆሙ ፡ ተሟጋቾች ፡ ቁጥር ፡ መጨመር ፡ ጉዳይ ፡ ሰዎች ፡ ራሳቸው ፡ በይግባኝ ፡ ክርክራቸውን ፡ በበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመቀጠል ፡ ያላቸውን ፡ ችሎታ ፡ የማይተማመኑበት ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል ።

## የነገር ፡ መዘግየት ።

በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ከሚሰሙ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክሶች ፡ ይልቅ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኞች ፡ ፈጥነው ፡ ውሳኔ ፡ ያገኛሉ ። ይህም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ እነዚህን ፡ ይግባኞች ፡ በሚመለከትበት ፡ ጊዜ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ አድርጎ ፡ ሳይሆን ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፋይሎችን ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ስለሚጠቀምባቸው ፡ መሆኑ ፡ አያጠራጥርም ። ቢሆንም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መዝገብ ፡ ያልተብራራ ፡ ወይም ፡ የሚያደናግር ፡ ስለነበር ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነገሩን ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ መስማት ፡ ነበ

ረበት ። የፋይሎች ፡ በብዛት ፡ መጠራቀም ፡ ችግር ፡ በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ስለሌለ ፡ ብዙ፡ ቀጠሮዎች ፡ ቢያስፈልጉም ፡ እንኳ ፡ ረጅም ፡ ቀጠሮ ፡ መስጠት ፡ አያሻም ።

ሆኖም ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መመላለስ ፡ ከፍርድ፡ ቤቱ ፡ ርቀው ፡ በሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል ።

ተከሳሾች ፡ በቃል ፡ በተፈጸመ ፡ የዱቤ ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ዕቃ ፡ ገዝተው ፡ ዕዳቸውን ፡ ለከሳሽ ፡ ሳይከፍሉ ፡ ቀርተዋል ፡ በመባል ፡ ተከሳሾቹ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ቀርቦባቸው ፡ ታሠሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ ባስታራቂ ፡ ሽማግሎች ፡ አማካይነት ፡ አንደኛው ፡ ተከሳሽ ፡ ዕዳውን ፡ ሊከፍል ፡ ሌላው ፡ ተከሳሽ ፡ ደግሞ ፡ ለከፋይ ፡ ዋስ ፡ ሆኖ ፡ ስምምነት ፡ አደረጉ ። ተከሳሾች ፡ ከእሥር ፡ ቤት ፡ ወጡ ። ተከሳሾች ፡ ዕዳቸውን ፡ ሳይከፍሉ ፡ ስለቀሩ ፡ በወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክስ ፡ ቀርቦባቸው ፡ ንብረታቸው ፡ ተሸጦ ፡ ዕዳው ፡ እንዲከፈል ፡ ተፈረደ ። ተከሳሾቹ ፡ ዕዳውን ፡ እንዲከፍሉ ፡ በተዋዋሉበት ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ባለመክፈላቸው፡ ታስረው ፡ ስለነበር ፡ ስምምነቱ ፡ በማስገደድ ፡ የተፈጸመ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ይግባኝ ፡ አሉ ። በይግባኙ ፡ ክርክር ፡ ላይም ፡ በሚቀጥሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ነገሩ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተቀጠረ ። (፩) ስለመጀመሪያው ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ሰነዶች ፡ እንዲቀርቡ ፡ አስፈለገ ፤ (፪) አንድ ፡ ዳኛ ፡ ጐደለ ፤ (፫) በመጀመሪያው ፡ ቀጠሮ ፡ እንዲቀርብ ፡ የታዘዘው ፡ ሰነድ ፡ አልቀረበም ፤ (፬) ያው ፡ ሰነድ ፡ አሁንም ፡ ስላልቀረበ ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወረዳውን ፡ ፖሊስ ፡ አዛዥ ፡ ራሱ ፡ ይዞ ፡ እንዲቀርብ ፡ አዘዘ ፤ (፭) በመጨረሻም ፡ የቀረበውን ፡ ሰነድ ፡ ለመመርመር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጊዜ ፡ አስፈለገው ፤ (፮) መልስ ፡ ሰጪዎች ፡ ክርክራቸውን ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ ጊዜ ፡ ተሰጣቸው ፤ (፯) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመመካከር ፡ ጊዜ ፡ አስፈለገው፤ (፰) ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ ነገሩን ፡ ለመመርመር ፡ ተጨማሪ ፡ ጊዜ ፡ አስፈለገው ፤ (፱) ፡ ከወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምርመራ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ሰነድ ፡ እንዲቀርብለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዘዘ ፤ (፲) ይግባኝ ፡ ባይ ፡ አልቀረበም ፤ (፲፩) ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ሳይቀርቡ ፡ ስለቀሩ ፡ ከአራት ፡ ወር፡ ተኩል ፡ በኋላ ፡ የይግባኙ ፡ ፋይል ፡ ተዘጋ ። በክርክሩ ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፭ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከተው ፡ ክርክር ፡ ለአንድ ፡ ክርክር ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ረጅም ፡ ጊዜና ፡ ብዙ ፡ ቀጠሮ ፡ ማስፈለጉን ፡ ለማስረዳት ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ አለመሆኑን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ። ሆኖም ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ጉዳዮች ፡ የተለመዱ ፡ ናቸው ። በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ በይግባኝ ፡ ለሚያዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ በፖሊሶች ፡ በፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ በተሚጋቾች ፡ እንዲሁም ፡ በፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ በምስክሮች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ትብብር ፡ ገና ፡ ፍጹም ፡ አለመሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ለክርክሩ ፡ አስቸኳይ ፡ ውሳኔ ፡ የነዚህን ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ ቅንጅት ፡ ክፍሎች ፡ ትብብር ፡ የሚጠይቅ ፡ አስቸጋሪ ፡ ጭብጥ ፡ ቢነሳ ፡ ነገሩ ፡ መጎተቱ ፡ የማይቀር ፡ ነው ።

## <u>የወንጀል ፡ ክርክሮች ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ክርክር ።</u>

በ፲፱፻፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ከተሰሙት ፡ የወንጀል ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ስድሳ ፡ ሰባት ፡ በመቶው ፡ ስለስርቆት ፡ ነበሩ ። በገጠር ፡ ይፈጸማሉ ፡ ተብለው ፡ እንደሚገመቱ ፡ ወንጀሎች ፡ ሁሉ ፡ አብዛኞቹ ፡ ስርቆቶች ፡ ቀላል ፡ የሆነ ፡ የከብት ፡ ስርቆትን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነበሩ ። ሌቦች ፡ በብዛት ፡ የሚሰርቁት ፡ በሬዎችን ፡ ይመስላል ። ከስርቆቱ ፡ ዓላማ ፡ በስተቀር ፡ የሚከተለው ፡ ለዚህ ፡ መሰሉ ፡ ወንጀል ፡ ዓይነተኛ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ተከሳሽ ፡ ዘጠኝ ፡ በጎችና ፡ ዘጠኝ ፡ ፍየሎችን ፡ ሰርቋል ፡ ተብሎ ፡ ተከሰሰ ።
ተላልፎአል ፡ ተብሎ ፡ የተጠቀሰበት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴ ፡ ነበር ። በመጀመሪያዎቹ ፡ ሁለት ፡ ቀጠሮዎች ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ምስክሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አልቀረቡም ። በሶስተኛው ፡ በተከሳሽ ፡ ላይ ፡ ስለ መሰከሩበት ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ እስራት ፡ እንዲቀጣ ፡ ተፈረደበት ። ይህ ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ መቀጫ ፡ የተጣለበት ፡ ተከሳሽ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በስርቆት ፡ የተቀጣ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴ ፡ ፩፻፺፫እና ፡ ፮፻፴፮ ፡ ተጠቅሰው ፡ ነበር ። የተቀሩት ፡ ወንጀሎች ፡ ስለ ቤት ፡ ዕቃና ፡ ስለእርሻ ፡ ውጤቶች ፡ ስርቆት ፡ ሲሆኑ ፤ በጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ ስርቆት ፡ ምክንያት ፡ የቀረቡ ፡ ክሶች ፡ በጣም ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ።

በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ከተሰሙት ፡ የወንጀል ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ በመቶው ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፴፰ን "አስቦ ፡ ለተደረገ ፡ ከባድ ፡ የአካል ፡ ጉዳት" ፡ መተላለፍን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ወንጀል ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሚሰሙት ፡ ተመሳሳይ ፡ ወንጀሎች ፡ የሚለየው ፡ በተጐጂው ፡ ላይ ፡ በተፈጸመው ፡ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ከባድነትና ፡ በተከሳሹ ፡ የአእምሮ ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። የዚህ ፡ ወንጀል ፡ ክስም ፡ በግል ፡ አቤቱታ ፡ ብቻ ፡ መቅረብ ፡ እንደሌለበት ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ። ቢሆንም ፡ ብዙዎቹ ፡ ክሶች ፡ የሚመነጩት ፡ የተጐጂው ፡ ወገን ፡ ለፖሊስ ፡ አቤቱታ ፡ ሲያቀርብ ፡ ነው ።

ተከሳሽ ፡ ከሳሽን ፡ ሆዱና ፡ ደረቱ ፡ ላይ ፡ በጩቤ ፡ወግቷል ፡ ተብሎ ፡ ተከሰሰ ። ከሳሽ ፡ የተከሳሽን ፡ እናት ፡ በመምታት ፡ ነገሩን ፡ ቢጀምርም ፡ ተከሳሽ ፡ ካስፈላጊው ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ አድራጎት ፡ ፈጽሟል ። በማለት ፡ አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሽን ፡ በሶስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ እንዲቀጣ ፡ ፈረደበት ። የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፭፻፩ ፡ ፭፻፳ ፡ ፮፻፳ ፡ እና ፡ ፭፻፴፰ ፡ ተጠቅሰዋል ። ክርክሩ ፡ በጠቅላላ ፡ የፈጀው ፡ ሶስት ፡ ወር ፡ ከስድስት ፡ ቀን ፡ ሲሆን ፡ ፮ ፡ ጊዜ ፡ ተቀጥሮ ፡ ነበር ።

የቀሩት ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ በመቶው ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ የታዩት ፡ የወንጀል ፡ ክሶች ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ በማድረስ ፡ በሚሠራው ፡ ወንጀል ፤ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶፫) ፡ የጭነት ፡ መኪናዎችንና ፡ የአውቶቡሶችን ፡ የመጓጓዣ ፡ ደንቦችን ፡ በመጣስ ፡ የሚፈጸመው ፡ ወንጀልና ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፳፱ ፡ (ተጠርጣሪውን ፡ በተያዘ ፡ በ፵፰ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለማቅረብ) ፡ የሚያዘውን ፡ የሚመለከቱ ፡ ነበሩ ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወንጀሉ ፡ ከተፈጸመበት ፡ አካባቢ ፡ ርቆ ፡ መገኘት ፡ ከመጓጓዣና ፡ ከመገናኛ ፡ ችግር ፡ ጋር ፡ ተጣምሮ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ በሚሰሙ ፡ ብዙ ፡ ክርክሮች ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ ይፈጥራል ። ፖሊሶች ፡ ዘወትር ፡ ብዙ ፡ ወንጀሎች ፡ በሚፈጸሙባቸው ፡ ሥፍራዎች ፡ እንዲኖሩ ፡ የሚደረግ ፡ አይመስልም ። ስለዚህ ፡ በታላላቅ ፡ ከተሞች ፡ ያሉት ፡ ፖሊሶች ፡ ለሚቀርቡላቸው ፡ ክሶች ፡ ከጭቃ ፡ ሹሞችና ፡ ከአጥቢያ ፡ ዳኞች ፡ በሚያገኙት ፡ መግለጫ ፡ ላይ ፡ መተማመን ፡ ይኖርባቸዋል ። ከዚያም ፡ መግለጫው ፡ የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ያየው ፡ ዘንድ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መምጣት ፡ ይኖርበታል ። ምርመራው ፡ አልቆ ፡ ነገሩ ፡ እስኪሰማም ፡ ድረስ ፡ ተጠርጣሪው ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በፖሊስ ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ ይቆያል ።

## ጠበቆች ።

በስርቆትና ፡ አስቦ ፡ በተደረገ የአካል ፡ ጉዳት ፡ ወንጀል ፡ በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ የተከሰሱት ፡ አብዛኞቹ ፡ ተከሳሾች ፡ ችግረኞች ፡ መሆናቸው ፡ ሊታወቅ ፡ የሚችል ፡

ቢሆንም ፡ የመዛግብቱ ፡ ምርመራችን ፡ ለችግረኛ ፡ ተከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ እንዲቆም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያዘዘበት ፡ አንድም ፡ መዝገብ ፡ አላየንም ።

ሆኖም ፡ ከታዩት ፡ ክርክሮች ፡ ውስጥ ፡ አሥር ፡ በመቶው ፡ ጠበቃ ፡ ነበራቸው ። እነዚህ ፡ ጠበቆች ፡ የአካል ፡ ጉዳትን ፡ በማድረስና ፡ በስርቆት ፡ በቀረቡ ፡ ክሶች ፡ ተከሳሾችን ፡ እንደወከሉ ፡ ቢቆሙም ፡ በአንድ ፡ በተለየ ፡ ክርክር ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ አይመስሉም ።

ጠበቆች ፡ በተለይ ፡ ደንበኞቻቸውን ፡ በነፃ ፡ ለማስለቀቅ ፡ የሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ አልተሳካላቸውም ። ጠበቃ ፡ ኖሯቸው ፡ በነፃ ፡ የተለቀቁት ፡ ተከሳሾች ፡ ቁጥር ፡ ያለጠበቃ ፡ በነፃ ፡ ከተለቀቁት ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ነበር ። (ከግማሽ ፡ በላይ ፡ የሚሆኑት ፡ ተከሳሾች ፡ ጥፋተኞች ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል) ።

## የነገር ፡ መጓተት ።

በወንጀል ፡ ክሶች ፡ ውስጥ ፡ የነገር ፡ መጓተት ፡ ተቀዳሚ ፡ ምክንያት ፡ የዐቃቤ ፡ ሕግና ፡ የመከላከያ ፡ ምስክሮች ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ አለመቅረብ ፡ ነው ። እነዚህን ፡ ሰዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርቡ ፡ የሚደረግበት ፡ ዘዴም ፡ ቀና ፡ አይደለም ። የዘዴው ፡ መሳካት ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሥራቸውን ፡ ሳያዛንፉ ፡ በቅልጥፍናና ፡ ባፋጣኝ ፡ መሥራት ፡ ላይ ፡ የተደገፈ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የራሱ ፡ የሆነ ፡ መጥሪያን ፡ ለምስክሮች ፡ የሚያድል ፡ ሠራተኛ ፡ ስለሌለው ፡ የዚህን ፡ ተግባር ፡ በባላገሩ ፡ ለማከናወን ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአጥቢያ ፡ ዳኞችና ፡ በጭቃ ፡ ሹም ፡ ላይ፡ መመርኰዝ ፡ ይኖርበታል ። በተጨማሪም ፡ አንድ ፡ ምስክር ፡ አልቀርብም ፡ ባለ ፡ ጊዜ፡ ፖሊሶች ፡ ይዘው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፡ የቻሉ ፡ አይመስሉም ። የአስፈላጊ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ሰነዶች ፡ አለማግኘት ፡ ችግር ፡ የአንዳንድ ፡ ክርክሮችን ፡ ፋይል ፡ እንዲዘጋ ፡ አድርጓል ።

> ተከሳሹ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፴ ፡ የሚያዘውን ፡ በመተላለፍ፡ በፈጸመው ፡ የአሥራ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ስርቆት ፡ ተከሰሰ ። ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የተከሳሹን ፡ ጥፋተኝነት ፡ የሚያረጋግጡ ፡ ሦስት ፡ ምስክሮች ፡ አሉኝ ፡ አለ ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፖሊሶችን ፡ እነዚህን ፡ ምስክሮች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ደጋግሞ ፡ አዘዛቸው ።
>
> ፖሊሶች ፡ ግን ፡ ምስክሮቹን ፡ ለማግኘት ፡ አለመቻላቸውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመለከቱ ። ምስክሮቹን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፡ ከአራት ፡ ጊዜ ፡ ሙከራ ፡ በኋላ ፡ ፋይሉ ፡ ተዘጋ ።

## የወንጀል ፡ ይግባኞች ።

ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ውጭ ፡ ከሆኑ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚመጡ ፡ የወንጀል ፡ ይግባኞች ፡ በባላገር ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙ ፡ ወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚቀርቡትን ፡ የወንጀል ፡ ክሶች ፡ መሰል ፡ ጠባይ ፡ አሳይተዋል ።

አብዛኞቹ ፡ ይግባኞች ፡ (ከመቶ ፡ አርባ ፡ ሰባቱ ፡) በጐረቤት ፡ ባለመሬቶች ፡ መካከል፡ የሚነሳን ፡ ክርክር ፡ ይመለከታሉ ። እነርሱም ፡- "በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ የከብት ፡ መንጋ ፡ አሰማርቶ ፡ ስለማበላሸት ፡" (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶፱ ፡ "በሰው ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ስለማድረስ" ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡

ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶፩) ፤ እና ፡ "የወሰን ፡ ምልክቶችን ፡ ከሥፍራቸው ፡ ስለማዛወርና፡ ስለማንሳት ፡" (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፶፪) ፡ ናቸው ።

ተከሳሽ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፵፱ን ፡ በመተላለፍ ፡ ከብቶቹን ፡ እተከሳሽ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሣር ፡ አብልቷል ፡ ተብሎ ፡ ተከሰሰ ። የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሽ ፡ በከሳሽ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ከብቱን ፡ እንዳያግጥ ፡ በከሳሽ ፡ ተደጋግሞ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ የተሰጠው ፡ መሆኑን ፡ ስለደረሰበት ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ በሃምሳ ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ እንዲቀጣ ፡ ፈረደበት ። ተከሳሽ ፡ ምስክሮች ፡ እንዳላቀርብ ፡ ተከልክያለሁ ፡ በማለት ፡ ለአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ አለ ።

የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ የተከሳሽ ፡ ጥፋተኛነት ፡ የተረጋገጠው ፡ በትክክል ፡ መሆኑን ፡ ሲያጸና ፡ የተጣለበት ፡ መቀጫ ፡ ግን ፡ ሚዛናዊ ፡ አይደለም ፡ አለ ። በክርክሩ ፡ ወቅት ፡ የታሰረውን ፡ በቂ ፡ አድርጎ ፡ ቆጥሮለት፡ አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሽ ፡ እንዲፈታ ፡ አዘዘ ።

በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ከተሰሙት ፡ የወንጀል ፡ ይግባኞች ፡ ከመቶ ፡ አስራ ፡ አምስቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ በመድፈር ፡ ስለተፈጸሙ ፡ ወንጀሎች ፡ መሆናቸው ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ክሶች ፡ የቀረቡት ፡ ሙሉ ፡ ቃሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተጻፈው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፵፫ ፡ (፩) መሠረት ፡ ነበር ።

"ማንም ፡ ሰው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ምርመራ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ በሚከናወንበት ፡ ወይም ፡ በችሎት ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱንና ፡ ዳኛውን ፡ የደፈረ ፡ የሰደበ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱና ፡ በዳኛው ፡ ወይም ፡ ከአባሎቹ ፡ በአንደኛው ፡ ላይ ፡ ያፌዘ ፡ የዛተ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ አድራጎት ፡ የሥራውን ፡ መልካም ፡ አካሄድ ፡ በማሰናከል ፡ ሁከት ፡ ያደረገ ፡ እንደሆነ ፡ እስከ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በሚደርስ ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ለመድረስ ፡ በሚችል ፡ የገንዘብ ፡ መቀጮ ፡ ይቀጣል ፤ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ቀጠሮ ፡ ሳያደርግ ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ወዲያውኑ ፡ ቅጣቱን ፡ ይወስናል ።"

እነዚህን ፡ ክሶች ፡ በሙሉ ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ገልብጧቸዋል ። ተከሳሽ ፡ ባላጋራውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በመስደቡ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፵፫ን ፡ ተላልፏል ፡ ተብሎ ፡ ተከሰሰ ። የመጀመሪያው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሽን ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ስላገኘው ፡ በሃምሳ ፡ ብር ፡ መቀጮ ፡ እንዲቀጣ ፡ ወይም ፡ ለስድስት ፡ ወር በእሥር ፡ ቤት ፡ እንዲቆይ ወሰነበት ። ተከሳሹ ፡ ለአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ አለ ። የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተከሳሽ ፡ ላይ ፡ የተወሰነበትን ፡ በመገልበጥ ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ ፋይል ፡ ሳይከፍት ፡ ተከሳሹን ፡ ሊፈርድበት ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ ወሰነ ።

የፍርድ ፡ ቤትን ፡ መደፈር ፡ የሚመለከቱ ፡ በተመሳሳይ ፡ ምክንያት ፡ የተገለበጡ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ጉዳዮች ፡ በመዝገቦች ፡ ውስጥ ፡ ተገኝተዋል ። ለማንኛውም ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ የመጋፋት ፡ ወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ቅጣት ፡ ሊወስን ፡ እንዲችል ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፵፫ ፡ ቢፈቅድም ፡ አዲስ ፡ ፋይል ፡ ሳይከፍት ፡ ሊያደርገው ፡ መቻሉን ፡ አይናገርም ።

ሌላው ፡ የፍርድ ፡ መገልበጥ ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ የሚወስደው ፡ ምክንያት ፡ የሌለው ፡ እርምጃ ፡ ነው ።

ጠበቃው ፡ ተከሳሽ ፡ በአንድ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ተከሳሽ ፡ ሆኖ ፡ ለቀረበ ፡ ሰው ፡ ዋስ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በመደጋገም ፡ ቢያዘውም ፡ ተከሳሹን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፤ ሳይሞክር ፡ ቀረ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህንኑ ፡ ጠበቃ ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ በመጋፋት ፡ ወንጀል ፡ ከሶ ፡ ለስድስት ፡ ወር ፡ ከሥራው ፡ እንዲታገድ ፡ ሳያቋርጥ ፡ ለፖሊስ ፡ ሂዶ ፡ እንዲያመለክትና ፡ በሕዝብ ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ እንዳይገኝ ፡ ከለከለው ። ከሳሹ ፡ ይግባኝ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ የወሰናቸው ፡ ቅጣቶች ፡ በቍጥር ፡ ፩፻፵፫ ፡ ላይ ፡ የተመለከቱ ፡ አይደሉም ፡ በማለት ፡ ፍርዱን ፡ ገለበጠው ።

የትራንስፖርት ፡ ደንቦችን ፡ መጣስ ፡ የሚመለከቱ ፡ ይግባኞች ፡ ከጠቅላላው ፡ የይግባኞች ፡ ቁጥር ፡ በመቶ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ በመሆን ፡ በብዛት ፡ የሚቀጥለውን ፡ ደረጃ ፡ ይዘዋል ። እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የአውቶቡሶችና ፡ የከባድ ፡ ጭነት ፡ መኪናዎች ፡ ከተወሰነው ፡ የጭነት ፡ ልክ ፡ በላይ ፡ የመጫን ፡ ክሶች ፡ ናቸው ። በነዚህ ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የወሰኗቸውን ፡ ቅጣቶች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አቃሏቸዋል ።

ቁጥራቸው ፡ ይህንኑ ፡ ያህል ፡ የሆነ ፡ የእጅ ፡ እልፊት ፡ ማለት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፭፻፶፪ ፡ ፭፻፴፱ ፡ እና ፡ ፭፻፵፩ን ፡ የመተላለፍ ፡ ክስ ፡ ይግባኞች ፡ ለመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርበዋል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ለነዚህ ፡ ክርክሮች ፡ መነሻ ፡ የሆነው ፡ የመሬት ፡ ይዞታ ፡ ጉዳይ ፡ ስለሆነ ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጠው ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ መጀመሪያ ፡ የባለሀብትነት ፡ ክርክሩን ፡ መወሰን ፡ ይጠይቃል ።

ተከሳሾቹ ፡ ከሳሹ ፡ መሬቱን ፡ እንዳያርሱበት ፡ ለመከላከል ፡ ሲሞክር ፡ ደብድበውታል ፡ በመባል ፡ ተከስሰው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ ተወሰነባቸው ። ለአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ አሉ ። የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ተከሳሾቹ ፡ መሬቱን ፡ ለማረስ ፡ መብት ፡ ስለነበራቸውና ፡ ከሳሹም ፡ የቆሰለው ፡ ተከሳሾቹ ፡ እንዳያርሱ ፡ ለማድረግ ፡ ሲሞክር ፡ የበሬው ፡ ቀንድ ፡ ወግቶት ፡ መሆኑን ፡ ምስክሮች ፡ ስላረጋገጡ ፡ የወረዳውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፍርድ ፡ ገለበጠው ።

ከዚህ ፡ የተረፉት ፡ የወንጀል ፡ ይግባኞች ፡ በስም ፡ ማጥፋት ፡ (የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፹፫) ፤ አነስተኛ ፡ በሆኑ ፡ በማታለል ፡ ሥራዎችና ፡ (የወንጀለኛ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፷፪) ፡ በግብር ፡ ውዝፍ ፡ ክሶች ፡ መካከል ፡ እኩል ፡ የተከፋፈሉ ፡ ናቸው ።

በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ከተሰሙት ፡ የወንጀል ፡ ይግባኞች ፡ ግማሾቹ ፡ ፍርዳቸው ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የተገለበጠ ፡ ይግባኙ ፡ ከመምሪያ ፡ ጋር ፡ እንደገና ፡ ወደ ፡ መጣበት ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተላከ ፡ ወይም ፡ ፍርዳቸው ፡ የተሻሻለ ፡ ናቸው ።

ከመቶ ፡ ሃያ ፡ ሁለት ፡ የሚሆኑት ፡ ፍርዶች ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የተገለበጡ ፡ ናቸው ። ይኸም ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመጨረሻ ፡ ለክርክሩ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ፍርድ ፡ ሰጠ ፡ ማለት ፡ ነው ። ፍርዱ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የሚገለበጥበት ፡ ምክንያት ፡ ዳኞች ፡ ፍሬ ፡ ነገሮችን ፡ ያለመንገዱ ፡ ሲጠቀሙባቸው ፡ ወይም ፡ ሚዛናዊ ፡ ያልሆነ ፡ ፍርድ ፡ ሲሰጡ ፡ ነው ።

ይግባኝ ፡ ባይ ፡ የአባቱ ፡ ንብረት ፡ የሆነውን ፡ የማር ፡ ድርቆሽ ፡ በመስረቁ ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የአርባ ፡ ብር ፡ መቀጫ ፡ ወሰነበት ። ተከሳሽ ፡ ወደ ፡ አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ቢወስድ ፡ አውራጃው ፡ ፍርድ

ቤት ፡ ተከሳሽ፡የተፈረደበት ፡ በቀበሌው ፡ ልማድ ፡ መሠረት ፡ ለአባቱ ፡ የሚገባውን ፡ ክብር ፡ ባለመስጠቱ ፡ መሆኑን ፡ ስለደረሰበት ፡ ፍርዱን ፡ ገለበጠው ።

የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበለትን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በደንብ ፡ አለመመርመር፡ በይግባኝ ፡ ላይ ፡ የፍርዱን ፡ መገልበጥ ሊያስከትል ፡ ይችላል ።

ተከሳሽ ፡ በከሳሽ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ የባሕር ፡ ዛፎችን ፡ በመትከሉ ፡ ያላግባብ ፡ በሰው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ በመግባት ፡ ክስ ፡ ቀረበበት ። የክርክሩ ፡ ጭብጥ ፡ የተባለው ፡ መሬት ፡ የማንኛቸው ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነበር ። ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ለመሬቱ ፡ ባለቤት ፡ መሆናቸውን ፡ ቢያስመስክሩም ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሣሽን ፡ ባለቤት ፡ አድርጐ ፡ በተከሳሽ ላይ ፡ ፈረደበት ። ፍርዱን ፡ የሰጠው ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ስለባለሃብትነት ፡ ጭብጥ ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ መሬቱን ፡ ራሱ ፡ ማየት ፡ ነበረበት ፡ በማለት ፡ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተከሳሽ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ እንዲሰረዝ ፡ አዘዘ ።

ፍርዳቸው ፡ ሙሉ፡ በሙሉ ፡ ከተገለበጠው ፡ ይግባኞች ፡ ቁጥራቸው ፡ አነስ ፡ ያለ፡ የይግባኝ ፡ ክርክሮች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያት ያልተሰሙ ፡ ምስክሮች ፡ እንዲሰሙ ወይም ፡ ያልቀረቡ ፡ ማስረጃዎች ፡ እንዲቀርቡ ፡ ወደ ፡ በታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገባቸው ፡ ተመልሷል ።

ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ፍርድ ፡ አውራጃው ፡ በማሻሻል ፡ ብቻ ፡ የሚያልፈው ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተጣለው፡የእሥራት ፡ ወይም ፡ የገንዘብ፡ መቀጫ ፡ ከልኩ ፡ ያለፈ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሲገምት ፡ ነው ። መሻሻል ፡ ያስፈለጋቸው ፡ የወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ፍርድ ፡ ቁጥር ፡ ሲታይ ፡ ዳኞች ፡ እንደፈለጉ ፡ በሚወስኑት ፡ ቅጣት ፡ ምክንያት ፡ የሚፈጠረውን ፡ የፍትኅ ፡ ጉድለት ፡ ለማስወገድ ፡ የመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ትልቅ ፡ ኃላፊነት ፡ እንዳለበት ፡ ያሳያል ።

በመጨረሻም ፡ በይግባኝ ፡ ላይ ፡ የቀረቡ ፡ ጭብጦች ፡ እምብዛም ፡ የሕግ ፡ አተረጓጐም ፡ ልዩነት ፡ አለማሳየታቸውን ፡ መገንዘብ ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ዘወትር ፡ ይግባኝ ፡ ያስፈለገበት ፡ ምክንያት ፡ በፍሬ ፡ ነገር ፡ ጭብጦች ፡ ላይ ፡ የተሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ትክክለኛ ፡ ስላልነበረ ፡ ነው ።

## ጠበቆች ።

ይግባኝ ፡ ከተባለባቸው ፡ የወንጀል ፡ ክርክሮች ፡ ውስጥ ፡ ከመቶ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ በሚሆኑት ፡ ለተከሳሾች ፡ ጠበቆች ፡ ነበሯቸው ። በመናገሻ ፡ አውራጃ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ፋይሎች ፡ ምርመራ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለአንድ ፡ ችግረኛ ፡ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ጠበቃ ፡ የቆመለት ፡ መሆኑን ፡ ፈጽሞ ፡ አያሳይም ።

ተከሳሾችን ፡ ለይግባኝ ፡ ክርክራቸው ፡ ጠበቃ ፡ እንዲይዙ ፡ የሚገፋፏቸው ፡ የተለዩ ፡ የወንጀል ፡ ክርክሮች ፡ አልነበሩም ። ጠበቆች ፡ የቆሙባቸው ፡ ክርክሮች ፡ ሁኔታም ፡ በዚህ ፡ ደረጃ ፡ (በይግባኝ ፡ ክርክር) ፡ ጠበቃ ፡ የገዙትን ፡ ሰዎች ፡ የገንዘብ ፡ አቋም ፡ አያሳዩም ።

## የነገር ፡ መጐተት ።

በአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ክርክሮችን ፡ የሚጐትቱት ፡ ምክንያቶች ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሚሰሙ ፡ የወንጀል ፡ ክርክሮችን ፡ ቀጠሮ ፡ ከሚያበዙት ፡ ምክንያቶች ፡ ጋር ፡ በጣም ፡ ይመሳሰላሉ ። ቢሆንም ፡ በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ስላለው ፡ የክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ ነው ። የማስረጃዎችና ፡ የምስክሮች ፡ አስፈላጊነት ፡ እስከዚህም ፡ ባለመሆኑ ፡ በዚህ ፡ አለመቅረብ ፡ ምክንያት ፡ የሚፈጠረው ፡ የነገር ፡ መጐተት ፡ የተቀነሰ ነው ። ሆኖም ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክርክሩን ፡ በወቅቱ ፡ ሳያዘጋጅ ፡ መቅረት ፡ ወይም ፡ የዳኞች ፡ አለመሙላት ፡ ችግር ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በየክርክሩ ፡ ያንድ ፡ ተጨማሪ ፡ ቀጠሮ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖአል ።